مؤسسة دار الفكر
Dar Al-Fiker Foudation
فنفني - إثيوبيا

# إعادة اكتشاف الصلاة
## مختصر إدارة الصلاة
أحمد بسام ساعي

# ሰላትን እንደገና ማወቅ
## (ሰላትን ማስተዳደር)
ከተሰኘዉ መጽሐፍ የተከለሰ ዕትም

አዘጋጅ:

አህመድ በሳም ሳዒ

ተርጓሚ፡-

ዳር አልፍክር ፋውንዴሽን

ፊንፊኔ- ኢትዮጵያ 2017 G. C

# إعادة اكتشاف الصلاة
# مختصر إدارة الصلاة

**أحمد بسام ساعي**

# ሰላትን እንደገና ማወቅ

## (ሰላትን ማስተዳደር)

ከተሰኘዉ መጽሐፍ የተከለሰ ዕትም

አዘጋጅ:

አህመድ በሳም ሳዒ

**ተርጓሚ፡-**

**ዳር አልፍክር ፋውንዴሽን**

የቅጂ መብት በህጋዊ መንገድ ለዳር አልፍክር ፋውንዴሽን የተጠበቀ ነው።

ፊንፊኔ- ኢትዮጵያ **2017 G. C**

**DF-E-TrBs-17/30**

## ይዘት

ሶላት.....................................................................................6
ሦስተኛው እትም መግቢያ፡ የመጀመሪያ እና የሁለተኛ እትሞች የመስልገለፃ..................8
ቀጠሮ ከአሏህ ጋር.....................................................................19
"እሷ ከባድ ናት".. ለምን?!.............................................................25
ጉዞ ከግዴታ ወደ ሙብት................................................................27
በግዴታ እና በሙብት መካከል ያሉ ድንበሮች..............................................30
ለመስገድ የመንቃት ደስታ................................................................31
የትዕግስት ደስታ.........................................................................35
ሶላት የትዕግስት ትምህርት ቤት ነች፣ ትዕግስት የሥልጣኔ ትምህርት ቤትነች--------.-36
ለምን እንሰግዳለን?.......................................................................39
ሶላት እኛን እንደገና እየቀረፀን /እያቀናጀን ነው.............................................40
የሶላት ምት እና የሕይወት ምት..........................................................48
ብዝሃነት-የመጀመሪያው የሥልጣኔ ትምህርት ቤት........................................50
የብዝሃነት አስፈላጊነት ለትህትና (ኹሹዕ)...................................................53
ሁኔታዎች እና እንቅስቃሴዎች መለዋወጥ .. ለምን?......................................54
ወደ ሶላት ጥሪ (አዛን) እና አሥሩ አስገራሚ ነገሮቹ......................................56
ሁለቱ እጥበቶች (ዉዱዓን)..................................................................63
የቡድን ሶላት፡ የሥልጣኔ ምስጢር........................................................66
የአርብ ስብከት : የልማት ዑደት..........................................................74
ከዚህ እንጀምራለ.........................................................................79
አምስቱ የሶላት መስመሮ.................................................................84
ቀዩ ቁልፍ ቁጥር1: አላህ ታላቅ ነው......................................................91
በማንበብ እና በመከተል መካከል.........................................................94
አዲሱ የቅዱስ ቁርአን ቋንቋ...............................................................96
ግልፅ ቋንቋ እና ክፍት አረንጓዴ ቦታ.....................................................98
የአል-ፋቲሃ ሚና እና ንባቡ..............................................................100
በአሏህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ እጅግ በጣም አዛኝ...................................102
እጅግ በጣም ሩህሩህ እጅግ በጣም አዛኝ...............................................107
ቀዩ ቁልፍ 2: አንተን ብቻ እንገዛለን ባንተ ብቻም እንታገዛን.............................109
ቀጥተኛውን መንገድ ምረን ፡፡ የነዚያን መንገድ........................................112
በአል-ፋቲሃ ምዕራፍ ዉስጥ የማራዘሚያ ቦታዎች.......................................116

የሩኩዕ እና የሱጁድ ማዕከላዊነት........................................................117
ቀዩ ቁልፍ 3: ሰላምታ ለአሏህ........................................................120
ቀዩ ቁልፍ 4፡ ሰላም በእኛ እና በፃድቃኑ የአላህ ባሮች ላይ ይሁን........................124
የጸሎት እና ዉዳሴ ክፍለ ጊዜ........................................................126
ሚዛኑ........................................................128
መገጣጠሚያዎችዎ እስኪረጋጉ ድረስ........................................................131
የሶላቱ የሶስትዮሽ ትርጉም........................................................133
ከሶላት ፕሮግራም የተገኙ ጥቅማቅጥቅሞች........................................................137
ከሶላት ጥቅማቅጥቅሞ ያመለጣችሁ ነገር........................................................140
ሕይወትዎ በሶላት የተሞላ ይሁን........................................................141
ለራስዎ የመንገድ እቅድ ያስቀምጡ........................................................146
የመጀመሪያው እርምጃ........................................................148
ሁለተኛው እርምጃ........................................................152
ሦስተኛው እርምጃ........................................................153
ደረጃ አራት........................................................154

መብቱ በህግ የተጠበቀ አይደለም፡፡ ይህንን መጽሐፍ ወይም ማንኛውንም የመፅሓፉን ክፍል በማተም፣ በመቅዳት ወይም በማንኛውም መንገድ ማሰራጨት ይፈቀዳል፡፤ ፎቶ ኮፒ ማድረግ ወይም መተርጎም ሲፈልጉ ለፀሐፊው ያሳውቁና አዲስ እትም ይዉሰዱ፡፡ ይህ የአሏህን ፊት ብቻ የምፈልግበት መጽሐፍ ነው፡፡ እናም እያንዳንዱን አንባቢ የምያሳስበዉ ነገር የወደፊቱ እትሞች በማንኛውም ቋንቋ ቢሰራጭ የተሟላና ግልፅ ሆኖ እንዲታይ የታዘቡትንና አስተያየቶቻቸዉን እንዲሰጡበት እጠይቃለሁ፡፡ በዚህም በአሏህ ቢፈቅድ የበጎ አድራጎት ተግባራት ውስጥ ተካፋይ ይኖናሉና፡፡

**የመጨረሻው ሽፋን፡-**

በጠቅላላ ሕይወታችን እና በዩኒቨርሲቲ ዲፓርትመንቶቻችን ውስጥ የኢንዱስትሪን፣ የንግድን፣ የእርሻን እና የከተማ ልማት ፕሮጀክቶችን ትርፋማነት ሊያመጡ በሚችሉ የተለያዩ የትምህርት መስኮች እና ዘርፎችን ለማስተዳደር የተሻሉ መንገዶችን ማጥናት ያሳስባቸዋል፡፡ ነገር ግን በትምህርት ቤቶቻችን፣ በተቋማቶቻችን ወይም በዩኒቨርሲቲዎቻችን ውስጥ፣ የትምህርት መስክ ከመፍጠር የተሻለ፣ ከነዚህ ፕሮጀክቶች ሁሉ እጅግ የላቀ፣ የበለጠ ጥቅም ያለዉ፣ ረዘም ላለ ጊዜ የሚቆይ፣ አስተማማኝ ውጤት እና ለቅርቢቱ ዓለምም ሆነ ለመጪው ዓለም አጠቃላይ ጠቀሜታዉ የገዘፈ ነገር አስቦ ኖሯልን? ይኻዉም የአምልኮ ሥርዓቶች አስተዳደር ነው፡፡

- መጽሐፉ ሶላትን እንደገና ለማወቅ እና ማብራራት የልማድና እና ድንገተኛነት አቧራ ለማስወገድ የሚደረግ ሙከራ ነው ፡፡
- ሶላት ከ“ግዴታ” ወደ “መብት” እና ከ “ሸክም” ወደ ተድላ ወይም ደስታ እንዴት ይለወጣል የሚለዉን ይመልሳል፣
- ሶላት በውስጣችን ባለው የሕይወት፣ የጊዜና የልማድ ቫይረስ የተበላሸውን እቅድ እንዴት ዳግመኛ ይመልሷል የሚለዉን ይዳስሳል፣
- ሶላት እንዴት ህይወታችንን እንደገና እንደሚያቀና እና አስተሳሰባችንን ያቀናኛል፣
- ሶላት፣ ለቅርቢቱ ዓለምም ሆነ ለመጭው ትልቁ የኢንቬስትሜንት ፕሮጀክት እና እስላማዊ ስልጣኔን ለማደስ ትልቁ ፕሮግራም ነዉ፣

**ደራሲው፡-**

የተወለደው በ1941 በሶሪያ ላዚቂያ ውስጥ ነው፡፡ በአረብ እና በእንግሊዝ ዩኒቨርስቲዎች አስተምረዋል፡፡ በ1991 የኦክስፎርድ የድህረ ምረቃ ጥናቶች አካዳሚ መሠረተ፡፡ በበርካታ የብሪታንያ (ኢንግሊዝ) ሳይንሳዊ ምክር ቤቶች እና ተቋማት ውስጥ ሰርቷል አሁንም እየሰራ ይገኛል፡፡ በአሁን ሰኣት በብሪቲሽ ካውንስል ለተቋማት እና ለዩኒቨርሲቲዎች እውቅና መስጫ (BAC) ምክር ቤት ውስጥ ከፍተኛ ኢንስፔክተር በመሆን እየሰራ ይገኛል፡፡

**ከመፃሕፍቶቹ መካከል፡-** የዘመናዊ ግጥም እንቅስቃሴ በሶርያ ውስጥ በታዋቂዎቹ (1978)፣ በሬቶሪክ (አጻጻፍ) እና ሂስ መካከል ያለው ገፅታ (1984) ፣ እስላማዊ ተጨባጭነት በስነ-ጽሁፍ እና በሂስ (1985) ፣ ሙስሊሞች እስልምናን ከመከላከል አንፃር፣ ክርስትያኖች ክርስትናን ከመከላከል አንፃር (2008) ፣ (ተአምር ፣ በቅዱስ ቁርአን ውስጥ የቋንቋ ተዓምራቶችን እንደገና ማንበብ ወይም ማጥናት፣ ጥራዝ 1 (2012) ፣ ጥራዝ 2 (2015)፣ ሶላትን ማስተዳደር፣ ሁለተኛውን የእስልምና ምሰሶ እንደገና መዳሰስ ወይም መፈተሽ (2015) ፣ ከነቢዩ የበለጡ ነብያት? የሃይማኖታዊ ጽሑፍን እንደገና ማጥናት (2017) ። bassamsaeh@hotmail.com

በአሏህ ሥም እጅግ በጣም ሩህሩህ እጅግ በጣም አዛኝ

## ሶላት

አቤቱ አምላክ ሆይ፣ ከነዚህ ሀሳቦች እና ገጾች ፊትህን እና የወደፊት ሕይወቴን ብቻ እንደፈለግሁ ታውቃለህ፤ በውስን እና ደካማ ሰዋዊ ቋንቋዬ ወደ አንተ ዞርኩ፣ ምክንያቱም ቃሎቼን አላሳምርም፣ እና ተራ ሰዎችን የሚያናግር ተራ ሰው ነኝ፤ ለአክብሮትህ የማይበቁ ዉስን፣ ግርማ ሞገስህን እና ግርማዊነትህን የማይከብዱ ንግግሮቻችን እንጂ፡፡ ወደ አንተ በምሄድበት ጊዜ እሩጫዬ ከቀነሰ እና ከተንሸራተትኩ፤ እናም በትክክል ከተሳሳትኩ፣ ወይም አንደበቴ ከእኔ ፈቀቅ ካለ፣ አንተ ብቻ ታውቃለህ፣ እኔ በመጀመሪያም በመጨረሻም አንተ ወደምትፈልገዉ መድረስ ብቻ እንደፈለግሁ፡፡ በእውነቱ አንተ ወደምትፈልገዉ ነገር ግን የጥበብህ ዓላማዎች አድማሶች፣ እና ለመልዕክተኛህ የገለጥከለትን ምስጢሮች እኛ ለሰው ልጆች እንዴት ልንደርስበት እንችላለን፤ሶላታችን በሕግ ሲደነገግ፣ መለኮታዊ ትዕዛዛትን በታላቅ ድምቀት ስንቀበል፣ የሁሉንም ጥቃቅን ዝርዝር ነገሮች እና ሚስጢሮች ወደ እኛ የመምጣት ሚስጢር እንዴት እንረዳለን?

በእኛ በደካማ እና በጎደሎ ሰብአዊነታችን ልናስተናግድ እና ልንረጋጋበት የምንችለው ነገር ሁሉ ፣ሶላትን ለምእመናን ምህረት ሲባል መደንገግህ ነው፤ በዋጋ የማይተመኑ በየቀኑ ከአንተ ጋር የሚያገናኙበት ጊዜያት፤ እናም በነፍሶቻቸው ዉስጥ ያማከሩሃል፣ እና ከባድ ኃጢአቶችን ባንተ ያራግፋሉ፤ እና ጀርባዎቻቸውን ወደ ካልካዩ ግድግዳህ ያዞራሉ፤ እናም እስከ ከፍተኛ የሰው ልጅ ደረጃዎች ድረስ ለእነሱ የሚዘረጋውን ሰፊ መንገዳቸውን ያያሉ ።ነፍሳቸውን ወደ አንተ ከፍ በማድረግ፣ ፍላጎቶቻቸውን ወደ ደጃፍህ በማስጠጋት እና ምህረትህ በደጅህ ላይ እንዲፈስ በመከጀል ወደ አንተ ይጣላሉ፣ ከብርታትህ በጣም ኃይለኛ እንደሆንክ እና ምህረትህ ሰፊ መሆኑን ስለሚያዉቁ፤ አስፈላጊዉን ቅሬታቸውን፣ ቁስሎቻቸው እና ጉዳቶቻቸዉን፣ ደስታና ሀዘኖቻቸዉንም እንደዚያዉ፡፡ እናም በጨለማ ውስጥ ነፍሶቻቸው ለእነሱ ያበራሉ፡፡ እና አንተ ትላቸዋለህ፡ ‹‹ እርሱ ያ በእናንተ ላይ የሚጸልይ ነው መላእከቱም፤ ከጨለማዎች ወደ ብርሃን ሊያወጣችሁ፤ እርሱም ለምእመናን አዛኝ ነበር>>..

አቤቱ አምላኬ ሆይ፣ በፃፍኩት ነገር ላይ ጥሩ የሰራሁትን ነገር ለፃድቃኑ አገልጋዮችህ በሚትመነዳ በጎ ነገር መነዳኝ፣ እንዲሁም በክህደት ወይም በአድናቆት ወይም በትርጉም ወይም በአገላለጽ የተሳሳትኩ ነገር ካለ ይቅር በለኝ፣ ምላሴ ከቀደመኝ ታላቅነትህ እና ላንተ ያለኝ አክብሮት በእጥፍ ይበልጣል፣ እናም ብዕሬ ስለ ጥበብህ ሰማይ እንድደርስ በነገረኝ ፃፍኩትና ያንን እንድሰራ አደረከኝ፣ ክብር ለአንተ ይሁን፣ በብርሃንህ ማብራት ብቻ እንደፈለግኩ ታዉቃለህ፣ ወደ ቀጥተኛ መስመርና ምህረትህ ምረኝ፡፡ አንተ ቀጣይ ነህ፣ እዝነትህ፣ምህረትህ፣ ዉዴታህና ችሮታህ ቀጣይ ነዉ ፣ አንተም አዛኝ ከሆነው ሁሉ እጅግ አዛኝ ነህ፡፡

ምህረትህን ፈላጊ፣
የኦክስፎርድ እንግዳ
.. ባሳም ሳዒ
ሐሙስ ማለዳ ፣ ሰፈር 17፣ 1438
ህዳር፣ 17 ቀን 2016 እ.አ.አ.

## ሦስተኛው እትም መግቢያ፡ የመጀመሪያ እና የሁለተኛ እትሞች የምስል ገለፃ

የቤይሩት የመጀመሪያ እትም (እ.ኤ.አ.) 2015) ካለቀ በኋላ በቀጣዩ ዓመት የተደገሙት ቀጣይ እትሞች ነበሩ፣ እና የደማስቆ ሁለተኛ እትም (2016) አለቀ፡፡ ያም የተጨመረ እና የተሻሻለ እትም ነገር፡፡ መጽሐፉ ወደ ብዙዎች ቋንቋዎች ከተተረጎመ በኋላ፣ ከነዚህ ውስጥ ከሰላሳ በላይ ትርጉሞች እስካሁን ድረስ ታትመዉ ተሰራጭቷል፡፡ ከዚያ በኋላ ወደ ሰፊ እና ሰፋ ያሉ ሀገሮች ደርሰዋል፡፡
መፅሃፉን ለማቀናበር በወሰድኩበት ጊዜ ካሰብኩት በላይ ለአንባቢው በማቅረብ የበለጠ ኃላፊነት እንደተሰማኝ ሆኗል፡፡ በዚህም ወደ ትክክለኝነት እና ሁሉን አቀፍነት፣ እንዲሁም ሶስተኛ እትም ላይ ተጨማሪ እስክሪብቶቼን ለማሳለፍ ማሻሻያዎች፣ እርማቶች፣ ስረዛዎች እና ተጨማሪዎች እንዲሁም ማብራሪያዎችን እንዲያካትት አድርጎኛል፡፡ የተለያዩ ሀዲሶችም እንዲካተቱ፤ አዳዲስ እዉቀቶችና ግኝቶች በተቻለ መንገድ እንዲጨመሩ፣ ግን የሰው ልጅ ደካማ እና ውስን ስለሆነ አይደለም ወደ ፍፁማዊነት መድረስ ወደእሱ ሊቃረብም አይችልም፡፡

በዚህ አዲስ እትም አስፈላጊ ተጨማሪዎችን ስጨምር፣ ለብዙዎች አንባቢያን ጓደኞች፣ ወንድሞችና እህቶች መጽሐፉን ሲያነቡ በሰጡኝ አስተያየት ምላሽ መስጠት ነበረብኝ፣ (እንግዲያውስ) (ለራስዎ የመንገድ እቅድ ይፍጠሩ) በሚል ርዕስ አንድ ወሳኝ ክፍል እንድደመድም ወሰንኩ፤ በግል ልምዴ ተነሳስቼ፣ በእያንዳንዳችን ፊት ቆሞ በማዘናጋት ከሶላት የሚያርቀንን ሸይጧንን በማስታወስ፡፡

ሸይጧን ወደማያውቁት ቦታ ወደሚፈልገው ነገር ያታልልዎታል፤ ከሶላቱ በፊት ያላሰቡትን ያስታውሰዎታል፡፡ ክቡር ነቢያችን (ሰ.ዐ.ወ) እንዲሁም እንዳረጋገጠልን፣ ከዚያ በሃሳብ ይጋብዝዎታል፣ እናም ይህ ወደ ሌላ፣ እና ያ ደግሞ ወደ ሌላ ይመራዎታል ወዘተ፣ ከዚያ ወደ ራስዎም፣ ወደ አሏህም አይመለሱም፣ ሶላትዎን ደግሞ ለማጠናቀቅ ተቃርቦዋል፡፡ ሁሉን ቻይ የሆነው አምላክ ከአንድ በላይ በሆኑ አንቀፆች ውስጥ የሸይጧን “እርምጃዎችን” ገልጾልናል፤ እና ተከትለናቸዉ እንዳንጎተትም አስጠነቀቀን፤ ስለሆነም መስመሮቹን የሚያስቆርጡ እቅዶችን ማውጣት አስፈላጊ ነበር፤ “እርምጃዎቹን” የሚጋፈጡ ድንጋጌዎችን መተግበርምን ጨምሮ፡፡ ስለሆነም በመጨረሻ ወደ አክብሮት (ኹሹዕ) ስኬት እንቀርባለን፤ የበለጠ ተጨባጭ ለመሆን ከፈለግን ደግሞ ሶላታችንን ነዉ የተሟላ ለማለት ወደሚያስችለን ኹሹዕ፡፡ ያዉ

የተፈጠርንበትን ሰዋዊ ድክመታችንን መቀበል አለብን፣ የሰው ልጅ በሶላቱ እንኳ የሚሠቃይበትን ድክመት፡፡

ከዚያ በአስተያየት ሰጪዎች እና በትዊተሮች ከተሰጡት አስተያየቶች ዉስጥ የቀሩትን አገላለፆች መሠረት በማድረግ በዚህ በመግቢያ መግለፃ ማከል ነበረብኝ፤ በሀሳብ አመንጪዎች መካከል ምሁራዊ እና ባህላዊ ርቀቶች እና የሰው ልጅ ልዩነቶች፣ ተፈጥሮአዊ ተቃርኖዎች በአስተያየታቸው ውስጥ የሚጠበቁ ቢሆኑም፡፡ ያ (ሶላትን ማስተዳደር) የሚለዉን መጽሐፍ "በሰው ልጅ የተጻፈው እጅግ አስደናቂ መጽሐፍ" ነው፤ ወይም "ከከበሩ ድንጋዮች እና ማዕድናት ሁሉም የበለጠ ውድ ሀብት" ነዉ ይላሉ፤ ሌሎች ደግሞ ‹‹እሱ ብዙ ዝርዝሮችን እና መደጋገሞች ይዞዋል "ወይም" በግማሽ ማሳጠር ይቻል ነበር" ይላሉ፡፡ ነገር ግን፣ ፍትሃዊ ከሆንን፣ መጽሐፉ ለዚህም እና ለዚያም አይደለም፡፡

(የሶላት አስተዳደር) እስልምናን እና በእስላማዊው ጽሑፍን እንደገና ለማጣራት በምሞክርባቸው ተከታታይ መጽሐፍት ውስጥ ከሚገኝ ትዕይንት የዘለለ አይደለም፣ (ኢስላማዊ ተጨባጭነት በስነ-ጽሁፍ እና ሂስ-1985) ከሚለዉ መጽሐፍ በመጀመር፣ ከዚያም (ሙስሊሞች ከእስልምናን ከመጋፈጥ፣ ክርስቲያኖች ከክርስትናን ከመጋፈጥ አንፃር (2008)፣ በሚለዉ መጽሐፍ በማለፍ ፣ ከዚያ (ታምራት፣ በቅዱስ ቁርአን ውስጥ የቋንቋ ተዓምራቶችን እንደገና በማንበብ (ክፍል 1: 2012, ክፍል2: 2015) ከሚለዉ መጽሐፍ ቀጥሎ ደግሞ ‹‹ከነቢዩ የበለጡ ነቢያት? የሃይማኖታዊውን ጽሑፍ እንደገና ማንበብ (2017) በሚል መጽሐፍ መደምደሚያ ተደርጓል ፡፡ በቅርቡ አሏህ ቢፈቅድ፣ (እስልምና አሏህ እንደተናገረው እና የአሏህ መልእክተኛ "ሰ.ዐ.ወ" እንደተናገሩት) የሚል መጽሐፍ ይነበባል፡፡

መጽሐፉ አሁን ካለው መጠን ባነሰ ሊወጣ ይችል ነበር፣ እና ከወንድም እህቶች እነዚህን አስተያየቶች ወይም ጥቆማዎች ከመስማቴ ወይም ከማንበቤ በፊት በእውነት አሁን ካለዉ ከሩብ በታች በማሳነስ ላማዉጣት ቆሜ ነበር፡፡ የማጠቃለያ እትሙ "ሶላትን እንደገና ማወቅ" የተሰኘው የመጀመሪያው እትም ከታተመ ከጥቂት ወራት በኋላ ወጣ፣ ያዉ (እ.ኤ.አ. በ 2015 በዋሺንግተን ውስጥ በአለም አቀፉ የእስልምና

አስተሳሰብ ተቋም የታተመ ሲሆን ይህ ትርጉም የዚያ ምስል ሆኖ ይህ መግቢያ ታክሎበት) ነዉ፡፡ ግን አሁን ምክር ቢጠይቁኝ፣ እና ሁለቱን እትሞች ያስቀመጥኩ እኔ ሆኜ ሳለዉ፣ የመጀመሪያውን የተራዘመ ንባብ እንዲያነቡ ነዉ የሚመክርዎች፤ ምንም እንኳን በመጨረሻው የርዕሶችን ቁጥር ማሳጠር ብሞክርም፡፡ ከዚህ ከአጭሩ ሁለተኛውን እመርጣለሁ፡፡ ምክንያቱም፣ በእያንዳንዱ ርዕስ ስር የሚመጣው መጣጥፉ ሳይሆን፣ ያን ያደረኩት፣ ሶላትን በተረጋጋና ዘና ባለ ምት በመስገድ መካከል እና ስለ ሶላት ከማዉራት ምት መካከል ያለዉን ልዩነት ለመጠበቅ ነዉ፡፡ ስለዚህ የመጽሐፉ ምት ከመጽሐፉ ርዕስ ምት ጋር የሚስማማ ይሆናል ማለት ነዉ። እናም የተረጋጋ መንፈሱም የእሱን ርዕሰ መንፈስ ጉዳይ ላይ የተንተረሰ ይሆናል፡፡

የ “ሶላትን ማስተዳደር” መፅሐፍ የመጀመሪያ ዓላማ የሰጋጁን ህይወት፣ ከከፍተኛ አውራ ጎዳና እና ከመጠን በላይ ከተጨናነቁ፣ እና ከሁሉም አቅጣጫዎች በእብደት መሬቱን እየዘረፉ ከሚንቀሳቀሱ የጭነት መኪናዎች፣ ከዓለማዊ ጭንቀቶች እና ፍላጎቶች፣ ከህይወት ኑሮዎች፣ ከችሎታችን የሚበልጡ ከጭንቀት ተሸከርካሪዎች፣ ከጽናታችን በላይ ከሆኑ ጭንቀቶች እና ህመሞች ለማዳን ነበር፡፡ ልክ በምሕረት የለሽ ተሸከርካሪዎቻቸዉ ጥርሶች ሊበሉን እስከሚችሉ ድረስ የሚፈጥኑ፡፡ እናም በመጽሐፉ በኩል ይህንን ሰጋጅ ጸጥ ወዳለ ታማኝ መንፈሳዊ ማረፊያ ለመቀየር በመሞከር፣ እና ፈጣኑን የሕይወት አውራ ጎዳና፣ በፈለገዉ ጊዜ እና በግድየለሽነቱ የልባችን ምቶች ሊቆም ከሚችለው መንገድ ለማምለጥ በጥላው ስር በመጠለል፣ እና በአሰቃቂ ቅኝቱ እኛን ከሚያዳክመን እንዲሁም የአንጎል ሴሎቻችንን በእጅጉ ከሚጎዳን ነገር ለማዳን ነዉ፡፡

ቅዱስ ቁርአን የወረደው አረቦች (በላገት-አል ኢጃዝ-የአነጋገር ስልት) የሚለውን ወሳኝ መርህ በተቀበሉበት ጊዜ ነው፡፡ ሆኖም፣ ምንም እንኳን ከዚያ በፊት ያልታወቀ እና በኋላ ላይም ያልተከተለዉ ተዓምራዊ የቁርአን የአነባበብ ስልት ቢሆንም፣ ለቁጥር የሚቸግሩ ስዕሎች፣ አረፍተ ነገሮች እና መግለጫዎች ላይ፣ አንባቢው የሚነካቸው በእያንዳንዱ የአሏህ መጽሐፍ ገጽ ላይ ያሉ ቁርአናዊ ታዓምራት አሉ፡፡ ለምሳሌ “ ፈላጊ እና ተፈላጊ ምንኛ የደከሙ ናቸዉ”፣ “ዓይኖችን ይገነዘባል ግን ዓይኖች አይደርሱበትም ” እና “ አላህን በአጠገቡ አየ ” እና “ለዉይይት ተለዩ” የሚሉ ናቸዉ፡፡ እንደነዚህ ያሉት አጭር የቁርአን መብራሪያች ሁል ጊዜ ወደ ቁርአን አውድ ውስጥ፣ አስፈላጊውን

የአነባበብ ምት ለማሳካት፣ በተራዘመ እና ምንአልባትም በተደጋገመ አኳሆን፣ ነፍስን ከአሏህ ጋር ለመገናኘት ይመጣሉ፡፡ የቁርአን ንባብ ፣በውስጡ ካሉ ሌሎች በርካታ ተአምራዊ አካላት ጋር፣ ቀደም ሲል (ተአምራቱ) በሚል በመጽሐፋችን እንደጠቀስን፣ እንደ ሶላት ነዉ የሚቆጠረዉ፡፡ ቁርአን፣ ከዚህ አንፃር፣ ለሚፈወሱ ሰዎች ፈውስ፣ መድህን እና ምህረት ነዉ ማለት ነዉ፡፡ ብዙሃኑ የቁርኣን አንቀጾች የሚያረጋግጡትም ይህንኑ ነዉ፡፡ ለምሳሌ

وَنُنَزِّلُ مِنَ ٱلْقُرْءَانِ مَا هُوَ شِفَآءٌ وَرَحْمَةٌ لِّلْمُؤْمِنِينَ ﴿٨٢﴾ الإسراء: 82

"**እኛ ከቁርአን ፈውስ እና እዝነት ያለዉን ነገር ለምእመናን እንወርዳለን** *[አል-እስራዕ፡ 82]* ፣

قُلْ هُوَ لِلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ هُدًى وَشِفَآءٌ ﴿٤٤﴾ فصلت: 44

"**በላቸው፡ ለእነዚያ ለአማኞች መመሪያና ፈውስ ነው** *[ፉስለት፡ 44]*

እኔ ዛሬ ይህ በማኅበራዊ አውታረ-መረቦቻችን ላይ የሚሞከሩትን አዲስ አጭር የንግግርን ዘየን አልቃወምም፤ መላውን ዓለም በሁለት መስመር፣ የሰውን አቋም በሁለት ቃላት የተጠቃለለ አድርጎ ሲያሳዩን ማስተዋል ያለብን ነገር፣ የአዉታሩ ምት ዛሬ የሕይወታችን ፈጣን እና ምንአልባትም የእብድ ይመስል ምት መሆኑን መገንዘቡ ምንም ጥርጥር የለውም የሚለዉን ነዉ፡፡ ግን በእውነቱ ይህንን ኃይለኛ ምት መቆጣጠር፣ አስፈሪዉን ፍጥነቱን በተረጋጋና በተስተካከለ ምት መመጠን በጣም ያስፈልገናል፡፡ እንቅስቃሴውን ወደ ሚዛናዊነት እና ወደሚታዘዘዉ ፍጥነቱ፣ ወደ አዕምሮው ጥበብ፣ ወደ መረጋጋት እና መስከን እንዲመለስ ማለት ነዉ። ለእነዚህ የሶላት ምት፣ ወደ ደከሙ ነፍሳት እና ከህይወት ሩጫ በስተጀርባ ሆነዉ በእብደት ወደ ሚደፉ ልቦች ሚዛንን ከመመለስ ዉጭ ሌላ ምርጫ አላገኘሁም::

በመጽሐፉ ውስጥ ድግግሞሽ አለ፣ አዎን፣ እና እንዴት በሶላት መጽሐፍ ላይ እንደዚያ ሊሆን አይችልም? ሶላት ረከዓን የሚታስከትል ረከዓ፣ ተክቢርን የሚያስከትል ተክቢር፣ ተስብሂህን (ውዳሴን) የሚያስከትል ተስብሂህ፣ ፋቲሃን የሚጣስከትል ፋቲሃ፣ አይደለችምን ? የረከዓቶች ፣ የተክቢር ፣ የውዳሴ እና የንባብ መብዛት ድግግሞሽ ነዉን? እና በመፅሃፉ ዉስጥ እንደዚህ ያሉ ሀረጎች (አክብሮት (ኹሹዕ)፣ እርካታ፣

ማረጋገጫ፣ሰላም፣ መረጋጋት እና ደህንነት) በሶላታችን ዉስጥ ከእያንዳንዱ ሐረግ በስተጀርባ እስካነበብናቸዉ ድረስ እንዴት አይደገሙም? እያንዳንዱን ቃል ያለ ልዩነት፣ ከአክብሮት፣ ከእርካታ፣ ከማረጋገጫ፣ ከሰላምና ደህንነት አንፃር ስለምንደጋግም፡፡

የምስራቃውያን ተመራማሪዎች በቅዱስ ቁርአን ላይ ከሰነዘሯቸው በርካታ ክሶች መካከል "በጣም ብዙ ጊዜ የተደጋገመ እስከ ማሰልቸት ድረስ› የሚል ነበር፡፡ ከዚህ ከነርሱ ግንዛቤ አንፃር የነፍስ ምት እና የቁርአን ቋንቋ ቅኝት ይለያል፣ የሶላት ቋንቋ ምትም እንዲሁም፡፡ እንዲሁም በእስልምና ውስጥ የአቶሚክ ውቅር ያለው የአምልኮ ምት ለማስቀመጥ ነዉ፣ እንዲሁም፣ በሁሉም ሃይማኖቶች ውስጥ የአምልኮን ምት መኖር እንዳለበት ለማድረግ ነዉ፡ ማንኛውም የአምልኮ ዘይቤ በሚያስቀምጠዉ መሰረት፡፡

በሶላት እና በሁሉም የአምልኮ ሥርዓቶች ዉስጥ መደጋገም እና ከዚያ ስለ ሶላት ወይም ስለ አምልኮ ማውራት እንደማንኛውም ሌላ ሰዋዊ ልምዶቻችን አይደለም፤ በቁርአን ውስጥ ያለው ድግግሞሽም እንደዚህ ተብሎ ሊጠራ እንደማይችል ሁሉ፡፡ በሶላት ውስጥ የማራዘሚያ ጊዜ ፣አትኩሮት፣ ትእግስት፣ ማስተንተን፣ መደጋገም ሳይኖር፣ እንዴት ለአክብሮታችን (ለኹሹዕ) ቦታ ይኖራል? በፆም ውስጥ ሰፋ ያለ ጊዜ ፣ አትኩሮት፣ ትእግስት፣ ማስተንተን፣ መደጋገም ሳይኖር፣ እንዴት ፆም ይሟላል? የሀጅ ስነ-ስርዓት ውስጥ ጊዜ ፣አትኩሮት፣ ትእግስት፣ ማስተንተን፣ መደጋገም ሳይኖር፣ ሀጅ እንዴት ሊከናወን ይችላል?
ሁሉን ቻይ የሆነው ኃያሉ አምላክ ስለ ሶላት አስቸጋሪነት ማረጋገጫ አልሰጠንምን? ከታጋሾች ሰጋጆች ውጭ ላሉት

وَإِنَّهَا لَكَبِيرَةٌ إِلَّا عَلَى ٱلْخَٰشِعِينَ ﴿٤٥﴾ البقرة : 45

" **እና በትሑታን ላይ በስተቀር እሷ ከባድ ናት** " ብሎ አፅዕኖት አልሰጠምን? [አል በቀረህ: 45]
ከዚያ በላይ በብዙ አናቅፅቶች፣ በሶላትና በአምልኮ እና፣ በሌላ በኩል በትዕግሥት መካከል ያለውን ኦርጋኒክ አንድነት አረጋግጦልናል፡፡ ሁለቱ ወገኖች ከአንድ የአቶሚክ እምብርት የሚያስተጋቡ እና ለአንድ ዓላማ የሚያገለግሉ ይመስላሉ፡፡ ይህም ነፍሳችን በቁሳዊ እና በመንፈስ፣ በምድር እና በሰማይ መካከል፣ በህይወት ምት እና በምድራዊው

ነፍስ ምት መካከል ያለዉን ሚዛን ወደነበረበት ለመመለስ ነው፡፡ ከዚያ የሕይወትን ውጊያ እንድንቋቋም እና ይህንን የእጣ ፈንታ ጦርነት እንድናሸንፍ ይረደናል ማለት ነዉ፡

وَٱسۡتَعِينُواْ بِٱلصَّبۡرِ وَٱلصَّلَوٰةِۚ ﴿٤٥﴾ البقرة: 45

‹‹ **እና በትዕግሥት እና በሶላት እርዳታ ይፈልጉ?** [አል-በቀራህ፡ 45]

فَٱعۡبُدۡهُ وَٱصۡطَبِرۡ لِعِبَٰدَتِهِۦۚ ﴿٦٥﴾ مريم : 65

"***ተገዛዉ፣ለአምልኮውም ታጋሽ ሁን***" [መርየም፡ 65]
ከዚህ እውነታ አንፃር ሶላት፣ ነፍሶቻቸው ፈጣኑን የሕይወትን ምት ለተቆጣጠሩት ለአንዳንዶቹ አድካሚ ሊሆን ይችላል፡፡ ይህንን ቁጥጥር ማምለጥ እና ከምርኮው ነፃ የመሆን ችሎታውን አጥተዋል ወይም መቋቋም አልቻሉም፡፡ እና በማንኛውም የሕይወታቸው ገጽታ ውስጥ እንኳን ከቀስታ እና ከተረጋጋ ምት ጋር የመላመድ ችሎታ ስለማይኖራቸዉ ፣ ከሶላት ወይም ስለ ሶላት መናገር ፣ ወይም ከቁርአን እና ሀዲስ ወይም ስለ ቁርአን መናገር ተስናቸዋል ፡፡

ሶላት የትእግስት ትምህርት ቤት ነው፣ እናም ዘመናዊ ህይወታችን፣ በሙሣሪያዋ እና በማሽኖቿ ልታቀናብር ብንተዋት፣ ትዕግሥት የምንጨርስበት ትምህርት ቤት ነው የሚትሆነዉ። ዋናዉ ነገር፣ ከሕይወት ፍጥነት ጋር መጓዛችንን መቀጠል የማይታለፍ አስፈላጊ መሠረት ከሆነ፣ በሁለቱ ትምህርት ቤቶች መካከል የስነ-ልቦና፣ የመንፈሳዊ እና የአካላዊ ደህንነታችን ሚዛናዊነት መጠበቅ አለብን ማለት ነዉ። እና ይህ መጽሐፍ በእውነቱ ከርዕሱ ጋር የሚሄድ ከሆነ፣ እና ከዚህ ርዕስ ባህሪ ጋር የሚስማማ ከሆነ፣ በተግባራዊ ለአተገባበር መስማማት ከቻለ፣ የእሱ ምት ከሶላት ምት ጋር ትይዩ መሆን አለበት፤ መንፈሳዊነቱም (የሶላት) መንፈሳዊነቱን (የመፀሃፉን)፣ እናም ማራዘሙ እና መረጋጋቱ፣ ማራዘሙ እና መረጋጋቱን፡፡ አነባበቡም በተመሳሳይ ሁኔታ ልክ እንደ ሶላት ዓይነት እንዲሆን ይፈለጋል ፡፡ አለበለዚያ፣ በዚህ መጽሐፉ ውስጥ ለማብራራት እንደሞከርነው ህይወታችን ሁሉም ሶላት አይደለችም እንዴ? እና ሁሉን ቻይ በሆነው በታላቁ መጽሐፉ ላይ እንዳረጋገጠው

وَمَا خَلَقۡتُ ٱلۡجِنَّ وَٱلۡإِنسَ إِلَّا لِيَعۡبُدُونِ ٥٦ الذاريات: 56

"የጂኖች እና የሰው ፍጥረታትን አልፈጠርኩም እንዲያመልኩኝ እንጂ" እንዳለዉ? (አዛሪያት፡56) ፡፡

ለማሳካት በምንሞክረው እያንዳንዱ ሥራ ዉስጥ የሶላትን መንፈስ ለምን አናሰራጭም፣ ስለዚህ በነፍሳችን ውስጥ እና በምንግባባበት መንገድ ሁሉ፣ ከከባድ ግዴታ ወደ ውድ መብት፣ከሸክም ወደ ሽልማት፣ እና ከኃጢአትና ከቅጣቱ፣ ወደ መልካምና ክፍያዉ ለምን አንለውጥም? በሕይወታችን ምት መሠረት የሶላታችንን ቅኝት እንዳናስተካክል ለምን የእራሳችንን ሽይጧን እንዲያሳምነን ፈቀድን? ለምን?
እኛ እንደየሶላታችን ምት የሕይወታችንን ምት ለማስተካከል አንሞክርም፡፡ ስለዚህ በሰጋጁ ሰው መንፈስ ለምን አናስብም፣ እናም በሰጋጁ መንፈስ አናቅድም፣ በሰጋጁ መንፈስ አንናገርም፣ በሰጋጁ መንፈስ አንሰራም፣ እንዲሁም በሰጋጁ መንፈስ ከሌሎች ጋር አንገናኝ ወይም አንደናርም፣ እና በሰጋጁ መንፈስ ለሚሳደቡን ሰዎች ምላሽ አንሰጥም?
በዘመናችን ያሉትን ብዙ ጭንቀቶቻችንን፣ ጉዳዮቻችንን እና ክስተቶቻችንን በሶላት ምት ውስጥ ብንመለከት ኖሮ፣ የሕይወታችን ጉዳዮች፣ ንግግራችን፣ ባህሪያችን፣ አስተሳሰባችን፣ ንባቦቻችን እና ጽሑፎቻችን ዉስጥ፣ የሶላት አስተዳደራችን ጋር ማገናኘት እንችል ነበር፡፡ እናም በትህትናው የምንሰግድ ከሆነ፣ ከክብሩ፣ ከመረጋጋቱ፣ ከትዕግስቱ እና ከትዕግስት መንፈስ ማዳበሩ አንፃር፣ ከዚያ ችግሮቹ ሁሉ በቀለሉልን፣ እና መፍትሄቹ በተገኙ፣ እናም በዱንያም ሆነ በመጨረሻው ዓለም የስኬት እና የብልጽግና መንገዶች በፊታችን በተከፈቱ ነበር፡፡

አየህ፣ ለሰፊው የሕይወት ፍሰት ከተሸነፍን፣ በየቀኑ እና በየሰዓቱ እየጨመረ እና እየተባዛ ለሚሄድ ፍጥነቷ ሱሰኛ ከሆንን፣ የሶላት አወቃቀር እና መጠን እንደገና እንድናጤን የሚመጣዉ ትውልድ እንዲነግረን ፈልገን ነዉ? የእሷ ምት ከዘመናዊ ህይወታችን እና ትዊቶቹ ምት ጋር እንዲመቻች? ስለዚህ፣ ልክ በመኪና ውስጥ ለመብላት እንደምንገዛው እና እንደምንበላው የተዘጋጀ ምግብ ሁሉ፣ ሶላታችን ፈጣን የአምልኮ ምግብ እንዲሆን ነዉን? ወይስ በዚህ ዓለም እና በዚያኛዉ ዓለም ውስጥ ብልጽግናችንን ማሳደድ ነበረብን? ወይስ በሕይወት ዘመናችን ውስጥ፣ ለልባችን፣

ለአእምሮአችን፣ ለነርቮቻችን፣ ለአካሎቻችን እና ለነፍሳችን ጤና ለመሆን፣ ህይወታችን እንደገና ለመገንባት እለታዊ ፕሮግራሞቻችንን ዘና ባለ፣ በተስተካከለ እና በተረጋጋ የሶላት ምት ማሳደስ ነበረብን? በመጨማሪም፣ ትዕግሥትን፣ ትኩረትን እና አክብሮትን (መተናነስን) ያስተማረን ሶላት፣ ልዩ የመሆነ እርካታን፣ ጸጥታን፣ ፈውስን እና መረጋጋትንና ደህንነትን ይሰጠናል ማለት ነዉ? እና ስኬትን፣ ብልጽግናን እንዲሁም የዚህ ዓለም እና የወዲያኛው ዓለም ትርፍን ለማግኘት ፕሮግራሞቻችንን ማሳደስ አይኖርብንም?

የተከበረውን የቁርአን "መጠን" እንደገና እንድናጤነው የሚቀጥለው ትውልድ ይመጣልን? በዘመናዊው ህይወታችን ውስጥ ረጅም ጊዜ ያላቸዉ እነርሱ ስለሆኑ፣ ሰፋ ያሉ ፕሮግራማችን ለማስተናገድም ሰፋፊ ስለሆኑ? ስለሆነም ከዚያ ጋር የሚመጣጠን አጭር ቅጅ እናገኛለን? እንደዚያ ሲሆን፣ በፅሑፍ መልእክቶቻችን ቋንቋ፣ በትዊተሮቻችን፣ በስራ እና በፍላጎት በተሞሉ የፕሮግራማችን ባህሪዎች እና ለትላልቅ መጽሐፍት ቦታ የሌላቸው ዕለታዊ ግንኙነቶች እና ቀጠሮዎች ጋር በሚስማማ አጭር ቅጅ አንመጣለን ማለት ነዉን?

የተከበረውን ቁርአን ወደ አስር ወይም ሃያ ገጾች ብናወርደው ምን ይሆን ነበር? ብዙ መለኮታዊ ሀዲሶችን ወይም ረዣዥም ትንቢታዊ ዉዳሴዎችን ወደ ጥቂት ቃላት ብናጠቃልል ኖሮ ምን ይሆን ይችላል? የሚከተለውን ጥያቄዬን ከመጠየቄ በፊት ይህንን ቀልብ የሚስብ የቁድሲይ ሐዲስ ከእኔ ጋር ያንብቡ፦

- **ከነቢዩ (ሰለላሁ አለይሂ ወሰለም) ከተባረከዉ እና ከኃያሉ ከአሏህ በዘገበዉ እንዲህ ብሏል፡ "ባሮቼ ሆይ ! እኔ በደልን (ጭቆናን) በእራሴ ላይ ከተከለከሉት ነገሮች መካከል አስቀምጠዋለሁ፣ በመካከላችሁም እርም (ክልክል) አድርጋለሁ፤ ስለዚህ አትበዳደሉ፣ ባሮቼ ሆይ! ሁላችሁም አመፀኞች ናችሁ፣ እኔ የመራኋቸዉ በስተቀር፣ ምረት ጠይቁኝ እመራቸኋለሁ፤ ባሮቼ ሆይ ! ሁላችሁም ረሃብተኞች ናችሁ እኔ ያበላኋቸዉ በስተቀር፣ ማብላትን ጠይቁኝ ኣበላቸኋለሁ፤ ባሮቼ ሆይ ! ሁላችሁም ራቁታቸውን ናችሁ፣ ካለበስኳቸው በስተቀር፣ ማልበስን ጠይቁኝ አለብሳቸኋለሁ፤ ባሮቼ ሆይ! ፣ እናንተ በሌሊት እና ቀን ስህተት ትፈጽማላችሁ፣ እኔ ሁሉንም ኃጢአቶች ይቅር እላለሁ፣ ስለዚህ ምህረት ጠይቁኝ ይቅር እላቸኋለሁ፣**

**ባሮቼ ሆይ! እናንተ እኔን መጉዳትን ልትጎዱኝ አትችሉም፣ እናም ጥቅሜን ልትጠቅሙኝ እትችሉም፣ ባሮቼ ሆይ! ከእናንተ የመጀመሪያ እና የመጨረሻ፣ ሰዎችም ጅኖችም፣ በአንድ ሰዉ ልብ ዉስጥ ያህል ፈሪሀ-አሏህ ሆነዉ ቢሰበሰብ ፣ ያ ለንግስናዬ ምንም አይነት ነገር ወይም ቅንጣትን ያህል አይጨምርም ፤ ባሮቼ ሆይ! ከእናንተ የመጀመሪያ እና የመጨረሻ፣ ሰዎችም ጅኖችም፣ በአንድ ሰዉ ልብ ዉስጥ ያህል አመፀኛ ሆነዉ ቢሰበሰብ ፣ ያ ከንግስናዬ ምንም አይነት ነገር ወይም ቅንጣትን ያህል አይቀንስም፣ ባሮቼ ሆይ! ከእናንተ የመጀመሪያ እና የመጨረሻ፣ ሰዎችም ጅኖችም፣ በአንድ ሜዳ ላይ ሆነዉ ቢጠይቁኝ እና ለያንዳንዱ ሰዉ የጠየቀዉን ብሰጥ፣ ያ ከንግስናዬ ምንም አይነት ነገር ወይም ቅንጣትን ያህል አይቀንስም ፣ ልክ መርፌ ባህር ሲገባ ከዉሃዉ የሚቀንሰዉን ያህል ከቀነሰ እንጂ፤ እኔ ሥራዎቻችሁን ነዉ የምቆጥርላችሁ፣ ያንኑ ነዉ የሚሰጣችሁ፣ መልካሙ ነገር ያጋጠመዉ ሰዉ፣ ፈጣሪዉን ያመስግን፤ ከዚያ የተለየ ነገር ያጋጠመዉ ሰዉ፣ በእራሱ እንጂ በሌላ ሰዉ እንዳያማርር** [ሙስሊም ከአቡ ዘር አል-ግፋሪይ የዘገከ **]። ሰኢድ ኢብን አብዱልአዚዝ እንደተናገሩት** -እሳቸዉ ከሐዲሱ ተራኪዎች አንዱ ናቸዉ- **አቡ ኢድ ሪስ አል-ካውላኒ - - -** እንዲሁም ከሐዲሱ ተራኪዎች ሰንሰለት ውስጥ አንዱ የሆኑት- **ይህንን ሐዲስ ሲናገሩ በጉልበታቸዉ ተንበርክኮ ነበር-** አሉ፡፡

የዚህን የረጅሙ ሀዲስ አል ቁድሲይ ትርጉም በእንደዚህ ዓይነት መንገድ የሚቀጥሉት ጥቂት ቃላት ማጠቃለላችን ለማናችንም ቀላል እንደሆነ አያጠራጥርም፡፡ ምንአልባትም በትንሽ ቃላት፡ (ባሮቼ ሆይ አትጨቋቋኑ፣ ብትጠይቁኝ እሰጣችኋለሁ፤ መስጠቴ በንግስናዬ ምንም አይቀንስም፤ እናንተ አጥቅሙኝም አትጎዱኝም፤ ነፍስም ሁሉ በስራዋ መጠን የሚትጠየቅ ትሆናለች) ቢል፣ ከሐዲሱ መሠረታዊ ትርጉሞች ውስጥ አንዳች ነገር ይቀር ይሆን? እኔ አይመስለኝም፣ ግን እያንዳንዳችን እራሳችንን እንጠይቅ፡ አቡ ኢድሪስ አል ካውላኒ ወይም ማናችንም ይህንን ሐዲስ በአጭር ቃላቱ ሲሰሙ በጉልበታቸው ይንበረከካሉን? አቡ ኢድሪስ አሁን እንደለመደዉ?

ካውላኒ ይህንን ሐዲስ ሲያነቡት (ሲደጋግሙት) በሶላት ውስጥ እንዳሉ ተሰምቶዋቸዉ፣ እራሳቸዉን ቀስ በቀስ “ልዩ ሶላት” ድባብ ዉስጥ ሆኖ ያገኛሉ፡፡ ስለዚህ ሁሉን ቻይ ለሆነው አምላክ በፍርሃት፣ በአክብሮት እና በውርደት ይንበረከካሉ

ማለት ነዉ። የሰው ልጅ ሰዋዊ ቀመር ያንን መንፈሳዊ ጥራትን ከሐዲሱ ስለነጠቀ፣ ‹የተቀደሰ› ኃይሉን አጥቶ፣ ወደ ፍርሃት፣ እርጋታ፣ መከጀል እና መንበርከክ ከሚስበን ‹ሶሎት› ወደ መደበኛ የዜና ዘገባ፣ ወይም ልክ አንድ ፈጣን 'ትዊተር' የሚጋብዝ ብቻ ተለወጠ፡፡

ሶላታችን ወደ ትዊተር፣ እና ሁሉን ቻይ የሆነው የአሏህ መጽሐፍ ንባባችን ወደ ትዊተር፣ ውዳሴያችን እና ጸሎታችን እና ትዝታዎቻችን ወደ ትዊተር፣ ንባባችን፣ ባህላችን፣ ሳይንሳችን፣ ሰብአዊ ግንኙነታችን፣ ስሜታችን እና ማህበራዊ ንግግራችን፣ የዕለት ተዕለት ኑሮውኣችን ትዊት ብቻ ሆነ፡፡ ስለዚህ የትኞቹ "የሰው" ንጥረ ነገሮች በውስጣችን ይቀራሉ፣ እና ለራሳችን የምንተወዉ የተፈጥሮ ምሰሶዎች ምንድናቸው? ለራሳችን እምቅ የሰው ልጅ ደቃቃ ስሜት መሰረቶች፣ በዚህ ዓለምም ሆነ በመጨረሻይቱ ዓለም ስኬታማ እንድንሆን መንገዱን የሚጠርግልን መንፈሳዊ ሀይል ምን ተወዉን ?

እኔ የትዊተር እና ትዊተረኞች ተቃዉሞ የሌብኝም፤ እንዴት፣ እኔ እራሴ ከእነርሱ አንዱ ሆኜ? ስማርት ስልኮችንም አልቃወምም፤ እና ከማንኛውም ዘመናዊ የመገናኛ ዘዴዎች ጋር ተቃርኖ የሌብኝም፡፡ ግን፣ እኛ የምንቆጣጠራቸው እና እኛን የማይቆጣጠሩን ከሆነ፣ እና እኛ ፕሮግራም የምናደርጋቸዉ እኛን ፕሮግራም የማያደርጉን ከሆነ፣ ጊዜዎችን ለመቆጠብ፣ ጊዜዎቻችን ላለማጥፋት፣ እንዲሰጡንም እና እንዲያበለፅጉንም አይደለም፣ ከእኛ እንዲወስዱም እና እንዲነሱንም፣ ገንዘብ እና ንብረት እንዲወስዱብንም አይደለም፡፡ ይልቁኑ፣ የምለው ጊዜያችንን፣ የአእምሮ መረጋጋትን፣ ልባችንን፣ ዕድሚያችንን እና ሕይወታችንን እንዳይሰርቁብን ነዉ፤ ባጠቃላይ በጣም አደገኛ የስርቆት ዓይነት፡፡ ይህ በደረታችን ውስጥ ያለዉ ትንሹ ጡንቻ፣ ማለትም ልብ፤ በደካማ እና ውስን አቅሙ፣ የተንቀጠቀጡ፣ ደቃቃ እና ፈጣን ጅማቶቹ፣ ደካማ ግፊቶች እና በትክክል የተሰላ ጉልበቱ፣ እና ይህ ደግሞ በጭንቅላታችን ውስጥ ያለው ትንሹ አንጎል፣ ከነለስላሳ እና ትናንሽ ፀጉሮቹ፣ እና በፍጥነት ከሚያልቁ የተጎዱ ህዋሶቹ፣ ከነግዝፈታቸው፣ ጥንካሬያቸው እና ቅቡልነታቸዉ፣የተፈጠሩት ዛሬ በዓለም ላይ እየታዩ ላሉት ክስተቶች አልነበሩም ፡፡ እናም ዜናዉ በተለያዩ ፈጣን መንገዶች እና ተከታታይነት ወደ እኛ ከመድረሱ ጋር፣ በድምጽም እና በምስልም፣ በሁሉም የዓለም ሀገሮች ምን እየተከናወነ እንዳለ ከንዉኖችን በደቂቃዎች ውስጥ የሚሸፍኑ ፈጣን

ግንኙነቶች፣ ክስተቶች፣ ጦርነቶች፣ ሐዘኖች፣ ወንጀሎች፣ የግለሰብ እና የጋራ ተፈጥሯዊ እና ተፈጥሮአዊ ያልሆኑ አደጋዎች ይደርሱናል፡፡ ስለሆነም ለእነዚህ ሁለት ጥቃቅን መሳሪያዎች ደህንነታቸውን የሚጠብቅ፣ ሁኔታቸዉን የሚያረጋጋ፣ ሕብረ ሕዋሳቶቻቸውን ውጥረት የሚያስወግድ፣ ወደየተግባራታቸዉ ሥርዓት የሚያስመልሳቸዉ ነገር አይኖርም፤ በሁሉም ዓይነት አምልኮቻችን ዉስጥ ቀለል ያሉ መለኮታዊ ምቶች፣ ዋናዎቹም፡ ሶላት፣ ንባብ፣ ዉዳሴዎች እና ፀሎቶች በስተቀር፡፡

ኦክስፎርድ፣ አርብ ጧት ፣ ታሕሣስ 26፣ 1439,

ከየካቲት 9 ቀን 2018

## ቀጠሮ ከአሏህ ጋር

አንዱ በአግራሞት እንዲህ አለኝ፡-ሶላትን ማስተዳደር?! ለሶላት አስተዳደር አለን?! እኔ እንዲህ አልኩ፡ የዓለም የንግድ ሥራ አመራርን የሚያጠኑት የተሻለ ፍሬ እንዲያፈራ ማድረግ እና የሚፈልጉትን ትርፍ ለመሰብሰብ ከሆነ፣ የሚያልፍ ትርፍ ቢሆንም፣ ለምን ለኣኺራ ሥራዎችም ማስተዳደር አይኖራቸዉም፣የተሻለ ፍሬ እንዲያፈራልን፣ ከፍተኛውን ትርፍ ለመሰብሰብ/ለማጨድ፤ እንዴት አይቻልም፣ ትርፉ የማያልቅ እና የማይቀለበስ ሽልማት ሆኖ ሳለ? ለኢንቨስትመንት( ልማት)፣ ለመልካም አስተዳደር እና ለቁጠባ የሚበቃ ንግድ፣ እንደ ሶላት ያለ የዚህ ዓለም እና የኣኺራ ሥራን ለማስቀመጥ ምቹ የሆነ ነገር አለን?

አንድ ቀን በረመዷን ዉስጥ በኦክስፎርድ የሚገኘው የሳውዲ የተማሪ ማህበር ኢፍጣር ላይ ንግግር እንዳደርግ ጋበዞኝ ነበር፡፡ ስለዚህ ስለ (ሶላት ማስተዳደር) ከእነሱ ጋር ለመነጋገር መረጥኩ ፡፡

በቀጠሮው ሰዓት ስለ ሶላት ሁለት ጥቅሶችን እና ሁለት ሀዲሶችን የፃፍኩበትን ወረቀት ይዤ ወደ መድረክ ላይ ወጣሁ ፡፡ መደበኛውን ሰላምታ አደረስኩ፤ ከዚያም ወረቀቱን ከፈትኩ እና በውስጧ ያለዉን መረዳት በማይችሉበት ፍጥነት አነበብኩ ፡፡ በአንድ ደቂቃ ውስጥ ወረቀቱን አንብቤ ጨረስኩና ወረቀቷን በችኮላ ፍጥነት ጠቅለልኩ እና እየፈጠንኩ መድረኩን ለመልቀቅ: ለዚህ ጥድፊያ ይቅርታ እጠይቃለሁ፣ ግን አሁን ትቼያችሁ ልሄድ ነዉ፣ ከእናንተ የበለጡ አስፈላጊ ሰዎች ጋር ግዴታ ቀጠሮ አለብኝ .. ሰላም ለእናንተ ይሁን ..ብዬ ሻንጣዬን ወስጄ ወደ በሩ እየሮጥኩ፣ በዓይኖቼ ጫፍ የመደንገጥ ምልክቶች እያየሁ፣ ምላሶቻቸው ተሳሰረዉ፣ ከፊታቸውም ላይ የተቃውሞ፣ የመገረም እና ያላማመን ድብልቅ፣ እና ምንአልባትም አለመቀበል እና መበሳጨት እየታየ ወጣሁ..

ከጥቂት ሰከንዶች በኋላ ለተከሰተ ነገር ይቅርታ ለመጠየቅ ወደ ተማሪዎች ተመልሼ መጣሁና: ተናደዳችሁብኝ እንዴ? ደህና ፣ ይህን አንድ ጊዜ ነው ከእናንተ ጋር ያደረግሁ፣ እና በይቅርታ ተመለስኩ፣ ግን እኛ በየቀኑ አምስት ጊዜ ከአሏህ ጋር እንደዚያ እናደርጋለን ፡፡
ከዚያም ይቅርታ እየጠየቅን ወደሱ በጭራሽ አንመለስም ፡፡

ቃል በገቡላቸው ሰዎች ላይ እንዲህ ባለ ጠባይ ጨዋነት የጎደለው ባህሪይ ላይ እንደዚያ ዓይነት ምላሽ ከሰው ልጅ ሲያጋጥመዎ፣ ይህንን ከአሏህ ጋር ብናደርግ ምላሹ እንዴት ሊሆን ይችላል ብለው ያስባሉ?

ምን ዓይነት ጥሩ አጋጣሚ፣ ምን ዓይነት ታላቅ ቀጠሮ፣ ምን ዓይነት የተከበረ ቀን በእጅዎ የሚያበላሹና በጊዜዎ በአሏህ ላይ የምነፍጉት እና እንደዚህ የመሰለ ሶላት የሚፈፅሙት ፣ ያም ሶላት ናት ብለን መጥራት ትክክል ከሆነ?

ለሳዑዲ ተማሪዎች ጥቅሶችን እና ሐዲሶችን በእጄ ከያዝኩት ወረቀት እንጂ ከአእምሮዬ/ ከትዝታዬ እንዳላነበብኩ አስተዉሎዋልን? ለአድማጮች የትኛው ነው የበለጠ ውጤታማ? በወረቀት ላይ ለእነሱ ማንበብ ወይም የሚፈልጉትን መናገር ይሻላል? ብዙውን ጊዜ በሶላታችን ዉስጥ በወረቀት ላይ በሚያነቡ ሰዎች ዓይነት ነው የምናነበው፡፡ ምክንያቱም ከከንፈሮቻችን የምትወጣ ንባብ ናት እንጂ ከአእምሮዋችን/ከልባችን የምትወጣ አይደለችም፡፡ እና ከከንፈሮቻችን ወደ አሏህ በመስገድ እና “በልቦናችን” ማንበብ መካከል ልዩነቱ ምንኛ ትልቅ ነዉ!

ሁሉን ቻይ የሆነዉ አሏህ ሁሉን አቀፍ በወርቅ ሳህን ላይ ያቀረበልን ግዙፍ የኢንቨስትመንት (ልማት)ፕሮጀክት እና ግን በግዴለሽነት ያለ ምክንያት ውድቅ አደረገን፣ እና በባዶ ተመለስን፣ በጭራሽ ምንም ሳይኖረን፡፡ የምንጠብቀዉ ነገር ካለ፣ ከራሳችን ጋር ሎጂካዊ የምንሆን ከሆነ፣ አንድ ነገር ነዉ፣ ከተቃውሞው እና ከአመፅ፣ ምንአልባትም ቅጣት በስተቀር ምንም የለም፡፡ ለዚያ ሰላምታም ቢሆን፣ ከሰላምታ ይልቅ ወደ ፊዝ የተጠጋ ነበር ተጋባራችን? ግን ከማን ጋር?

ከሥራ የሚያደናቅፍዎ አምልኮ ኑሮዎን አያሳጣዎትም እንዲሁም ከአምልኮት የሚያደናቅፍዎ ሥራ አይጠቅምዎትም፣ ይልቁንም ይጎዳዎታል፡

**- ኃያሉ አሏህ ይላል፡ የአደም ልጅ ሆይ! ለአምልኮዬ ተለይ፣ ደረትህን በሀብት እሞላለሁ፤ ድህነትህን እጋርድልሃለሁ፤ ያን ካላደረክ እጆችህን በጭንቀት እሞላለሁ፣ ድህነትህን አልጋርድልህም/አልመልስልህም** (ከአቡ ሁረይራ (ረ.0) በአል-ቲርሚዚይ የተዘገበ ሲሆን አል-አልባኒም አረጋግጦታል)።

እራሳችንን፣ሥነ ሥርዓቶቻችንን እና በዙሪያችን ያሉትን ነገሮች እንደገና መፈለግ እና ወንዶች፣ ሴቶችና ልጆችን በዙሪያቸው ያሉትን ሁሉንም ነገሮች እንዲያስተነትኑ የሚረዳቸዉ የእውቀት ዘዴ ላይ ማሳደግ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ ያ ማለት በእጃቸው ያሉት እነዚህ ፈጠራዎች እንኳን ሳይቀር፣ ከወግ አጥባቂዎች እና የባህላዊ ሰዎች ደረጃ ወደ አሳቢዎች እና የተሃድሶ አራማጆች እንዲሻገሩ ከፈለግን ማለት ነዉ፡፡

በአርባዎቹ መገባደጃ ላይ አስታውሳለሁ በሰባት ወይም በስምንት ዓመቴ እናቴ፣ አሏህ ምህረቱን ይስጣትና በከተማዬ (ላዚቂያ) የክርስቲያን ቤተሰብን ወዳጇን ጎብኝታ ተመልሳ ስትመጣ፣ ልጃቸዉ ከፈረንሳይ ይዞ ስለመጣ “አስደናቂ ሬዲዮ” አጫወተችን፡፡ እዚያ ትምህርቱን ከጨረሰ በኋላ፡፡ እናቴ በጭራሽ የማይረሳቸውን ቃላት፡ በዚህ “ሬዲዮ” ዉስጥ የሚናገረውን ሰው ማየት የሚችሉበት መስኮት አለ!ብላ ነገረችን፡፡

በዚህች ሳጥን ውስጥ “ስላጨናነቁት” እና ስለ ቆለፉበት ምስኪኑ ዘጋቢ ትንሹ ልጅ እያሰብኩ በዚያ ሌሊት መተኛት አልቻልኩም፡ እንዴት አድርገዉ እዚህ ዉስጥ ሊያኖሩት ቻሉ? በአካል በጣም ትንሽ የሆነዉን መርጠውት መሆን አለበት ሳጥኑ ዉስጥ ለማስገባት የቻሉት፤ ደህና ፣ ግን ፣ ምስኪኑ ሰውዬዉ እንዴት ይችላል ..? ይቅርታ ፣ እኔ ትንሽ ልጅ ሆኜ እንደዚህ ነበር የማስበዉ፡፡ እንዴት ይበላል? የት ይተኛል? ማታ ወደ መጸዳጃ ቤት እንዴት ይወጣል? እናም መቶዎች ከእንደነዚህ አይነት ጥያቄዎች በዚያች ሌሊት ተራ በተራ እየመጡብኝ እንድተኛ አልፈቀዱልኝም እና ከዚያ በሀሳቤ እየተንከባለልኩ ቀጠልኩ ፡፡ በመጨረሻ “ቴሌቪዥን” መሆኑን ከማወቄ በፊት ለረጅም ጊዜ ሲያሳስበኝ ነበር፡፡

ሳስበዉ የነበረ ነገር፣ የአቅራቢው ምስል በሬዲዮ መስኮቱ ውስጥ የሚታየው በምን ዓይነት ትርጓሜ ነዉ፣ በየትኛው አተረጓጎም፣ ምስሉ በሽቦዎች በኩል እየገሰገሰ ከሆነ በቀር ፣ እንዲዉም በጭራሽ ያለ ሽቦዎች፣ ከዓለም መጨረሻ እስከ መጨረሻ..አይቻልም እያልኩ ማሰቤን ቀጠልኩ፡፡

ልጆቻችን አሁን የሚወለዱት በፊታቸዉ፡ ሬዲዮ፣ ቴሌቪዥን፣ ኮምፒተር፣ ስማርት ስልኮች ፣ ዲስኮች እና ሳተላይቶች የኢንዱስትሪ ማሽኖች፣ አውሮፕላኖች፣ መኪኖች እና አስደናቂ የኤሌክትሪክ መሳሪያዎች በቤታቸው እና ከቤታቸው ውጭ ሆነዉ ነዉ፡፡

እናም ስለ እነዚህ ግኝቶች እና ታላቅነታቸዉ፣ የፈጠራቸው እና ያገኙዋቸው ሰዎች ታላቅነት እና ስለወቅቱ ታላቅነት እያሰቡ ያድጋሉ፡፡ የእነዚህን ነገሮች ታላቅነት እንደገና ለማጣራት፣ ታላቅነትን ለመፈለግ የሚሰጣቸዉ ሥልጠና የነዚህ ፍጥረታት ፈጣሪዎች እና እንዴት እንደፈጠሯዉ የፍጥረትን ታላቅነት በራሳቸው እና በአካባቢያቸው/በዙሪያቸው ውስጥ እንደገና እንዲያገኙ ይመራቸዋል ፡፡ እና በዚህ ፍጥረት ውስጥ የአሏህን ታላቅነት እንደገና ወደ ማወቅ፣ ከዚያ እራሳቸውን፣ ሃይማኖታቸው እና አምልኮቻቸውን እንደገና እንዲያወቁ ይመራቸዋል፡፡ ስለዚህ ስለህይወት ቀድመዉ የሚያዉቁትን፣ የለመዱትን እና ሁል ጊዜ የሚታያቸዉን አቧራን ያራግፋሉ፤ በዓይኖቻቸው ውስጥ ሁል ጊዜ አዲስ እንድትሆን፣ ለመጀመሪያ ጊዜ እንደሚያውቋት ወይም እንደሚለማመዱዋት አይነት ነገር፡፡ ከቁርአን ሰዎች መካከል ከሆንን፣ ቅዱስ ቁርአን ያሰለጠነን በዚህ መንገድ ነው፣ በብዙ ጥቅሶቹ ውስጥ “እንደገና የማግኘት/የማወቅ” ተግባርን ነዉ ያሰለጠነን፡፡

ٱلَّذِى خَلَقَ سَبۡعَ سَمَٰوَٰتٍ طِبَاقًاۖ مَّا تَرَىٰ فِى خَلۡقِ ٱلرَّحۡمَٰنِ مِن تَفَٰوُتٍۖ فَٱرۡجِعِ ٱلۡبَصَرَ هَلۡ تَرَىٰ مِن فُطُورٍ ﴿٣﴾ ثُمَّ ٱرۡجِعِ ٱلۡبَصَرَ كَرَّتَيۡنِ يَنقَلِبۡ إِلَيۡكَ ٱلۡبَصَرُ خَاسِئًا وَهُوَ حَسِيرٌ ﴿٤﴾ الملك:3-4

**- ያ ሰባት ሰማያትን አነባብሮ የፈጠረ፣ እጅግ በጣም ሩህሩሁ (አራህማን) በፈጠረዉ ዉስጥ ምንም መዛነፍን አያዩም ፡፡ ከዚያ ዐይንዎን መላልሰዉ ይመልከቱ ከስንጥቆቹ ኣንዳችን ያያሉ? አሁንም ብዙ ጊዜ ዐይንዎን ይመላልሱ ፣ ዐይንዎ የተዋረደ እና የተዳከመ ሆኖ ወደ እርስዎ ይመለሳል** (አልሙልክ፡ 3 - 4)

أَوَلَمۡ يَرَوۡاْ إِلَى ٱلطَّيۡرِ فَوۡقَهُمۡ صَٰٓفَّٰتٍ وَيَقۡبِضۡنَۚ مَا يُمۡسِكُهُنَّ إِلَّا ٱلرَّحۡمَٰنُۚ إِنَّهُۥ بِكُلِّ شَىۡءٍۭ بَصِيرٌ ﴿١٩﴾
الملك : 19

**- ወደ አእዋፍ በላያቸው ክንፎቻቸዉን ዘርግተዉ ተንሳፋፊዎች የሚሰበሰቡም ሲሆኑ አላዩምን ? ከአረህማን በቀር (በአየር ላይ) የሚዛቸዉ የለም** [አልሙልክ፡ 19]

قُلۡ أَرَءَيۡتُمۡ إِنۡ أَصۡبَحَ مَآؤُكُمۡ غَوۡرًا فَمَن يَأۡتِيكُم بِمَآءٍ مَّعِينٍۭ ﴿٣٠﴾ الملك: 30

**- አያችሁን? ዉሃችሁ ሰራጊ ሲሆን ፈሳሽን ዉሃ የሚያመጣላችሁ መነዉ?** [አልሙልክ፡ 30]

ይህ የቁርአን አካሄድ አብዛኞቹን ሱራዎችን እና አንቀፆችን ያደራጃል፤ ስለዚህ በዚህ ዘዴ ላይ የተፈጠረው ህብረተሰብ እራሱ እና አካባቢያቸው “እንደገና በማወቂያ” ሁኔታ ውስጥ ይኖራል፤ ከዚያ በኋላ በስልጣኔ እና በእምነት ሁኔታ ከትውልድ ትውልድ ቀጣይነት ባለዉ መልኩ ያለማቋረጥ ይደግማል:: በየቀኑ ጠዋት ዓይናችንን እራሳችን ለመፈተሽ እና በዙሪያችን ያለውን ዓለም ለመጀመሪያ ጊዜ እንደምናየው በአዲስ መነፅር እንድንመለከት ተጋብዘናል፤ በዚያን ጊዜ ምን ያህል በነዚህ መነፅሮች ወደ አሏህ እንደተቃረብ እናያለን..

በሕዝባዊ ሕይወታችን እና በእኛ የትምህርት እና የዩኒቨርሲቲ ክበቦች ውስጥ የተለያዩ የትምህርት ዓይነቶች እና የአስተዳደር ሳይንስ መስኮች ተስፋፍተዋል፡፡ ይህ በኢንዱስትሪ ፣ በንግድ፣ በግብርና እና በግንባታ ፕሮጀክቶች ላይ ኢንቬስት የማድረግ ምርጥ እና የተሻሉ መንገዶችን በማጥናት ያሳስባል፡፡ በመንግስትም ይሁን በግል ትርፍ ሊያመጣ የሚችል እና ለሰዎች ጥቅም ሊያመጣ በሚችል ነገር ሁሉ ላይ ኢንቬስት ማድረግ እንዳለብን መቼም እናስባለን፡፡ በትምህርት ቤቶቻችን፣ በተቋማት ወይም በዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ ከዚህ በተሻለ ኢንቬስት ለማድረግ አንድ ልዩ መስክ፣ የበለጠ ጠቃሚ፣ ረዘም ላለ ጊዜ የሚቆይ፣ ውጤታማነቱ ይበልጥ የተረጋገጠ እና ለዓለምም ሆነ ለመጪው ዓለም አጠቃላይ ጥቅም ያለዉን ትምህርት ወይም ፕሮጀክት ለመፍጠር አስበናል? ይልቁኑ ፕሮጀክቱ ለእነዚህ ጊዜያዊ ዓለማዊ ፕሮጀክቶች ስኬታማነት መሠረታዊ ነገር ነው:: ያም የአምልኮ ሥርዓቶችን ማስተዳደር እና እንደገና መፈተሽ ነዉ:: እና ከፕሮጄክቱ ዉስጥ ዋነኛዉ የሶላት ማእዘን ነዉ፡፡ እሱም፡ ከአሏህ ጋር ቀጠሮ ነዉ፣ ግን ምንም ዓይነት ቀጠሮ?

ይህ በአምልኮ ዝርዝሮቻችን አናት ላይ ያለ ስብሰባ ነው፣ ወይም የእኛ ሥነ-መለኮታዊ ዓለማዊ ኢንቨስትመንቶች። የጂሃድ ግዴታ ቅደም ተከተል፣ አድካሚ፣ ውድ እና አደገኛ ተግባር የሆነዉ፣ በኢስላማዊ ህግ ውስጥ የመጀመሪያው እና ሁለተኛው ሆኖ ካልመጣም አይደነቁ፡፡ ጂሃድ በሦስተኛው ቅደም ተከተል ነዉ የመጣ፣ የወላጆች ጽድቅ እራሱ ከጂሃድ በፊት በመምጣቱ፣ እና ከሁሉም በፊት ሶላት በሰዓቱ የሚል በመምጣቱ አይደነቁ ማለቴ ነዉ፡፡

**- ከአብደላህ ቢን መስዑድ (ረ.ዐ) እንዲህ አለ፡ የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ጠየኩ፡ ለአሏህ በጣም ተወዳጅ የሆኑት የትኞቹ ተግባራት ናቸው? እሱም አለ፡ ሶላት በሰዓቱ ነው፤ ከዚያስ ምን አልኩ? እርሱም፡እንግዲያውስ ወላጆችን ማክበር ነዉ፤ እኔም አልኩ፡ ከዚያስ ምን? እርሱም፡ከዚያ በአላህ መንገድ ትግል (ጅሃድ) ማድረግ ነዉ›** አለ [በሙስሊም የተዘገበ]

ይህ ግሩም ሐዲስ ነው፣ አብዛኞቻችንም የኩራት መተላለፍ ብናልፈዉም ፡፡ ሶላት በትዕግሥት፣ በጽናት፣ በበጎነት፣ በሽልማት፣ በብዙ እጥፍ ጂሃድን የመብለጥዋ አስፈላጊነትን ቆም ብለን ማሰብ እና ማስተዋል አለብን፡፡ በተለይም ጌታችን እሷ (ከባድ) ናት ብሎ ገልፀዋታል እና ግን (ትሁት የሆኑትን) አወጥተዋል የሚለዉን ማሰብ አለብን፡፡ የሚተናነሱት ሰዎች ከባድ ናት ብለዉ አያስቡም፤ በአክብሮታቸው (በኹሹእ) ደስታን፣ ማበረታቻን፣ መጽናናትን እና በሕይወታቸው ውስጥ የሚደገፉበትን የማይበገር ግድግዳ ስለሚያገኙ፡፡ በዚህ በማንበብ፣ በእንቅስቃሴ እና በሚያንፀባርቁት የአክብሮት፣ የመረጋጋት እና የትዕግሥት ቁርጠኝነት በተጨማሪም፣ በትዕግስት እና በአእምሮ ትኩረት፣ በማዳመጥ፣ በመተናነስ፣ የሌላውን በጥሩ በመቀበል፣ እሱን በደንብ በማዳመጥ ፣ የነርቮች መረጋጋት እና ውሳኔዎችን ለማስተላለፍ ትዕግስት እና ብስለት ላይ ለመሠልጠን መንፈሳዊ ትምህርት ቤት ናት፡፡ እናም የአመለካከት ልከኝነት፣ በፍርድ ውሳኔዎች ግትርነት እና  አክራሪነት አለመኖር፣ ከሰዎች እና ከህይወት ጋር የመግባባት ጥበብ ያስፈልጋል ማለት ነዉ፡፡ እንግዲያውስ ሁሉን ቻይ የሆነው አምላክ በነዚህ አንቀፆች ትዕግሥትንና ሶላትን አንድ ላይ መቋጠሩ አይገርምም፡

وَٱسۡتَعِينُواْ بِٱلصَّبۡرِ وَٱلصَّلَوٰةِۚ وَإِنَّهَا لَكَبِيرَةٌ إِلَّا عَلَى ٱلۡخَٰشِعِينَ ﴿٤٥﴾ البقرة: 45

**- በትዕግሥትንና በሶላት እገዛን ፈልጉ፡፡ ከባለ ትሕትናዎች በስተቀር እሷ ከባድ ነችና** [አል-በቀራህ ፡45]

وَأۡمُرۡ أَهۡلَكَ بِٱلصَّلَوٰةِ وَٱصۡطَبِرۡ عَلَيۡهَاۖ ﴿١٣٢﴾ طه: 132

**- ቤተሰብዎ እንዲሰግዱ እዘዝ፤ በእሷ ላይም ዘዉትር (ፅና)** [ጧሀ፡ 132]

ሆኖም፣ ይህ ስለ ሶላት ድንጋጌዎች፣ እንዲሁም በእነዚህ ጉዳዮች ላይ በአስተሳሰብ ት/ቤቶች መካከል የሕግ ክርክር መጽሐፍ አይደለም፡፡ ወደነዚህ ውዝግቦች እና ዝርዝሮቹ ውስጥ ስለሚያገባኝ ነገር ሁሉ ላለመናገር የተቻለኝን ሁሉ ሞክሬያለሁ፡፡

በአጭሩ መንገድ ወደ መጽሐፉ ዋና ዓላማ ለመድረስ፡ ይህንን ሁለተኛውን ታላቅ የእስልምና ምሰሶ እንደገና መፈተሸ ብቻ ነዉ ትግሌ፡፡

ሶላትን ማስተዳደር ህይወትን ማስተዳደር ነው፡፡ የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ለእኛ ያስከፈቱን ይህንን አስደናቂ ምትሃታዊ ሱቅ፤ሁሉንም ዓለማዊ ዓለምዊ መደብሮች፣ ሸቀጦች እና ትርፋቶችን በቀጣይነቱ እና በዋስትና፣ በሚዛን ክብደት፣ በዓለማዊ እና በወደፊቱ ዓለም ሂሳብ ወደሚበልጠው ንግድ በጋራ እንግባ፡፡

**የአንባቢ መመሪያዎች፡**

- ለተከበሩ ሀዲሶች፣ ተራኪዎቹ በሐዲሱ ላይ የጨመሩትን ማብራሪያዎች ወይም አስተያየቶች በመደበኛ ቅንፎች () ውስጥ በማስቀመጥ፣ እንዲሁም በሐዲሶቹ ወቅት የተጠቀሱትን አንቀጾች ተለይተዉ በ{} ቅንፍ ውስጥ አስቀመጠናል፡፡ እና በሐዲስ ቃላት እና ሀረጎች ላይ ያከልናቸውን ማብራሪያዎች ሁሉ በሁለት _ _ መካከል አሰቀምጠናል፡፡
- በተለምዶ ፀሐፊዎች ከሚያደርጉት በተቃራኒ፣ ህዳጎችን በማስተካከል እና ለአንባቢ በማመቻቸት ረገድ በሚነበበው ፅሁፍ እና በመጨረሻው ህዳግ መካከል ያለውን እይታ እንዳያዛውር ከማድረግ አንፃር፣ ብዙ ደራሲያን በመመጨረሻ ገፅ ከሚያደርጉት በተቃራኒ፣ ህዳጎችን የምዕራፉ መጨረሻ ወይም የመጽሐፉ መጨረሻ ላይ በዝቅተኛ ፊደል [ ] ዉስጥ አድርገናል፡፡

**"እሷ ከባድ ናት".. ለምን?!**

ሶላት ለምን?

ለሶላት ወደ በመስገድ ስንንቀሳቀስ፡ ቀጠሮዎቻችንን ለምን እንሰርዛለን፣ ለምን ስራችንን እንተወዋለን፣ ንግዳችንን እናቋርጣለን፣ምንም ያህል አስፈላጊ ቢሆኑም፣ሁሉንም የዕለት ተዕለት ሕይወታችን ተጋባራት ለምን እናግዳለን?

መልእክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) ሶላትን በእምነት እና ባለማመን መካከል ወሳኙ ልዩነት ለምን አደረጋት? የሞት አፋፍ ላይ ሆኖ (አሏህ አሏህ  በሶሎት ዉስጥ፣ አሏህ አሏህ በሶሎት

ዉስጥ) እያለ መልእክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) ደጋግሞ አበክሮ ከተናገረዉ ውስጥ የመጨረሻው ሶላት ለምን ሆነ?

በመጀመሪያ ሶላት ቅጣት ወይስ ሽልማት ነበር? ክብደቷ የቱ ጋር ነዉ፣ ሙብት ሙብት ከሆነች ችግሩ የቱ ጋር ነዉ? በእውነቱ ደስታ ከተሰማን በውስጧ አስደሳች ነገር ምንድነው? በእነዚህ ጊዜያት ለምን? ለምን በነዚህ እንቅስቃሴዎች እና የረከዓዎች ብዛት ሆነች? ለምን እነዚህ ሐረጎች እና ንባቦች? በሁሉም ሃይማኖቶች ውስጥ ለምን ተገኘች? እና እንዴት ከጂሃድ፣ ከውጊያ እና ከሰማዕትነት በጦር ሜዳዎች እና በጦርነት ድል ከማድረግ፣ ከአስፈላጊነትና አደጋዎች አንፃር አሏህ እና መልእክተኛው ዘንድ በደረጃ ከነዚህ ሁሉ የበለጠች?!

በሶላት የበለጠ ሁሉን አቀፍ ኢንቬስትሜንት እንዳገኘሁ ከማወቄ በፊት፣ ለሃምሳ ዓመታት እንደሰገድኩ መቀበል አለብኝ፤ ሁሉን ቻይ የሆነዉ አምላክ የንግድ ፕሮጀክት አድርጎልኝ ከዚህ ከሚዛኑ በባንክ ሂሳቤ ውስጥ አስገብቶልኛል ማለት ነዉ፡፡ እና ትልቁን ፈይዳ እና ታላቅ ደስታን ከእሷ አገኝ ዘንድ እሷን ለማስተዳደር እና ለማስኬድ በጣም ጥሩውን መንገድ ለመምረጥ እና ፣ በዚህች ምድር ላይ ባለው ሰው በሕልም ሊመኘው የሚችለዉን ሁሉ ደስታ ለማግኘት መጣር ይኖርብኛል፡፡

አንድ ጊዜ ዕድለኛ ከነበሩ እና በትንሽ ቁራጭ ስኳር ላይ በሁለት የጉንዳኖች ቡድኖች መካከል ውጊያ ከተመለከቱ፣ እያንዳንዱ ጉንዳን ሌላዉን ለማሸነፍ ይሞክራል፤ ስለዚህ በሌላው ጀርባ ላይ ይዘላል፣ እናም ያ ደግሞ ትናንሽ ጥፍሮቹን ከስኳር እንዳትደርስ ለመከላከል ወደ ጠላት አካል ይሠነዝራል? በሁለቱ ትናንሽ ወታደሮች መካከል ያለው እንግዳ ውጊያ ያለ ጥርጥር እየሳቁ ከጎኑ ይቆማሉ እና ስለ ምን? ስለ ዋጋ ቢስ እና ስለማያስፈልግ ስለ ስኳር ቁራጭ።

እውነተኛ እና የተሟላ ሶላት ከሰገዱ፣ በሷ ከዓለም ተነስተው ወደ አሏህ እንደሚወሰዱ የሚሰማዎት ሶላት ማለት ነዉ፣ ከእነዚያ ከፍ ካሉ ቦታዎች ከስርዎ ያለውን ከዚህ ዓለም ዉስጥ ወደ እታች ያያሉ፡፡ ያቺ በሶላትዎ ለመለየት የተዉትን ዓለም፣ በውስጧ ያለውን ሁሉ ያያሉ፣ ምንም እንኳን በአይነዎ ፊት ትልቅ ወይም ትንሽ እና ለዓይን እምብዛም የማትታይም ብትሆን፡፡ ያ ጉንዳኖቹ የሚዋጉባት ትንሽዋ የስኳር ቁራጭ፣ ተራ ዓለማችን

እንጂ ምንም እንዳይደለች እና እነዚያ ትናንሽ ሞኞች ጉንዳኖች፣ በእርስዎ እይታ፣ ያንን ቁራጭ ለማሸነፍ ሲታገሉ እና ሲያወሩ ነበሩ ማለት ነዉ፡፡ ያ ደግሞ እርስዎ ነዎት፣ እና በእነሱ ወይም በእርስዎ መካከል ጠላት የሆኑ የሰዎች ቡድን እና እርስዎ ስዋጉዋቸው ወይም ሲዋጉዋቸው እና በመጨረሻ፣ በቁራጭ ስኳር ያሸነፏቸው፣ ወይም እነሱ ያሸነፉዎት እንጂ ሌላ አይደለችም..

## ጉዞ ከግዴታ ወደ መብት

አዎ፣ በርግጥ ሶላት በሸሪዓችን መሰረት ግዴታ ሆኖ ሊጀምር ይችላል፤ (ልጆቻችሁ ሰባት አመት ከደረሱ ወደ ሶላት እዘዙ፤ እድሜያቸዉ አሥር ከደረሰ ምቷቸዉ (ከአምር ቢን ሹኤይብ ከአባቱ ከአያቱ የዘገበዉ (እና ለዚያም ነበር) (በሰውየው እና በክህደት/አለማመን መካከል ሶላትን መተዉ ነዉ (በሙስሊም የተዘገበው ከጃቢር ቢን ዐብደላህ) የተባለዉ፡፡

ግን ይህ “ግዴታ” በሰው ልጅ ሕይወት ውስጥ በኋላ ላይ አይቆምም፣ ልጁ ሲያድግ ፣ እራሱ የሶላትን ምንነት እና አስፈላጊነት ይገነዘባል፤ እናም ከጌታው ጋር የግንኙነት መስመር አስፈላጊነትን ይረዳል፤ የ “ግዴታ” ጽንሰ-ሀሳብ ከዚያ በኋላ በእሱ ላይ እንደገና መቀነስ ይጀምራል፤ ቀስ በቀስም በ “መብት” ፅንሰ-ሀሳብ ይተካል ማለት ነዉ::

ትንሹ ልጅ መድሃኒት እንዲወስድ ማስገደድ ስንፈልግ አይተዋልን፣ እሱ እምቢ እያለ? ግን ፣ ከጊዜ ጋር እና ትንሹ ልጅ ቀስ በቀስ ወደ ትልቅ ወንድ ወይም ሴት ሲለወጥ፣ የመድኃኒቱ ፅንሰ-ሀሳብ ከግዴታ ወደ መብት መለወጥ ይጀምራል፤ እናም አሁን ይህ መድሃኒት ነፍሱን ሊያድን የሚችል መሆኑን ሙሉ በሙሉ የመገንዘብ ደረጃ ላይ ደርሷል ማለት ነዉ፡፡

ብዙ የወደዱትን አንድ ትልቅ ቤት ለመከራየት እንደፈለጉ እና በውበቱ፣ በስፋቱ እና በጥሩ ስፍራው እንደተማረኩ ያስቡ፡፡ እንዲሁም የቤት እቃው የቅንጦት በመሆኑ፣ ስለሆነም በአእምሮዎ ላይ ከቀረፁ፣ ጉዳይዎን ከወሰኑ እና ከቤቱ ባለቤት ጋር ቁጭ ብለው ከተደራደሩ፡ የኪራይ ዋጋ በእሱ ዘንድ ሆነዉ በራሱ ወጪ በየቀኑ አምስት

ምግቦችን መመገብ ነው ከተባለ፣ ከዚያ የበለጠም ያነሰም አልፈልግም! ቢል፣ ምን ይሰማዎታል?

ይህ ምን ዓይነት ትርዒት ይመስልዎታል? ደህና፣ ሁሉን ቻይ የሆነዉ አሏህ በእርሱ መሬት ላይ እንድንኖር ያደረገው በተመሳሳይ ነገር ነዉ፡ በፀጋዎቿ እንድንደሰት፣ በግኝቶቿ እንድንጓጓ፣ እና በግንባቷ ላይ እንድንሳተፍ ነዉ።

ለምግቦቻችን ምንሰጠዉን የዕለት ተዕለት ሰዓታትን ለሶላት "ግብዓቶች" አለመስጠታችን በራሳችን ኢ-ፍትሃዊነት አይደለምን? በምግባችንን ግብዓቶች እንደምንደሰት ለሶላት ግብዓቶች አለመደሰታችን ለራሳችን ፍትሃዊነት አይደለምን? ለምን ለነፍስ ምግብ በተዘጋጀ ጊዜ የገላችንን ምግብ እናጥባለን? እንቆርጣለን? ለእኛ ይበልጥ አስፈላጊ የሆነው የትኛው ነው፣ እስቲ እዩት?

ሸላሚዉ መጀመሪያ ተሸላሚዉ ሌላዉን ትልቅ ሽልማት መቀበል ካልወደደ በቀር ሊሸልም ስላልፍለገዉ ስለ አንድ ትልቅ ሽልማት ሰምቶዋል? ያ ሽልማት ምን አይነት ሽልማት ነው? ሽልማቱ ሶላት ነው ፡፡ በሶላት ላይ ታላቅ ሽልማትዎን ከአምላክ አያገኙም፣ በሶላት አፈፃፀም በመደሰት ታላቅ መንፈሳዊ ሽልማትዎን ከመቀበልዎ በፊት፣ ሶላት በእርስዎ ላይ ግዴታ ወይም ሸክም ሳትሆን መብት መሆኗን አዉቀዉ ከመደሰትዎ በፊት፡፡

ደጋግመው ሶላትዎን -በአሏህ ታላቅ ነው- ሲጀምሩ፣ መላእክት ኃጢአቶችዎን ተሸክመዉ ሲመጡ ሲመለከቱ፣ ሁሉንም ኃጢአትዎን፣ በትከሻዎ ላይ እንደ ከፍ ያሉ ሁለት ማማዎች ለማስቀመጥ፣ የበለጠ ሩኩዕ ወይም ሱጁድ ሲወርዱ፣ ኃጢአቶችዎ ከነዚህ ሁለት ማማዎች ንብርብር ሲወዳድቁ፣ ምን ዓይነት ደስታ ይሰማዎታል፡

**- አገልጋዩ/ባሪዉ ለሶላት በቆመ ጊዜ፣ በኃጢያቶቹ ሁሉ ተይዞ ይመጣና ከዚያም ትከሻዉ ላይ ይጫናል፤ ስለዚህ ሩኩዕ ወይም ሱጁድ በሚወርድበት ጊዜ ከሱ ይወዳድቃሉ** [ከኡቅበተ ኢብኑ ዑመር፣ አል-አልባኒ በተከታታይ ተክክለኛ ሰዲሶቹ አረጋግጧል]

**- ማንም ሙስሊም ውዱዕ የሚያደርግ ዉዱኡንም የሚያዳርስ የለም ፣ ከዚያ በሶላቱ ላይ ቆሞ የሚናገረውን የሚወቅ፣ እናቱ እንደተወለደችበት ቀን ሆኖ ቢመለስ እንጂ** [በሳሂህ አል-ታርጊብ ውስጥ በአል-አልባኒ የተረጋገጠ ከዑቅባ ቢን ኣምር]

ስለዚህ ሩኩዕዎን ወይም ሲጁድዎን ያርዝሙ ወይም ያሳጥሩ፣ በየትኛውም ሁኔታ አሸናፊ ስለሆኑ፣ አለበለዚያ ተሸናፊ ይናሉ፡፡ በእጃችን ያለ መብት ወደ ግዴታ መቀየሩ እንዴት ቀላል ነው፣ ምንአልባትም በተቻለ ፍጥነት ልናስወግደው ወደምንፈልገው ወደ ከባድ ግዴታነት፡፡ ይህ ለአሏህ በሚሰጠው/በሚስደዉ ጥቂት ረከዓዎች ጠቃሚ ጊዜዉን "እየወሰደበት" ወይም "እያጣ" ወይም "እንደባከነ" ሆኖ የሚሰማው ሰው ሁኔታ ነው።

"ግዴታ" ሁል ጊዜ በማስታወሻችን ውስጥ ከ "ሸክም" ጋር የተቆራኘ ነው ፣ ሸክም ለነፍስ ከባድ ጉዳይ ነው። በውስጡ አንድ ወሳጅ አካል ያያሉ ለጋሽ አያዩም፤ ምክንያቱም የተወሰነ ጊዜዎዋን ወይም መብቷን ስለሚያሳጣት። ከዚህ ማበላሸት ይጀምራል፣ እናም ከዚህ ነዉ፣ ብዙዎች ሶላትን በተቻለ ፍጥነት "ለማስወገድ" እና እንደ ሸክም ሃስበዉ ከትከሻዎቻቸው ላይ ለማዉረድ የሚሞክሩት፡

**- ቢላል ሆይ በሷ (በሶላት) አሳርፈን** [ከቢላል ቢን ረባህ በአል-አረቂ የዘገበዉ]

ታዲያ ጥያቄው፣ ሶላትን ሰግደዋል ወይ አልሰገዱም አይደለም? የዚህ ጥያቄ አስፈላጊነት እና አሳሳቢነት ላይም አይደለም፣ ግን ይልቁን ከእያንዳንዱ ሶላት በኋላ ለራሴ ማቅረብ አለብኝ ያ ጥያቄ ነው፡ ከዚህ ሶላት የተሰጠኝን ሽልማቴን ተቀብያለሁ? ከዓለማዊ ፍሬዎች በቀመስሁበት፣ በሶላት ሰዓት እና ከዚያ በኋላ፣ ተስፋ ሳደርግ በእውነቱ ተደሰትኩ?፣ ለኣኽራዬ ካስቀመጥኩት ውስጥ የሚከጀሉትን ፍሬዎቿን ሳደንቅ ተደሰትኩ? ብሎ እራስዎን ይጠይቁ፡፡

ከሶላትዎ አስደሳች ነፃ የጉዞ ትኬት ያበጁ፣ እኔ የምናገረው ስለ ዓለም ሳይሆን፣ ስለ መላው አጽናፈ ሰማይ ነው፡፡ ለእዚህ ከአጽናፈ ሰማይ ንጉስ እና ፍጹም ገዢዉ ጋር ግንኙነት ፍጠሩ ማለቴ ነዉ፡፡

## በግዴታ እና በሙብት መካከል ያሉ ድንበሮች

በሕይወታችን ውስጥ ብዙውን ጊዜ ግዴታ ከሙብት ጋር ይደባለቃል፣ እናም በመካከላቸው ያሉትን ድንበሮች አናውቅም፡ ግዴታው የት እንደሚቆም ሙብት የት እንደሚጀመር እና ሙብት የት እንደሚያበቃ እና ግዴታው የት እንደሚጀመርም እንደዚያዉ?

ሀጅ ግዴታ፣ ተግባር፣ ጉዞ፣ ወጭ፣ ጭንቀት፣ እና ምንአልባትም አደጋዎች ያሉበት ነው ፡፡ ግን በእያንዳንዱ እርምጃ ከሽልማት ወይም ምንዳ አንፃር ምን እንደምናገኝ ስናስብ፣ ይህ የግዴታ ስሜት ከራሳችን ላይ ይተናል፣ እናም ሙብት ቦታዎቹን መያዝ ይጀምራል፤ በነፍሳችን ውስጥ የግዴታ ስሜት ቦታ እስከማይኖረው ድረስ፡፡

በጎ አድራጎት (ሰደቃ) ግዴታ፣ ጥረት እና ወጭ ነው፣ እና እኛ ከፍቃድ የምንከፍለው ከሆነ እና የሚሰጠንን ሽልማት (በረከት) ካወቅን፣ እና በደስታ ከተሟላን፣ እርካታ ባገኘነው ነገር ላይ የሰላም ሞገሶች እና የመተማመን ሞገዶች በእኛ ላይ ሲወርዱ ይሰማናል ። ጌታችን ከወደደልን እና ለተቸገሩ ሰዎች ጥበቃ፣ ድጋፍ እና ደህንነት ስለሰጠናቸው።

ጾም ግዴታ፣ ግዳጅ፣ ረሃብ፣ ጥማት፣ ጽናት እና ችግር ነው፡፡ ግን በየደቂቃው በምናሳልፈዉ ጊዜ የሽልማት ደስታ ይሰማናል፣ ወደ አሏህ የመቅረብ ደስታ፣ እና የእሱን ትእዛዛት የመቀበል እና ክልክሎችን የመከልከል ጣዕም፣ እንዲሁም ቃል የገባልን የሽልማት ቀን መቃረቡን ስናስብ፡፡ ከረጅም የረሃብ እና የጥማት ቀን በኋላ በምግብ መገደብ ብቻ ሳይሆን፣ የነፍሳችንን ምኞት ለማሳጣት በሚደረግነው ውጊያ የማሸነፍ ደስታችን እና በእሱ ላይ የበለጠ በመደሰት የማይሞት መለኮታዊ የባንክ ሂሳባችን ሲጨምር የሚሰማን ደስታንም ያጠቃልላል ።

በሐላል እና በሐራም መካከል ያለዉ ልዩነትም ተመሳሳይ ነው፡፡ ሁሉን ቻይ የሆነው አምላክ እኛን ከጉዳቱ ከመጠበቅ በስተቀር ከማንኛውንም ነገር አልከለከለንም፤ የዚህን ጉዳት ተፈጥሮ አወቅንም አላወቅንምም፣ እና እሱ ጥቅሙን እና ፋይዳዉን እንድናገኝ እንጂ ማንኛውንም ነገር ሐላል አላደረገም ወይም እንድጠቀም አላዘዘንም፡፡ የዚህን ጥቅም ተጨባጭ አወቅንም ወይም አላወቅንም፣ምንም ዝቅተኛ የማሰብ ችሎታ ቢኖረን

እንኳን፣ የዚህ ጥቅም ተፈጥሮ ወይም ለሀላል እና ለሐራም ተጨባጭ መግለጫን ፈልገን ኢኮኖሚያዊ ፣ ስነልቦናዊ ፣ ወይም ጤና-ነክ ነገር ላይ ብንደርስ እንኳ፣ በሁለት ቃላት ነዉ የምናጠቃልለዉ፡ ጠቃሚ እና ጎጂ ፡፡

በእጃችን ያሉ ሁሉም መብቶች ወደ ግዴታዎች መለወጥ እንዴት ቀላል ነው፣ ግን ደግሞ ቀላል፣ አስደሳች እና አስደናቂ ነገር ሁሉም ግዴታዎች በእጃችን ወደ መብቶች መጠቃለላቸዉ ነዉ፡፡

ከሆኑት ተቋማት ከአንዱ ትልቅ የገንዘብ ሽልማት ያገኙ ከሆነ፣ እና ሽልማቱን ለመቀበል እንዲጓዙ ሲጠየቁ፣ ሽልማትዎን ለመሰብሰብ ሁሉንም ጊዜዎን እና ጥረትዎን መስዋዕት በማድረግ እና በማዝናናት በደስታ እና በጋለ ስሜት በፍጥነት ይሄዱ የለም? ወደ እሱ በሚወስድዎት መንገድ ላይ ሊገጥሙዎት የሚችሉ ችግሮች ሁሉ አስወግደዉ?

ስለዚህ፣ እንደዚህ የመሰለ ጥረት ለሶላት ሽልማት ማድረግ አይገባዎትም? እንዲያዉም በበለጠ ደረጃ? የቱንም ያህል ታላቅ ቢሆን ከየትኛውም ዓለማዊ ሽልማት የሶላት ዋጋን የሚያህል የት አለ?!

ወደ ዛፉ እጆዎን ካልዘረጉ በፍሬው ጣዕም እንዴት ልደሰቱ ይችላሉ? እና የሚተኙበትን ቦታ ካላመቻቹ፣ ካላነጠፉት፣ አልጋው ላይ ምቾት፣ በቂ አንሶላዎች እና ከባቢ አየር፣ ጸጥ ያለ እና ትንሽ ብርሃን ያለው፣ ከድምጽ ጩኸት የራቀ ክፍል ካላገኙ በምቾት መተኛት እንዴት መደሰት ይችላሉ?።
በርግጥ እንዲህ ብለዉ አመኑም፡ እውነት ነው፣ አእዋፍት ምግባቸውን የሚሰጣቸዉ አሏህ ነው፣ ግን በምግብ ጣዕም ለመደሰት ወደ እሱ መብረር አለባቸው።

## ለመስገድ የመንቃት ደስታ

እኔ ትንሽ ሳለሁ፣ እናም ለሱብሂ ሶላት በ ‹እኩለ ሌሊት› መነሳት ነበረብኝ! እኔ ያሰብኩት እንደዚህ ነበር- ለኔ በዚያን ጊዜ በራሴ እና በነፍሴ መካከል እጠያየቅ ነበር- ለምን በሌሊት ጊዜ?! አሏህ ለእሱ አምስት ሶላቶችን መስገድ እንዳለብን ይፈልጋል፤ ታዲያ በዚህ አስቸጋሪ ወቅት ለምን ማድረግ አለበት? በጣም አስደሳች በሆነው

የእንቅልፍ ሰዓታችን ውስጥ ሳለን እንድንነቃ ይጠይቀናል?! በሰባት ሰዓት ወይም ስምንት ወይም ጠዋት ወይም አስር ይህንን ሶላት ብንሰግድ ምን ችግር አለብን? ሶላት በምንም ሰዓት የሚሰገድ ሶላት ጋር ተመሳሳይ አይደለምን?

በኋለኛው ክፍል የምናነበዉ በቀደመው ክፍል ከምናነበዉ ጋር ተመሳሳይ አይደለምን? እና ሶላት ከአሏህ ጋር ያለን "ግንኙነት" ለማቆየት ከመጣች እና ሸይጧንን ከእኛ ለማራቅ ከሆነ፣ ሸይጧን በእኛ ላይ ምን ሚና አለው በመተኛት እንድንገፋ የሚያደርገን? በእንቅልፍ ዉስጥ ሆነን የመገናኛ ጊዜን ወይም ያለመገናኘትን፣ ወይም ለበጎም ሆነ ለክፉ ማቀድ እስካላወቅን ድረስ፣ ከአሏህ ጋር ያለንን ግንኙነት ለማጣት እና ወደ ሸይጧን ፍቅር መንሸራተት ለምን እንፈራለን?

እነዚህ ጥያቄዎች በትናንሾቹ ብቻ ሳይሆኑ በአዋቂዎችም አእምሮ ዉስጥ ሊነሱ የሚችሉ ናቸዉ፡፡ በመጨረሻ ላይ ግን አዋቂዎቻች ሶላቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ ሁሉን ቻይ ከሆነው አምላክ ጋር የመገናኘት ሂደት ብቻ አለመሆኑን መዘናዘብ ብቻ ሳትሆን፣ ወደ ፊት እንደምናየውም የሕይወት ፕሮግራም ናት..

ከእንቅልፉ መነቃቃትን ጣእም የሚቀምስ፣ ከዚያ የመጀመሪያዎቹን እርምጃዎች ይዞ ወደ መስጊድ የሚወጣ፣ ከዚያ በኋላ የዕለት ተዕለት ሥራውን ለመጀመር ፀሐይ ከመዉጣቷ በፊት ከመስጊዱ የሚወጣ፣ ሥራው ምንም ይሁን ምን፣ነህ ሲቀድ በንጹህ ነፋሳት ውስጥ የመተንፈስ ዋጋም፣ በማለዳ ፀጥታም በመደሰት እና በውስጡ ያለው ለአሏህ ያለው ርቀትም፣ በፈጅር ሰላት ወቅት ብቻ ሳይን ከዚያ በፊት፣ በሰዓቱም እና በኋላምይህ ሰው ብቻ ነዉ የሱብሂን እሴት የሚያዉቀዉ ማለት ነዉ፡፡

ከእንቅልፍ በኋላ እንደገና የሕይወት መነቃቃት ይታይዎታል፤ ቀን ከሌሊቱ ነዉ እየቀነሰ የሚመጣዉ እና የመጀመሪያዎቹም የንጋት ክሮች ከሌሊቱ ማህፀን ነዉ በዓይኖችዎ ፊት የሚወለዱት፤ሰማይ፣ምድር፣ዛፎች፣ዕፅዋትና አበባዎች ሽፋኖቻቸዉን ይገልጧቸዋል፤ በሀፍረት ከፊትዎ ትመለሳለች፣ እና እንደገና በእርስዎ እይታ ስር ህይወት ታንሰራራለች፡፡ አሁን የመጀመሪው የፍጥረት ቀን አስደናቂ መለኮታዊ አቀራረብ እንዴት እንደ ተጀመረ እና ማታ በቀን ዉስጥ የመግባቱ ተዓምር እንዴት እንደ ተከሰተ፣ እናም ለመጀመሪያው የሕይወት ትንሳኤ በአጽናፈ ሰማይ ምንጮች ውስጥ እየተሰራጨ፣

ይህንን ልዩ ሰዓት የተመለከተ ሰዉ ሁሉ አዕምሮው፣ሀብቱ እና አስተሳሰቡ ወደ ልደት እና መስጠቱ በፍጥነት እየፈነጠቀ መሆኑ እንዲሰማዎ ነው፡፡ ይህም ደግሞ ተጨማሪ ኃይል፣ እንቅስቃሴ፣ መነቃቃት፣ ማምረት እና ፈጠራ ይሰጠዎታል፤ አዲስ ድንግል ሕይወት እንደተሰጠዎት ይመስል፡፡
እሱ ሱብሂ ነዉ፤ እሱም ከአጽናፈ ሰማይ ምስጢሮች የሚመለከቱበት እና የፍጥረትን ተዓምራት የሚያገኙበት አዲስ ዐይን ይሰጥዎታል፤ እርስዎ በሌሎች የቀንዎ ጊዜያት እሱን ሊያገኙት ያልነበሩትን/ የማይችሉትን ነገር።

በእነዚህ በቀኑ የመጀመሪያ ሰዓቶች ተነስቶ ለመስራት የሞከረ ሰዉ፣ በዚህ ጊዜ ዉስጥ ለሁለት ወይም ለሶስት ሰዓታት የተሰሩ ስራዎች፣ እንዴት በቀሪው ጊዜ በሚሰሩ ስራዎች እንደሚስተካከሉ በትክክል ያውቃል፡፡ በእራስዎ እና በስኬት መካከል በእነዚህ ልዩ ሰዓቶች የእንቅልፍዎ ሸይጧን አለ፡፡ በመጀመሪያው ቀን መቃወም እና ማሸነፍ ከቻሉ፣ ከዚያም በሁለተኛው፣ ከዚያም በተከታታይ ጥቂት ቀናት፣ የመጀመሪያዎቹ አስቸጋሪ ቀናት ከጾም ጋር ከመጠባበቅ ጋር የሚመሳሰል ቁርጠኝነት እና ቃልኪዳን ቀደም ብሎ እንደገቡ ለራስዎ ቃል ይገባሉ፡፡ ከዚያ በኋላ በአካላዊ አመጣጥዎ ላይ የተመሠረተ ልማድ እና የዕለት ተዕለት ፕሮግራምዎ አስደሳች ክፍል ይሆናል፤ መተው የማይችሉት እንቅስቃሴ፡፡

እዚህ ገና በፍራሽዎ ላይ ሆነዎ ዓይኖችዎን ይከፍታሉ፣ እና እዚህ ሸይጧን ራስዎን ወደ ትራስዎ ጎትቶዎት እንዲህ እያለ፡ ውዴ ዓይኖችዎን ይዝጉ እና ይተኙ፣ በእንደዚህ አይነት ያለ ጣፋጭ የእንቅልፍ ሰዓት ውስጥ ጊዜዎን አያባክኑ፤ የጠዋቱ ማለዳ በጣም አስደሳች የእረፍት፣ የስንፍና እና ጥልቅ እንቅልፍ ጊዜ ነዉ፣ ጥሩ እንቅልፍ፣ የምን መቸኮል?

ስለዚህ የሚደጋገሙ የሸይጧን ወሬዎች፣ፈተናዎች እና ሹክሹክታዎችን እንዴት ይቃወማሉ? የአሏህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እሱን ለማለፍ እና ለማሸነፍ የሚያስፈልግዎት ነገር ሊረዳዎት እየሞከረ ነው፡

**- አንድ ሰው በተኛ ጊዜ ሸይጧን ጭንቅላቱ ላይ ሶስት ጨርቅ (ቋጠሮ) ያስራል፤ እያንዳንዱን ቋጠሮ በማኅተም ይመታበታል፡ ረዥም ሌሊት አለዎት ይተኙ፣ ከእንቅልፉ ከተነሳ ታዲያ አላህን ካወደሰ፣ አንዷ ቋጠሮ ትፈታለች፤ ውዱእ ካደረገ፣**

**አንድ ቋጠሮ ትፈታለች፣ ከሰገደ ቋጠሮዎቹ ሁሉ ይፈታሉ፤ እና በህይወቱ ደስተኛ ይሆናል- አለበለዚያማ- ለሶላት ካልነቃ- ነፍሱ የቆሸሸ፣ ስልቹ ይሆናል** (በቡኻሪ የዘገበው ከአቡ ሁረይራ)።

ቶሎ ለመነሳት በመጀመሪያው ሌሊት የሚተኙትን ሰዎች ፊት ለመመልከት ሞክረው ያውቃሉ? እስከ ሌሊቱ መጨረሻ ድረስ ከሚቆዩ እና ከዚያ የሱብሂ ሶላት ካመለጣቸዉ በኋላ ለመስገድ ከእንቅልፋቸዉ ከሚነሱ ሰዎች ፊት ጋር ለማነፃፀር ምክሯልን? ይህን አድርገዉ ብሆን ኖሮ፣ “ሰው” ተብሎ የሚጠራው፣ የዚህ አስገራሚ ማሽን አንዳንድ ምስጢሮችን በተገነዘቡ ነበር፤ እንዲህም ፈጣሪው ሲፈጥረዉ ያከበረዉ፣ አንድ ገራሚ አካላዊ ሕግ ነዉ ይላሉ፡ ይህንን ማሽን ከእንቅልፍ በኋላ “እንደገና ለመጀመር” የተሻለው ጊዜ ፀሐይ ከመውጣቷ በፊት እንጂ ከዚያ በኋላ አይደለም፡፡ ስለሆነም እንደዚህ ነዉ የጥበብ ፈጣሪ በቁርጥ ውሳኔው የፈጠረዉ፡፡ ምንአልባት እኛ ልንረዳቸው ወይም ላንረዳዉ እንችላለን፡፡ እና የዚህ የሰው ማሽን ምስጢሮችን ፣ የተገለጡትም ሆኖ ያልተገለጡ ከፈጣሪዉ የበለጠ ማን ያውቃል?

أَلَا يَعْلَمُ مَنْ خَلَقَ وَهُوَ ٱللَّطِيفُ ٱلْخَبِيرُ ﴿١٤﴾ الملك: 14

‹‹ አዋጅ፣ (እሱ) የፈጠረውን ያውቃል፣ እርሱም ደግ እና አዋቂ ነው>> (አል-ሙልክ፡ 14)

ተፈጥሮ ከፍራሽዋ፣ በፈጣሪዋና በፈጣሪያችን እንደ ተቀናጀችልን፣ የሕይወትን ደስታ ሁሉ በአቅራቢያዎ እንድታበራልዎት ተሰጥቶዎታለች፡፡ ከመጀመሪያው የንጋት ክር ጋር እንዲተኙ ሳይሆን፣ እንዲነሱ እና እንዲሰሩ ምድርን እንዲያለሙ ነዉ የምትፈልገዉ፡፡ ስለዚህ ይህንን መለኮታዊ ፀጋ ዋጋ አያቃጥሉ፤ እናም ይህንን አሏህ ያገራልዎትን ኃይል በከንቱ እንዲባክን አያደርጉ፤ ለእርስዎ እና በአካባቢዎ ያሉ ሁሉም ፍጥረታት አዲሱን ቀንዎን ለመጀመር እንዲችሉ ማለት ነዉ፡፡ ፀሐይ በመጥለቋ የዐይን ሽፋኗን የዘጋዉን አበባ በመጀመሪያው ንጋት ብርሃን ሲያብብ ወይም ፈካ ፈካ ሲል አላዩምን?፣ እናም አእዋፍ፣ ቀደም ሲል በሰማይ ላይ ሲሳይ ፍለጋ ሲበሩ፣ እናም ላሞች፣ በጎች፣ ፍየሎች እና ዶሮዎች እንዲሁም በምድር ላይ የሚኖሩ አሏህ የፈጠሯቸው እንስሳቶች ሁሉ፣ የሕይወትን ዑደት እንደገና ለመጀመር ከመጀመሪያዎቹ የንጋት ክሮች (ጧት) በንቃት ሲነሱ አላዩምን?

የሕይወትን ጣዕም ይገንዘቡ እና ፍሬዎቹን ያጭዱ፤ ባቡርዋ በጭራሽ ላይመመለስ ከማምለጥዋ በፊት፡፡

## የትዕግስት ደስታ

ወደ ሥራ ወይም አንድ ቦታ መኪና ስንነዳ፣ በምንነዳበት ወቅት ዋናው ጉዳያችን በተፈቀደው ፍጥነት ወደ ትክክለኛው ቦታ ከመድረስ ዉጪ ሌላ አይደለም፣ ወይም በተፈቀደው ፍጥነት ላይሆን ይችላል የምንሄደዉ፡፡ ይህ ግዴታዎቻችን በጭንቅላታችን ላይ እንዲበዙና አቅማችን እንዲዳከም የሚያደርግ መንገድ ነዉ፡፡

አነዳዳችንን በእውነት አስደሳች ብናደርግስ? ጊዜ እንጠቀማለን፣እንታገሳለን፡፡ ስለዚህ በትንሹ ቀደም ብለን እንወጣለን፤ መኪናችንን በጥንቃቄ ለማሽከርከር ጊዜ እንዲኖረን፣ በዙሪያችን ያሉትን የመንገድ ትዕይንቶች ለመመልከት እድል ይኑረን ዘንድ፣ በቀደሙት ጉዞዎች ላይ ያላገኘነውን በማግኘት እና የማሽከርከር ደስታ ውስጥ እንድንገባ፣ አካላችንን ስላለፉት ጊዜያት ደስታ ማሰላሰል ሳንጠቀማቸዉ፣ ወይም እስከ አሁን ምን ያህል መሄድ እንዳለብን ሳናስብ?

ለጉዞዎ ተጨማሪ ጊዜ መመደብ አይፈልጉም? እናም ለእርስዎ እና ከእርስዎ ጋር ላሉት አስደሳች እንዲሆን ለማድረግ? እና በእውነትም በደስታ የሚጠቀሙት ጊዜ፤ በእርስዎ እና በእነሱ ላይ ከባድ ግዴታ ሳያደርጉ? ስለዚህ በሶላትዎ እንደዚህ ያድርጉ፡፡

እርስዎ በትዕግስት ላይ መፅናትን የሚረዳዎትን አጭር የመግባቢያ ስምምነት ከጊዜ ጋር መፈፀም ብቻ ነው የሚጠበቅቦዎት፡፡ ስለዚህ ይህ ትዕግሥትን በራሱ ደስታ ያደርጋሉ፡፡ ግን የትዕግሥትን ጥፍጥና ጾም እስኪፈታ ድረስ በመጾም አልሞከሩም፤ እንዲሁም በችግር ላይ መታገስን እፎይታ እስኪያገኙበት ድረስ፣ እና በበሽታው ላይ ትዕግስት እስኪድኑ ድረስ ፣ እና የመሰለፍ ድብርት ትዕግስት በመጨረሻ ወደ ክብረ በዓሉ አዳራሽ እንዲገቡ ከመፈቀዱ በፊት፣ በትምህርት ላይ ትዕግስት እስኪሳካልዎት ድረስ..አልሞከሩምን?

ማድረግ እየቻሉበት በትዕግሥትዎ ምክንያት ያጡት ነገር ጊዜ አጋጥምዎታል/ሞክረዋል? አንድ የከረሜላ ቁራጭ፣ አዲስ ሸሚዝ ወይም አዲስ መኪና የመግዛት

ችሎታዎ እያለ ገንዘብ ለሌላቸው ከእርስዎ ጋር ላሉት ሰዎች አክብሮት ሲሉ፣ ወይም መርህን ለማክበር፣ ቃልዎን ለመሟላት ወይም በትህትና ምክንያት ከመግዛት መታቀብዎ ዉስጥ ያለዉን የትዕግስት ደስታ አይተዎልን? የሶላት ሁኔታም እንደዚያ ነዉ፡

**- ለቤተሰብዎ እንዲሰግዱ እና በእሱም እንዲታገሱ አስተምሯቸው (እዘዝዋቸዉ)** (ጧሀ፡ 132)

በሶላት ላይ መታገስዎ ከአሏህ የሚመጣ መከራ፣ ፈተና እና ቅጣት ማለት አይደለም፤ ይልቁንም በሶላት ላይ የመታገስ ጉዳይ የሚፈልጉትን ማንኛውንም ደስታ ለማግኘት ከሚደረገዉ ትዕግስት ጋር ተመሳሳይነት ያለዉ ጉዳይ ነዉ፡፡ ትዕግሥት በጨመረ መጠን ዋጋውም ወይም ምንዳዉም የበለጠ መሆን አለበት ከደስታ መጠን እና ከክብደቷ መጠን ጋር ፡፡ እና በፈጣሪዎ ፊት ከመቆምዎ ደስታ የሚበልጥ ነገር አለ? አሏህን ልያመሳጥሩት፣ እና ጭንቀትዎን ከትከሻዎ ላይ በደጃፉ ላይ ለመጣል፣ ከዚህ የቅርብ ስብሰባ በኋላ ዳግመኛ እንደተወለዱ ከኃጢአትዎ ታጥበዉ ለመውጣት?

## ሶላት የትዕግስት ትምህርት ቤት ነች፣ ትዕግስት የሥልጣኔ ትምህርት ቤት ነች

በምዕራባዊያን ሥነ-ጽሑፍ ውስጥ ስለ (ትዕግሥት) ደረጃ ሙሉ በሙሉ መጥፋቱ ግራ ተጋብቶኛል፡፡ ስለዚህ ስለ ሰው ልጅ መሠረታዊ በጎነቶች ሲናገሩ ይህ በጎነት በጭራሽ ለእነሱ ቦታ የለዉም፡፡ እነዚህን ጽሑፎች እውነታ ከእኔ በላይ የሚያነቡት ይመሰክራሉ፡ ፡ ስለ ድፍረት፣ሐቀኝነት እና ውሳኔ፣ ሥራ፣ ልግስና፣ ጭፍሮች፣ እገዛ፣ ጽድቅ፣ ቅንነት ፣ ፍቅር፣ ፍትህ፣ እኩልነት፣ እና ነፃነት፣ ዲሞክራሲ፣ ትህትና፣ ድሆችን እና ችግረኞችን መርዳት እና ስለ ሌሎች ብዙ ባህሪዎች ያወራሉ፡፡ ግን በሚገርም ሁኔታ፣ ስለ ትዕግስት ገፅታ አይደለም የሚናገሩት፤ ምንም እንኳን የሌሎች በጎነቶች ሁሉ መሠረታዊ ቢትሆንም፡፡ በሌላ በኩል፣ ደግሞ የቃሉን (ትዕግሥት) እና ተወላጆችዋ በቅዱስ ቁርአን ውስጥ ስቆጥር፣ ከ (103) ያላነሰ ጊዜ እንደተደገሙ አግኝቻለሁ፤ በተከበረዉ ሐዲሱ ውስጥም በመቶዎች የሚቆጠሩ ጊዜያት ከተጠቀሱት በተጨማሪ፡፡

እኔ የምለው (በሚያስደንቅ ሁኔታ) የምእራባውያንን ስልጣኔ ስመለከት እና በፈጠራቸዉና በግኙታቸዉ እራሳቸዉን በአለም ላይ ያላቁት፤ እና ሁላችንም ትዕግስት የፈጠራ ባለሙያው ራሱን ጠንካራ አቅም ለማካበት የሚችልበት የመጀመሪያ መሳሪያ መሆኑን እናውቃለን። አብዛኛውን ቀኑንና ሌሊቱን ሳይደክም በቤተ ሙከራው ውስጥ

ይከታተል ስለነበር፣ አዲስ ግኝቱን በመፈለግ አድካሚ በሆኑ ሙከራዎቹ ላይ ሲሠራ፡፡ ታዲያ ሌሎች ሊያደርጉት ያልቻሉት ላይ ለመድረስ አጥብቆ በመጠየቅ ያለ አንዳች ችኩልነት፣ ቁርጠኝነት፣ ጽናት እና ትዕግሥት ይቻላልን? ምንአልባትም በልዩ የሳይንሳዊ ግኝቶች እና በዓለም ለየት ያሉትን ዉጤቶች፣ በአስተሳሰብ፣ በቋንቋ እና በምድር ላይ ማስገኘት ሁሉም ወደ፣ ትዕግሥት፣ ጽናት እና በሰዉ ልጆች አብሮ የመኖር ተፈጥሮ ዉስጥ ጠንካራ አካላት ናቸው፡፡ ምንአልባት በጽሑፎቻቸው ውስጥ ለመጥቀስ ምንም ምክንያት አላገኙም ይሆናል፡፡

በእስልምና ዉስጥ ሶስቱን በጣም አስፈላጊ ኢባዳዎችን (አምልኮዎችን) ከተመለከቱ፡ ሶላት፣ ጾም እና ሐጅን፣ እያንዳንዳቸው በትዕግስት ላይ ሥልጠና ለመስጠት እና ታጋሹን ለማስተማር የተቀየሰ ትምህርት ቤት መስሎ ብቅ ይላል፡፡ ለራስዎ እንዲህ ይሉ ይሆናል፡ ፆም እና ሀጅ፣ ውስጥ የትእግስት ገፅታ ግልፅ ነው፣ ግን በትእግስት ዉስጥ የሶላት ጉዳይ ምንድ ነው?
ትዕግሥትን ለማስተማር እና ለማሠልጠን ከሆነ ተቋም የሥልጠና ኮርስ ተገኝተዋል ብለው ያስቡ፣በዚህ ኮርስ ላይ ምን አይነት መርሃግብሮች እና ስልጠና ይሰጣሉ ብለው ተስፋ ያደርጋሉ?

ሶላት ከአክብሮት (ትህትና) ጋር በስተቀር የአምልኮ ሥርዓት ካልሆች፣ ይህም በሰጋጁ "ምን እንደተናገረ የሚያወቅበት) አክብሮት፣ ታላቁ ነቢያችን (ሰ.ዐ.ወ) እንዳረጋገጡልን፣ ያ ትህትና ከትኩረት ዉጭ ሊገኝ ይችላል? ትኩረትን ደግሞ በትዕግስት እና በጽናት በስተቀር ማግኘት ይቻላል? እያንዳንዱ የሚሰግዱት ሶላት በተግባር፣ በትኩረት ውስጥ አጭር እና ጠንካራ አካሄድ ነው፣ እና ትዕግሥትን ለመለማመድ አጭር እና ወሳኙ ትምህርት ነዉ፡፡

በንግድ ሥራ ውስጥ በጣም ቀላል የሆነው እና በጣም ርካሽ የሆነው፣ ግን ትርፋማነቱ ዝቅተኛ የሆነው፣ የሁሉም ንባብዎ፣ የምስጋናዎ እና የትህትናዎ ዘርፍን ማፋጠን ብቻ በሶላት ውስጥ "ምን እንደሚሉ አያዉቁ›› ከሆነ ነዉ፡፡ ግን በጣም አስቸጋሪው፣የበለጠ ንግድ እና የበለጠ ትርፍ ያለው፣ አስር ሥራዎች እና ተያያዥ ጉዳዮች በደጅ ሆነዉ ቁጥር በቁጥር፣ በቃል በቃል የሚጠብቁዎት፣እና ከእያንዳንዱ ቃል በኋላ ለአፍታ ቆም ማለት ሲፈልጉ "ምን እንደሚሉ እስኪያዉቁ" ድረስ ማንበብ ከቻሉ ነዉ፡፡

እንደ (አሏህ ታላቅ ነው…) የመሰለዉን ክፍት ሐረግ መደጋገምዎ *[ስለ ክፍት ቋንቋ በኋላ ለመነጋገር እናቀርባለን]* ከዚያ መቆምዎ፣ ከዚያ በኋላ ያንን የአእምሮዎን ባዶ ቦታ ለመሙላት አሥርት ሥራዎች ከበሩ ሲጠብቁዎት፡ አሏህ ታላቅ ነው ከማን? ከምንድን? ትዕግሥትዎን የሚፈልግ ሥራ፣ ይልቁኑ ብዙ ትዕግሥት ይፈለግብዎታል፡፡ እንዲሁም ክፍት የሆኑ ውዳሴዎችን (ክብር ለጌታዬ ለታላቁ /ለልዑሉ ይሁን) መደጋገምዎ ከዚያ ከእያንዳንዳቸው በኋላ ማቆምዎ፣ ከዚያ በኋላ ያንን የአእምሮዎን ባዶ ቦታ ለመሙላት አሥርት ሥራዎች ከበሩ ሲጠብቁዎት፡ አሏህ በምንድንነዉ የምያከብረዉ/የምያተልቀዉ? ከምንድን ነዉ የምያጠራዉ? ይላሉ፤ ትዕግሥትዎን የሚፈልግ ሥራ፡፡ ይልቁኑ ብዙ ትዕግሥት ይፈለግብዎታል፡፡ ነቢዩ (ሰለላሁ አለይሂ ወሰለም) እንዳራዘሙት ለእያንዳንዳቸው ሀረጎች (በአሏህ ስም)፣ (እጅግ በጣም ርህሩህ) እና (እጅግ በጣም አዛኝ) ስያራዝሙ፣ የትርጉም እና የስብዕናቸዉን ልዩነት በምረዱበት አኳሆን፣ እና አስርት ስራዎች በር ላይ ይጠብቁዎታል፣ ይህም ትዕግስት ይፈልግብዎታል፡፡ እንዲያዉም ብዙ ትዕግስት፤ እናም እያንዳንዳቸውን (አት-ተህያቱ-ሰላምታ ለአሏህ)፣ (አስ-ሰለዋቱ-ሶላቶች ለአሏህ) እና (አጥ-ጧይባቱ-ጥሩ ነገሮች) ካነበቡ በኋላ ይቆማሉ፣ ስለዚህ በእያንዳንዱ ለአፍታ ማቆም ጋር ስሜት ይሰመዎታል፣ እና አስርት ተግባራት በበሩ ላይ ይጠብቁዎታል፡፡ ሁሉን ቻይ ከሆነው ከአሏህ የሚገኘውን ምላሽ የሚያሟላ ደስታ አንግበዉ፣ ከዚያ በኋላ ለነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሰላምታ ስያቀርቡ ይቆማሉ እናም መልሱን በመቀበል ለመደሰት፤ እንዲሁም ለ(ጻድቃኑ የአሏህ አገልጋዮች ላይ ሰላምታ) ስያቀርቡ እና ከእነዚህ ሁሉ የሰላምታን ዋጋ የመቀበል ደስታ ለመቀበል ይቆማሉ፣ በዝርዝር እንደምናየው፡፡ ይህ ሁሉ ትዕግስት ይፈለጋል፣ እንዲያዉም ብዙ ትዕግስት፤ በእንቅስቃሴ እና በእንቅስቃሴ መካከል፣ በንባብ እና በንባብ መካከል እና በቁጥር እና በቁጥር መካከል ማቋምዎ፣ ለእያንዳንዳቸው ታማኝነት እና አክብሮት ስሰጡ፣ ሁሉን ቻይ አምላክ ዘንድ ተቀባይነት እንዲያገኙ፣ አስርት ስራዎች በር ላይ ይጠብቁዎታል፤ እናም ከእርስዎ ትዕግስት ይጠበቃል፣ እንዲያዉም ብዙ ትዕግስት..

ሁሉንም ስኬቶችዎን፣ ሁሉንም ለዉጥዎን፣ ሁሉንም ባህሪዎችዎን ካሰላሰሉ፣ በአእምሮዎ ውስጥ ትዕግስትን ያገኛሉ፡፡ እንዲሁም ሁሉንም ውድቀቶችዎን፣ ወንጀሎችዎን ሁሉ፣ ኃጢአቶችዎን ሁሉ ካሰላሰሉ፣ በስተጀርባቸዉ ትዕግሥት ማጣትን

ባገኙ ነበር። የትኛውም የስኬት እና የመዳን አስደናቂነት ትምህርት ቤት ትዕግስት ነው፣ እና የትኛውም የሶላት ድንቅ ትምህርት ቤት ትዕግስት ነው!

ክቡር ነቢያችን (ሰለላሁ አለይሂ ወሰለም) እንዲህ ይላሉ፡ (ከዚህ ህዝብ የመጀመሪያው የሚነሳ/የሚወሰድ ነገር ቢኖር አክብሮት (ኹሹዕ) ነዉ)፣ ከሶላታችን አክብሮት ሲነሳ ትዕግሥትም አብሮት ይነሳል፤ ትዕግሥትም በተነሳ ጊዜ የዚህ ሕዝብ ሥልጣኔ አብሮ ይነሳል፡፡ በዚህ ዘላለማዊ እውነታ ለምድር ላይ ስኬታማነችን እና በትህትናችን ዉስጥ ከሰማይ ጋር የምገናኝ መሆኑን ኃያሉ አሏህ አላረጋገጠልንም እንዴ፣ እንዲህ ሲል፡

قَدۡ أَفۡلَحَ ٱلۡمُؤۡمِنُونَ ١ ٱلَّذِينَ هُمۡ فِي صَلَاتِهِمۡ خَٰشِعُونَ ٢

**-ምእመናን ተሳክቶላቸዋል፣ እነዚያ በሶላታቸው ትሑታን የሆኑ** (ሙዑምኑን፡ 1-2) ከእያንዳንዱ የግዴታ ወይም ከሱና ሶላት በኋላ እራስዎን ለመጠየቅ ይሞክሩ፡ ከዚህ ሶላት ምን ያህል የትዕግስት ኃይል አገኘሁ? በማለት፡

## ለምን እንሰግዳለን?

ለምን ሶላት? ለትግስት ብቻ ነው እንዴ?
እንግዳ የሆኑ እንቅስቃሴዎችን ለማድረግ በየቀኑ ሁለት ወይም ሶስት ሰዓታት /ጊዜያችንን ለምን እናባክናለን፣ ከዚህ በፊት ደጋግመን በመቶዎች ጊዜያት ያነበብናቸዉን ቃላት? ወይ ያንን ጊዜ ሌሎችን በመርዳት ወይም ማንኛውም ሌላ ጠቃሚ የበጎ አድራጎት ወይም ሰብዓዊ ሥራ በማከናወን ማሳለፍ ለእኛ የተሻለ ነበርን? ሶላት ከሌለስ?

ሁሉም የዓለም ስልኮች፣ የስልክ መስመሮች እና ሞባይል ስልኮች በድንገት ቢዘጉ፣ ሁሉም የመገናኛ ግንኙነቶች ቢቋረጡ አስቡት፡፡ የሳተላይት፣ የምድር ጣቢያዎች እና ኢንተርኔት ቢቆሙ፣ እናም ሁሉም የመሬት ላይ መንገዶች ቢስተጓጉሉ፡፡ የባህር ኃይል፣ የአየር ኃይል እና ወዘተ .. ዓለም ምን ይሆናል? ምን አይነት ትርምስ፣ ምን አይነት ብስጭት፣ ምን አይነት ብክነት፣ ምን ያህል መጥፎ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ፖለቲካዊ፣ ባህላዊ እና ስልጣኔያዊ ውድቀቶች ያጋጥማሉ?

ይህ በእኛ እና በአሏህ መካከል ሶላት የምትጨወተዉ ሚና ነዉ፡፡ ለአንድ ቀን እንኳ ከሶላት ዉጪ መኖር እንችላለን? ሶላት ቢደበቅስ፤ በእኛ እና በአሏህ መካከል ያለዉ የሞቀ የግንኙነት መስመር ቢቋረጥስ? ለዚህ አሏህ የሰጠንን አስደናቂ የግንኙነት ስርዓት እራሳችን እንደገና መመለስ ነበረብን።

ሶላቱ ከተሰራበት ከዚህ እጅግ የላቀ "ቀመር" ወይም "አሰራር" የተሻለ ቅጽ እናገኛለን? ይህችን ሶላት የሚበልጡ ማናቸውም የሚከሰቱ ያልተለመዱ ድርጊቶች፣ ልዩ ጥምረቶች፣ የተመረጡ ትክክለኛ ቃላት እና የተለዩ ገላጭ ምልክቶች ይገኛሉ?

## ሶላት እኛን እንደገና እየቀረፀን /እያቀናጀን ነው

ለቀናት እና ለዓመታት የሚሽከረከሩ ሞገዶች የባህር ዳርቻ ድንጋዮችን እንደሚሽከረክር ሁሉ፣ ሕይወትም እንደዚያ ታደርገናለች፤ በጊዜ፣ በመተዋወቅ፣ በመደጋገም እና በአኗኗር ዘየ ጋር ተመሳስላ፡፡ ሶላት በነፍሳችን ውስጥ ባስገኘው ከዕለት ተዕለት ሕይወት ዑደቶች፡ ከብርታት፣ ሚዛናዊነት እና መንጻት አንፃር፣ በእኛ ውስጥ የሚትለማመዱ በዚህ መንገድ ነው፡፡ ስለዚህ እነዚህ ዓለማዊ አካላት በተከታታይ ሞገዶቻቸው እንደ ፍላጎታቸዉ መስመር ሊያቀናጁን ይሞክራሉ፤ ከሰዓት እስከ ሰዓት፣ ከቀን ወደ ቀን እና ከዓመት ዓመት፣ እና ከዘመን ጋር እንደተለዋወጥን እንዳይሰማን፡፡ እናም ከመጀመሪያው ተፈጥሮአዊው ስሪት ያርቁናል፣ ለእኛ ከተቀመጠው መለኮታዊ ፕሮግራም በ"ፈለሽ ዲስክ" ሆኖ ሊዛባ የማይችል ማንኛውንም (ቫይረስ) ከሌለበት፣ ከመጀመሪያው መርሃግብር ከሰማያዊው አመጣጥ ያሸሹናል፡-

**-እምነት በዉስጣችሁ ያልቃል- ማለትም-ያረጃል- ልክ ልብሶቻችሁ እንደሚያረጅ ሁሉ፣ ስለዚህ አሏህን በልባችሁ እምነትን እንዲያሳድስ ይጠይቁ** [ከአብዱላህ ቢን ዐምር (ረዐ) በሳሂህ አል ጀሚ`ዕ ውስጥ በአል-አልባኒ ተረጋግጧል]::

እናም አሏህ በእኛ ላይ ካለዉ ቸርነት፣ እኛ፣ ከሌሎች ህዝቦች እና ሀይማኖቶች በተለየ፣ አሁንም የዚህን የእምነት ፕሮግራማችን "ፍላሽ ዲስክ" የመጀመሪያውን ቅጂ እንጠብቃለን፤ እንደገና በመመለስ ህይወታችንን ዳግም እንቀርፃለን፣ ነፍሳችንን እንደገና ለመቅረጽ (ለማቀናጀት) እንችላለን፤ እናስተካክላታለን፣ እናም ወደ እሷ የፈሰሱትን

(ቫይረሶችን) ሁሉ ፣ ወይም ማናቸውንም ማዛባቶችን ወይም በሽታዎችን እናስወግደዋለን።

እስከ አሁን የቅዱስ ቁርአን መርሃ ግብር ልክ እንደወረደ ሳይለወጥ፣ ሳይዛባ፣ መጨመር ወይም መቀነስ ሳያጋጥመዉ ለእኛ የተጠበቀ ቅጅ ነው፣ እና ከሌሎች ሃይማኖቶች ሁሉ በተቃራኒ፣ ለእኛ የተጠበቀ ቅጅ፣ እና በቃል ትረካ ውስጥ የተብራራ፣ ብዙ ምንጮች እና ተራኪዎች ያሉት፣ በቃልም በተግባርም የተከበረው ነቢያዊ ሶላት ፕሮግራም፣ ክቡር ነቢያችን (ሰ.ዐ.ወ) በአራት ቃላት እንደሚያብራራልን፡

- **አሰጋገዴን አይታችሁ ስገዱ** (በሳሂህ አል-ጃሚእ ውስጥ በአል-አልባኒ ተረጋግጧል፣ ከማሊክ ቢን አል-ሁዌይሪስ አል-ሌይሲ)።

ተመልከት፣ ሶላት ባይኖር፣ ስለ ህይወታችን ከዚህ ከታላቅ አስተናባሪ፣ እና ሁሉን ቻይ የሆነው የዓለማችን እና የአጽናፈ ዓለማችን አደራጅ ጋር የሚያገናኘን ሶላት “መፈልሰፍ” ይቻለን ነበር? እናም ይህ የሰው ልጅ “ግኝት” በመገናኛ ዘዴዎች ምን ዓይነት ነው ብለው ያስባሉ? ይመልከቱ? ስለእሱ ብዙ በማሰብ አይሰላቹ፣ ያን ከኛ ዉጪ የሆኑት ሰርተዉታል፡፡

አሁን በእጃችን ያለዉን ተዉራት እና ወንጌልን (ኢንጂል) ቢመረምሩ በውስጣቸው ስላለው የሙሳ ሶላት ወይም የክርስቶስ (ኢሳ) ሶላት አይነት፣ ሰላም በሁሉም ላይ ይሁን፣ ምንም ዝርዝር መረጃ አያገኙም፤ በሶላት ውስጥ ተከታዮቻቸው ምሳሌያቸውን እንዲከተሉ ዘንድ፡፡ እነዚህ ሰዎች ዛሬ የሚያደርጉት ሶላት መፈልሰፋቸው ለእውነታ ነበር፤ እናም ከወላጆቻቸው እና ከአያቶቻቸው ስለ ወረሱት፡፡

ግን፣ ሰጋጁ ከእነሱ ምን ይናፍቃል፣ እና ስለዚህ፣ በጣም የጎደለው ምንድነው? ያለምንም ጥርጥር፣ ለአንድ ሙስሊም ሰጋጅ የሚሰማውን ያንን አስደሳች ደስታ ይናፍቃል፡፡ እናም ምንም ዓይነት ደስታ በእውነቱ የማይስተካከለዉ፡፡ ያ ከነቢዩ ቃል በቃል የወሰደውን ሶላት እያነበበ መሆኑን የሚሰመዎት ደስታ ነዉ፡፡ ነቢዩም ቃል በቃል እና በቀጥታ ሁሉን ቻይ ከሆነዉ አምላክ እንደወሰደዉ።

በእነዚህ ሁለት የተከበሩ ነቢያት ሶላት በኦሪትም (ተዉራት) ሆነ በወንጌል (ኢንጂል) ውስጥ፣ በሶላቶቻቸው ተከታዮቻቸዉ እነሱን ተንተርሰዉ እንዴት መስገድ እንዳለባቸዉ ምንም መግለጫ የለም፡፡ ለምሳሌ ኢንጂል ውስጥ ያለዉ፣ እንድ የክርስቶስ (ኢሳ) ደቀ መዛሙርት (ተማሪ)፣ ሰላም በእሱ ላይ ይሁን፣ እንዲህ አለዉ፡ ዮሐንስ (መጥምቁ) ለደቀ መዛሙርቱ እንዳስተማረ እንድንሰግድ ነዉ ያስተምረን፤ ስለዚህ ኢየሱስ (ኢሳ) እንዲህ አላቸዉ፡ ስትሰግዱ እንዲህ በሉ ...ብሎ የ 35 ቃላትን ፀሎት አነበበ (እንደ የሉቃስ ወንጌል፣ እንደ ማቴዎስ ወንጌል 42 ቃላት ነው)፡ [ማቴዎስ፡ 6፡ 9-13፣ እና ሉቃስ፡ 11: 2-4] ፡፡ ይህ ከጾም ጋርም ተመሳሳይ ነዉ፤ እያንዳንዱ ቡድን ለራሱ ሁኔታዎችን እና ሕጎችን፣ ፈቃዶችን፣ ክልከላዎችን፣ የፆሙን ጊዜ እና ያሁኔታዎችን በራሱ ያመቻቻል፡፡ ይህ ከሀገር ሀገር፣ ከህዝብ ህዝብ፣ ከጊዜ ወደ ጊዜ ይለያያል፡፡

አንዳንድ ጊዜ ሙስሊሞች በውስጣቸዉ አነስተኛ በሆኑ ጥቃቅን ጉዳዮች ላይ ባለመግባባት አንዳቸው ከሌሎቻቸዉ ሊጣሉ እናያለን፡፡ ለምሳሌ ከእያንዳንዱ ተክቢር ጋር እጃችንን ከፍ እናደርጋለን፣ ወይም አንዳቸዉን ከሌላው፣ ወይም ከኢህራም ተክቢር ብቻ? በቆምንበት ጊዜ እጃችንን የት እናደርጋለን-እምብርት ላይ? ከእምብርት በላይ? ትንሽ ከፍ አድርገን? እና ስለዚህ በሶላት ውስጥ ስለ ሌሎች ዝርዝሮች ብዙውን ጊዜ ወደ ጠብ፣ አለመግባባት እና መከራከር ይመራሉ ፡፡ እኔ ግን፣ የሚሰማኝ እምነት፤ ጉጉት እና ደስተኛነት ነዉ! እንዴት አይሆንም፣ በተወዳጅ ነብያችን (ሰለላሁ አለይሂ ወሰለም) ላይ የተደረገው የሶላት ቅርፆች ሙሉ በሙሉ ተዘርዝረዉ፣ ተደጋግመዉ፣ ከሰሃቦች ከአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) በበርካታ ሰፋፊ ትረካዎች ወደ እኛ ሲደርሱ፣ እንዴት አልደሰትም፤ እንደዚህ ባሉ ብዙ ዝርዝሮች ላይ ትንሽ እና ደቃቃ ልዩነቶች ቢኖሩም፡፡ በእስልምና ውስጥ ሁሉም ፍርዶች ከሰማይ ወደ ምድር የወረዱ ናቸዉ፤ ከሶላት በቀር፣ የአለማት ጌታ ነቢዩን ወደ እርሱ ወደ ሰማይ በመዉሰድ እና ዋናዉን መለኮታዊ ቅጂ ከእሱ ለመቀበል እና ለሙስሊሞች እንደ ስጦታ ከሰማይ ወደ ምድር ለመውሰድ ስለ መረጠዉ፡፡

አሏህ .. ከመመለሻችን እና ከታሪካችን በእነዚያ በተሞሉት ሀብቶች እንድንደሰት የሚያደርገን ከሰማይ የወረደ ምን አስደናቂ ስጦታ ቢሆን ነዉ፤ እዚህም ወይም እዚያም

በአንዳንድ ዝርዝሮች ላይ እስከ አለመስማማት ብንደርስም?! እና የተሟላዉን መልእክት ከሰማይ በቀጥታ ከጌታው እንደተቀበለው ወደ እኛ የተሸከመው ይህ ምን ዓይነት ታማኝ ነቢይ ቢሆን ነው? እነዚህን ዝርዝሮች ወደ እኛ ለማስተላለፍ ከፍተኛ ፍላጎት የነበረው እና በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ እጅግ አስደናቂ እና በቀላሉ የመጓጓዣ ዘዴ እኛን ወደ ላይኛው የቦታ ንብርብሮች፣ አሏህ ወዳለበት፣ ቦታ የሚወስደን!!

ወደ ሰማይ ባረገበት ሌሊት ከአምላኩ እንደተቀበለዉ፣ ከነብያችን (ሰ.ዐ.ወ) የተቀበልነዉ የሶላቱ ሙሉ ዝርዝር ቅርፅ መኖሩ ዋጋውን ያውቃሉ? ሰፋ ካሉት ዝርዝሮች ላይ በመስማማት እና አንዳንዴም በትንሽ ዝርዝሮቻቸው ላይም እንዲሁ፣ እንደ ሁሉም የሙስሊሞች አካሄዶች አቅጣጫ?

በሶላቱ ውስጥ የሚያስተጋባው ቃሎች፣ እንቅስቃሴዎቹ፣ የሚያከብራቸው ጊዜያት፣ የሚያደርጋቸው ልምምዶች፣ ዝግጅቶች እና እርምጃዎች፣ ከሶላት በፊትና በኋላ፣ ከአሏህ የተወሰደ ቃል፣ እጅግ በጣም ትክክለኛ እና በሐቀኝነት ያስተላለፈልን ሁሉን ቻይ ከሆነው አምላክ ከታማኝ መልእክተኛችን (ሰ.ዐ.ወ) መሆኑን ስገነዘቡ የሚሰመዎት ስሜት እና በሌላ በኩል፣ በዚህ ዓለም ውስጥ ማንኛዉም ሰጋጅ፣ ሲሰግድ ለእራሱ የቀየሰውን ወይም የፈለሰፈውን የሰው ጥረት ወይም ፈጠራ በመለማመድ፣ ሰብዓዊ ጥረታቸውን ያደረጉ የሰው ልጆች ከአምላካቸው ጋር የሚያገናኛቸው መንገድ የሚያበጀዉ፣ መካከል ያለውን ልዩነት አስዉሎዋልን? በሙስሊም ሰጋጅ ዘንድ የደስታ ታላቅነትን፣ እና ድምፅዎ ወደ ሌላ አካል ለመድረስ በመስመሩ ላይ መሆኑን ሲያወቁ የመረጋጋት፣ የደህንነት እና የመተማመን አስደናቂ ስሜቱን ይገነዘባሉ? እና በዚህ ከፍተኛ የቴክኖሎጂ መሣሪያ ጋር እየተገናኘ መሆኑን፣ በማይሳሳትና በማይበላሽ መሣሪያ፣ የዓለማት ጌታ የሰራዉና የፈጠረዉ መሣሪያ፡ እንዲህ አነፀ፣ እንደዚህ ዞረ፣ እንዲህ ተዘጋጀ፣ እነዲህ ጀመረ፣ እንዲህ ተንቀሳቀሰ፣ እንዲህ አጠናቀቀ…እያለ?

ግን ከዚህ እና ከዚያ በበለጠ፣ በህይወታችን ውስጥ ያሉትን ነገሮች ሁሉ የሚሸፍን “ሱና” በእስልምና ያለውን አስፈላጊነት ይገነዘባሉ? በነብያችን (ሰለላሁ አለይሂ ወሰለም) ህይወት ውስጥ ስላለው ነገር ሁሉ እንደተገፀልን?

የሱናን ዋጋ ማወቅ የሚችሉት ሌሎች ሀይማኖቶች ከእርሷ ነፃ መሆናቸዉን የተገነዘቡት ብቻ ናቸዉ:: እና እኔ በጣም የሚገርሙኝ፣ እጅግ ከፍተኛ ርህራሄም እየተሰማኝ፣ በእነዚያ ምንም ሳይገነዘቡ በእነዚያ ሃይማኖቶች ተጽዕኖ ስር ወድቀዉ፣ ሙስሊሙን ከሱና በማራቅ በቅዱስ ቁርአን ብቻ ወደ መብቃቃት የሚጣሩት ሰዎች ናቸዉ!

እስልምናን ከሱና ማራቅ የሚፈልጉት ከምን ዓይነት ሀብት፣ ልዩ ሙያ፣ ከምን ዓይነት ሞቅ ያለ ሽፋን፣ ደህንነቱ የተጠበቀ እና ግልጽ መንገድ ቢሆን ነው፤ ኃያሉ አሏህ "ሱና" ን በታላላቅ መጽሐፉ ዉስጥ በአስር አንቀጾች እንዳልገለፀዉ እና እኛ ከሱ (ሰ.ዐ.ወ) ተቀብለን አጥብቀን እንዳልተከተልነዉ የሚጥሩት፡

وَمَآ ءَاتَىٰكُمُ ٱلرَّسُولُ فَخُذُوهُ وَمَا نَهَىٰكُمۡ عَنۡهُ فَٱنتَهُواْۚ ﴿٧﴾ الحشر: 7

**- መልእክተኛውም ወደ እናንተ ያመጣዉን ያዙት እና እሱ የከለከላችሁን ነገር ተከልከሉ** (አል-ሐሽር፡7)

وَأَطِيعُواْ ٱللَّهَ وَأَطِيعُواْ ٱلرَّسُولَ ﴿٩٢﴾ المائدة: 92

**- አላህንና መልክተኛውንም ታዘዙ** [አል-ማኢዳህ፡ 92]

ይልቁንም ለእርሱ ያለንን ታዛዥነት እና ለነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) ያለንን መታዘዝ ሲያስተካክለዉ፡

مَّن يُطِعِ ٱلرَّسُولَ فَقَدۡ أَطَاعَ ٱللَّهَۖ ﴿٨٠﴾ النساء: 80

**- መልክተኛውን የሚታዘዝ ሰው አላህን ታዘዘ** [አን-ኒሳ: 80]

ከሱናዉ፣ ከማንነቱ እና ከባህሪው ጋር ያለንን ትስስር ሲያረጋግጥ ፣ ይህንን አገናኝ "ጥሩ ግንኙነት" ብሎ ጠርቶልናል:

لَّقَدۡ كَانَ لَكُمۡ فِي رَسُولِ ٱللَّهِ أُسۡوَةٌ حَسَنَةٌ ﴿٢١﴾ الأحزاب: 21

**- በአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ውስጥ ጥሩ ምሳሌ ነበራችሁ**

(አል-አህዛብ፡ 21)

የሱና አስፈላጊነት ከዚህ ነው የመጣው፣ እናም ከእዚህ ጀምሮ ነዉ የሶላታችን አስፈላጊነት እና በሁሉም እንቅስቃሴዎቹ፣ ጽሑፎቹ፣ ዝርዝሮቹ፣ አፈፃፀሙ አስፈላጊነት ግልጽ የሚሆንልን:: ይህ የተሟላ፣ ያተኮረ፣ በፍጥነት የሚሰራ፣ የአጭር ጊዜ ክዋኔና

ፕሮግራም የመጀመሪያ መለኮታዊ ስሪት ነው፡፡ በየቀኑ አምስት ጊዜ ነፍሳችንን እንደገና ለማቀናጀት፣ ይህም በሌሊት ወይም በቀን ሰዓታት በሕይወታችን ስርዓተ-ኮምፒተር እና በአስተሳሰባችን ውስጥ ዘልቆ በሚገባ ማንኛውንም ቫይረስ ለማስወገድ በቂ ነው:: ነገሩ፣ በአንድ በኩል፣ እኛ እና መለኮታዊ ባህርያችን ተሰውሮ የነበረው የጥመት ቫይረስ የሚርቀንን የመጠባበቂያ ግንብ ይለግሰናል፤ በሌላ በኩል፣ በእያንዳንዱ ማእዘን ውስጥ የሚቃጠሉ የኃጢአትን፣ ጭንቀቶችን እና ሀዘኖች ደኖችን ወይም የዓለማዊ ሕይወታችን ምሰሶዎች ያጠፋል ማለት ነዉ፡፡

**-ይቃጠላሉ ይቃጠላሉ፣ ከዚያም ሱብሂ ከሰገዱ ይታጠብዎታል፤ ከዚያም ይቃጠላሉ ይቃጠላሉ፣ ከዚያም ዙሁር ከሰገዱ ይታጠብዎታል፤ ከዚያም ይቃጠላሉ ይቃጠላሉ፣ ከዚያም አሰር ከሰገዱ ይታጠብዎታል፤ከዚያም ይቃጠላሉ ይታጠብዎታል፤ ከዚያም መግሪብ ከሰገዱ ይታጠብዎታል፤ ከዚያም ይቃጠላሉ ይታጠብዎታል፤ ከዚያም እሻአ ከሰገዱ ይታጠቧታል፤ ከዚያ ይተኛሉ እስኪነቁ ድረስ ስለእርስዎ አይጽፍም** ( በሳሂህ አት-ትርጊብ ውስጥ በአል-አልባኒ እንደ ሳሂህ የተመደበ ፣ ከአብደላህ ቢን መስዑድ)

አንዲት ጃፓናዊ ወጣት ዶክተር ጠየቀችኝ፡ እውነት ነው እንዴ ሙስሊሞች በቀን አምስት ጊዜ ይሰግዳሉ? እኔም መለስኩላት፡ አዎ፡፡ ወደ ተቃውሟ በተቃረበ ሁኔታዋ፡ "እንዴት ይህን ትችላላችሁ?" አለች በመደነቅ ቃና፤ ይህ በጣም ብዙ አይደለም? አለች፡፡ እኔም አልኳት: እርስዎ ሀኪም ነዎት እና በስራዎ ወቅት ብዙ ቁጥር ያላቸውን ህሙማንን ይገናኛሉ እና ያክማሉ፣ በቀን ስንት ጊዜ እጅዎን ያፀዳሉ?? እርሷ አለች፡ ሰላሳ .. አምሳ .. እናም እኔን ተመለከተችኝ እና ማለት የፈለግኩትን (ከማለቴ በፊት) እንደተገነዘበች በአይኖቿ አየሁ ፡፡

 - **ተነስ ስገድ፣ ምክንያቱም በሶላት ውስጥ ፈውስ አለ** (በኢብኑ ማጃ የተዘገበ ፣ ከአቡ ሁረይራ)

በአካባቢያችን ያለች ሕይወት በቫይረሶች የተሞላች ነች፣ ከፈተናዎች፣ ከአሳሳቾች፣ ከሰው ድክመት፣ ከሰይጣናዊ ማዛባት እና ምኞቶች፤ እና የዚህ ሁሉ ማፅጃ ውሃ አይደለም፣ ግን ሶላት ነዉ። ውሃው ሰውነታችንን ከውጭ ያጸዳል፤ ሶላት ከውስጥ ሊያነፃን የሚችል መሳሪያ ነው፡፡ ሰጋጁ ልክ እንደገባ ከሶላት መዉጣቱን ከተሰማው፣

እናም በእሱ ውስጥ የሆነ ነገር እንደተለወጠ አልያም በእርሱ ውስጥ የተቀረቀረው ብዙ ነገር ወይም ኃጢአትን ጨምሮ፣ እንዳስወገደው አልተሰማውም ከሆነ፣ ወይም እንደገና እንደ ተወለደ ሆኖ አልተሰማውም  እንደሆነ፣ ይህ ማለት “እንደገና የማቀናጀት” ዲስከን አልተጠቀመም ማለት ነው፡፡ በዚህ ሶላቱ ውስጥ በትክክል የተጠቀመበት ፕሮግራም ባለመኖሩ፣ አሁንም ቫይረሶች በጥልቀት እየበከሉት መሆኑን በማስረጃ አይቷል፡፡ እና አሁን ከሶላቱ ወደ ተለመደዉ ድክመት እና መዛባት ይመለሳል ፡፡

የሰጃዱን፣ እውነተኛዉን ሰጋጅ እና የማይሰግደዉን ሰው ሕይወት ብናነፃፅረው፣ በኋለኛው ላይ በእሱ ዘመን የሚያገጥመውን እያንዳንዱን እውቀት፣ክስተት ወይም አደጋ ሁሉ የሚጠቀምበትን ይህን አስፈላጊ መሳሪያ በማጣቱ እናዝናለን፡፡ እና ከሰጋጅ፣ ከእውነተኛ ሰጋጅ፣ ምንም እንኳን ችግሮች ቢደራረቡበትም፣ ፊቱ ፈካ ብሎ ሲበራ፣ እናም ከአይኖቹ በሚንፀባረቁ የምህረት፣ የለስላሳነት እና የትህትና ምልክቶች ግራ መጋባት ይይዘናል፤ ምንም ያህል ከባድ ፈተናዎች ቢኖሩም፤ በአጠገብዎ ያሉትን ሰዎች ፊት ሲመለከቱ እንኳ የሚሰግዱትንና የማይሰግዱትን እስክለዩ ድረስ፡፡ ይህ ምህረት ያለማቋረጥ የመጀመሪያውን አይኔን እንደሚያደበዝዝ መስገድ እስኪመስለኝ ድረስ እና የተከበረችዉ ጥቅስ እንደሚታመለክተዉ፣ በተለይ ስለ በሰጋጆቹ ፊት (ሲማ) ስታወራ፡

تَرَىٰهُمۡ رُكَّعٗا سُجَّدٗا يَبۡتَغُونَ فَضۡلٗا مِّنَ ٱللَّهِ وَرِضۡوَٰنٗاۖ سِيمَاهُمۡ فِي وُجُوهِهِم مِّنۡ أَثَرِ ٱلسُّجُودِ ﴿٢٩﴾

الفتح: 29

**-አጎንባሾች ሰጋጆች ኾሀዉ ታያቸዋለህ፤ ከአሏህ ችሮታንና ዉዴታን ይፈልጋሉ፣ ምልክቶቸዉ በስግደቶቻቸዉ ፈለግ ስትሆን በፊታቸዉ ላይ ናት** (አል-ፈትህ፡ 29)

ነገሩ፣ አሏህ ሁል ጊዜም እጅጉኑ አዋቂ ነው፣ እንደ አንዳንድ ሰዎች ግንባሮች ላይ የምናየው ያን ጥቁር ምልክት አይደለም፤ አንዳንዶቻችን ለመረዳት እንደምንወደዉ፣ እናም በእውነቱ የታሰበው ያቺ ቢትሆን ኖሮ፣ ጥቅሱ (ምልክቶቻቸዉ በግምባራቸው) ባለ ነበር። ፊት ላይ የሚንፀባርቁ፣ ሰጋጁ ብቻ ሊያገኛት የሚችሏቸው ከፍ ያሉ ባህሪዎች ናቸው፤ እናም የአማኙ አይን በሰጋጆቹ ፊት ላይ አይቶ መለየት አይከብደዉም፡፡

ከእኛ የሚፈለጉት ሁሉም የአምልኮ ተግባራት በእውነቱ ምንም ልዩነት ቢኖራቸውም የነፍሳችን “ዳግም ፕሮግራም ማድረጊያ/ማቀናጂያ” እንጂ ሌላ አይደሉም፤ ከእነዚህ የአምልኮ ተግባራት የትግበራ እና የጊዜ ስፋት ባሻገር።

ጾም በህይወታችን ኮምፒውተር ለማድረግ “የወረደ” ረጅም ፕሮግራም ነው፤ ግን በጣም ውጤታማ ነው፡፡ ሙሉ በሙሉ ለማውረድ አንድ ወር ይወስዳል፤ ግን ውጤታማነቱ ለአንድ ዓመት ሙሉ ይዘልቃል። በጾም ባለፈው ዓመት በቫይረሶች ሸክም የሆንብንን ምኞቶቻችንን እንደገና ፕሮግራም እናደርጋለን፤ በሰው እይታ እና በሸይጧን ፈተናዎች ድክመት ያጋጠመዉን ዕይታዎቻችንን እንደገና እናስተካክላለን፤ ለወራት ስህተት ከእዉነት፣ ሀላል ከሀራም፣ ከፉ ከመልካም፣ እዉነት ከሀሰት የተደባለቀበትን ምላሳችንን እንደገና እናቀናጃለን፤ ዓመቱን በሙሉ ሸይጣናዊ መድኃኒት በውስጣችን ሰርጎ ገብቶ በውስጣችን ያለውን የምህረት ዘር፣ እውነት፣ ፍትህ፣ ጥሩ አስተሳሰብ፣ እርካታ፣ ትህትና፣ ትዕግሥት፣ ጽድቅ፣ ምስጋና፣ የእምነት ጣፋጭነት እና ጥሩ ንግግር የሚገድልባትን ነፍሳችንን እንደገና እናቀናጃለን፡፡

ይህ ደግሞ የሐጅም ተግባር ነው፣ ግን በረዘመ እና ጥልቀት ባለው ደረጃ። ተቀባይነት ያለው ሐጅ ብቸኛው ምንዳዉ ጀነት ነው፡፡ ሐጁንም አሏህ የተቀበለዉ ሰዉ ሁሉ ክቡር ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንደነገረን ከኃጢአቱ (እናቱ ወለደቺዉ) ሆኖ ይመለሳል፡፡ እዚህ የዛሬዎቹ ሶላቶች የሕይወት አጋንንት ጥቃት በተሰነዘሩቦዎት ፍጥነት ልክ ቀስ በቀስ ያፋጥናሉ፡ መጀመሪያ ፈጅር ሶላት ይሰግዳሉ፣ ከዚያ ዙህርን ከመስገድዎ በፊት ግማሽ ቀን ሙሉ ይጠብቃሉ፣ ግን የሚቀጥለው ጊዜ አጭር ነዉ፤ ከዚያ የቀኑ ሁለተኛው ግማሽ፣ የአስር ሶላት አጋማሹ ይሆናል፤ በፀሐይ መጥለቂያ ሶላት (መግርብ) ከማጠናቀቅዎ በፊት፣ ከዚያ ከምሽቱ ሶላት (እሻዐ) ጋር ህይወትዎን እስኪያገኙ ድረስ ከአንድ ሰዓት እና ከግማሽ ሰዓት በስተቀር ምን ይኖራል፣ ከዚያ ወደ መተኛት ይሄዳሉ::

ይህ የሶላት ልዩነት ነው፤ እናም ያ ጊዜያቸው እርስ በእርሳቸው ከሚቀራረቡት አንዳንድ ምስጢሮች ሆነዉ እያንዳንዳቸውን በቀን አምስት ጊዜ እንደግመዋለን፡፡ በዓለም ላይ ባሉ ሁሉም የጦር መሣሪያ ፋብሪካዎች ውስጥ በጣም ዘመናዊ እና በጣም ብቃት ያለው፣ ውጤታማ እና ትክክለኛ መሳሪያዎች የት ያገኛሉ? በጥልቀት የሚወረውር እና ዒላማዎችን የመምታት ይዘት ለባለቤቱ ድልን የሚያረጋግጥ እንዲሁም የተፈለገውን ውጤት የሚስገኝ፣ ከዚያም በላይ፣ እንደዚህ አይነት መሣሪያ፣የት ያገኛሉ?

## የሶላት ምት እና የሕይወት ምት

በክረምት አንድ ሰው ሙቀትን፣ በበጋ ብርድን ፣ በሕመም መድኃኒትን፣ በረሃብ ምግብን ፣ በጥማት ውሃን፣ በጩኸት ፀጥታን እና በፍርሃት ደህንነትን ይፈልጋል፡፡ የሕይወት መሽከርከሪያ ጎማ፣ በተለይ በዚህ በሜካኒካዊ ዘመን ውስጥ፣ ካሉት በጣም ብዙ የኤሌክትሮኒክ መሣሪያ እንኳን እጅጉኑ እየፈጠነ ከሆነ፣ እና ሶላታችን ከዚህ በጎማ ፍጥነት ከሚጓጓዘዉ ህይወት የሚጠብቀን መጠጊያችን መሆን አለበት፡፡ አለበለዚያ፣ ተረግጠን፣ በጠጣር የብረት ጥርስ ተበልተን እናልቃለን፡፡ ስለዚህ እኛ ከሶላት የምናገኘዉ ተቃራኒው መሽከርከሪያ ጎማ፣ የበለጠ ጠንካራ፣ ዘና ያለ፣ የተረጋጋ ፣ እና ታዛዥ እንደሚሆን ግልጽ ነው፡፡

የሶላት ምት ከህይወት ምት፣ ከከፍተኛ ፍጥነት እና ምንአልባትም እንደ እብደት እንደሚመሳሰል አስበው ያውቃሉ? ታዲያ ሶላት፣ በእውነቱ በብዙዎች ዘንድ እንደሚከሰት፣ ከሕይወት ሸክሞች መካከል ወደ ሌላ ሸክም በተቀላቀለች ነበር፣ ወደ ሌሎች ሜካኒካዊ ሸክሞች፣ እና ሁላችንም በማናባክነዉ በትርፍ ጊዜ፣ ጥረት፣ እንቅስቃሴ ወይም ነርቮች አንፃር ሸክም ሆነዉ ይከብዱናል፡፡ ስለዚህ ቶሎ ለመተግበር እና ለመገላገል እንፋጠናለን፤ ከሌሎች ሜካኒኮች ጋር እንደተያዝን ሁሉ እሱን ለማጠናቀቅ እና በተቻለ ፍጥነት ለማስወገድ እንጥራለን፡፡ ይልቁኑ ምንአልባት ከእነዚህ ሙሉ በሙሉ ተስፋ አስቆራጭ ውጤቶች አንፃር፣ ይህንን ሜካኒካዊ "ግዴታ" ለመሻር ፈለግን ይሆናል፤ በሙሉ ሕይወታችን ውስጥ ተጨማሪ የሆነዉን ነገር ለመቀነስ፡፡ ይህ በእውነቱ በብዙ ሙስሊሞች ላይ እንደሚከሰት ነዉ፤ በሕይወታችን ዉስጥ ከእነዚያ ዓይነት ሥራ ከሚበዛባቸው መካኒካዊ “ግዴታዎች” ብዙ ርቀት የለዉም፡፡

መጀመሪያ ላይ ለእኛ ቀላል እንደማይሆን አውቃለሁ .. እንዴት ፍጥነት መቀነስ እንችላለን? አንድ ሺህ ሥራ እና የቤት ሥራ ሀላፊነት፣ ቀጠሮ፣ ፕሮግራም፣ ስብሰባ፣ ጉብኝት፣ አቀባበል፣ ጥናት እና ውሳኔ በር ላይ የሚጠብቀን ሆኖ ሳለ?!

ወደ ሶላት ቦታ ለመብረር ስንዘጋጅ በእውነት ይህ የአስተሳሰባችን መንገድ ከሆነ፣ በሶላታችን የጠፈር መንኮራኩር ውጫዊ የጠፈር ቅርፊት ብቻ መሻገር በጭራሽ አንችልም፣ እና መንኮራኩሯ ከመነሳትዋ በፊት ትቃጠላለች፡

- - **ስላልሰገድክ ተመልሰህ ስገድ፤** (አል ቡኻሪ ዘግቦታል፤ከአቡ ሁረይራ)፡፡

በዚያ በመመስረት ላይ፣ የቀን ሶላት ድምፅ ምስጢራዊ የሚሆንበት፣ መደበኛ የማንበብ ድምፅ የሚለሰልስበት ከዚህ ምስጢራዊ ተፈጥሮ እና በዚያ ጫጫታ ክፍል ውስጥ ከፍተኛ ድምጽ ካለው የሕይወት ምት ጋር በተቃራኒው ይዛመዳል፡፡ የሰዎች ድምፅ ከፍ ማለት፣ የፀሐይ ብርሃን ከፍ ማለት እና ሙቀቷ፣ በአካባቢያችን ያለው ከፍተኛ የእንቅስቃሴ ምት፣ የሥራ እና የእንቅስቃሴ ፍጥነት መጨመሩ እና በተጨናነቀ፣ ፈጣን እና በፍጥነት ወደ ስራ ማፈላለግ፣ ገንዘብ እና ስኬት ለማግኘት መጣር/መልፋት የተለመደ ነገር ነዉ፡፡

ስለ ምሽት ሶላት ደግሞ በተፈጥሮው ከሌሊቱ ዝምታ፣ ጸጥታ፣ ምስጢራዊነት እና ከጨለማ ጋር በተቃራኒው የተዛመደ ነው፡፡ የእንቅስቃሴው ጎማ መቀነስ፣ የኑሮን ሁኔታ በፍጥነት ከማሳደድ መቀነስ፣ የሕይወት ወፍጮ ከጫጫታው እና ከጩሀት ይቆማል፡ ስለዚህ የከፍታ ንባባችን ይህንን ክፍተት ለመሙላት እና በነፍሳችን ገፅታ ውስጥ ሚዛንን ለማስመለስ ነው፤ እና የሕይወትን ምት በውስጣችን እንዲቆይ እና ከዚያ በውስጣችን ያለውን የድምፅ ምት፣ ምስል እና እንቅስቃሴ ለመቆጣጠር ነዉ፡፡ በዚህም ጊዜ ልናጣው በቀረብንን የስነልቦና ሚዛናችንን እናሳከለን ።

ርዝመትን እና ብዝሃነትን በተመለከተ ቀናችንን በኢሻዕ ሶላት እናጠናቅቃለን፡፡ አሁን አራት ረዥም ረከዓዎች አሉን፤ ሁለቱን ከፍ በማድረግ እናነባለን፣ ከሌሊቱ ምስጢር እና ፀጥታው ጋር በተፃራሪ፤ ቀኑ የተመለሰ ይመስል በድምጽዎ ሊሞሉት እና ወደ አሏህ ሊደፍሩት የሚችለውን አስፈላጊ ቦታ ከፊትዎ በመተው፡፡ ከዚያ ሶላቱ በሁለት ሱና ረከዓዎች፣ በአንድ ረከዓ፣ ወይም ረከዓዎች እና በውትር ረከዓ ይነበባል።
ስለዚህ ይህን የመጨረሻ አንድ፣ ሶስት፣ አምስት ወይም ከዚያም በላይ ማድረግ ይችላሉ፡፡ እና ይህ በቁጥሮች ውስጥ ክፍተት እንደምናየው፣ ብዙዎቹ አምልኮቶቻችን ዉስጥ፣ ሶላትን ለማራዘም ተለዋዋጭ ፈቃድ ነው፤ ከቀኑ መጀመሪያ ጀምሮ ካከማቹት ኃጢአት መጠን ጋር ሊመጣጠን የሚችል እርዝመት፣ እናም ያጠቃዎታል እናም ከሌሊት ሸይጣኖች ይፈትናዎታል ብለዉ ከሚፈሩትም፡፡

እዚህ ላይ ልብ ይበሉ፣ በሶላቶቻችን ውስጥ ሱናዎች የግዴታ ሶላቶች በሚበዙበት መጠን ይበዛሉ፤ እነሱ በሚቀንሱበት ደግሞ ይቀንሳሉ፡፡ ይህ የሚገልፅልን ነገር፣ የሕይወታችን ሁኔታ ሲቀያየር በእያንዳንዱ የሶላት ከረከዓቶች ውስጥ ያለዉ ቁጥር ጋር

ይዛመዳል፡፡ ከዚያ ቀን ወይም ማታ ወይም አልፎ አልፎ ከአሏህ ጋር ለመገናኘት ያለን ፍላጎት መጠን ይጨምራል፡፡

## ብዝሃነት-የመጀመሪያው የሥልጣኔ ትምህርት ቤት

መቼም አንድ ጊዜ እራሴን እንደጠየቅኩ እራስዎን ጠይቀዉ ያውቃሉ፡-ሶላታችን ለምን እንደዚህ መጣ፣ የተለያየ ርዝመት እና ብዛት ያላቸው ረከዓዎች፣ እንቅስቃሴዎች፣ ንባቦች፣ ጊዜያት፣ ስሞች እና ዓይነቶች? ለምን እንደ ሌሎች ብዙ ሃይማኖቶች ሶላት በተመሳሳይ ቅርፅ፣ ርዝመት እና አንድ ቀለም አልመጣም?
ለምን እነዚህ ብዝሃነት እና "ውስብስቦች" እና "ችግሮች" እና "ግራ መጋባት"?፣ የፈጅር፣ የዙሁር፣ የአስር፣ የመግሪብ እና የእሻዕ ሶለቶች መካከል የረከዓዎች ቁጥር ለምን የተለያዩ ሆኑ? ለምን በግዴታ፣ በሱና እና በነጠላ (ውትር)፣ በቅድሚያ እና በድህረ ሶላት፣ በበጣም አስፈላጊና በአስፈላጊ፣ በቀንና በሌሊት/ማታ ሱናዎች፣ በሚደበቅና ከፍ ተደርጎ በሚነበብ፣ በጋራ እና በግል በሚሰገዱ ሱናዎች ወይም ሶላቶች መካከል ልዩነት ተፈጠረ? ስለሆነም፣ የሚሰግድ ሰው እንዴት እንደሚሰግድ ማወቅ እንዲችል አስቸጋሪ እና ከፍተኛ ደረጃ ትምህርታዊ ስልጠና ለማጥናት እና ሙሉ በሙሉ በማስተናገድ በውስጡ ለማለፍ ብዙ ጥረት ማድረግ ያለበት ይመስላል። ይህ ለወጣቶች፣ ለአካለ አዳም ላልደረሱ፣ መሃይማን እና አላዋቂ ሰዎች ችግር አይደለምን? እንዴት ነዉ፣ የማያነብ እና የማይፅፍ መሃይም ሕዝብ መካከል እስልምና ሲገለጥ?

ጎደሎዋ አእምሮአችን ለነዚህ ጥያቄዎች መልስ ለመፈለግ ሲትሞክር በታላቁ መለኮታዊ ጥበብ አትከበብም፣ እኛ ግን ሙስሊሞች እንደመሆናችን መጠን "ማሰብ" እና "ማመዛዘን" እና "የአሏህን ፍርድ" እንድናጤን ታዝዘናል፣ ሁሉንም ካልደረስን የተወሰኑትን ለመድረስ በመሞከር ለመመለስ፡፡

ምን ያህል ተጠያየቅን እና ዓለም ከእኛ ጋር ተጠያየቀ፡ እስልምና እንደዚህ ባለዉ ሪኮርድ ፍጥነት አረቦችን ማጓጓዝ የቻለው እንዴት ነው፣ አንድ ሰው አንድን መልእክት ለማንበብ ከሚፈልግበት ሕዝብ ውስጥ ዛሬ ከኮምፒተር አብዮት በፈጠነ እንቅስቃሴ ሊያልፈው እንዴት ቻለ፣ በአንድ ቀን ደብዳቤ ተፅፎ የሚመለከተውን ሰው ለማግኘት ወደ ሌላ ከተማ የሚሄድ መልእክት፡ ወደ አንድ ብሔር ቋንቋ፣ ሰዋስው እና ሥነ-

መለኮታዊ ሳይንስ ከሁለት ወይም ከሦስት አስርት ዓመታት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ተመሥርቶ፣ እና መዝገበ-ቃላት፣ ንግግሮች፣ ነቀፋዎች፣ ትርጓሜዎች፣ ንባቦች ፣ሀዲስ፣ የህግ፣ የሕይወት ታሪክ፣ ሰዎች እና ምድር፣ ታሪክ፣ ጂኦግራፊ፣ ፍልስፍና፣ አመክንዮ፣ ህክምና፣ አስትሮኖሚ፣ ሂሳብ፣ ወዘተ ሳይንስ ሁሉ ወዳስገኘ ሕዝብ መድረስ ቻለ?

የእስላማዊ ስልጣኔ ልደት በዚህ አስገራሚ ፍጥነት ማደጉ ውስጥ ሶላት ከፍተኛ ሚና ነበረው፤ ከዚህ በፊትም ከዚያ በኋላም የሥልጣኔዎች ታሪክ ዉስጥ ባልታወቀበት ፍጥነት፡፡

ይህ በሶላት እንቅስቃሴዎች፣ በሚያነቧቸው ንባቦች፣ በማንበብ መንገዶች፣ በጊዜዎቹ፣ በቅጾቹ፣ አስቸጋሪ የሆነ ብዝሃነት እናም የረከዓቶቹ ቁጥሮች እና የእነዚህ ረከዓ አይነቶች፣ የሙስሊም ልጅ አንጎል ተግባራዊ የሆነበት የመጀመሪያ ትምህርት ቤት ነው። አካላዊ እንቅስቃሴዎቹ፣ አንጎልን ለማስፋት እና ለማሰብ፣ ለማስታወስ፣ ለመተንተን፣ ለፈጠራ እና ለፈጠራ ዝግጁ እንዲሆኑ ያዘጋጃቸዋል፡፡ የልጆቻችን አእምሮዎች ሀሳባቸውን እንዲያስተካክሉ፣ ጉዳዮቻቸውን እንዲከፋፈሉ እና ርዕሶቻቸውን እንዲመድቡ የሚማሩበት ትምህርት ቤት ብዝሃነት ነዉ፡፡ ብዝሃነት መረጃዎችን ይተነትናል፣ እናም ሳይንሱን እና የሰለጠነ አድማሶችን ያሰፍናል።

እስልምና እነዚህን መሃይምነቶች፣ በእንደዚህ ዓይነት የትምህርት ዘዴዎች፣ ወደ ግዛቶች አልልም፣ አፈ-ታሪክ ናቸው፣ እንደ ሞንጎሊያውያን እና እንደ ታታር ያሉትን፣ ገዳይነት እና ድብድብ በስተቀር ምንም የማያውቁ የነበሩትን፣ ወደ ተቀናጀ የአስተሳሰብ፣ የባህል፣ የሳይንስ እና የስነምግባር ስልጣኔ ለመለወጥ  አልቻለም ነበር?

እዚህ በምዕራቡ ዓለም ያለው ተማሪ በአምስት ዓመቱ ትምህርት ቤት ይገባል፤ እና በአብዛኛዎቹ አረብ እና እስላማዊ አገራቶቻችን ውስጥ በስድስት ዓመት፡፡ እንደ እስልምና ትምህርት ቤት ደግሞ በሰባት ዓመቱ ትምህርት ቤት ይገባል፤ ይህ ልጆቻችንን በሶላት እንድናዝዝ የታዘዝንበት ዕድሜ ነው ፡፡

ሶላት፣ በዚህ ብዝሃነት እያንዳንዱ ሙስሊም ወደ እውቀት፣ አስተሳሰብ፣ ባህል፣ ስልጣኔ እና መገንባት ትምህርት ቤት መግባት ያለበት በእንደዚህ ዓይነቱ ዕድሜ ላይ ነዉ ማለትን ታመላክታለች፡፡ እናም ትምህርት ቤቱ በኃላፊነት፣ በማዋሃድ እና በመጠበቅ

ረገድ ከሚሰጡት ነገሮች ሁሉ፣ ዝግጁነት፣ ዝግጅት፣ እና ለስኬት፣ ለላቀ እና ለፈጠራ ችሎታ ማቀድን ነዉ የሚያስተምረዉ፡፡ ከእንግዲህ መሃይምነት እና ድንቁርና የለም ፡፡ ምንም ስንፍና፣ መዘናናት፣ አለመፈፀም፣ ወይም ለተወረሰው ድንቁርና እጅ አይሰጥም። እርስዎ ሙስሊም ነዎት፤ ከዚያም የተማሩ ነዎት፤ እርስዎ ሙስሊም ነዎት፤ ከዚያም ስልጡን ነዎት ፡፡

በእስልምና ትምህርት ቤት ውስጥ ማጥናት ያለብዎት የመጀመሪያ ርዕሰ ጉዳይ፣ እናም ማጥናት እና ማሳካት ያለበዎት፣ ከዚያ በእሱ ውስጥ የምያልፉት እናም የምኖሩት ነገር፣ የሶላት ትምህርት ነው። ቁጥሮቻቸውን፣ዘመናቸውን፣ ስማቸውን፣ ዓይነቶቻቸውን እና ቅርጻቸውን ማስታወሱ እና እንቅስቃሴዎቹን፣ ጽሑፎቹን፣ ግዴታዎቹን፣ የሚፈቀዱትን እና እገዳዎቹም እንደዚያዉ በመተግበር ከዚያ እውነተኛ ሙስሊም መሆን የግድ አስፈላጊ ነው፡፡ ዛሬ ዛሬ እየተከናወነ ካለው በተለየ ሁኔታ፣ ተማሪዎቻችን ከትምህርት ቤቶቻችን እና ዩኒቨርስቲዎቻችን ትምህርቱን እንደተረዱ እና ከትምህርት ቤቱ እንደተመረቁ ወዲያውኑ ተግባራዊ ባላማድረግ ትምህርቶች፣ እዉቀቶች እና ክህሎቶች ከዉስጣቸዉ የተደመሰሱ ወይም እየተሰረዙ ያለዉ ሆነዉ እናገኛቸዋለን፤ የያዙትን የምስክር ወረቀት ሥራ ለማግኚያ መንገድ እና ለመተዳደሪያ ብቻ ስለሚጠቀሙበት፡፡

ይህ ከእስልምና ትምህርት ቤት ውስጥ የመጀመሪያ ርዕሰ፣ ከከበረው የቁርአን ርዕሰ ንባቡን በደንብ ከመያዝ፣ ከማስታወስ እና ከመተግበር ጉዳይ ጋር ጎን ለጎን፣ ከዚያም የተከበረውን የነብዩን ሀዲስ በማስታወስ፣ በመረዳት እና አስተምህሮቹን ተግባራዊ በማድረግ፣ ወጣቱን ሙስሊም ሌሎች ትምህርቶችን ከእስልምና ሳይንስ፣ ቀስ በቀስ እንዲያጠና፣ እንዲረዳ እና እንዲገነዘብ ይመረዋል፡፡ ከዚያም እንዲያስታወስ እና እንዲተገብረው የሚገባውንም በቃል ይሸመድዳል እና ይተገብራቸዋል፤ እናም ከዚያ በኋላ ወደ ሕይወት ሳይንስ ማወቅ መግቢያ ይሆናል እና በዉስጧ ይዋኝ እና ምስጢሮቿን ያገኛል፡፡

ሶላት ማለት ለሙስሊሙ ባህል እና ሳይንስ ማለት ነው፣ ከዚያም ስልጣኔ ነዉ፡፡ አለበለዚያ፣ በሰጋጅ ቤት ውስጥ ያደጉ ተማሪዎች፣ ብዙውን ጊዜ፣ በባዶ ቤት (የማይሰገድበት) ውስጥ ካደጉ ተማሪዎች በድንገተኛ ክስተት የሚበልጡ መሆናቸዉን እንዴት በግልፅ መረዳት ይቻላል?

ሆኖም፣ ይህ ብዝሃነት ከዚህ መሰረታዊ ስልጣኔያዊ ተግባር ውጭ ሌላ መሰረታዊ እና አስፈላጊ ተግባር አለው፣ አስፈላጊው ነገርም ነዉ- አክብሮት/ትህትና (ኹሹዕ) ፡፡

**የብዝሃነት አስፈላጊነት ለትህትና (ኹሹዕ)**

ድግግሞሽ፣ ሥርዓት ዝግጅት ወይም እንቅስቃሴዎች ያለው ነገር ሁሉ መጨረሻው ከአዕምሯዊ ገደቦች ዉጪ ማስተዋልን በማጣት፣ እና ከዚያም ወደ መዘናጋት፣ እና ምንአልባትም መተኛት ሊያመጣ ይችላል...
መኪናዎን በከፍተኛ፣ ቀጥ ባሉ እና በተራዘሙ መንገዶች ላይ ሲያሽከረክሩ አስተውለዎታልን፣ እንቅልፍ፣ መሰላቸት እና ምንአልባትም መዘበራረቅ እንዴት ያሳስባችኋል፣ የማይቀያየር መንገድ፣ አንድ መንገድ፣ እና እምብዛም በማይጨምር ወይም በማይቀንስ አንድ ፍጥነት? የመጀመሪያው የሶላት እና ትርጉሞቹን የማሰላሰል ትህትና እና ማስተዋል ጠላት፣ በዚያም ወደ አሏህ ለመድረስ፣ ለክብር እና ለልማድ እጅ መስጠት ነው፣ እና ብዝሃነትን በሚገባ አለመጠቀም ነዉ፡፡ ይህቺ አምልኮ በሚፈቅደድልን የልዩነቶች አይነት መሰረት፤ ወደ “ከፍተኛ መንገድ” በቀጣይነት መገስገስ ነዉ፣ ቋሚ እና ወጥ ነጠላ መንገድ ገፅታ ላይ፣ በንዑስ፣ ቀጥታ እና በተከታታይ በሚለወጡ ጎዳናዎች ውስጥ አይደለም…

የአምስቱ ዕለታዊ ሶላቶች አምስት ራከዓዎች ብዛት መለያየት፣ የእነዚህ ሶላት ጊዜያትም መለያየት፣ በውስጧ የአነባበብ ሁኔታዎች መለያየት፣ እና በሶላት ዉስጥ የአካል ክፍሎች እና የአካል ኣንጓዎች እንቅስቃሴ መለያየት፣ እና የንባብ ልዩነት የሰውነት እንቅስቃሴዎች ጋር መኖር፣ እና ከሌሎች የብዙኃነት ንበባት የዘረዘርናቸው ብዙ ነገሮች፣ በሶላት ከምንለማመደው ወይም ከምንናገረው ነገር ውስጥ የተሳሳተ ወይም አእምሮን እና ነፍሳችን ከሚያስጨንቀን ጉዳዮች ያድኑናል፡፡ በተጨማሪም ነፍሶቻችንን ከልማድና ግትርነት በማራቅ እና እንግዲያውስ ስለምንናገረው ነገር የበለጠ እንድንገነዘብ፣ ከአሏህ ጋር ያለን ግንኙነት የበለጠ አክብሮት (ትህትና) እና ስሜት እንድኖረን፣ በዚህ የእለት ተእለት አምልኮችን ዉስጥ መሠረታዊ ምሰሶዎችን በአግባቡ እንድንተገብር ያደርገናል፡፡ ከዚህም ባሻገር፣ አስደናቂ ተግባራዊ ሥልጠና ከመሆኑ በተጨማሪ ለተጨማሪ የትኩረት ትምህርቶች፣ የትዕግስት ትምህርቶች፣ እና ለጽናት

ትምህርቶች ዕድሎችን ያመቻቻል፡፡ እነዚህ መሠረቶች፣ ሁል ጊዜ የሰው ልጅ ስልጣኔ የምንገነባበት ምህዳር ናቸዉ፤ ሆነዉም መቆየት አለባቸዉ፡፡

የሶላት ትምህርት፣ በልዩ ሁኔታዉ፣ ከባድ ትምህርት አይደለም፡፡ እናም ሰውን መገንባት ቀላል ስራ ሲሆን፣ ስልጣኔዎችን ማቋቋምም ቀላል ጉዳይ ይሆናል፡፡ እና ሀገራትን ማቋቋም እና መገንባት ያለዚህ መንፈስ ሊገኝ የሚችል ነገር ነበርን? እና ካለእንደዚህ ያለ ከፍተኛ መንፈስ ከሌለ ይፈጸማልን?

አየህ፣ ለሃይማኖታችን ሁለተኛው ምሰሶ ውስጥ እንደዚህ ላለው እንግዳ ልዩነት፣ እና እንደዚህ ላለው "አስቸጋሪ ትምህርት" አንድ ሙስሊም ልጅ ከሰባት ዓመቱ መቀበል አለበት? የዓለማት ጌታ ታላቁን ነቢያችንን ወደ እርሱ "ሊጠራ" ፈለገ? ከእስልምና ትምህርቶች ይህን አስቸጋሪ፣ ረዥምም እና አስፈላጊ ትምህርት ሊያስተምረዉ በሲድረት አል-ሙንተሃ ጋር? የተቀሩትን ትምህርቶች ጅብሪል ነብይን (ሰ.ዐ.ወ) ባስተማረበት መንገድ ለየት ባለ መልኩ?

እና በመጨረሻም፣ ብዝሃነት እንዲሁ ሌላውን የመቀበል እና ተቀባይነት ያለው ትምህርት ቤት ነው። የነቢዩ ትምህርት ትንቢት በተለዋጭነት እና በልዩነት የማይረሱ ትምህርቶችን አስተምሮናል፤ በሶላትም ይሁን በሌሎች ጉዳዮች፣ በተለይም በሱናዎቹ ዉስጥ፡፡ ይህ የመለጠጥ ችሎታ በምሳሌነት በእውነቱ እስልምናን የመቻቻል፣ የመካከለኛነት፣ ከአከባቢው፣ ከዘመኑ እና ከሁኔታዎች ጋር የመጣጣም፣ በእያንዳንዱ ሰው ሊለያይ የሚችል መንፈስን ያሳያል::

## ሁኔታዎች እና እንቅስቃሴዎች መለዋወጥ .. ለምን?

በሶላት ወቅት የሚደረጉ የሰውነት ሁኔታዎች እና ልዩነት መብዛት በከንቱ አይደለም፤ አለበለዚያማ፣ ሁሉንም ነገር ምንም እንቅስቃሴ ሳናደርግ፣ እንደተቀመጥን፣ ቆመን፣ ተኛን፣ በተጠጋን፣ ባለንበት፣ ባነበብን ነበር፡፡ ለምሳሌ፣ በምንም እቅስቃሴ ለመቆም ሳንገደድ፣ በታመመ ወይም ደካማ በሆነ ሰዉ ሶላት ሁኔታ..

የእንቅስቃሴዎች ሚና በሶላት ወቅት የ"ብዙኃኑን" አካል በመስጠት እና በመድገም አደጋን ከማስወገድ ረገድ፣ (እንዲህ) ብለን ልንጠይቅ እንችላለን፡ በሶላት ውስጥ የንባብ

ለውጥ ከሰውነት አቀማመጥ ጋር ለምን ተዛመደ፣ ለምን እያንዳንዱ ሁኔታ የተለየ ንባብ ሆነ? ለምንድነው (ክብር ለታላቁ ለጌታዬ) የሚትለዉ የምስጋና ሀረግ ለምሳሌ ከ (ሩኩዕ) የመጣቸዉ፣ ለምንድነዉ ከ (ሱጁድ) ጋር ያልመጠቸዉ፣ሱጁድ ዉስጥ (ክብር ለጌታዬ ለልዑል አሏህ ይሁን) የሚለዉ ሲመጣ? ለምንድን ነዉ፣ የቁርአን ጽሑፎች ላይ መቆም፣ የነቢያት ጽሑፎችን (ኢብራሂማዊ ሰላምታዎችን እና ሶላቶችን) ስናነብ ደግሞ በመቀመጥ ላይ ብቻ የተብቃቃነዉ? እና ለምን፣ እና ለምን?

በሶላት ውስጥ ሁኔታዎቻችን መለዋወጥ፣ ነቅተን እንድንቆይ እንዲሁም በሙሉ ትኩረት ወደ እሱ ዞረን ከእሱ ጋር ማውራት ለመጀመር ዝግጁ እንድንሆን ይረዳናል፡፡ በተጨማሪም፣ እነዚህ ንባባችንን የሚከተሉት ተለዋዋጭ ሁኔታዎች ጋር የምንለውን የምንረዳበት እና አተገባበራችን እና እንቅስቃሴያችን ከከንፈሮቻችን የሚመጣውን እንዲያረጋግጡ የሚያደርጉ ልምምዶች ናቸዉ፡፡ ይህ ድርጊታችን ጋር ከተናገርነው ጋር የሚገኝ መሆኑን እና እኛ በምንናገረዉ ሙሉ እምነት እና አመኔታ እንዳለን ማረጋገጫ ይሆንልናል፡፡

ስለ እነዚህ ሁኔታዎች ያለን ግንዛቤ እና ስለእነሱ ያለን ፍልስፍና ምንም ይሁን ምን፣ ይህ ፍልስፍና ከመለኮታዊ፣ የተሟላ እና እውነተኛ የትርጓሜ አንፃር ጉድለት ያለበት ቢሆንም፣ እነዚህ የሚለዋወጡ ሁኔታዎች፣ በሶላት ውስጥ ያሉትን የእንቅስቃሴዎችን መስመር፣ ከቃሉ መስመር ጋር በጠበቀ መልኩ ያቆያሉ፤ ይህ እዉነተኞች መሆናችንን ለማመላከት፣ በቅን ልቦና እና በቅንነት የምንፈልገዉን ለማነጋገር መሰረታዊ እና አስፈላጊ ነገር ነዉ፣ገና እንደምናየው፡፡

በሶላት ዉስጥ እንቅስቃሴያችን ብቻ አይደለም ሌሎች እንዲንመለከቱን የሚያደርጉን ነገሮች፤ መረጋጋታችንም ጭምር ነው፡፡ ይህ በሶላቱ ሁሉ ወደ ቂብላ አቅጣጫ ለማመላከት እና ያለማቋረጥ የሱጁድ ቦታ ማየታችን፣ ወደ ግራ ወይም ወደ ቀኝ ላለመዞር እና ከሚያነጋግረንን ሰዉ ምላሽ ከመስጠት በተሟላ ቁርጠኝነት መቆጠብ ላይ ፅናት ማድረግ፣ ምክንያቱ ምንም ይሁን ምን፣ ይልቁንም በእኛ እና በቂብላ መካከል ማንም ሰው እንዲያልፍ የማንፈቅድበት የተከለከለ ቦታ መሆኑን ለማሳወቅ ነው፡፡ ይህ ሁሉ ሌሎችን የሚያስደንቅ ነው፤ እናም እኛ በሶላታችን “በጣም ልዩ ሁኔታ” ውስጥ

የምኖር፣ ምንም የማይመስለዉ፣ ማንኛውም ዓለማዊ ጉዳይ ጣልቃ እንዲገባ የማፈቅድ ያደርጋቸዋል፡፡

## ወደ ሶላት ጥሪ (አዛን) እና አሥሩ አስገራሚ ነገሮቹ

*አሏህ ታላቅ ነው፣ አሏህ ታላቅ ነው፣ አሏህ ታላቅ ነው፣ አሏህ ታላቅ ነው፣*
*ከአሏህ በቀር ሌላ አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ፣ ከአሏህ በቀር ሌላ አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ፣*
*መሐመድ የአሏህ መልእክተኛ መሆኑን እመሰክራለሁ፣ መሐመድ የአሏህ መልእክተኛ መሆኑን እመሰክራለሁ፣*
*ወደ ዘካ ኑ፣ ወደ ዘካ ኑ ........*

ከዚህ በፊት እንዲህ ዓይነቱን የሶላት ጥሪ ሰምተዋልን? እኔም አልሰማሁም .. እራሴን ከፍ ለማድረግ ለመሞከር የፈለኩት ጥሪ ነው፡፡ እና ጽሑፉ ለመጀመሪያ ጊዜ በቢላል እንደ ተሰማና እንዳነበበው እንደማንሰማ ወይም እንዳናነብ ከሚከለክልዎት የግንኙነት ትስስር እናነሳዎታለን፡፡

የሶላት ጥሪ እንዲሁም ኢቃማህ፣ የልማዳችን እና የጭካኔያችን ሰለባ ከሆኑት ነገሮች መካከል ናቸው፤ በውስጣቸው ከአስደናቂ ሚና ያለዉ ቢሆንም፣ በእጆቻችንን ቢያንስ አስር ሚናዎችን ለመዳበስ እንሞክራለን፣ እኛ በሰው ልጅ አቅም የምንችለው ሁሉ ወይም ቢያንስ የእኔ የግል ችሎታ ለማብራራት እንሞክራለን፡

በመጀመሪያ- ከእኛ መካከል አንድ ጊዜ አስቦ ራሱን ጠየቀን አለን፡ ከአምስት እስልምና ምሰሶዎች መካከል ለምን ሶላት ብቻ በዚህ በቅድመ አፈፃፀም “ማስታወቂያ” ሆነ? አዛን በድምፅ ወደ ሶላት ጥሪ ስለ መነሳታችን የምናሳውቀው አይደለምን? በዚህ በአስፈላጊ የኢስላም ምሰሶ? ለምን ወደ ጾም ጥሪ አናደርግም? ለምን ሶላትን እናቋቁማለን እና ጾም አናቋቁምም ? ምንአልባት ዘካ፣ ከጥቂት ጊዜ በፊት በፈጠርኩት ሶላት ጥሪ እንዳደረግኩት? የሰው ልጅ ራዕያችን አድናቆት ይህንን ሶላትን መግቢያ ብቻ ለይቶ ባሳየው መለኮታዊ ጥበብ ሊደርስበት አይችልም፡፡ ይልቁን ከ ሁለቱ መግቢያዎች፡ ለሶላት ጥሪ እና ለኢቃማ፣ ግን በመጀመሪያ የዚህን ትርጉም አስፈላጊነት መገንዘብ እንችላለን፡፡

ያ ማለት ለሰጋጁ የሚያረጋግጥ እና ሁል ጊዜ የሚያስታውስ ነገር ቢኖር፣ እኛ በጣም የምንረሳው፣ ሶላት፣ አንድ ሰው ብቻውን ከሌሎች ጋር በተናጠል የሚያከናውን ግለሰባዊ እርምጃ እና ግዴታ አለመሆኑን እና የአጠቃላይ የጋራ ተግባር፣ በመጀመሪያ ደረጃ የሚጋራ ስራ መሆኑን ያጠናክራል፡፡ እናም ወደ ሶላት ጥሪ ማድረግ የዚህ "የጋራ" ሶላት መገለጫ እንጂ ሌላ አይደለም። እናም አንድ ሰው ይህንን ጥሪ እንዲመልስ ለስብሰባው እና አፈፃፀሙ በአንድነት በአንድ ቦታ ከአንድ ሰው ጀርባ እና "የጋራ ሥራ" እንዲዘጋጅ ነዉ፡፡ እና የሶላት ሚና በባሪያዉ እና በጌታው መካከል ባለው ግንኙነት ብቻ የሚገደብ አይደለም ፣ ግን ከዚህ ባሻገር ጥሪዉ ወደ ግንኙነት፣ ወደ አንድነት፣ በባሪያዉ እና በተቀሩት የአሏህ ባሪያዎች መካከል፣ ከአማኞች መካከል ወደ መቀራረብ ፣ መተባበር ፣ መግባባት እና መወዳጀት ። የሚሻገር ነዉ፡፡ ብዙውን ጊዜ በተናጥል የሚከናወኑ የሱና ወይም የነዋፊል ሶላት አዛን ወይም ኢቃማ አልተጠየቁም፣ ምንም እንኳን እነሱ ከግዴታ ሶላት የተለዩ ባይሆኑም፡፡

ዉዱእ በብዙ ሌሎች የሥልጣኔ ገጽታዎች መካከል አንድ የሶላት ገጽታ ሲሆን፣ (የጋራ ሶላት የስልጣኔ ምስጢር) በሚለዉ ፕሮግራም ዉስጥ በዝርዝር የምንገልፀዉ ይሆናል፡፡

በሁለተኛ ደረጃ- አዛን እና ኢቃማ በትንቢቱ ሕይወት ውስጥ ለመገለጥ (መንፈሳዊ መልእክት) ቅርብ ወደ ሚሆኑበት ደረጃ ከፍ የሚያደርጋቸው አስደናቂ የልደት ታሪክ ናቸው፣ እራሱ መገለጥ ባይሆንም፣ግን ከመሣሪያ/መለኪያ እና ከሰው ልዩነት ጋር። መለኪያዉ አመጣጣቸዉ በምናብ/በራዕይ እንጂ በንቃት ውስጥ አይደለም፡፡ ሰዎችንም በተመለከተ፣ በተላለፈው የሶሃባዎች ራዕይ ውስጥ ነው ፣ ለመልእክተኛው አይደለም ፡፡

በዚያው ምሽት ራዕይ ያዩ ሶሃቦች ተመሳሳይ ራዕይን፣ ተመሳሳይ ቃላትን እና ተመሳሳይ ዝርዝሮችን ነዉ ያዩት ፡፡ ግን ከእነዚህ ሁሉ ዝግጅት በጣም አስፈላጊ እና ሳቢ የሆነው ሁለት የተከበሩ ባልደረቦች አንዱ ዑመር ቢን አል-ኸጧብ (ረ.ዐ) ከጻድቃን ኸሊፋዎች ሁለተኛው መሆኑ ነው፡፡

ይህ የአዛን ጥሪ ልዩ ልደትን፣ ከሶላት ልደት በቀር፣ ሌላ ግዴታ አይወዳደረዉም ፣ በልዩነቱ ላይም ተጽዕኖ አያሳድርም። ሁሉም እስልምና ከሶላት በስተቀር፣ ቁርአን እና በሱናን ጨምሮ፣ በራዕይ ነዉ የተገለጠዉ ፡፡ በርግጥ የአሏህ መልእተኛ (ሰ.ዐ.ወ)

ከዓለማት ጌታ ዘንድ፣ሶላትን በዝርዝሮቹ ሁሉ ለመቀበል ወደ ሰማይ በልዩ ተአምራዊ ጥሪ ተጠርቶ፣ የሶላት ጥሪ (አዛን) በስተቀር፣ ሁሉን ቻይ በሆነው አምላክ ይህንን ልዩ፣ ተከታታይና ታላቅ መልእክት ለታማኝ ነቢይ አስተላለፈ፡፡

በሦስተኛ ደረጃ-የሶላት ጥሪ በእውነቱ ፣ በአቀራረቡ እና በትርጉሙ ፣ አማኙን ለሶላት የሚከተለው ረዥም ሶላት የሚያዘጋጅ አጭር የመግቢያ ሶላት ነው፡፡ አዲስ የተወለደ ህፃን በጆሮው ላይ የሶላት ጥሪ ማቅረብ/ማንበብ መላ ሕይወቱን ለሚጠብቀው ረዥም ሶላት ለማዘጋጀት አጭር የመግቢያ ሶላት ወይም ሱና ነው ፡፡ የሶላት ጥሪ ለአራስ ሕፃናት ሁሉ፡ ሕይወት ውስጥ ገብተዋል የሰዉ ልጅ ሆይ፣ እንደሚል ነው:: ከዚያ ሶላትን እና አምልኮን ለመጀመር የማያልቅ መንፈሳዊ ግንኙነት ከአሏህ ጋር ለመጀመር ይዘጋጁ፣ እስከተው ድረስ ፡፡ እዚያ ረዥም የኣኸራ ጉዞዎ ከአሏህ ይጀምራል ፣ ይህም ከእርስዎ አጭር ፣ አላፊ ከሆነው ዓለማዊ ጉዞዎ የተለየ ነው ፡፡

ሕይወታችን፣ ከነሁሉም ዝርዝሮቿ፣ የሶላት ዓይነት ብቻ እንጂ፣ ምንም አይደለችም ፤ ግን በተለያዩ መንገዶች እና የተለያዩ ቅርጾች ፡፡ ሕይወታችን ሁሉ፣ ከልጅነት እስከ ሞት ድረስ፣ የምናቀርበው አምልኮ እንጂ ሌላ ነገር እንደሌለ፣ ልዑል አሏህ አልደነገገውም፣ ቅዱስ ቁርዓን ይናገራል:

وَمَا خَلَقۡتُ ٱلۡجِنَّ وَٱلۡإِنسَ إِلَّا لِيَعۡبُدُونِ ۝٥٦ الذاريات: 56

*(እና ጂን እና የሰው ልጆች እኔን እንዲያመልኩ በስተቀር አልፈጠርኩም? (አል-ዛሪያት:56)::*

*እርስዎ ይማራሉ/ ያስተምራሉ፤ እርስዎ በሶላት ውስጥ ነዎት፣ እራስዎ ን እና ቤተሰቦችዎን ለመደገፍ እየሰሩ ነው፣ እና እስከትተው ድረስ፣ ሰዎችን እና ህብረተሰብን እያገለገሉ ነው፣ ከዚያ እርስዎ በሶላት ውስጥ ነዎት ፣ ለመኖር ትበላለህ እና እራስዎን ያፋፋሉ፣ ከዚያ እርስዎ በሶላት ውስጥ ነዎት፣ ጤናዎን ይንከባከባሉ፣ ከዚያ እርስዎ በሶላት ውስጥ ነዎት... ህይወታችን በሙሉ ከ ሀ እስከ ፐ አምልኮ እና ሶላት ነዉ ፡፡ ወደ የሶላት ጥሪ የሚደረጉትን ቃላቶች በእርጋታ ይመልከቱ፣ እና አጭር ሶላት ሆና ቃላቶቿ መንገድዎን ለዝርዝር ሶላት የሚጠርግልዎት እንጂ ሌላ እንዳልሆነ ይገነዘባሉ።*

አራተኛ- በጭራሽ የሶላት ጥሪን ወይም ቃላቱን መቼም አልሰሙም ብለው ያስቡ ፤ ለመጀመሪያ ጊዜ አሁን (አሏህ ታላቅ ነው) የሚለዉን ሐረግ እየሰሙ ነው ብለው ያስቡ ፡፡ ምንም እንኳን ከራሱ ከሶላት ጥሪ የምትቀድም ቢትሆንም፣ ሙስሊሞች ከጌታችን ዘንድ የተከበረው ነቢያችን የምዕራጅ ምሽት ሶላትን ከተቀበሉ ጊዜ ጀምሮ ነዉ የሚያውቋት ፡፡ ስለ ትርጉሙ፣ ስለ ልዩ ቋንቋው እና ሰዋሰዎው ያስቡ፣ የተለየ ሐረግ እና ያላለቀ ነዉ፡፡ ስለሆነም በአዕምሮዎ እና በእውነታዎ ሊሟሉ ለሚችሉ የተለያዩ ዕድሎች ወይም ትርጉሞ ክፍት ነው፡፡አሏህ ይበልጣል .. ከእሱ ከሚያደናቅፈኝ አለም ይልቅ፤ አሏህ ይበልጣል .. በዚህ በእጄ ካለው ገንዘብ፤ አሏህ ይበልጣል .. ሕይወቴን የሚረብሸው ጭንቀት፣ አሏህ ይበልጣል .. ከሚጋፈጠኝ ጠላት ይልቅ፣ አሏህ ከኃያላን፣ እኔን የሚያሳድዱኝ ጨካኞች ሁሉ ይበልጣል እና... ወዘተ [ይህንን አስደናቂ ሐረግ በልዩ ክፍል ውስጥ በስፋት እንገልፃለን/እንዳስሳለን ፡፡

**(አሏህ ታላቅ ነው)** ሁሉንም የሶላት ጥሪ በእውነት የሚያጠቃልል ሐረግ ነው፤ ቃሉ በእውነቱ እስልምናን ሙሉ በሙሉ የሚያጠቃልል ሐረግ ነው ። እኛ “ሙስሊሞች” ነን “መስጠታችንን” እና መቀበላችንን ስላወጀን፣ እኛ ተገዢ የምንሆን ስለሆንን ከሁሉም የሚበልጠውና ታላቅ ሀይል እንዳለ አምነናል ፡፡ በአጭሩ እሱ “እስልምና የሚለው ቃል” .. (አሏህ ታላቅ ነው = እስልምና)፡፡

በአምስተኛ ደረጃ- ለአረቦች አዲስ በሆነ ልዩ የቋንቋ ዘይቤ፣ እንዲሁም የተወሰኑ ቃላቶችን በመያዝ ነዉ የሶላት ጥሪ የመጣ፤ እንዲሁም በዚያን ጊዜ አረቦች ያልሆኑም የማያዉቁት፡፡ ይህ ዘዴ ከዘመናት በፊትም አልፎ ነበር ፡፡ ከእነዚህ አረፍተ ነገሮች ዉስጥ፣ አንዳቸውም በአያያዥ መሳሪያዎችም ሆነ በለመድናቸው ባህላዊ የቋንቋ አገናኞች አልተያያዙም፡፡ ለምሳሌ (ያ) ወይም (ምንአልባት) ወይም (አለን) ወይም (እና) ወይም (ረ) ወይም በሌሎች እንዳልተዛመዱ ልብ ይበሉ፡፡ ይህ በእውነቱ በሞባይል ስልኮቻችን ዛሬ በምንለዋወጥባቸው ፈጣን መልእክቶቻችን ዘይቤ አያስታውስዎትም? የሶላት ጥሪ ለአረቦች በዚህ መልኩ እንዲታጠር ተደርጓል፣ በጥቂቶች፣ ቀጥተኛ እና በግልጽ ቃላት፣ በምክንያቱ፣ ጣዖቶቻቸውን፣ የሃይማኖት መግለጫቸውን እና አለማወቃቸውን ትቶ የአዲሱ ተልዕኮ መንፈስ የተላበሱት::

ስድስተኛ- ግን በጣም ያልተለመደ ነገር፣ ይህ አጭር ሶላት ከዚህ የቴሌግራፊክ ቋንቋ ተፈጥሮ ጋር የሚስማማ መሆኑ ነው፤ በታላቁ ሶላታችን በጣም አስፈላጊ ክፍል ቋንቋ የመጣው ፍጥነት ጋር፣ አል-ፋቲሃ። አል-ፋቲሃ እንዲሁ ለመድናቸው እና ከየትኛው አረቦች በቋንቋቸው ከለመዱት የቋንቋ ትስስር ባዶ አልነበረም? በእኔ እርግጠኝነት፣ ጉዳዩ ወደ ተራ የሰው ቋንቋችን ከተተወ፣ ፋቲሃ እንደዚህ ያለ ነገር ይሆን ነበር፡

እኛ (የዓለማት ጌታ) እናውቃለን (እርሱ ምስጋና ይገባዋል) አሁንም እርሱ (እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ) እና እርሱ ብቻ ያለ ነው፤ ሌላ (በፍርድ ቀን ንጉስ)፣ ስለዚህ አቤቱ ጌታ ሆይ! እኛ አንተን እና (ለዚያ) አንተን ማምለክን ለማረጋገጥ መጥተናል፣ በሁሉም የሕይወታችን ጉዳዮች ውስጥ (እገዛን) እንይቃለን ፣ ስለዚህ ያንን እየጠየቅን ወደ እርስዎ እንሄዳለን (ወደ ቀጥተኛው መንገድ ይምራን) ...

ሰባተኛ- ለሶላት ጥሪ በአምልኮታችን ውስጥ ሥነ-ምግባሩ እና መስፈርቶቹ በሚያዘው አቋም ምክንያት፣ እኛም፣ በነቢዩ ሱና መሠረት፣ ቃላቶቹን በቃላት በቃል ማስተጋባት አለብን፤ ተጓዳኝ በሆኑ ቃላት ምላሽ በመስጠት፤ በዚያም አያበቃም፤ በመጨረሻ ከሙአዚኑ በኋላ በምንደግማቸው ሌሎች ትንቢታዊ ቃላት እንማልዳለን፡፡

ከኮምፒዩተር ጋር በምንለማመድባቸው በይነተገናኝ ስርዓቶች ውስጥ ዛሬ እንደነበረው እና ከእሱ የሚገኙ ሌሎች አስደናቂ መሣሪያዎች እና ስርዓቶች፣ከአዛን ጋር ያለን ግንኙነት፣ ክቡር ነብዩ (ሶ.ዐ.ወ)ከአስራ አራት መቶ ዓመታት በፊት እንዳስደነገጉልን፣ በሰው እና በተፈጥሮ መካከል ኮምፒተር ወይም መስተጋብር ስርዓት ከመኖሩ በፊት፣ ከሶላት ጥሪ ጋር ያለን ግንኙነት በተቀባዩ ሞገዶች እና በሚያንፀባርቁ ሞገዶች መካከል በይነተገናኝ ዙሪያ ወደ ኋላ እና ወደ ፊት የሚለዋወጥ ግንኙነት ነው፡፡ ሙአዚን በሰጠው እያንዳንዱ መግለጫ/ሐረግ ፊት ለፊት በአድማጩ የሚስተጋባ ሌላ ሐረግ እንዳለ ግልፅ ነዉ ፡፡

ስምንተኛ- በሶላት ጥሪ እና አዛት ጥሪ መካከል በዚህ አስደናቂ የቋንቋ ስምምነት መካከል የሶላት ጥሪ በተሰራበት ይህ የቋንቋ መዋቅር ነው፣ እያንዳንዱ ሐረግ ሁለት ጊዜ ስለሚደገም ፡፡ ይህ ሁለትነት በመጀመሪያ ደረጃ የአዛንን ገለልተኛ የቋንቋ ባህሪ

ያጠናከረዋል ፣ እና በሚገርም ሁኔታ ፣ በዚህ ረገድ፣ ከአጠቃላይ የሶላት ግንባታ ጋር ስምምነቱን ሊያሳድግ ይችላል ማለት ነዉ፡፡

ቁጥር (ሁለት) በእስልምና ሥነ-ሥርዓቶች ፣ ዚክር እና ትረካዎች ከተለመዱት ማዕከላዊ ቁጥሮች አንዱ አይደለም፤ ብዙውን ጊዜ፡ ሶስት፣ ሰባት፣ አስር፣ ሃያ ሰባት፣ ሰላሳ ሶስት እና ዘጠና ዘጠኝ እና አንድ መቶ ቁጥሮች ይበዛሉ ፡፡
በተጨማሪም የሶላት ጥሪ ሀረጎች ሁለት ጊዜ ተደጋግመዋል፣ ስለሆነም ከዚህ ሁለትነት ጋር ከሚስማማው እና የሚጣጣሙ፡ ሶላቶቻችን በሁለት እጃችን ኢህራም ተክቢራ ውስጥ ስናነሳ እና በየሁለት ረከዓዎች በኋላ በሶላታችን ውስጥ ቁጭ ብለን ስንሰግድ፣ እያንዳንዱ ረከዓ ሁለት ሱጂዶች ስላደርግ፣ ከዛም በሶላታችን መጨረሻ ሁለት ጊዜ ሰላምታ እንለዋለን ፡፡ ይህ እንደገና ስሜታችንን ያሳድጋል፤ ወደ ሶላት ጥሪ ስናደርግም በእውነቱ አጭር የመግቢያ ሶላት በከፍተኛ ድምፅ እየደገምነው ነው ማለት ነዉ፡፡
ዘጠነኛ- ለሶላት ጥሪ መግለጫዎች ተውላጠ ስምን በማይገልጽ ገለልተኛ ቋንቋ እንዴት እንደመጡ አስተውሎዋል-የተወሰነ ፣ ተናጋሪ ፣ አናጋሪ ፣ የሩቅ ፣ ነጠላ ወይም ብዙ ሳይኖረዉ? ከሁለቱ ሸሃዳዎች በቀር ሌሎች ከዚህ አይለዩም፤ በሁለቱ ዉስጥ የየራሳቸዉ ሃላፊነት ትርጉም ስላላቸዉ እና ይህን ሃላፊነት በሚሉት ሰዎች ቃል የማረጋገጥ አስፈላጊነትም ስላለ (አሽሀዱ-እኔ እመሰክራለሁ)ሲል ። (ኑ) የሚለው የግሥ ስም እንኳን በቋንቋው ነጠላ ፣ ብዙ ፣ ተባዕታይ ወይም ሴት ተውላጠ ስምን አያመለክትም ፡፡ እንዲህ አይነት የቋንቋ ዘይቤ ገለልተኛና በቋንቋው እምብዛም ያልተለመደ ሲሆን ብዙውን ጊዜ በምስጋና በዝክር እና በሶላቶች ጽሑፎች ላይ ብቻ የተወሰነ ነው፡፡ ግን እንደገና ይህ ገለልተኛነት ከ(አል-ፋቲሃ) ዘይቤ ጋርም ይጣጣማል፣ የሶላት አምድ። የሱራ አል-ፋቲሃ የመጀመሪያ አጋማሽ ብዙም ባልተለመደ ሁኔታ አልመጣም? ይሄ፣ በአንድ በኩል፣ ከጊዜ ልኬቶች ሙሉ በሙሉ የፀዳ ሲሆን፣ ብዙውን ጊዜ ልኬቶቹ ከሚከሰቱባቸዉ ከሦስቱ ተውላጠ ስሞችም የፀዳ ይሆናል፡፡ በሌላ በኩል፣ በምንናገረው ወይም በምንጽፈው አብዛኛው ቋንቋች ዉስጥ የምንጠቀማቸዉን ማለት ነዉ፡፡

አሥረኛ- ምንአልባት አንዳንዶቻችን ስለ ሶላት ጥሪ ትኩረት ሊገባቸዉ የማይችል ጥቃቅን የቋንቋ ልምድ አድርገን እናያለን፤ ብዙውን ጊዜ ሶላትን ዉስጥ እነሱም እንንቃለን እና ከሶላቱ በፊት ለማከናወን ችላ እንላለን፡፡ ግን መልእክተኛው (ሰ.ዐ.ወ)፣

ለእኛ በጣም ጉጉት ያላቸው፣ ለመልእክቱ ታማኝ፣ እና ጌታው (ለአማኞች ርህሩህ እና አዛኝ) ሲል የገለፀው በሌላ መንገድ እንዲህ ብሎ ይለናል፡

**- ወደ ሶላት ጥሪ የማያደርጉ እና የጋራ ሶላት የማይሰግዱ ሶስት ሰዎች የሉም ሸይጧን ካላገኛቸዉ በስተቀር (**አህመድ የተዘገበው ፣ከአቢ ዳርዳ)

- በአብደላህ ቢን አብዱራህማን ቢን አቢ ሰዐሰዐ ከአባቱ አቡ ሰዒድ አል-ኹድሪ እንደነገረው: ፊየል እና ገጠርን እንደምትወድ አየሃለሁ፣ ፊየልህ እና ገጠርህ ዉስጥ ስትሆን እና ከዚያም ድምፅ ከፍ አድርገህ አዛን በል፡፡ ምክንያቱም የሙእዚን መጠን ፣ ጂንም ሆነ የሰዉ ልጅ ማንም አይሰማዉም በትንሳኤ ቀን ቢመሰክሩለት እንጂ ፡፡ [በቡኻሪ የተዘገበ]

ይመልከቱ ፣ ይህ ጥሪ የማስጠንቀቂያ መሣሪያ ብቻ ቢሆን ኖሮ፣ ለእርሱ ፣ ለበጎች ፣ ለበረሃዎች እና ሕይወት ለሌላቸው ነገሮች ማሰማት ለምን ያስፈልጋል? እና አዛን ያልተደረገበትን መንደር ወይም ሰዎችን እንዴት ሸይጧን ይይዛል? እነዚህ ለጋስ ትንቢታዊ ምልክቶች ለቀድሞዎቹ ሙስሊሞች ወደ ሶላት ጥሪ ዋጋ እና ወደ ኢቃማ መጥሪያ ምልክቶች፣ በሕይወታቸው ውስጥ አምልኮን ለአምላክ የማድረግ ሚና፣ ነበሩ፡ ፡ እናም ይህንን አምልኮ ላለማጣት ይሞክሩ እና በጣቶችዎ ውስጥ ያንሸራትቱ ፡፡

ዛሬ ከተጠየቅኩኝ፡-ስንት የሶላት አይነቶች አሉ? (ተብዬ) እመልሳለሁ፡ ሚስጥራዊ እና ገሃዳዊ እና ጮክ የሚባል-በዚህ የመጨረሻ ማለቴ: - ወደ ሶላት ጥሪ (አዛን) ፡፡ እያንዳንዳቸው እነዚህ ሶስት ሶላቶች ህይወታችንን እና መልካምነታችንን ለማስተዳደር የተለዩ ፣ አስፈላጊ እና የተጨማሪ ሚናዎች አላቸው፡፡

አዛን  የህብረት ሶላት ጥሪ፣ ለመጨረሻው እና ለታላቁ የኢንቨስትመንት (ልማት) ፕሮጀክት (ሶላት) የሚያዘጋጅን፣ አጠር ያለ የኢንቨስትመንት (ልማት)  ፕሮጀክት ነው::

## ሁለቱ እጥበቶች (ዉዱዓን)

**- ህዝቦቼ ላይ ባይከብድ ኖሮ በእያንዳንዱ ሶላት ላይ በእጥበት አዛችሁ ነበር፤ በእያንዳንዱ እጥበት ደግሞ በመፋቂያ** (አህመድ የዘገበዉ እና በአል-አልባኒ የተረጋገጠ ከአቡ ሁረይራ)

እኔ ብዙ ጊዜ ከዚህ ሀዲስ ፊት ቆሜ ጠየቅሁ፡-በእያንዳንዱ ሶላት ለምን?! ውዱእ አንዴ እስካደረኩና ንፁህ እስከሆንኩ ድረስ፣ የሱና ባለቤት ከሆንኩ፤ ታዲያ የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንገና ዉዱእ እንድያደረግ ለምን ፈለጉ?! ዳግመኛም ውዱእን ብያደርገስ፣ ይህ በውኃ ፍጆታን ማባከን አይደለምን? ቦታዉ የበረሃ እምብርት፣ ምንም ከወንዞች ወይም ተራራዎች የሆነ ዉሃ የሌለበት ቢሆንስ፣ ይህንን እንዴት ይመከራሉ?!

ሦስቱን ቅዱሳን መጻሕፍትን አንብቤአለሁ፣ አሏህም ከተከበረዉ ሐዲስ ስብስቦች እንዳነብ ያሻለኝን ያህል አንብቤያለሁ፣ እምነቱን፣ ግንኙነቱን፣ አምልኮቱን እና ስልጣኔውን ሁሉ በንጽህና፣ በእጥበት እና በውዱእ የሚያገናኝ ሃይማኖት አላገኘሁም፤ እስልምና እንዳደረገው:: እናም እኔ ሕዝቡን ወደ ንፅህና፣ ንፅህናን እንዲወስድ እና መልካም ቁመና እንዲኖረዉ ህዝቡን የመከረው ነቢይ አላገኘሁም፡፡ ነብዩ መሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) የእርሱን ህዝብ እንደመከረዉ፤ ከዚህ ሁሉ ጋር፣ እስልምና ከሚያስተምራቸው ትምህርቶች ሙስሊሙ ኡማ (ህዝብ) የት ነዉ ያለ?
ይህ ተደጋጋሚ ንፅህና ላይ ያለው አፅንዖት ንፅህና፣ ጤናማ፣ ባህላዊ እና ስልጣኔያዊ ገጽታ ብቻ ስለሆነ አይደለም፡፡ እሱ ግልፅ የሸሪዓ ዓላማዎች እና ተፈላጊ ዓላማ ነው፣ ይልቁኑም እሱ እዚህ በመታጠብ (ዉዱእ) የተመሳሰለውም እንዲሁ በውስጠኛው ነፍስ ንፅህና ጋር የሚገናኝ ስለሆነ ነዉ፡፡ ሰውነትዎን ወይም ልብስዎን ከሚያረክስ ነገር ሁሉ በተሟላ ውጫዊ ንፅህናዎ መጠበቅ፣መጨረሻው ተፈጥሯዊ ውጤት ነው፣ እውነተኛ ውስጣዊው ንፅህናዎ የሚንፀባረቅበት እና ውጫዊውም ላይ የሚታይ (አንዳንድ የመዝሀቦች ትምህርት ቤቶች ሃሜትን በፅዳት አፍራሾች ውስጥ ያካትታሉ) ነዉ፡፡

በዚህ አመክንዮ ሁለት ዓይነት የዉዱእ ዓይነቶች አሉ ማለት እንችላለን፡-ውስጣዊ እና ውጫዊ፤ እና የመጀመሪያው በጣም አስፈላጊ ነው:: ሁለተኛው ከሌለ አንደኛዉ አንዳች ፋይዳ የለውም እና በቆሻሻ ጉድጓድ ውስጥ የተዘፈቀ ሰው እንዴት ነው ውዱእ ማድረግ

የሚችለው? ለራስዎ ማረጋገጥ ያለብዎት፣በውጭኛው ከፍተኛ የስሜት ህዋሳትዎ ላይ የመንጻት ሂደቱን በሚለማመዱበት ጊዜ፣ ከእሷ ጋር እንደዚያዉ በውስጠኛው የስሜት ህዋሳትዎ ላይ የመንጻት ተግባር ፈፅሞዋል ማለት ነው፡፡ ይህም በውኃ ወይም በየሙም (በአፈር) የሚነፃ አይደለም፣ ይልቁንም የነፍስን ቆሻሻ በማስወገድ ነው፡፡ ማለትም በውስጥዎ የተከማቹትን፣ ከምቀኝነት፣ ከቅናት፣ ከቁጣ፣ ከወራዳነት፣ ከራስ ወዳድነት፣ ከውሸቶች፣ ከተንኮል፣ ከቸልተኝነት እና ከምስጋና ቢስነት እና ከብቸኝነት፣ ከነፍስ ትርጓሜ፣ ካለመታዘዝ፣ ካለመተማመን እና ከረዥም እጣ ፈንታ ጋር የተያያዙትን ቆሻሻዎች፡፡

ወንድም፣ ቢቻል እንኳን ከዚህ ሁሉ ቆሻሻ እራስዎን ለማፅዳት ይሞክሩ፣ ደረጃ በደረጃም ቢሆን፣ ለዚህ ፊትዎን፣ ልብዎን፣ ነፍስዎን እና ቃላቶችዎን ለአሏህ ብቻ ማድረግ እስኪችሉ ድረስ፤እርስዎ ወደ አሏህ ለመምጣት እና ከፊቱ ሊቆሙ ስለሆነ፤ ቃላትዎን ወደ እሱ ለመላክ፣ እሱም ይቀበላል፣ ሚስጥርዎን ይነግሩታል፣ እሱም ይሰማል፣ እናም ይቅርታን ይለምኑታል፣ እርሱም ይቅር ይልዎታል፡

**- አንድ ሰው ወደ ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) መጥቶ እንዲህ አለ፡‹እገሌ በሌሊት ይሰግዳል፣ ሲነጋ ይሰርቃል› ሲል፤ ነብዩ እንዲህ አለ፡ ‹ሶላቱ ከስርቆት ይከለክሏል›- ይሄ ማለት ሶላቱ ከስርቆት ይጠብቃል ማለት ነዉ፡፡** *[ሚሽካት አል-መሳቢህ እና አል-አልባኒ አርመውታል፣ ከአቡ ሁረይራ]*

**- የከሰረ ማን እንደሆነ ያውቃሉ? እነሱም፡- በእኛ ውስጥ ገንዘብ የሌለው ዲራሃምና ዕቃ ያለው ነው፡፡ እሱ፡-ከስረኛው ከህዝቦቼ የትንሳኤ ቀን በሶላት፣ በጾም እና በዘካ ይመጣል፤(ግን) ያን ሰድቧል፣ ይህን መትቷል፣ ይህን ደግሞ በድሏል፣ እናም የዝህን ገንዘብ በልቷል፤ የዝህን ደም አፍስሷል ወዘተ፣ ስለዚህ ከበጎ ስራዉ ፣ለዚያም ከመልካም ሥራዎቹ ይሰጣል፣ ዕዳውን ከፍሎ ከመጨረሱ በፊት መልካም ሥራዎቹ ካለቁ፣ ከኃጢአታቸው በሱ ላይ ይወረወራል፣ ከዛኛዉም ተደስደዉ በሱ ላይ ይጣላል፤ ከዛም ወደ ጀሃነም ይጣላል፡፡** *[ሙስሊም ከአቡ ሁረይራ ዘገበ]*

ስንቶቻችን ነን ከከሳሪዎች የሆንን? ስንቶቻችን ነን አምልኮን ከልምምድ ለየነው? ሲሰግዱ፣ በግንባራቸው ሲወርዱ ያዩዋቸዋል፤ ፊቶቻቸዉ ላይ የስግደት ምልክት

*ተድርጎ ነበር፣ ነገር ግን ያ እርስዎ ምልክት በኑሮ አያያዝ (ማህበረሰባዊ መኗኗር) እና ሥነ ምግባራዊ ተጽዕኖ ላይ አልታየም፡፡*

إِنَّ ٱلصَّلَوٰةَ تَنْهَىٰ عَنِ ٱلْفَحْشَآءِ وَٱلْمُنكَرِ ۗ ﴿٤٥﴾ العنكبوت: 45

***-ሶላት ከዝሙት እና ከሀፍረት ትታደጋለች*** *[አል-አንከቡት፡ 45]*
በሙስሊሞች መካከል በአምልኮ እና በስራ መካከል ያለ የመለያየት ሁኔታ ኢስላምን በዓለም ፊት ገፅታዉን ከሚያዛቡ በጣም አደገኛ ነገሮች አንዱ ሆኗል፡፡ መልእክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) ሰዎችን ሲያስተምር፣ በእርሱ የወረደውን ቁርአን እና በቁርአን መስራት መካከል አይለያዩም ነበር፡፡

**- ከአቡ አብዱረህማን አስ-ሰለሚ ከኡስማንና ከኢብኑ መስዑድ እና ከኡበይ ኢብኑ ከዕብ የአሏህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) አሥር ያስተምራቸዉ ነበር-እንቀፆች-በዉስጧ ያለዉን ተግባር እስኪማሩ ድረስ ወደ ሌላ አሥራ አያልፏም ነበር፣ ስለዚህ ቁርአንን እና ስራችንን ሁላችንም ተማርን** [ተፍሲር አል-ቁርጡቢ ፣ ክፍል 1፣ ገጽ 39]

*አምልኮታችንን ከቀን ወደ ቀን እንደገና መፈለግ፣ ሶላትን እንደገና ማወቅ ወይም ዉዱእን እንደገና ማወቅ አለብን፤ የዚህ ልዩ የእስልምና ሥነ-ስርዓት ታላቅነት ስሜት በውስጣችን የሚገድል ነገር በተቃረበበት ጊዜ፣ ከሌሎች ሃይማኖቶች የጎደለዉ ነገር ፡፡*

*ዉዱእን ለመጀመሪያ እንደ በሰማዎ ጊዜ እያከናወንዎ መስሎ ለመታጠብ ሞክረዎ ያውቃሉን? ያን ለማድረግ ይሞክሩ፣ ከዚያ ወደ እራስዎ ይመለሱ፡ በውስጡ ምን አገኘሁ? የበለጠ በጥልቀት ካሰቡ፣ ዉዱእ፣ በእውነቱ እንደ ሶላት ሁሉ፣ የተሟላ የሕይወት ስርዓት መሆኑን ያገኙታል፡፡*

*በመጀመሪያ፣ እሱ ንፅህና ነው፡ የተማሩ ሰዎች በሱ ይለያሉ፤ እና በሁለተኛ ደረጃ እንክብካቤ፣ ትክክለኝነት እና ክትትል ነው፡ እናም በእሱም ውስጥ ስኬታማዎቹ ይለያሉ፡፡ እና ሦስተኛው፡ ቅደም ተከተል፣ ዝግጅት፣ ጥንቃቄ እና የቀጠሮዎች ማሟላት መከታተል ነዉ፡ እና የሰለጠነው ህዝብ የሚለይበት በሱ ነዉ፡፡ እና አራተኛው ነው፣ አምስተኛው እና አሥረኛዉ ተከታታይ እና አስቸኳይ ነፍስን መገምገም፣ እና በሁለቱ እጥበቶች መካከል ባለው ጊዜ ውስጥ ሊኖሩ ከሚችሉት የሕይወት ግድፈቶች መንጻት፡*

በእርሱም አማኞች ከማያምኑ እንደ አሏህን የሚፈሩት ከማይፈሩት/ጻድቃን ያልሆኑ፣ ጥሪ ተቀባዮች ከጠፉት እና ከከሠሩት ሰዎች ተለይተው ይታወቃሉ፡፡ ያዉም የነዚህን ፊቶች ከነኛዉ ሰዎች ፊቶች እንኳን የተለዩ መሆናቸዉን፣ ውዱእ ያደረጉ እና ያላደረጉ ሰዎች እስኪለዩ ድረስ ማለት ነዉ፡፡

ተየሙም (በአፈር ዉዱእ ማድረግ) በዚህ ሁኔታ ውስጥ እንዳለ የሬዲዮ መልእክት ነው፡፡ ልብን የሚነካ መልእክት፣ ልብን ከአሏህ ጋር ለመገናኘት ለማዘጋጀት፣ እና ከእሱ ጋር የሚደረገዉን ግንኙነት ሊጎዱ የሚችሉ ነገሮችን ሁሉ ለማስወገድ፣ እሱ ዉስጥዎን አዋቂ ስለሆነ፣ የደብቁ እና በገሃድ የሚያሳዩትን አዋቂ። ስለ ዉዱእ ፣ ከዚህ አንፃር፣ የውሃ መልእክት ሆኖ ምልክቶቹ እና መልእክቶቹ እራሳቸውን ወደ ልብ ያንቀሳቅሳሉ፣ ግን በሌላ መንገድ፡፡

(ውዱእ) የሚል ቃል የተገኘው ከ (ከብርሃን) ነዉ፤ ምክንያቱም ዉዱእ በፊትም ሆኖ በልብ ብርሃን ስለሚፈጥር ነው፡፡ ፊት ግን የነፍስ እና የልብ ውስጣዊ ብርሃን ነፀብራቅ ነው፡፡

በሕይወትዎ ውስጥ ዉዱእ  ቢኖርዎት እንጂ እንዳይቆዩ ይሞክሩ፤ ወደ ሥራ ሲጓዙ በአየር ውስጥ እንደሚበሩ ይሰማዎታል፡፡ ለሰዎች ሰላምታ ሲሰጡ ከመላእክት መካከል እንደሆኑ ይሰማዎል፣ እንዲሁም ሥራዎን ሲሰሩ በእሱ ላይ ባለው ስኬት ሙሉ እምነት እንዳላቸዉ ይሰማዎታል፤እና ራስዎን በትራስዎ ላይ ሲያደርጉ፣ የእራስዎን አፈፃፀም በትክክል እንዳከናወኑ ይሰማዎታል፤ እና በመጨረሻም እራስዎን በታማኝ ጠባቂ፣ ይቅር ባይ፣ መሐሪ እጅ ውስጥ ያስገባሉ።

## የቡድን ሶላት፡ የሥልጣኔ ምስጢር

እኔ እራሴን እንደጠየቅኩ መቼም እራስዎን ጠይቀዉ ያውቃሉ? ስልጣኔ ትርጓሜው ምንድነው? ማሽኑ እና ፋብሪካው ነው? ኮምፒዩተሩ፣ ሚሳኤሉ፣ የባህር ኃይል እና የአየር መርከቦች፣ የጠፈር መንኮራኩሮች እና የአቶሚክ ቦምቦች ናቸዉን? እነዚህ በሙሉ የስልጣኔዉ ዉጤቶች ናቸዉ፤ እነዚህን ፍራፍሬዎች የበቀለው ስልጣኔ እራሱ በአስር ዘሮች ተጠቃሏል፡፡ (1) ንፅህና፣ (2) ትክክለኛነት እና ብቃት፣ (3) ሰዓት አክባሪነት፣ (4) አደረጃጀት እና ተግሣጽ፣ (5) ሐቀኝነት አመኔታ፣ (6) የቡድን ሥራ

ወይም የጋራ ሥራ፣ (7) መቻቻል፣ ትሕትና እና ሌሎችን መቀበል፣ (8) ሙያዊነት እና የግለሰብ ሃላፊነት፣ (9) ትዕግስት፣ ጽናት እና ቆራጥነት፣ (10) ፍትህ እና እኩልነት ናቸዉ።

እኔ እራሴን እንደ ጠየኩ አንድም ጊዜ ራሳችሁን ጠየቃችሁ፡-የቡድን ሶላት በመሠረቱ ለምን ነበር? ለምን ከቤቶቻችን፣ ከቢሮዎቻችን፣ ከመደብሮቻችን ወይም ከፋብሪካዎቻችን በየቀኑ አምስት ጊዜ መውጣት ነበረብን? እና በተወሰነ ጊዜ፣ እንዲያዉም ከባድ ዉሳኔ፣ በትክክል አምስት ደቂቃዎች ከዘገየን ይህንን ቀጠሮ እንዳያመልጠን የምንሰጋ? እናም እኔ ራሴን እንደ ጠየኩ አንድም ጊዜ ራሳችሁን ጠየቃችሁ?

ለምን (ኀፍረተ ገላችን የምንሸፍንበትን) ጌጣችንን እንወስዳለን በየመስጊዱ (በየሶላቱ)? ከዚያ በፊት ለምን ንፅህና? ለምንስ መታጠብ (ዉዱዕ)? ይህ ጉዳይ የአሏህን ቤት ከማክበር እና በአሏህ ፊት ለመቆም ብቁ የሚያደርገን ንፅህና ጋር ይያያዛል፣ ወይስ ከስልጣኔ ተግባራት ጋር በንጽህና፣ በግል ንጽህና፣ በመጋጌጥ እና በአዘገጃጀት ጋር? በአክብሮት እና በብቃት ከአምልኮ ሥርዓት ትይዩ ሌሎች ስርዓቶች?

ቀጠሮዎችን ማክበርን በተመለከተ የቡድን ሶላት ለስልጣኔ ችቦ ብቁ ለመሆን ሙስሊም ተመራቂ የሆኑበት ምርጥ ትምህርት ቤት ነው፡፡ ከጋራ ሶላት ለአምስት ደቂቃ ሲዘገዩ፣ ከስሯል ማለት ነዉ፣ተመልሰው ደመወዝዎን የመጠየቅ መብት የለዎትም ማለት ነው፡፡ ይህ ለሙስሊሙ በየቀኑ አምስት ጊዜ የሚደጋገመው አስደናቂ ትምህርት አይደለምን? የአንድን ደቂቃ ዋጋን ያወቀ እና ባለማድረሱ በእሱ ላይ የሚደርሰውን ኪሳራ ዋጋ የሚገነዘብ ሙስሊምን ማስመረቁ በቂ አይደለምን? ከሌሎች ጋር የሚሰግድበትን ሰዓት ባለማክበርም እንዲሁ?

ብዙ ወጣት የመኖርያ ፈቃድን ሀሳብ በመከላከል፣ በወጣትነቴ ከሼይኽ አልባኒይ፣ አሏህ ይዘንለትና ተወያይቼ ነበር፡፡ በአንድ መስጂድ ውስጥ ያሉት ምዕመናን ተመሳሳይ ሰላትን በተመሳሳይ መስጊድ የሚሰግዱ ከሆነ፣ ከመጀመሪያው የጀመዓ ሶላት ዘግይተው እንዲሰግዱ ለምን አይፈቀድም? ከመካከላቸው ኢማምን በመምረጥ ሁለተኛ ጀመዓ

በማቋቋም እዲሰግዱ ማለት ነዉ፡፡ ከዚያ ሌሎች ይመጡና ሦስተኛውን፣ ከዚያም አራተኛውን ጀመዓ ያቋቁማሉ፤ እናም ይቀጥላል?

ሼይኽ አል-አልባኒ በአንድ መስጊድ ውስጥ ይህን የቡድኖች ብዛትን ላለመቀበል እጅግ በጣም ጥብቅ ነበሩ፤ እንደ አለመታደል ሆኖ፣ ተከፋይ ኢማሞች እንደዚህ ማድረግ እንደሌለባቸዉ አጥብቀዉ ይቃወማሉ፡፡ እኔ ግን የዚህን ፍርድ ጥበብ የተረዳሁት ዘግይቼ እንጂ ወዲያዉኑ አልነበረም፡፡ በመስጊዱ ውስጥ የቡድኖች ብዛት፣ የአመለካከት ብዛትን፣ የህቡዕ ቡድንን ብዛት፣ የአቅጣጫዎችን ብዛት ያስከትልና ልቦች ከመስጊዱ ውጭ ተራርቀዉ ይለያያሉ፡፡ አንድ ቡድን ሶላት ቀጣይነት ባለው መልኩ በየቀኑ መቀጠሉ መለኮታዊ፣ እለታዊ፣ ዘለቄታዊ ልምምድ ሆኖ፣ አንድን ቀጠሮ፣ አንድን አስተላለፍ፣ አንድን ልብ እና አንድ ህዝብ የማክበር ጉዳይ ነዉ፡፡

ንፅህና ወይም ጧሃራ እና ጌጣጌጥ መውሰድ (መሸፋፈን)፣ ወደ መስጊድ እንድንገባ የሚያደርገንን እና በአሏህ ፊት ለመቆም የሚያዘጋጀን ነገር ነዉ፡፡ አሁንም፣ ንፅህና ካለፈው ድንቁርና እና ከመሃይምነት ጨለማ፣ ከማይረባ ቆሻሻ፣ ከኋላ ቀርነት፣ ከመዘበራረቅ፣ ቸልተኝነት እና ግዴለሽነት ለመላቀቅ፣ ባለፈዉ እንዳልኩት፣ የሚያዘጋጀን ነገር ነው::
ከዚያም ወደዚያ ወደ ስልጣኔ ክበብ ብቁ ሆነን እንድንገባ፣ የንጽህና እና የመልካምነት መሰረታዊ ስልጣኔን ለማያሟሉ ሁሉ በሯን የሚትዘጋ፣ የአካል ብቃት እና የዝግጅት አቀማመጥ በአካላቸው እና በልብሳቸው ብቻ ሳይሆን በመስጊዶቻቸው እና በቤቶቻቸው፣ ቢሮዎቻቸው፣ ትምህርት ቤቶቻቸው፣ ሆስፒታሎቻቸው፣ በአገልግሎቶቻቸው፣ በጎዳናዎቻቸው ፣ በነብሶቻቸዉ እና በተለያዩ የሕይወት ዘርፎች፣ የምትሻ እና የምታዘጋጀን ንፅህና፡፡

እነሆ እኛ አሁን መስጂድ ውስጥ ነን፡፡ ይህ አዲስ ስም እስልምና የፈጠረው አምልኮ እና የእኛ የቋንቋ መዝገበ-ቃላት ዉስጥ ያስተዋወቀው አይደለም፡፡ አገልጋዩ፣ሱጁድ ዉስጥ ሆኖ፣ ለጌታው በጣም የቀረበበትን ጊዜ እና ያለበትን ሁኔታ ዘወትር ያስታውሰናል፡፡ ሱጁድ ማለት ክንድዎ፣ ግንባርዎ እና አፍንጫዎ በአፈር ላይ ሲሆኑ ነዉ፡፡ ይህ ማለት ከፍተኛው የትህትና እና የመተናነስ ደረጃ ነው፡፡ ራስዎን ዝቅ እና ግንባርዎን ዝቅ

ሲያደርጉ እና በጌታ አሏህ ፊት እራስዎን ሲያዋርዱ፣ እርሱን ቀርበበዉ ከእርሱ ዘንድ ደረጃዎ በሰማይ ላይ ከፍ ይላል፡፡

በዚህ በእለታዊ የሥልጠና እንቅስቃሴ ምእመናን በየሰዓቱና በሁለት ሰዓታት እና ከዚያ በላይ በሚለማመዱት ጊዜ፣ በሌሊትም እና በቀንም፣ በታላቁ ፈጣሪያቸው (በአምልኮአቸው የማይኮሩ) ኾነዉ፣ እሱ እንደገለፃቸው፣ የመላእክቱንም እንደገለፀዉ፣ ትህትና፣ በመተናነስና በትክክል ጽኑ ሆነዉ ቢሰግዱ፣ በሕይወታቸው ውስጥ፣ የእለት ተእለት ተግባራቸዉና ልማዳቸዉ ይሆናል፡፡ ስለዚህ ወደ እብሪት እንዳይመለሱ እና ከዚያ ወደ አለመግባባት በመካከላቸዉ እንዳይፈጠር፣ በመካከላቸዉ ሁሉን ቻይ የሆነው አምላክ በመጽሐፉ (ለምእመናን መተናነስ) እንዳዘዛቸውና ታማኝ መልዕክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) እንዳዘዙት (ክንፍዎን ለአማኞች ዝቅ ያድርጉ) ይሆናሉ ማለት ነዉ፡፡ ያኔ ወደ ሥልጣኔ ክልል ውሃዎች ለመግባት የመጀመሪያ እርምጃችንን እንወስዳለን ማለት ነዉ።

እኛ (መስጊድ) እንገባለን ስለዚህ ወደ ስግደት (ሱጅድ) ትምህርት ቤት፣ የትህትና፣ የመተናነስ፣ የስብራት እና ለምእመናን የመለሳለስ ትምህርት ቤት እየገባን መሆኑን እናስታውሳለን፡፡ እኛም (መስጂድ) ስንገባ "አንድ የሚያደርገን፣ ቀጥ አድርጎ የሚያቀናን፣ ልባችንንም የሚያስተሳስረን፣ ከነፍሳችን ላይ ጥላቻን እና መጠላላትን ከልባችን የሚያስወግድ መሆኑን እየተገነዘብን ነዉ፡፡ ሙግቶች ወይም ቅናቶች የሉም፣ ትልቅም ትንሽም፣ የተከበረ ወይም የተናቀ፣ ልዑል ወይም ድሃ፣ ጨቋኝ ወይም tጨቋኝ የለም፤ ሁሉም እኩል ነዉ፡፡

- **ተስተካከሉ፤ ከመላእክት ረድፎች ጋር ስለሚትሰለፉ፣ በእግሮቻችሁ መካከል አስተካክሉ፣ እና ክፍተቶችም ዝጉ፣ እና በወንድሞቻችሁ እጅ ተደግፉ፣ እና ለሸይጧን ቀዳዳዎችን አትተዉ፣ እናም ወደ ረድፍን የሚያስተካክል ሁሉ፣ አሏህ አራሱን ያገናኟል፣ እናም ረድፍን የሚያቋርጥ ሁሉ፣ አምላክ ያቋርጠዋል** [ከአብዱላህ ቢን አምር አል-አልባኒይ ሶሂህ ብሎታል፣ በሳሂህ አል ጃሚዕ ውስጥ]::

አሏህ .. ይህንን ክቡር የትንቢታዊ ምክሮችን ስንት ጊዜ አይተናል ወይም በሐዲስ፣ በስብከት እና በአርብ ስብከቶች ሰምተናል፣ መስጊድ ውስጥ ሶላትን ሲያሰግዱ ኢማሞቹ ስንት ጊዜ ደጋግመውልናል:: ግን ከእኛ መካከል ማን በውስጡ ያለው እያንዳንዱ ሐረግ ለመረዳት ቆመ፣ እና ከቃላቱ በስተጀርባ ያለውን እና በፅሁፎች መካከል ያለውን መልእክት አነበበ፣ ከዚያ ይህ የነቢይ ሐዲስ ረድፎችን የማስተካከያ ደንብ ብቻ እንዳልነበረ ይገነዘባል፤ ይልቁኑ ህይወትን ለማስተካከል የሚያስችል ህገ-መንግስት እና እንዲሁም እኩል እና የሰለጠነ፣ ማንም ከማንም የማይበልጥበት የተሟላ ስርዓት ያለዉን ማህበረሰብ ለመፍጠር እንደሆነ ይገነዘባል፡፡

በመጀመሪያ፣ ሀዲሱን በዚህ መልክ እያነበብነዉ፣ እንጠያየቃለን፡ ለምን (ረድፎችን ማዘጋጀት) እና (ትከሻዎችን መስተካከል) ለምን አስፈለገ? ለምን የረድፎችን እና የትከሻዎችን አቀማመጥ የማተካከሉ ትልቅ አስፈላጊነት ምንድ ነው? መልሱ ቀላል ነው፡-ስልጣኔ ከዚህ ስለሚጀምር፣ እሷ ከሶላት ዘሮች ሌላኛ ዘር ናት፡፡

በመጀመሪያ ስልጣኔ የጋራ እንጂ የግለሰቦች ተግባር ስላልሆነ በዚህ የህብረት ስብሰባ ወይም ሶላት እንድትሳተፉ ተደርጓል፤ የጋራ ሶላት የቡድን ስሜትን መፍጠሪያ፣ የራስ ወዳድነት እና የደስታ ስሜት መቀነሻ ነው። መጀመሪያ ስልጣኔ እራሱ ቡድን ነው::

በሁለተኛ ደረጃ፣ በየቀኑ አንድ ጊዜ ሳይሆን አምስት ጊዜ በትክክል እና በተወሰነ ቀጠሮዎ እንዲታዘዙ ተጠርተዋል፣ ከወንድሞቻችሁ ጋር ለመገናኘት፣ ከዚያ ትክክለኛነት፣ የቁርጠኝነት እና የተስፋዎች መንፈስ በደም ሥርዎ ውስጥ ይፈስሳል፣ እናም የእርስዎ የተፈጥሮዎ አካል ይሆናሉ፤ ሊተውት አይችልም። ስልጣኔ ለጊዜያችን እና ለሌሎች ሰዎች ሰዓት አክባሪነት፣ ቁርጠኝነት እና አክብሮት ነው።

እናም እርስዎ በሶስተኛ ደረጃ ከሌላው ቡድን ጋር በዚህ ስብሰባ ውስጥ ረድፎችን እንዲያዘጋጁ ተጋብዘዋል፡፡ ምክንያቱም መደበኛነትዎ እና ዝግጅትዎ በነፍሶዎ እና በአእምሮዎ ውስጥ፣ ቀጥተኛ ዝግጅት፣ የሥራዎ የበላይነትና የመሰብሰብ ችሎታን ያንፀባርቃሉ፡፡ ከዚህ ስብሰባ ሁሉም የተሳካለት፣ የተባበረ፣ የተቀናጀና የሰለጠነ ህብረተሰብ ሆነዉ እንዲወጣ ነዉ፡፡ ስልጣኔ ንግድ መሰብሰቢያ፣ ተጓዳኝ፣ መደበኛነት፣ ቅደም ተከተል፣ ትዕግሥት፣ ትሕትና፣ መቻቻል፣ የሌሎችን መቀበል እና መንገዶችን

ማሳመር፣ የግቦች፣ የልቦች እና ነፍሶችን ዓላማ ማስተካከል ነዉ፤ ሦስተኛው፣ አራተኛው፣ አምስተኛው እና አሥረኛውም እንዲዚያዉ፡፡

ያኔ ጎዳናው ይህንን ደንብ በእጃችን እንዲተው ለማድረግ አይሞከርም፡፡ ጥበቦቻችንን እንድንተዉ፣ እንዲናፈዙበት እና በሰብአዊነታችን እንደፈለግን እንድናደርግ አይሆንም፣ ግን በቀጥታ ከሰማይ ጋር በማስተሳሰር፣ አንዳችን እሷን ስለመተው፣ ማዛባት ወይም ስለማሻሻል እንዳያስብ ያደርጋታል፡፡ በአሏህ ፊት የምትቆሙ ሆይ፣ እነዚህ በምድር ላይ ያሉ የሶላቶቻችሁ ረድፎች፣ ሰማይ ውስጥ ካሉት የመላእክት ረድፎች ትይዩ መሆኑን አስታውሱ (እናንተ ከመላእክት ረድፎች ጋር ትሰለፋላችሁና)፡፡ ይሄ ከስልጣኔ መሥፈርቶችና በምድር ላይ ማቋቋሚያ እና እዚያ በሰማይ ውስጥ በሚከናወነው መካከል አስደናቂ እና ጥበባዊ ግንኙነት ነው፡፤ ሐዲሱ በጥቂት ቃላት ነግረናል፡ ትክክለኛው አምልኮ ትክክለኛ ሥልጣኔ ነው ፣ እናም ሰማይ ዉስጥ እንደ አለ፣ በምድር ላይም መኖር አለበት፡፡
ከዚያ እኛ፣ ከዚህ ሁሉ በኋላ፣ በሌላ ሁኔታ መስፈርት እንድንገዛ ተጠርተናል፡ (እና ከፈተቶቹን ሙሉ... እና(ምንም ቀዳዳ (መግቢያ) ለሸይጧን አትፍጠሩ) ይላል፡፡ ይሄ፣ ተዓማኒነት እና የግለሰብ ኃላፊነት በመፍጠር ረገድ ነው። እያንዳንዳችን ከየህዝቡ ጉድጓዶች ክፍተት ላይ ቆመናል። እያንዳንዳችን በልዩ ሙያ መስክ የተሰማራ ሲሆን፣ እያንዳንዳችን የራሱ ሚና እና የራሱ ችሎታ አለው፣ ስልጣኔዋን ለመገንባት ማለት ነዉ። እያንዳንዳችን ይህንን ክፍተት ለመሙላት ኃላፊነቱን በመወጣት፣ የሸይጧንን ክፍተት መዝጋት ማለት ነው ፣ አለበዚያ ያኔ በዚህ ግንባታ ውስጥ ኡማውን (ሙስሊሙን ማህበረሰብ) ሊያጋጥሙት የሚችሉት ክህደት፣ ኪሳራ፣ የመፍረስ እና መፈረካከስ ናቸው፡፡ ስልጣኔ ልዩ ሙያ፣ የግለሰብ ሃላፊነት፣ መጠነኛ እና ገንቢ ነው።

እና እንደገና ጎዳናው ይህንን ምድራዊ መሠረት ከሰማይ ጋር ያገናኛል ፣ ስለሆነም ተጠንቀቁ ፣ የአሏህ ባሪያ ሆይ፡ እርስዎ እዚህ ያሉትን ረድፎች ካገናኙ፣ አሏህ እዚያ ያገኛዎታል ፣ እና እዚህ ካቋረጡ፣ አሏህ እዚያ ይቆርጥዎታል (ረድፍን የቀጠለ፣ አሏህ ይቀጥለዋል፣ረድፍን የቆረጠ፣ አሏህ ይቆርጧል)። እናም ምን አይነት በምድር ላይ ግንኙነት ነዉ ከዚያ በሰማይ ውስጥ ካለዉ በላይ ግልፅ የሚሆነዉ፡፡ ነገሩ በአምልኮ መስፈርቶች እና በስልጣኔ መካከል ያለዉ አገናኝ ነው።

ከዚያ እርስዎ፣ ከዚህ እና ከዚያ ሁሉ በላይ፣ ጭካኔን ወደ መተው፣ ሶላት ዉስጥ ላሉት ወንድሞችዎ/ ወገንዎ/በህይወትዎ ወደ መለዘብ ተጠርተዋል (ወንድሞቻችን ሲሞክሩ ቀላል ኹኑላቸዉ)፡፡ ትከሻዎቻችን ዝቅ ማድረጋችን፣ማለት፡ ረድፎቻችንን እንድናስተካክል፣ እንድናልፍ፣እንድንቀደም ወይም ክፍተቱን እንድዘጋ… የሚረዱ ተግባራት መጨረሻው በልባችን እና በተፈጥሮአችን ላይ ነው የሚንፀባረቁ፡፡ ስለሆነም በሌሎች ላይ ጨካኝ አንሆንም፣ ወይም በአስተሳሰባችን ውስጥ ወደ ጽንፈኝነት፣ ዓመፅ እና ሸካራነት አንገባም፤ ጉዳዮቻችንን በማከናወን እና በእኛ አስተያየት ወይም ከእኛ የማይስማሙትን ጋር በመገናኘት ላይም፤ በአምልኮኣችን ዉስጥም እንደዚያዉ፡፡

የእኛ እምነት እንኳ፣ የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) በሕይወታቸው ዝርዝር ጉዳዮች ሁሉ ያሳሰቧቸው እንደነበሩ የአማኞች እናት አይሻ(ረ.ዐ) እንደነገሩን ነው የሚዘገበዉ፡፡

- .. አገልጋይም ሆነ ሴትን በጭራሽ አልመታም፣ የአላህ መልእክተኛ፣ ስለ አሏህ መንገድ ከታገለ በቀር፣ በጭራሽ በእጁ አንድም ሰዉ አልመታም፤ በሁለት ጉዳዮች መካከል ምርጫ ተሰጥቶት ከሁለቱ ተወዳጁንና ቀላሉን መንገድ ካልመረጠ በቀር፣ ኃጢአት ከሆነ ደግሞ፣ ከማንም ሰዉ በላይ ከኃጢአት ይርቅ ነበር፤ እናም ወደ እሱ ለሚመጣዉ ነገር ለራሱ ጥቅም ብሎ ተበቅሎ አያዉቅም፣ ነገር ግን፣ የአሏህ ሁሉን ቻይ የሆነውን አምላክ ህግ እስኪጣስ ድረስ፣ የዛኔ እርሱ ይበቀላል (አል-አልባኒ ሲልሲለት አስ-ሳሂህ ውስጥ ከአኢሻ ዘግቦታል)፡፡

ክብር ለአሏህ ይሁን፣ የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ)ትሁት እና እብሪተኛ እንዲሁም ድሆችን ለማለዘብ ምንኛ ቅን ነበሩ፡፡ እናም መካከለኛ እና ታጋሽ መሆን እንዳለብን ይመክረናል፣ ከዚያ እኛ አክራሪዎች እና ብርቱዎች ነበርን፣ እናም መግባባት እና መቀራረብ እንዳለብን፣ እና ግን ተለያይተናል፣ አልተስማማንም፣ እና እንገናኝ እና አንድ እንድንሆን ይመክረናል፣ እና ግን እራሳችን ጠንካራ እንሆናለን፣ እናም ተከፋፍለን ደካማ ሆነናል፡፡

ሙስሊሞች በሱኒዎች እና በሺአዎች መካከል በብዙ አንጃዎች ተለያይተዋል፣ ግን በመጠን አልተከፋፈሉም፣ በጊዜ እና በቦታ ርዝመት አኳያ፡፡ ግን ስለ ሶላት ምሰሶዎች፣

መሠረቶች፣ ቁጥሮች፣ እንቅስቃሴዎች እና ጊዜያት አልተለያዩም፡፡ ምክንያቱም፡ የጋራ ሶላት ቀመር ነዉ፡፡

እጅግ በጣም ወሳኙ የጋራ ግንባታ አምልኮታችን ከመበረዝ መጠበቅ ነዉ። ሙስሊሞች በቁርአን ጽሑፍ ላይ አልተጣሉም፤ ምክንያቱም እስልምና በጃህሪያ የጋራ ሶስት ጊዜ እና በተከታታይ በቀን ሶስት ጊዜ እንዲያነቡት ያስገድዳቸዋል፡፡ ይህ በየአገሩ፣ በየመስጊዱ፣ በየመንደሩ፣ እና በየቤቱ ይደረጋል፡፡ ኢማሙ ያነባል ሰጋጆትም ኢማሙን ተከትለዉ ያነባሉ፤ ሙስሊሞች በቁርአን አተረጓጎም ላይ ያልተስማሙት ትርጓሜዉ በጋራ ተግባራዊ ስለማይደረግ ነዉ፡፡ እነሱ በሶላት መልክ አልተለያዩም፣ በመስጊድ ውስጥ በጋራ ሆነዉ በተመሳሳይ መልኩ በየቀኑ አምስት ስለሚሰግዱ፣ ግን በእነዚህ ሶላቶች ውስጥ ልቦች መጀመሪያ ወደ ማን እንደሚሄዱ (እንደሚዞሩ) ላይ ተለያይቷል፣ ከአሏህ በቀር በልቦች ላይ ጠባቂ የለምና፡፡ በሐጅ ቅርፅ እና መሠረት ላይ አልተለያዩም፣ ምክንያቱም ዒባዳ ሆኖ በቡድን ቁጥጥር እና ጥንቃቄ ስለሚከናወን፣ ነገር ግን በውስጡ ባሉ መሠረቶች ላይ በማተኮር የተለያዩ ነበሩ፡፡ መሠረቶች ላይ ሳይሆን ቅርንጫፎች ላይ፡፡

ዛሬ የምድርን ህዝቦች ከተመለከትን በከተማ ሰልጥነዉ እና ኋላ ቀርተዉ፣ የሁለቱን ባህሪያት ለመለየት ከሞከርን፣ እነዚያ በጣም የሰለጠኑ በርግጥ ትህቶች፣ የተቻቻሉ፣ የተገናኙ፣ የተጣጣሙ እና ልዩ ሙያ ያላቸው ሆነው እናገኛቸዋልን፤ እናም እንደ ቡድን፣ አንድ እጅ፣ አንድ ልብ፣ በጋለ ስሜት፣ በቆራጥነት ለሀገራቸዉ ግንባታ ሰርተዋል፡፡ እነዚያ ኋላ የቀሩ ግን፣ እብሪተኞች፣ እልከኞች፣ ግትር፣ እንቅስቃሴ-አልባ፣ ችላ ባዮች፣ ካሃዲዎች፣ እና ልባቸው በተለየ፣ እያንዳንዳቸው በራሱ መንገድ ላይ የሚሄድ ናቸዉ። ሁለት ቡድኖቻቸው ተገናኙ፣ በመካከላቸው ጠብ ይፈጠራል፣ ወይም ጥል ወይም ፈታን እሳት በመካከላቸዉ ይቀሰቀሳል፡፡ እንደ አለመታደል ሆኖ፣ ይህ በአብዛኛዎቹ ሙስሊሞች በአብዛኛዎቹ ሁኔታዎቻቸው እና ሀገሮቻቸው ጉዳይ አይደለም?

እያንዳንዳችን የሚከተለውን ሐዲስ በዓይኖቹ ውስጥ ካደረግን፣ ከዚያ ቃላቱን ካሰላሰልን፣ ከዚያ በራሱ ላይ፣ በቤተሰቦቹ እና በአጠገቡ ባሉ ሰዎች ይጥላል፡፡ እናም መልእክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) በዚህ የጋራ ሶላት ላይ ጠንክሮ ሲገስፀን፡ የአንድነትን፣

የጥንካሬን እና የመተባበርን ሚስጥር ሊገልፅልን እንደሚፈልግ ማረጋገጫ ነዉ፡፡ አለበለዚያ፣ ለብቻ ተለይተዉ ለተኩላዎች ምግብነት እንደተዘጋጀ በግ እንሆናለን እናም በዚህ ዓለም ውስጥ በዙሪያችን ያሉት ተኩላዎች እንዴት ብዙ ናቸዉ?

**- በአንድ መንደር ዉስጥ ሶላት ሰዎች ካሉ የጀመዓ ሶላት የማይሰገድበት ከሆነ ሻይጧን ቢቀላቀላቸዉ እንጂ አይቀርም፡፡ ስለዚህ ቡድን አደራችሁን፣ ምክንያቱም ከፊየሎቹ የራቀ ከመንጋው ስለሚበላ -ወይም ከቡድኖቿ የተለየችዉን በግ** -*[በአቡ ዳውድ የተዘገበ ከአቡ አድ-ዳርዳዕ]*

አካላት ብቻ ሳይሆኑ በጋራ ሶላት ውስጥ ልቦች በአንድነት ሲሰበሰቡ፣ ያን ጊዜ በአጠቃላይ ህይወታችን እና አስተሳሰባችን ዉስጥ መታየት አለባቸው፤ ስለዚህ በጋራ እንሰራለን፣ እንመርጣለን፣ ወይም በጋራ አንመርጥም፣ እናም በጋራ እንቀበላለን፣ ወይም አንቀበልም፣ በጋራ እናስባለን፣ በጋራ እንሰራለን፣ በጋራ እንገነባል፣ በጋራ ደስተኞች እንሆናለን፣ በጋራ እናዝናለን፡፡ በዚህ ብቻ ነዉ ሙስሊሙ ከጃሂሊያ ወደ ጃሂሊያ፣ ከኋላ-ቀርነት እና ማሽቆልቆሉ ወደ እስልምና ስልጣኔ እና ሥነ ምግባሩ፣ እናም አመለካከቱ እና ሳይንሱ፣ ወደ የመሬቱ እና የልጆቹ አንድነት የተለወጡት፡፡ ስለሆነም ምድርን እና ሰማይን በአንድ ላይ አጣመሩ ህብረት እና ጀነትን ሰበሰቡ፡፡

**- ቡድን ይሁንባችሁ፣ ከክፍፍል አደራችሁን (ራቁ) ፣ሸይጧን ከአንዱ ጋር ስለሆነ፣ እርሱም ከሁለቱ እጅግ የራቀ ነው፣ እናም የጀነት የምስክር ወረቀት የሚፈልግ ምእመናንን መቀላቀል አለበት፡፡** *(አል-አልባኒ እንደ ሶሂህ ብሎታል፣ በኪታብ አሱሱና ዉስጥ ፣ከኡመር አል- ኸጧብ)* ፡፡

ስልጣኔ ማህበራዊ ነዉ፣ ንግግሩ፣ ማሚያ ነዉ፣ አንድነት ነዉ፣ ትክክለኛነት ነዉ፣ ትሁትነት ነዉ፣ ለስላሳነት ነዉ፣ መቻቻል ነዉ፣ የሌላውን መቀበል ነዉ፣ መቀራረብ ነዉ፣ መተሳሰብ ነዉ፣ ቆራጥነት ነዉ፣ እና ትዕግስት ነው።

## የአርብ ስብከት : የልማት ዑደት

የኦክስፎርድ መስጊድ አምላኪዎች/ሰጋጆች፣ የጁምአው ኢማም ንግግሩን በእንግሊዝኛ አድርጎ እና በአረብኛ አንድም ቃል ሳይናገር ሲያጠናቅቅ የተቃውሞ ስልፎችን አደረጉና፡

እናም የኢማሙ ስብከት ልክ አይደለም፣ በአረብኛ ባልሆነ ቋንቋ የሰበከ፤ ሁሉም አርብ ስብከቱ ተቀባይነት የለውም። በአረብኛ አልነበረም የተሰበከዉ ብለዉ አሉ፡፡

እኛ እዚህ ኢንግሊዝ ውስጥ እንደዚህ ባለው ክስተት ፊት ብዙውን ጊዜ በመገረም እና ግራ በመጋባት እንቆማለን፡፡ አረብኛ ለማይናገሩ ጥቂት ወንድሞቻችን በአድናቆት እና በአግራሞት ስንመለከት፣ እኛ የቋንቋ ተናጋሪዎች ያጣናዉን ከፍተኛ የቋንቋ ፍቅር፣ ቅድስና እና ክብር እንዳላቸው እናያለን፡፡ ይህ ለኛ ነውር መሆኑን እና የተወሰኑ ስሜታችንን ወደ ኋላ ለመመለስ እና በመተዋወቅ ከሚያስከትለው አሉታዊ ጉዳይ እና ተጽዕኖ እንድንላቀቅ ይረዳናል፡፡ ይኸዉም ለአረብኛ ቋንቋ ያለንን ክብር እና መውደድ፣ አድናቆት፣ መልሰን ዋጋውን፣ ደረጃዉን እና ቅድስናዉን ለመርዳት እንችላለን፡፡

ለእነዚህ እንደኛ ወንድሞች ያ በእውነት ብሩህ ገጽታ ነው ፣ ይህም እኛ አረቦች የጥፋተኝነት ስሜት እንዲሰማን እና በአፍ መፍቻ ቋንቋችን የረሳነው ቅዱስ ግዴታችንን እንድናስታውስ ያደርገናል፡፡ ግን ለዚህ ገፅታ እንዲሁ ሌላ የተለየ ጎን አለ፡፡

ወንድሞቻችንን በምንመለከትበት ወቅት የጁምዓ ስብከት ያለ አረብኛ እንዳይሆን አጥብቀው ይጠይቃሉ፤ ምንም ኳኳ ሌሎች ቋንቋዉን ባይረዱም፡፡ በዚህ ጊዜ፣ ከፊታችን የጎደለው እና ስብከት (ኹጥባ) የተቋቋመበትን ወሳኝ ሚና አንዳንድ ሙስሊሞች ዘንድ በተዛቡ ፅንሰ-ሀሳቦች እና ችግሮች የሚረዱ መሆናቸዉን ቁልጭ አድርጎ ያሳያል፡፡ አሁንም ግልጽ እንደሆነን በሃይማኖትና በሕይወት መካከል በሙስሊሞች መካከል ያለው አደገኛ ልዩነት መኖሩን፡ ስብከትዎን በቁርአንዎ እና በነብይዎ ቋንቋ ያስተላልፉ ፡፡ ከዚያ በኋላ የሚባለዉን ሌሎች ተረዱ አልተረዱም የሚል አያሳስብዎትም፡፡ አምስቱን ሶላትዎን ይስገዱ እና ከዚያ ቢሰረቁ፣ቢያታልሉ፣ ቢያመነዝሩ ችግር የለዉም፡፡ የአሳማ ሥጋ አይብሉ፣ ወይም ህጋዊ/ሀላል ያልሆነዉን ፣ እና ከዚያ የሚፈልጉትን ኃጢአት ሁሉ ዉስጥ ይዘፈቁ ይላል፡፡ በአንድ በኩል፣ የእስልምና ገፅታ እንዲህ ነዉ በምዕራቡ ዓለም ዘንድ የተዛባው እንደዚህ ነው፤ ሙስሊሞች የእስልምና ምስል በተሳሳተ መንገድ እስከተገነዘቡ ድረስ፣ እና በቅርንጫፎቹ ላይ ያተኮሩም ያህል፡፡ ግን የሃይማኖትን ፣ ምሰሶዎቹን እና መሠረቶቹን በማጥበብ ፣ በሌላ በኩል፣ እስልምና ሙስሊሞችን እስልምናቸውን ባለማወቁ ምን ያህል ኢፍትሃዊነት ገጠማቸዉ እና ምን ያህል ጥፋት እስልምና ላይ ተፈጠረ በእስላም ልጆች እጆች?

እነዚህ ወንድሞቻችን ኢማሙን ስብከታቸው በአከባቢያቸው ቋንቋ ወይም በማንኛውም ቋንቋ ወይም የባዕድ አገር የሚረዱት ቋንቋ ሳይሆን፣ በአረብኛ እንዲሆን ይጠይቃሉ ፡፡ ይህ ስብከት ብዙውን ጊዜ ከሚደጋገሙ ጥቂት ጥቅሶች እና ሀዲሶች የዘለለ ላይሆን ይችላል፤ ኢማሙ በእያንዳንዱ ስብከት ውስጥ በፊት ይደግማቸው የነበረዉ አንዳንድ ቃላትን እና ምሳሌያዊ ጥበብን ጨመረበት ወይም በጭራሽ አልጨመረበት፤ ከዚያ ሰዎች እንደገቡ ከዓርቡ ሶላት ይወጣሉ፡ ምንም አዲስ ነገር የለም፣ ማስተዋል የለም፣ መገሰፅ የለም፣ ጥቅም የለውም፣ መሳሰቢያ የለም ፣የብያኔዎች መግለጫ ወይም የሰዓቱ ጉዳዮች ጋር የተያያዘም የለም …ስለሆነም የአርብ ስብከትን (የጁምዓን ኹጥባ) መንፈስ በልዩነት ገድለነዋል፤ የቋንቋ አካሏ ብቻ ይቀራል ማለት ነዉ፡፡

ይህንን አስፈላጊ ሳምንታዊ መግለጫ ትርጉሙን እየነጠቅነው እና ወደ ሜካኒካዊ የቃል ሥነ-ስርዓት ብቻ እንለውጠዋለን፣ ሙሉ በሙሉ፡፡ ብዙ ሙስሊሞችም አምልኮታቸውን ከህይወታቸው ሲለዩ ከተግባራዊ ትርጉሙ ያራቁታል፡፡ ይሰግዳሉ እና ይሰርቃሉ፣ ይጾማሉ እና ይዋሻሉ፣ ሐጅ ይፈጽማሉ እና ያጭበረብራሉ፣ ይጨቁናሉ፣ ከሌላ አካል እርዳታ ይፈልጋሉ እንዲሁም ይሰድባሉ መብት ይጥሳሉ ..ወዘተ፡፡ የአሏህን ሕግ በመተላለፍ፣ ሲያደርጉ የነበሩትን ኃጢአቶችና ክፋቶች ሁሉ ይሠራሉ እና ይህ ያልተለመደዉን በሃይማኖታቸው እና በዓለማቸው መካከል ያለውን ልዩነት/ክፍተት ይለማመዳሉ።

አንድ ሰው ሲያስተምርዎት፣ እራስዎን ስለ ሀላል ስጋ መጠንቀቅ እና ተገዢ መሆን አስፈላጊ ስለመሆኑ ሊመክርህ ይሞክራል፤ ምንም እንኳን ግንዛቤዎ በዚያ ዙሪያ ኋላ ቀር ቢሆንም፤ የጎድን አጥንቶቹ ወይም ምንአልባትም የሐላል ሥጋ ሁኔታዎችን በተመለከተ የተለየ እና የበለጠ ትክክለኛ ግንዛቤ እንዳለዉ ያሳይዎል፡፡ ልክ እንደዚያዉ ሰዉዬዉ፡ አታላይ፣ አጭበርባሪ፣ ውሸታም፣ ሌባ፣ ወንጀለኛ፣ ሀሰተኛ ምስክር መስካሪ እና ተንኮለኛ፣ እና ምንአልባትም የአደንዛዥ ዕፅ ተጠቃሚ/አዟሪ ቢሆን፤ ይህ ሁሉ ከእስልምና አያወጣዉም፤ እውነተኛ ሙስሊም መሆኑን አጥብቆ ይናገራል፤ እስልምና እና እስልምናው መሥፈርቶች ትክክልም ይሁን የተሳሳቱ ካልተገለፁ፤ በሀላል ስጋ ፅንሰ-ሀሳብ ማለት ነዉ ፡፡

ሰፋ ያለ የሙስሊሞች ህይዎት መገለጫ የሆነው ይህ ነዉ፡ ይስገዱ ፣ ከዚያ የሚፈልጉትን ያድርጉ ፡፡ በስብከትዎ ውስጥ ማንኛውንም ነገር በሉ፣ ወሳኙ ነገር በአረብኛ መሆኑ ነው፡፡ በህይወትዎ እና ከሰዎች ጋር በሚኖርዎት ግንኙነት የሚፈልጉትን ያድርጉ፤ አስፈላጊው ነገር ቢኖር ከሀላል ስጋ አለመብላት ነዉ፡፡ እና ይህ ከሀላል ሥጋ በስተቀር ምንም ነገር አለመብላት በሚለዉ አካባቢያዊ ፅንሰ-ሀሳብ መሰረት ነው፡፡

ብዙዎች የጁምአ ስብከት በእስልምናው ማህበረሰብ ሕይወት፣ ዕድገትና ልማት ውስጥ ያለዉን ወሳኝ ሚና የማያውቁ ናቸው፡፡ የጁምአ ሶላት መከናወን ያለበት የአምልኮ ግዴታ ብቻ መስሎዋቸዉ ያልፋል፤ ይሄዉ ተነሱ እና ተገላገሏት፡-ወደ ሶላቱ በሰዓቱ ደርሰዋል፣ ስብከቱን አዳምጡ፣ ይሰለፉ እና በቀጥታ ረድፎች ተዘጋጁ፤ ሶላታቸውን አከናውኑ እና የአሏህ ሰላም እና እዝነት በእናንተ ላይ ይሁን፣ የአሏህ ሰላም እና እዝነት በእናንተ ላይ ይሁን ብለዉ ጨረሱ በቃ።

እንደዚህ ባለው ጉዳይ ፊት ለፊት መጠያየቅ ተገቢ ነው፡-የአርብ ስብከት ለመዳመጥ እና ወግ አጥባቂ ለመሆን የወጣ ነው? በስብከቱ ወቅት ዝም ለማለት እና ለመረጋጋት፣ በጨዋነት፣ ለኢማሙ አክብሮት እና ክብር መስጠት ብቻ ነዉ? ከዚያ በላይ ምንም ነገር የለም? የአርብ ስብከቱ በዚህ ረገድ የሃይማኖታዊ ተንቀሳቃሽ ስዕል እና ይዘቱ ምንም ፋይዳ የሌላቸው የአካል ብቃት እንቅስቃሴዎች ብቻ ይሆን? እና ለዚህ ይዘት ትርጉም የለዉም?

ሶላት አምልኮ ነው፤ ሰበካ (ኹጥባ) ደግሞ የድርጊት መርሃ ግብር ነው፡፡ ሰበካ የአርብ ሶላት አካል እና የማይነጠል ክፍል ነው፤ ይልቁንም የተከበረው ሀዲስ እንዳረጋገጠልን እራሱ የጁምአ ሰላት ነው እናም ሰበካ (ኹጥባ) ያመለጠውን ሰው የዓርብ ሶላት ሙሉ እንዳመለጠዉ አቋም እንዲይዝ አደረገው፡

- በአርብ ዕለት መላእክቶች በመስጊዶች በሮች ላይ ናቸዉ፤ የሰዎችን የአመጣጥ ደረጃዎች ይጽፋሉ፡፡ እገሌ በዚህ ሰዓት ነዉ የመጣው፣ እገሌ በዚህ ሰዓት ነዉ የመጣው፣ እገሌ ኢማሙ ኹጥባ እያደረገ ሳለ ነዉ የመጣዉ፣ እገሌ መጣ፤ ከዛም

ለሶላቱ ደረሰ፤ የጁምአውን ሶላት አላገኘም፤ ለስብከቱ ስላልደረሰ (በአህመድ የተዘገበ እና በአህመድ ሻከር ሀሰን ተብሎ የተመደበ፣ ከአቡ ሁረይራ)፡፡

ስለሆነም ኢማሙ እንደ አድማጮቹ መጠን እና እንደ እዉቀታቸዉ መጠን ስብከቱን ማስተካከል ነበረበት፡፡ እናም ሁኔታዎች እና ስጋቶቻቸዉ ተፈጥሮ፣ አድማጮቹ ከሰበካዉ የሆነ ነገር ይዘው እንዲወጡ ከፈለገ። የሰራተኞች አድማጮች ፊት የሚደረገዉ ስብከት በተማሩ ሰዎች አድማጮች ፊት ከሚደረገዉ ይለያል፤ እና ሌሎችም በትምህርት ቤት ተማሪዎች፣ በዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች፣ ፕሮፌሰሮች እና መምህራኖች እና እንዲሁም ሌሎችም እስልምናን አዲስ ከተቀበሉ ሰዎች ፊት የሚደረገዉም እንደዚያዉ ለመየት አለበት፡፡

ዛሬ ብዙዎች ኢማሞቻችን እንደሚያደርጉት፣ መልእክተኛዉ (ሰ.ዐ.ወ) በስብከቶቹ ውስጥ ጥቅሶችን በዘፈቀደ አይደጋግምም ነበር፡፡ ስለ ጥቂት ጥቅሶች፣ ሀዲሶች ወይም ተደጋጋሚ ሀሳቦች የሚናገሩት ኢማሞች ስብከቶቻቸዉን በፊታችን የሚደጋግሙት፣ ከማንበብ በቀር፣ ካለዉ ነባራዊ ሁኔታ ጋር ማገናኘት አልቻሉም፤ ከጊዜዉም ከቦታዉም አንፃር፡፡ ጥቅሶችን እና ሀዲሶችን፣ በአንድ አጋጣሚ በሰዎች ጆሮ ውስጥ ተገቢም ሆነ ባልሆነ እንኳን ስንደጋገማቸው እንበድላቸዋለን፡፡ ይህ በሰጋጆቹ መንፈስ ላይ በአሉታዊ ሁኔታ የሚያንፀባርቅ ስለሆነም፣ ለእነዚህ አንቀጾች እና ሀዲሶች ያላቸው ፍቅር ወደ ምቀኝነት እና ችላ ማለት ሊቀየር ይችላል፡፡ ይህ በቁርአን እና ሀዲሶች አንቀጾች ሁሉም ላይ ተንፀባርቋል፡፡

የስብከት ቋንቋ በይዘቱ ያለፈ ሳይሆን አሁናዊ  ጉዳይ የሚሆነው መቼ ነው? ሐላል ስጋ ደግሞ ተከታይ ዉሳኔ የሚሆነው መቼ ነው? የእስልምና ዘላለማዊ መሠረታዊ የሥነ ምግባር ትምህርቶች መሥራች ሳይሆን ተከታይ? እና ህይወታችን መቼ ይሆን የአምልኮታችን አተገባበር እና ማፅደቅ እነዲሁም የሃይማኖታዊ ስርዓቶቻችን አፈፃፀም የሚትሆነዉ?

እናም ክቡር ነቢያችን (ሰ.ዐ.ወ) እንዳረጋገጡን ሁሉን ቻይ የሆነው አሏህ በየመቶ ዓመቱ መሪዎችን ለሙስሊሞች ሃይማኖታቸውን እንዲያድሱ ከላከ፣ የአርብ ሰባኪው (የጁምዓ ኻጥብ) ሚና በእያንዳንዱ አርብ የሃይማኖታቸውን ውሳኔዎች፣ በሳምንቱ

ዉስጥ የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች እና ክስተቶች በዝርዝር ማደስ ነው፡፡ ዓላማዉም፣ የህይወት ጎማ ለማጓጓዝ እና ከእሱ ጋር ያላቸውን ትስስር ለማቆየት እንዲሁም ለማምረት እና ለእድገቱ አስተዋፅዖ ማድረግ ነዉ ፡፡ እያንዳንዱ ተቋም የራሱ የሆነ የልማት ሥልጠና መርሃ ግብር ካለው፣ ለሠራተኞቹ የሚያካሂደው ግዴታ ማለት ነው፡፡ የአርቡ ስብከት ለአንድ ሙስሊም ሕይወት የግዴታ የሥልጠና፣ የአቅጣጫ እና የልማት ፕሮግራም ነው፡፡ አሁንም፣ በእስልምና ተቋማት እና በሕይወት ተቋማት መካከል ለሰጋጁ ሳይንሳዊ፣ ተግባራዊ፣ ትምህርታዊ፣ ሥልጠናዊ እና በትምህርት ናቸው ፡፡

## ከዚህ እንጀምራለን

በመስጊድ አብሮኝ ይሰገድ የነበረ ወንድም አጣሁት፡፡ ከአሁን በኋላ ከእኛ ጋር እንደማይሰግድ እና ሌላ መስጂድ እንደሚመርጥ ተነግሮኛል፡፡ ምክንያቱም እዚህ ከሚሰግደው ከሌላ ሙስሊም ጋር ጠብ ውስጥ ስለሆነ፡፡ ከዛም ለረጅም ጊዜ ያላየሁትን ሌላ ወንድም አገኘሁ እናም ጠየቅኩት፡ ለምን ለረጅም ጊዜ መስጊዳችን ውስጥ አንገናኝህም? እንዲህ አለ፡ አንድ ሰባኪ ወደ መድረክ/ሚንበር በመዉጣት የሰው ልጅ ከተራቀተ የወንዱ የዘር ፍሬ ነዉ የተፈጠረ ከሚለዉ ሰባኪ ጋር አልሰግድም፡፡ የወንዱን የዘር ፍሬ እንዴት ይንቃል? ከዚያ ወደ አንዱ መስጊድ በሄድኩበት ጊዜ ከአንድ ሙስሊም ጓደኛ ጋር ተገናኘን እና በመንገድ ላይ ስለ ተነጋገርን እና በር ላይ ስንደርስ ተሰናበተኝ እና ባለ፣ እኔም በመገረም እንዲህ አልኩት፡ እዚህ አትሰግድም? ጭንቅላቱን ወደ ግራ እና ወደ ቀኝ በማዞር እንዲህ አለ-እኔ ሰለፊዎች በሚሰግዱበት መስጊድ ውስጥ አልሰግድም፡፡

እራሴን ጠየቅኩ፡ ሙስሊሙ ማኅበረሰብ በእነዚህ ሶስት የሰዎች ስብስብ ቢከፋፈል አስቡት፡- ከሱ ውስጥ አንድ ሦስተኛው ከእርሱ ጋር የሚከራከር ሰው በሚሰግዲበት መስጊድ ውስጥ አይሰግድም፣ አንድ ሶስተኛው ደግሞ ሰባኪ ወይም ኢማም ሲሳሳት አይምርም፡፡ ይህ ስህተት ነው ብለን ካሰብን እና አንድ ሦስተኛው ከሌላው በአመለካከት ወይም በትጋት ከማይስማማዉ ሰጋጅ ጋር በአንድ መስጊድ ውስጥ መገናኘት የማይፈልግ ከሆነ፡፡ ስለዚህ እንደዚህ ያለ ህዝብ ከዚያ በተጨማሪ አንድ ቀን ዓለምን ለመግዛት ብቁ ነው ብለው ያስባሉ? ራሱን ከመምራት አለፈዉ?

በመስጂዱ ሥነ ምግባር፣ በውስጡ ባለው የጋራ ሰላት ሥነ-ምግባርና ሁኔታ እንዲሁም የእስልምና ሰራዊቶች እና የእስልምና ስልጣኔ ተጀምሮ ለማስፋፋት የበቃበት ታሪካዊ ሚናዉስ ምን አደረግን? በአንድ ልብ እና በአንድ ፍላጎት፡ እስልምና፣ የእስልምና ስልጣኔ፣ እና የእስልምና ሥነ ምግባር እንዲስፋፉ፣ በቀላሉ እና በሰው ስልጣኔዎች ከዚህ በፊትም ሆኖ በኋላ የማያውቁት በሆነ ጊዜ ውስጥ?

በሚያዝያ ወር-2012 በዘመናዊ ሰበካ (የደዕዋ) ፋውንዴሽን (በካይሮ) በተካሄደው ትምህርታዊ ኮንፌረንስ ላይ እንድካፈል ተጠየቅኩ፡፡ ዓላማው "*ከአል-አዝሃር የተመራቂዎችን ምሳሌ በትምህርትና በባህሪ ለማሳየት ነው እና ከወጣት ትውልዶች ጋር ለመግባባት እና መካከለኛ እስልምናን መልእክት የማስተላለፍ አቅማቸዉን ለማየት ነበር››፡፡*

ለሁለት አስርት ዓመታት ያህል ለዩኒቨርሲቲዎች እና በከፍተኛ ተቋማት ውስጥ የኢንግሊዝ እውቅና ማረጋገጫ ካውንስል (ቢአሲ) ኢንስፔክተር ሆኜ ስሰራ ባገኘሁት ተሞክሮ፣ እና የማማከር ሥራ እና በቅርቡ ከኢንግሊዝ ውጭ ያሉ ዩኒቨርስቲዎችን እና ተቋማትን ለማካተት ከተደረገው የማስፋፋት ስራ ጋር ተያይዞ፣ ይህ ምን ማለት ነው፣ የብሪታንያ (ኢንግሊዝ) ልምዶች እና የሥልጣኔ ደረጃዎችን ወደ እነዚያ ዩኒቨርሲቲዎች ለማሸጋገር የታሰበ ነበር፡፡ (ዓለም አቀፍ የእስልምና እዉቅና ምክር ቤት) ብዬ የጠራሁት ተቋም መቋቋም እንዳለበት ለምክር ቤቱ ሀሳብ ያቀረብኩት ሲሆን፣ ዓላማዉም ከግብፅ ጀምሮ በተለያዩ የአረብ እና እስላማዊ አገራት የዚህ አዲስ ምክር ቤት መመሪያ መሠረት ለዩኒቨርሲቲዎች ወይም ትምህርት ተቋማት እዉቅና የመስጠት ተግባር የሚፈፅም ይሆናል፡፡ ተግባራቱ እነዚህ ፍላጎቶች ላይ ብቻ የተገደቡ አይደሉም፣ ሁሉንም የመንግስት ተቋማትን (ከትንሽ እስከ ትልቅ)፣ ኩባንያዎችን፣ ኤጀንሲዎችን፣ የመንግሥት ክፍሎችን፣ ጎዳናዎችን፣ የአነስተኛ ሰፈሮች እና የመኖሪያ ሕንፃዎችን፣ ሆስፒታሎችን፣ ክሊኒኮችን፣ ትምህርት ቤቶችን፣ ክለቦችን፣ መደብሮችን፣ መስጊዶችን፣ አብያተ ክርስቲያናት እና የህዝብ መናፈሻዎችን፣ የልጆች የአትክልት ስፍራዎች፣ የህዝብ የውሃ ወረዳዎች፣ የግንባታ ወርክሾፖች፣ ወዘተ ይሸፍናል፡፡

እና ሃምሳ ተሳታፊ ተማሪዎች ከ(ዘመናዊው የስብከት አካዳሚ) ትምህርት ቤት፣ በተለያዩ የግብፅ ግዛቶች ላይ ከተሰራጩ የተወጣጡ፣ እናም የዚህ አመለካከት

አፍቃሪያን መሆን አለባቸው፡፡ ከላይ ከተጠቀሰው እውቅና ሰጪ ምክር ቤት ጋር የተያያዙ በአነስተኛ እና የአከባቢ ድርጅቶች አማካይነት መስፈርቶቹና መመሪያዎቹ (ደንቦች) ተግባራዊ የሚሆኑት፡፡
እነዚህ አካባቢያዊ ድርጅቶች ስልጣኔን እና ሃይማኖታዊ የውድድርን መንፈስ በአካባቢያቸው ያሉ ተቋማት ዉስጥ እንዲያሳድጉ ታሳቢ ይደረጋል፤ በመጨረሻ የምክር ቤቱን ዕውቅና ለማግኘት ወደ እነዚህ ተቋማት ጥረት የሚደረግ ውድድር። ስለሆነም በዚህ በተከታታይ የእሽቅድምድም ሂደቶች ለእዉቅና ለምክር ቤቱ የማያመለክቱ ተቋማት በአካባቢያቸው እንደተለዩ ወይም ኋላ እንደቀሩ ይሰማቸዋል፡፡

ተጽዕኖዎቻቸው ወደ ተለያዩ በመስፋፋታቸው ምክንያት እነዚህ ፍላጎቶች እና ተግባራት በየወሩ እና በየአመቱ ይጨምራሉ፤ በግብፅ ምድር ውስጥ የሕይወት ገጽታዎች ማለት ነዉ፡፡ እና በአስር ወይም በሁለት አሥርት ዓመታት ውስጥ፣ በዚህ መርሃግብር ግብፅ በአውሮፓ አገራት ተርታ ወደ መሰለፍ ትለወጣለች፡ በጥራት፣ በብቃት፣ በስነ-ስርዓት፣ በንፅህና፣ በጥሩ ገጽታ፣ የምርት ደረጃ በመጨመር፣ በስራ ቦታዎች ላይ የደህንነት ደረጃ፣ በትምህርት ደረጃ፣ እና የአስተዳዳግ ደረጃ፣ እና በመግባባት/መናኗር ደረጃ፣ ወዘተ፡፡ እና ይህ በእርግጥ ወደ ጠፉት ሃይማኖታዊ እሴቶቿ ይመልሳታል፤ እርስ በእርሳቸው ስለሚረጋጉ፡፡

በእርግጥ ሀሳቡ ከጥር 25 አብዮት በኋላ በተከሰቱት አሳዛኝ ክስተቶች ምክንያት በወረቀት ላይ ከተቀመጠበት ወደ እውነታው ዓለም ያልተሸጋገረ እና ይህ በሌላ አቅጣጫ በዙር እንድናስብ ያደርገናል፡ እስላማዊውን መንግስት በመገንባት፣ይህን ትልቅ ንቅናቄ ለምን ከጥቃቅን ስልጣኔያዊ አንድነት ረገድ እንደጀመርን አልተደረገም፡ የመስጂድ ማህበረሰብ፣ መስጊድ በየመንገዱ፣ በየሰፈሩ፣ በየመንደሩ?

የእያንዳንዱ መስጊድ መሪ ኢማሙ እና ጥቂት የመስጊዱ ወጣት እና አዛውንቶች፣ከዋና ተግባሮቻቸዉ ጎን ለጎን፣ በዲስትሪክቱ (አከባቢዉ) ውስጥ ላሉት ተቋማት አካባቢያዊ እውቅና የሚሰጥ ምክር ቤት ሆኖ ማገልገል ይችላል፤ በንግግራችን ስለ (የቡድን ሶላት) የተነጋገርናቸው አስር የስልጣኔ መሠረቶችን ተንተርሶ ማለት ነዉ፡፡

የሚፈለገዉ ነገር (የኢንግሊዝ የእውቅና ምክር ቤት) እዉቅና ከሚሰጣቸዉ ተቋማት የሚፈልገው፣ በዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ ከመወሰን ወጣ ካለ፣ በሀገሪቱ ውስጥ ያሉትን ማንኛውንም አካላትን ጎጥ የሚጠቃልል ሆኖ፣ በእነዚህ መሰረታዊ ሁኔታዎች ተጠቃሏል፡

- የህንፃው ውጫዊ እና ውስጣዊ ገጽታ ፣
- ለሠራተኞች እና ለተቋሙ አገልግሎቶች ተጠቃሚዎች የጤና ፣ የንፅህና እና ደህንነት ሁኔታዎች ፣
- ተቋሙ ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች ዓይነት የግንባታ ፣ የቢሮዎች እና የክፍሎች ትክክለኛነትና ዝግጁነት መጠን ፣
- ለሠራተኞችም ሆነ ለተጠቃሚዎች አስፈላጊውን መድን ማቅረቡን ፣
- ተቋሙን በመምራት እና ግቦቹን ለማሳካት የአስተዳደሩ ስኬት መጠን ፣
- የሰራተኞቹ ብቁነት፣ የያዙት የምስክር ወረቀት ዓይነት እና በሰነዶቻቸው ተገቢ ልምዶች፣
    - ለሠራተኞች የሥልጠና እና የልማት ትምህርቶችን በመደበኛነት ማደራጀት፣
    - ለሁሉም ሰራተኞች ፍትሃዊ እና እኩል የደመወዝ ስርዓት ያላቸው ህጋዊ ውሎች መኖር፣
    - የሠራተኞችን የግል ተነሳሽነት ማበረታቻዎች ሥርዓት ማበረታቻ እና ችሎታዎቻቸውን ማጎልበት፣
    - የሰራተኞች እና የተጠቃሚዎች መዝገቦች እና ፋይሎች ትክክለኛ እና ወቅታዊ ስርዓት መኖሩ፣
    - ተቋሙ የሰራተኞቹን ሥርዓቶች፣ ፖሊሲዎች፣ ዕቅዶች እና ግዴታዎች ሁሉ በጽሑፍ እና በግልፅ ይጠብቃል፣
    - ፋውንዴሽኑ ያወጣው ማስታወቂያዎች እና ህትመቶች አስተማማኝነት፣
    - ተቋሙ ለሕዝብ የሚሰጠው የአገልግሎቶች፣ የሙያ ወይም የምስክር ወረቀቶች አስተማማኝነት፣
    - ከሌሎች ጋር የመግባባት ቋንቋ እና በሰፊው የተስፋፋው የጽሑፍ እና የንግግር ቋንቋ ሥልጣኔ፣

- አስተዳደሩ ከሠራተኞችና ከተጠቃሚዎች ጋር በመገናኘት አስተያየታቸውንና ለጥያቄዎቻቸው የምላሽ ይሰጣል፣
- ተቋሙ ለሠራተኞችና ለተጠቃሚዎች በተለይም ለየት ያለ ፍላጎት ላላቸው ተቋማት፣ ልዩ ድጋፍ ያለ ምንም የዘር፣ የጎሳ፣ የፓርቲ አድልዎ አገንግሎት ይሰጣል፣
- የውጭ ዳኞች በየአመቱ የተቋን ንግድ እና አገልግሎት በመገምገም ያደረጉት አስተዋጽኦ፣
- በእያንዳንዱ ሴሚስተር / ዓመት / ዙር መጨረሻ ላይ የተገኙትን ውጤቶች እና የመሳሰሉትን በገምግም መሠፈርቶቹን ለሚያሟት እዉቅና ይሰጣል ማለት ነዉ፡፡

የኢንግሊዝ የእዉቅና ምክር ቤት ውስጥ ኢንስፔክተሩ፣ ማንኛውንም ተቋም ሲጎብኙ፣ በቦርሳቸው ይዘውት የሚሄዱት ፋይሎች ማጠቃለያ ይህ ነው፡፡ በመሠረቱ ይህቺ ለሥልጣኔ ካቀረብናቸው አስር መርሆዎች አትለይም፣ እነዚህም በጋራ ሶላት ዉስጥ እንዲፀድቁ/ሰርፁ የሚደረጉት ጥሪዎች ናቸዉ፤ እናም የሥልጣኔን ምክንያቶችን ለማስመለስ፣ ከቡድን ሶላት የሚወጣው ንቅናቄ ተቀባይነት ሊኖረው ይችላል ነዉ፡፡

ይህ እንቅስቃሴ፣ በእያንዳንዱ ተቋም ውስጥ መኖር ያለባቸው በአስር መርሆዎችና ህጎች ላይ በመመርኮዝ፣ እዚህ መስጊድ እና እዚያ መስጊድ ውስጥ ሊጀመር ይችላል፡፡ እውቅና እንዲሰጣቸዉ የሚያስቡ መስጊዶች ማለት ነዉ፡፡ ከዚያ በኋላ፣ እነዚህ ጥቂት በመስጊዶች ደረጃ ያሉ ኮሚቴዎች በመገናኘት የጋራ/ወጥ ህጎችን እና መመሪያዎችን፣ ደንቦችን መቅረጽ እና ምክር ቤት ማቋቋም አለባቸዉ፡፡ እና ከዚያ እነዚህ ህጎች እየተሻሻሉ እና እየተስፋፉ የመሠረታዊ ሕግ (የብሔራዊ ዕውቅና ምክር ቤት) በሀገር ደረጃ ይመሰርታሉ፡፡

መስጂዱ ወደ እንደዚህ ዓይነት ደረጃ ላይ በመድረሱ ኢማሙ በሚችልበት ጥንቃቄ አስቀድሞ እቅድ ማቀድ አለበት፡፡ ከሌሎች የክልሉ መስጂዶች ኢማሞች ተሳትፎም ታክሎበት፣ እውነተኛውን ሥራ የተገነዘበ “የምእመናን ቡድን” በማቋቋም፣ ሶላትን በቡድን ለመፈፀም እና በአጠቃላይ ህይወትን ለማደራጀት እና ህብረተሰቡን በማሻሻል ውስጥ የሶላት ሚና ምን እንደሆነ ለመረዳት ማቀድ ያስፈልጋል፡፡ ይህ የመጀመሪያ

ቡድን ከመስጊዶች ውጭ ሌሎች ቡድኖችን ከክልል መስጊዶች የሚያካትት የአንድ ትልቅ ማህበረሰብ ኒውክሊየስ (እምብርት) ይሆናል እንደ ማለት ነዉ፤ በጋራ ሆነዉ ትልቁን እና ሰፊውን ማህበረሰብ (የእውቅና ከፍተኛው ምክር ቤት) እስኪያገኙ ድረስ፡፡

ይህ እንቅስቃሴ ሊጀመርበት ከሚችል ከግብፅ ወይም ከሌላው እስላማዊ አገር ሲሆን፣ ፕሮጀክቱ ወደ ቀሪው የእስላማዊው ዓለም ክፍሎች ይቀጥላል።

እንዲህ ያለው ምክር ቤት፣ በትክክል ከታቀደለት፣ በጥቂት አስርት ዓመታት ውስጥ፣ እስላማዊውን ዓለም ወደ መጀመሪያው ስልጣኔ ቦታው ይመልሳል፤ እና በውስጡ የሰለጠነ ሃይማኖታዊ አስተሳሰብ መንፈስን እንደገና ለማነሳሳት የአረብ እና እስላማዊ ዓለማት፣ በእስልምና ሃይማኖት ዉስጥ ተግባራዊ ጎንን በማደስ እና አምልኮን ከሕዝባዊ ሕይወት ጋር በማገናኘት፣ ከሶላት ጀምሮ እውነተኛውን የሰለጠነ የእስልምና ገፅታ ለዓለም ለማሳየት ይችላል፡፡

ይህ ትልቅ ሥራ ነው፣ ግን የመጀመሪያው ማይል/ርቀት አንድ እርምጃ ነው፤ እናም እኛ ጉዳዩን በቁም ነገር ከወሰድን፣ ይህንን መጅሊስ፣ እስከ አሁን ድረስ የመንግስታት፣ የአስተሳሰብ እና የአመራሮች ትውልዶች ማግኘት ያልቻሉበትን ስኬት ማሳካት እንችላለን።

## አምስቱ የሶላት መስመሮች

يَـٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ لَا تَقْرَبُوا۟ ٱلصَّلَوٰةَ وَأَنتُمْ سُكَـٰرَىٰ حَتَّىٰ تَعْلَمُوا۟ مَا تَقُولُونَ ﴿٤٣﴾ **النساء: 43**
**- እናንተ ያመናችሁ ሆይ የምትናገሩትን እስከታዉቁ ድረስ በሰከራችሁ ጊዜ ወደ ሶላት አትቅረቡ** [አን-ኒሳዕ፡ 43]
የዚህን አንቀፅ ግልፅ ትርጉም ስንት ጊዜ አንብበናል? ከዚያ ከእሷ ቃላት በስተጀርባ ያሉትን ትምህርቶች አላየንም፡፡ አንድ ሰው በመንገድ ላይ ከአጠገቡ ማንም ሳይኖር እጆቹንና ጭንቅላቱን እያንቀሳቀሰ ሲናገር፣ ስለዚህ የመጀመሪያው በአእምርዎት የሚመጣ ነገር ከአንድ ሰው ጋር የሚነጋገርበት የሞባይል ስልክ ግንኙነት ሊጭንለት ይችላል ብለው ያስቡ ይሆናል፡፡ ከዚያ ወደ ኋላ ሰውዬውን ሲመልከቱ እና በአግባቡ ቢያጤኑት፣ እናም በአፉ ውስጥ አስተላላፊ፣ በጆሮው ውስጥ እስቴስኮፕ (የጆር መዳመጫ)፣ ወይም በእጁ ወይም በኪሱ ዉስጥ ተንቀሳቃሽ መሣሪያ አያገኙም፡፡

በተጨማሪም እብድ፣ ጠማማ ወይም ሰካራም ነው ከማለት ውጭ ሌላ አማራጭ አይኖርዎትም፡፡ ያልኩትን እያጋነንኩ ነውን አንዴ?

ይህ በትክክል የብዙ ሰጋጆች ሁኔታ ነው፣ ግን በሁለቱ ጉዳዮች መካከል ካለው አስፈላጊ ልዩነት ጋር፡፡ እነሱን ትመለከታቸዋላችሁ፣ ከአጠገባቸው የሚያናግሯቸውን የሚታገኙ አይሆንም፤ እና አንዳቸውም ቢሆኑ የሚነጋገሩበት ሞባይል የላቸውም፣ እነሱም፣ በዚያ ላይ፣ እንግዳው፣ እነሱ የሚናገሩት በጭራሽ አንድን ሰው እያነጋገሩ ነው ለማለት በሚከብድበት ሁኔታ ነዉ፤ ወይም በንግግራቸዉ የተከበረዉን አንቀፅ ቀይረዉ የሚናገሩትን የማያዉቁት ደረጃ ላይ ደርሰዉ ይሆናል፡፡

አንድን ነገር ማለትዎ፣ ከፊትዎ እና ከመልከዎ እንዲታይ በመናገር እና ከአንድ ሰው ጋር እየተነጋገሩ መሆንዎን አፍዎን እና ምላስዎን ሳያሳዩ በማነቃነቅ በመናገር፣ ወይም የሆነ ነገር ማለት መካከል አስፈላጊ ልዩነት አለ፡፡ እና የመጨረሻው ጉዳይ በጣም እንግዳ፣ አደገኛ አስቸጋሪ ነው።

የነዚያ ሰዎች ንግግሮች፣ በመሠረቱ ትርጉም ያላቸውን ቃላቶች፣ ግን፤ በአካላቸዉ፣ ከፊታቸው ገፅታዎች እና ቃላቱ ከከንፈራቸው የወጡበት መንገዳቸዉ የማይታዩ፣ ግን የሆነ ትርጉም የሚይዙ አይነት ናቸዉ፡፡ ምክንያቱም በሚናገሩት መንገድ እና በፊቶቻቸው ላይ ያ ነገር አልተንፀባረቀም፣ እናም የዚህ ንግግር ቃና እና ቀለሞች በመለዋወጥ ላይ ተከታዮቹ ትርጉሞቹ፣ እንደማንኛውም ንግግሮቻችን፣ ፊት ለፊት ወይም በስልክ ከሌሎች ጋር የምናደርጋቸው ውይይቶች ወይም ንግግሮች አይደሉም፡፡

አሁኑኑ ይሞክሩ፣ ስልክዎን ይውሰዱ፣ ለጓደኛዎ ይደውሉ እና ሚስትዎን ወይም አንድ ሰው ከቤተሰብዎ ንግግርዎት እንዲቀዳ ይጠይቁ፤ በዚህ ጥሪ ወቅት፣ የፊትዎ ገጽታዎች፣ የድምፅዎ ቃና እና የተናገሩበት መንገድ ስንት ጊዜ እንደተለወጠ ለእርስዎ መዝግበዋልን?

ባህሪያቶቻችን፣ የንግግራችን ፍጥነት፣ የድምፃችን ቃና እና ምንአልባትም የእጆቻችን እንቅስቃሴ እና የሰውነታችን አቀማመጥ፣ ይለወጣሉ እንዲሁም ቀለም ይኖራቸዋል፡፡
ይህም፣ በተለመደው ጥሪ ወቅት ለአሥርት ተከታታይ ጊዜያት በመወያየት፣ በመውሰድ፣ በመመለስ፣ በመጠየቅ እና በመከጀል፣ በፍላጎት፣ በተስፋ፣ በብስጭት፣

በተቃውሞ፣ በመደነቅ፣ በመቀበል፣ ባለመቀበል፣ በነቀፋ፣ በጥንቃቄ፣ በተስፋ እና ልመና፣በምስጋና፣ በአድናቆት፣ በጥያቄ፣ በመልስ፣ በመደነቅ፣ በፍርሃት፣ በስግብግብነት፣ በፍርድ፣ በማረጋገጫ፣ በመካድ፣በልዩነት፣ ለአፍታ በማቆም፣ በመከታተል፣ በማፈግፈግ እና በማመንታት... ላይ ሳለን? እኛ እንደዚያ ካልሆንን እኛ ከሰው በላይ አይደለንም ሮቦት ነኝ ማለት ነው፡፡

እየሰገዱ እያሉ፣ እርስዎ “ሮቦት” ወይም ሰካራም ወይም እብድ አለመሆንዎን ለማረጋገጥ ሞክረዋልን፣ ምንአልባትም፣ አንድ ሰዉ ሶላት ዉስጥ እያለም ከአንድ ሰው ጋር በእውነት ይገናኛል፣ ልክ ከእኛ መካከል አንዱ ጓደኛውን፣ አስተማሪውን ወይም አለቃውን እንደሚጠራው ወይም እንዲያገነዉ ሁሉ፡፡ በመስመሩ ሌላኛው በኩል ደግሞ ሌሎች ህያው መንገዶች እና ከራስዎ ጋር የማይነጋገሩ፣ ወይም “ለማንም” የማይነጋገሩ ሰዎች ካሉ፣ ሰዎች በሮቦትነት፣ በአእምሮ ህመም ወይም በእብደት አይከሱዋችሁም?

በመስመሩ ማዶ በኩል አሏህ ከእርስዎ ጋር እንደሆነ በማመን በእውነቱ እርግጠኛ ከሆኑ እና እሱን ያነጋግራሉ እርሱም ያዳምጥዎታል፣ ያስታውሱታል እርሱም ያስታውሳችኋል፣ እናም ይጠይቁታል እርሱም ይመልስልዎታ፣ታዲያ ለአድማጭ ተመልካቹ ያ ምን ያረጋግጣል? ይልቁንም ኃያሉ አሏህ ለንግግርዎ ሰሚ፣ የልባችሁን ምት ዉስጥ አዋቂ፣ እና የልብዎን ዉስጠ-አዋቂ መሆኑን እና እየተነጋገሩት ያልዎትም ወደ እሱ እንጂ ወደ ‹‹ማንም›› አለመሆኑን እንዴት በእዉነቱ ማረጋገጥ ይችላሉ?

قَدۡ أَفۡلَحَ ٱلۡمُؤۡمِنُونَ ﴿١﴾ ٱلَّذِينَ هُمۡ فِي صَلَاتِهِمۡ خَٰشِعُونَ ﴿٢﴾ المؤمنون: 1-2

**-ምእመናን ተሳከቶላቸዋል ፡፡ እነዚያ በሶላታቸው ውስጥ ትሁት የሆኑት** *(አልሙዕምኑን፡ 1-2)*

فَوَيۡلٞ لِّلۡمُصَلِّينَ ﴿٤﴾ ٱلَّذِينَ هُمۡ عَن صَلَاتِهِمۡ سَاهُونَ ﴿٥﴾ الماعون: 4-5

**- ለሰጋጆች ወዮላቸው፤ በሶላታቸው ዉስጥ ዝንጉ የሆኑት** *(አል-ማዖን 4-5)* ምንም ቃላቶች ባይኖሩም፣ ከአሏህ ጋር የሚደረግ ማንኛውም ቅጽበት፣ እኛ ከምንደግማቸው ግን የማይሳኩ የግንኙነት ገጾች የተሻለች ነች፡፡ ሁሉን ቻይ የሆነው አምላክ ልባችንን ነዉ የሚመለከተው ወደ አንደበታችን አይደለምንና፡፡ ለስለሆነም

ኣንዳንዴ፣ ልባዊ ባልሆኑ ቃላት ለእርሱ ለመናገር ከመቼውም ጊዜ በበለጠ በተሻለው እና በላቀ መንገድ፣ አሏህን ቃላት ሳናወጣ በልብ እናነጋግረዋልን፡፡ ይህ በእውነቱ ወደ አሏህ መድረስ ከፈለግን ነው፡፡ እናም እንደገና ነፍሳችንን ከሱ በመገናኘት ስንፈልግ ነዉ፤ እና በብርሃኑና በምርጫዉ ወደ ደስታችን መንገድ መመለስን ለማግኘት፣ በእውነት ቃል እንደገባነው የልባችንን ኃጢአቶችና የነፍሳችንን ኃጢአቶች በሶላታችን መልካም ሥራ ለማጽዳት ከቆምን ነዉ፡

وَأَقِمِ ٱلصَّلَوٰةَ طَرَفَيِ ٱلنَّهَارِ وَزُلَفًا مِّنَ ٱلَّيۡلِۚ إِنَّ ٱلۡحَسَنَٰتِ يُذۡهِبۡنَ ٱلسَّيِّـَٔاتِۚ ﴿١١٤﴾ هود: 114

**- ሶላትን በቀን ጫፎች ከሌሊትም ክፍሎች ፈፅሙ፤ መልካም ሥራዎች ኀጢአቶችን ያስወግዳሉና** (ሁድ፡ 114)

ሶላት ለሰውነት የአካል ብቃት እንቅስቃሴ አይደለችም፤ ምንም እንኳን ከእንቅስቃሴ ዉጪ ባትሆንም፣ እና የተወሰነ ጊዜ ብቻ መድበን የምናስተላልፍበት፣ ከዚያ ወደ ሌላ ጊዜ ጉዳይ የምንሸጋግርበት ጉዳይ አይደለም፡፡ ማለትም ጊዜዉ ተጠብቆ መፈፀም እንዳለበት ግዴታ ቢሆንም፣ ሶላት ከንፈሮች እና ምላስ የሚንቀሳቀሱባቸው ቃላት አይደለችም፣ እነዚያ እንቅስቃሴዎች የልምምድ አካል ቢሆኑም እንኳ፡፡ ግን ይልቁንስ ባሪያው በሚያከናዉነው፣ እርስ በእርስ በተያያዙ እና በተደጋጋፊ፣ በአምስት መስመሮች መካከል ተሰራጭታለች፡፡
ሁሉን ቻይ ከሆነው አምላክ ጋር እውነተኛ ግንኙነት እንዲኖር የምንፈልግ ከሆነ፣ አንዳቸውም (መስመሮች) ቢሆኑ በራሱ እና ከሌሎቹ መስመሮች ተለያይተዉ ገለልተኛ መሆን የለባቸውም፡፡ በሶላት ምሰሶዎች መካከል የተጠቀሱትን መስመሮች አናገኝም፣ ግን ከእነዚህ ምሰሶዎች ከሆኑት ምሶሶዎች ናቸዉ፤ ስለሆነም ከነሱ በቀር ሶላትም ሶላት አይሆንም፡፡

1- **የጊዜ መስመር፡** በሶላቶቻችሁ ውስጥ በአምስት ወይም በስድስት ያሉት ደቂቃዎች ዉስጥ እያንዳንዱን ቃል ቦታ ላይ ዝምታዉን፣ ትርጉሙን አሚጠዉ በምሳሌነት ዙህርን፣አስርን ሰግደዋል ብለዉ ሊያሳምኑኝ ወይም አርስዎን ለማሳመን እንዳይሞክሩ፡፡ ለሶላትዎት የሚመድቡት ጊዜ፣ በትክክል ለመስገድዎ ወይም ከፈጣሪዎ ጋር ለመገናኘትዎ ወሳኝ ጉዳይ ነዉ፡፡ ምንአልባትም ከፊሉ የሶላትዎ ጊዜ ከቃላትና ቃላት፣ እንዲሁም አንቀፅና አንቀፅ መካከል በሚደረገዉ ዝምታ፣ የሚያልቁ ይሆናል፡፡ አንደበትዎ ላይ

ቃላቶችን አያብዙ፣ እንዱ ሌላ የሚከታተል አድርገዉ፡፡ ቃላቶችን ይጣጣሙ፣ ትርጉሞቻቸዉን በልብዎ ይቅመሱ አንዳችን በምላሱ ማርን እንደሚቀምስ ሁሉ፣ ጣዕሙን ለማጣጣም ሲባል፡፡ በሶላትዎ ዉስጥ፣ ለያንዳንዱ ሀረግ፣ ለያንዳንዱ ቃል፣ ዓ.ነገር ጥቂት የዝምታ ጊዜ ይስጡ፤ ትርጎሟን እንዲገነዘቡ፣ ጥፍጥኗን እንዲጣጣሙ፣ የዛኔ እንዳለቀሟት፣ግን በጥሞና እንደተረዷት ይገብዎታል፡፡ ክፍሉ ሶላትዎን በዝምታ፣ ከፊሏን በልባዊ እና በምስጢራዊ ኑዛዜ ያድርጉ፤ ከአንድ ምንጭ፣ ማለትም ከልብ የሚመነጭ ማላት ነዉ፡፡ በዚያም በአንድ ፊት ወደ አምላክዎት አሏህ አቅጣጫ ይዞራሉ፡፡

2 - **የምላስ መስመር፡** መልእክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) ለእኛ ያዘዙትን ቃላቶች፣ በተቻለን ሁሉ አጠናቅቀን አናነባለን፡፡ ለእያንዳንዱ ቃል እና እያንዳንዱ ትርጉም የመደመር፣ የመጥለቅ፣ የማራዘም፣ የመነሳት ወይም የመውደቅ መብቱን እንሰጠዋለን፡፡ ስለዚህ በእነዚህ ሁሉ አካላት መካከል አስፈላጊው እኩልነት እንዲገኝ፣ ትሁትነት በሷ ብቻ ሊገኝ የሚችልበት የእኩልነት ቀመር፣ የሶላት ኹሹዕ በሷ እንጂ መገኘቱ እና መረጋገጡ የማይታሰብበት፣ እንዲሁም ክፍሎቿ ሙሉ በሙሉ የሚስማሙበት ከሆነ በስተቀር ሶላቱ መገኘቱ የማይታሰብበት ሁኔታ ነዉ፡፡

**3- የሰውነት መስመር-** ስለዚህ የእኛ መልክ፣ ምስል እና የፊታችን ገፅታዎች ምላሳችንን የሚያስደስቱ እውነተኛ እና ማረጋገጫ ትርጓሜ ናቸው፡፡ ምክንያቱም አንደበታችን ባይናገርም፣ ሰዉነት፣ ፊት እና አይኖች አንደበታችን እንኳን የሚናገረውን ትርጉም እንዲገልጹ የተደረጉ ናቸዉ፤ ምለሱ የማይንቀሳቀስ ቢሆንም፡፡ የመናገር ችሎታ ያጣ ሰው እንዴት እንደሚሰግድ ያያሉ? የምላሱን አገላለፅ ለማካካስ ሁሉም ችሎታዉን በመጠቀም በአይኖቹ፣ በፊቱ እና በአካሉ ምልክቶችን ያስቀምጣል፡፡ ሶላትዎን መናገር ከተሳናቸዉ ሰዎች ይማሩ፤ ሶላትዎ በመጀመሪያ እና በዋነኝነት የመናገር ችሎታ የሌለው ሰው ሶላት ይሁን፣ ከዚያ በኋላ በንግግርም ሆነ በመግለጥ አሏህ በሰጠዎት ነገር ይደግፉት፡፡

4 - **የልብ መስመር፡** -ስለዚህ ልባችን የሚያንቀሳቅሰው ምላሳችን በሚንቀሳቅሰዉ ነገር ነዉ፤ አንዳቸው የሌላውን እንቅስቃሴ ስለሚያረጋግጡ፡፡ ስለዚህ ሥነ-ልቦና እና አባዜዎች በአንዱ ሸለቆ ውስጥ፣ ምላስ በሌላ ዉስጥ አይሆኑም፡፡ የዚህ መስተጋብር ውጤት እውን ከሆነ ጥሩ ነው፡፡ በሁለቱ መስመሮች መካከል፣ በሰውነት ውስጥ

*መንቀጥቀጥ፣ የፊት ላይ ንፅፅር፣ የጨኸት ድምጽ ወይም በዓይንዎት ውስጥ በጥልቅ የሚመላለስ እንባ ካለ ማለት ነዉ፡፡*

5- **የድርጊት መስመር-** *ሶላታችንን ስንሰግድ፣ በእለት ተእለት ህይወታችን ዉስጥ፣ ድርጊቶቻችን ዓላማችን እና ቆራጥነታችን እውነተኛ እንዲሆኑ ታሳቢ ማድረግ አለብን፡፡ እንደዚያ ሲሆን ነዉ ተግባራችን ንግግራችንን ያሚያረጋግጠዉ፣ ሕይወታችን በሶላታችን ውስጥ በምላስም ሆነ በልቦቻችን ከምንናገረዉ ጋር የሚትጣጣመዉ፡፡ ስለዚህ ይህ ሶላት የዕለት ተዕለት ሥነ-ሥርዓቶች እና ልምዶቻች ከሌሎች እና ከአሏህ ጋር ካለን ዝምድና የሚያለያየን ዲያግራም መሆን የለበትም፡፡ ልክ ሁለት ውርዶች እና ሁለት አይነቶች እንዳደረግነው ሁሉ፣ ሁለት ውጫዊ እና ውስጣዊ ሶላቶቻችንን እናድርግ፡፡ እናም ሶላት ሁል ጊዜ በክቡር ቁርአን እና በክቡር ሀዲስ ውስጥ፣ ከድርጊት ጋር የተቆራኘ መሆኑን እናስታውስ፡፡ ያዉ በመልካሙ ማዘዝ እና በክፉ መከልከል፡*

يَـٰبُنَيَّ أَقِمِ ٱلصَّلَوٰةَ وَأۡمُرۡ بِٱلۡمَعۡرُوفِ وَٱنۡهَ عَنِ ٱلۡمُنكَرِ ﴿١٧﴾ لقمان: 17

**- ልጅ ሆይ፣ ሶላትን ስገድ፤ በመልካሙን እዘዝ ፤ እናም ከክፋት ከልክል**
*[ሉቅማን፡ 17]*

۞ فَخَلَفَ مِنۢ بَعۡدِهِمۡ خَلۡفٌ أَضَاعُواْ ٱلصَّلَوٰةَ وَٱتَّبَعُواْ ٱلشَّهَوَٰتِۖ ﴿٥٩﴾ مريم: 59

**-ከዚያም ከኋላቸው ሶላትን ያባከኑና ምኞትን የተከተሉ ተተኩ** *[መርያም፡ 59]*
**- ሶላቱ ከዝሙት እና ከክፉ የማይከለክለዉ ሰው፣ ከአሏህ ርቀት ካልሆነ በቀር አይጨምርም፡፡** *(በአል-ጎፋሪኒ አል-ሀንበሊ የተዘገበ፣ ከአብደላህ ቢን አባስ፣ የሺሀብ መጽሐፍ ማብራሪያ ላይ)፡፡*

*በሩቅ አገር ውስጥ አንድ ትልቅ ክብረ በዓል ላይ እንዲገኝ ስለተጋበዘ አንድ ሰው፣ ስለዚያ ጥሩ ልብስ ስለለበሰ ሰዉዬ ሰምተሃል? እና የረጅም ጉዞው አስቸጋሪነት ከበደዉ፣ እናም ለጉዞ በቂ ጊዜ እና ገንዘብ አጠፋ እና አባከነ፤ ዕድሎች አምለጡት፡፡ እዚያም ወደ ተፈለገው ቦታ ሲደርስ፣ የግብዣ ካርዱን አቅርቦ ተፈቅዶለታል በመግባት በታዳሚዎች መካከል በታላቁ አዳራሽ ውስጥ አንድ ወንበር ተሰጥቶት የበዓሉን አጀማመር በመጠባበቅ ተቀመጠ፡፡*

ከደቂቃዎች በኋላ ሰውዬው በመቀመጫው ላይ በመተኛቱ መጋረጃው ሲወገድ ግና ጊዜዉ አለፈ … እና በድንገት ከእንቅልፍ ሲነቃ *ሥራቸውን መሥራት* እንዲችሉ ቦታውን ለቆ እንዲወጣ የሚጠይቁት የጽዳት ሠራተኞች ድምፅ ሰማ፡፡ ትርኢቱ ተጀምሯል፣ ተጠናቅቋል እናም አበቃ፣ እንግዶቹም ሄዱ፣ እና በዚያ ክፍል ውስጥ ከእንቅልፉሙ ጓደኞችን በቀር ምንም የቀረ ነገር የለም?!

ይህ ሶላቱን የሚያቅድ እና በከፍተኛ መለኮታዊ ግብዣ የሚጣራ፣ ዉዱኡ የሚያከናውን እና ወደ መስጊድ የሚሄድ እና ጊዜውን እና ምንአልባትም ከገንዘቡን የሚለግስ ሰው እንደዚህ ነዉ ማለት ነዉ፡፡ እዚያ ለመድረስ የሚያጠፋውን እና ከዚያም በመስጊድ ውስጥ ጊዜዉን ያሳልፋል፣ ቢረዝምም ቢያንስም፡፡ ግን ከዚያ በኋላ ሁሉ በመንፈሳዊ ትዕይንቶቹ ሳይደሰት ሶላቱን ጨርሶ ይወጣል፣ ከአመለካከቶቻቸው እና ከፍ ካሉ ትርጉሞቻቸው ጋር ሳይገናኝ፣ እናም ከፈጣሪው ጋር ያለውን ግንኙነቱን ሳያጣጥም፣ ወይም ለእሱ ምንዳ አገኛለሁ ብሎ ተስፋ አደረገዉን ሳያገኝ!!

መልእክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) በሙስሊሞች መካከል ወንድማማችነት ሲፈጥር፣ እና አንዳቸው ሲገደል፣ ከዚያ ሌላኛው ከሳምንት በኋላ ተቀላቀለው ብለዋል፡፡ ሙስሊሞች፡-አሏህ ሆይ፣ ይቅር በለው ከወዳጁ ጋር አገናኘዉ፡፡ ያኔ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ አለ፡ **ታዲያ ከሶላቱ በኋላ ሶላቱ የት ነበር… ከሥራዉ በኋላ ደግሞ ሥራዉስ? ሁለቱም መካከል ልክ እንደ ሰማይ እና ምድር ናቸው፡** *[በአቡ ዳውድ የተዘገበ እና በአል-አልባኒ የተረጋገጠ፣ ከኡባይድ ቢን ኻሊድ አል-ሰላሚ]*

አሏህ .. የአንድ ሳምንት ሶላት የሚሠራውን ሰዉ ከሰማይ እና ከምድር ጋር በሚመሳሰለው ደረጃ ከፍ ካደረገ፣ እና የዚህ የአንድ ሶላት ደረጃ ድርሻ ምን ያህል ከአዕምሮ በላይ ነው?! የተከበረውን ሐዲስ እንደገና ያረጋግጡ፣ በጥያቄው አልረካውም (ከሶላቱ በኋላ ሶላቱ የት ነው?)፣ ይልቁኑ ከእርሱ ሊለይ የማይገባውን ጥያቄ በቀጥታ አስከተለዉ፤ (እና ከስራው በኋላ ስራው?)፣ በሶላት እና በስራ መካከል አካላዊ አንድነት እንዳለ ሊያስታወስ (ሶ.ዐ.ወ) በማሳሰብ እና እንዳቸዉን ከሌላው መለየት አለመቻሉ ለመግለፅ ነዉ፡፡

ከእያንዳንዱ ሶላት በኋላ ራስዎን ይጠይቁ፡ ሶላቴ ምን ያህል ከፍ አደረገኝ? ከሰማያት በላይ? ከጨረቃ በላይ? ከደመናዎች በላይ? ከቤቴ ጣሪያ በላይ? ከራሴ ከአንድ ኢንች በላይ? በሁለት ጣቶች? በአንድ ጣት? ምንም?

ከዚህ ከደቂቃዎች በፊት የገቡት እርስዎ እንዳልሆኑ እርግጠኛ ካልሆኑ በስተቀር ከእያንዳንዱ ሶላት በኋላ ከመስጂድ አይውጡ እና በመጨረሻም፡

- ፊት እንደሌለህ በሰውነትዎ ገጽታዎች ጋር ይስገዱ፣
- አንደበት እንደሌለዎ በፊትዎ ገጽታዎች ይስገዱ፣
- እናም ሰውነት እንደሌለዎ በምላስዎ ይስገዱ፣
- የመጨረሻው እንደሆነው ያህል በልብ ምትዎ ይስገዱ፣
- ሶላትንም ያራዝሙና የመጨረሻው ሶላትዎ ይመስል ወደ አሏህ ይቅረቡ፡፡

## ቀዩ ቁልፍ ቁጥር1: አላህ ታላቅ ነው

ምንም እንኳን (‹አላሁ አክበር› አሏህ ታላቅ ነው) ሐረግ ዉስጥ ያለዉ ነገር በመሠረቱ ልዩ፣ ብቸኛ፣ አስደናቂ እና እኛን ከምድር ለመውሰድ የሚያስችለን ኃይል ቢሆንም፣- እንደምናየው- ለመክፈቻ ተክቢር ከልዩነትም በላይ ልዩነት አለ፡፡ እሷ ሐጅንም ‹‹የማስጀመሪያ’’ ተክቢር ናት፡፡ ይህ ማለት ለሐጅ እንደሚገባ ሁሉ ወደ “የተከበረው” የጊዜ ሰሌዳ አከባቢ ውስጥ መግባትን ያመለክታል፤ ልክ የሐጅ ተጓዦች መጀመሪያ ላይ የ “ማስጀመሪያ/ኢህራም” መድረክ እምደሚገቡ ሁሉ፡፡

አንድ ሰው እንዲህ ቢልዎት፡ (ጠላት ደካማ ነው) እና ከዚያ ዝም ካለ፣ እርስዎ የሚጠብቁት ነገር ምን ሊሆን ይችላል? ለራስዎ እንዲህ ይሉ ነበር፡-እና ከዚያስ? ዓ.ነገሩን ለምን አላጠናቀቀም?! ወይም ደግሞ ከራስዎ ጋር ይነጋገራሉ እነዲህ እያሉ፡ ምንአልባት አንድ ነገር ስላስታወሰ ዝም ብሏል፣ ወይም ምንአልባት እሱ በአንዱ ወይም በሌላ ምክንያት ሃሳቡን ለመለወጥ እና ለማሻሻል ፈለገ፣ ወይም ምንአልባት የጤና እክል በንግግሩ ላይ ተጽዕኖ አሳድሯልና ሐረጉን ማጠናቀቅ ኣቅቶት…በእርግጥ ይህ ማብራሪያ ይመጣልዎታል፡፡ ምክንያቱም እርስዎ በእውነት ልክ እንደማንኛውም መደበኛ ዓረፍተ-ነገር፣ ዓረፍተ-ነገሩ ይመጣል ብለው ተስፋ ያደርጉ ነበር፤ ልክ እንደ

ማንኛዉም የተዘጋ፣ የተሟላ ቅጽ ያለዉ ዓ.ነገር፡፡ ለምሳሌ፡ ከእነዚህ ውስጥ አንዱን ይመስላል፡-

ጠላት እኛን ለማሸነፍ በጣም ደካማ ነው፤ ወይም ጠላት እኛን ለማጥቃት በጣም ደካማ ነው፣ ወይም ጠላት እኛ ካሰብን በታች በጣም ደካማ ነው፤ ወይም ይህ ጠላት ካጋጠሙን ጠላቶች በጣም ደካማ ነው .. እንደዚህ የመሰለ ነገር፡፡ ስለዚህ (ደካማ) የሚለው ቃል፣ የትም ቢሆን እንደ ማለት ነዉ፡፡ (ከ) መስተዋድድ፣ እኛ ሁልጊዜ ከማብለጫ ስም ጋር የምናስከትላት እና ማንኛዉም ስም ሚዛኑ (አፍአለ) ከሆነ፣ እንደ መጀመሪያዎቹ ሶስት ዓረፍተ-ነገሮች፣ ወይም በመጨመር ዘይቤ ይከተላል ማለት ነው፤ ልክ እንደ የመጨረሻዎቹ ዓረፍተ-ነገሮች (በጣም ደካማ ጠላቶች)፡፡ ግን አስደናቂው የእስልምና ሐረግ (አሏህ ታላቅ ነው) ከሁለቱ አንዱንም አልያዘም፤ (ከ)ም ከኋለዋ) (የተጨመረዉም) የለም!! ..

ጎዳናው እንደዚህ (ክፍት) የተተወልን ሀረግ ናት፤ እና ከተለመች መስተዋድድ (ከ)፣ ወይም ከተለመዱት ተጨማሪ ቅጥያዎች ጋር ብትመጣ ኖሮ፣ እና እራስ የመቻል አቅምን ትአጣ እና ወደ (ተዘጋ) ሀረግ/ቃል ይለወጥ ነበር፡፡ ከእኛም ከሷ በኋላ ልኬቱ ምን ሊሆን እንደሚችል እና ምናባዊ ጥረት ለማድረግ አይገባንም ነበር፡፡ ከምን ይበልጣል?..

የ(አሏህ ታላቅ ነው) ቀመር ክፍት ሆና የመጠችዉ ከእሷ በኋላ ለብዙ መላምቶች ስለሚኖሩ ነዉ፡፡ እነዚህም ለሚነባትና በምላሱ ሳይሆን በልቡ ደግሞ ደጋግሞ ለሚደጋግማት ሰው ሰፊ ግምቶችን እና መቶዎች ወይም በሺዎች የሚቆጠሩ አጋጣሚዎች የሚትሰጥ ቀመር ናት፣

አሏህ ከአንተ ይበልጣል ሽይጧን ሆይ.. ከአንተ ጨቋኝ ሆይ..፣ ከአንተ ገንዘብ ሆይ..፣ ከአንተ ቀልድ ሆይ..፣ ወይ ሐዘን ሆይ..፣ ወይ ደስታ፣ ማን ከአሏህ ጋር ከመነጋገር ሊያዘናጋኝ የሚችል አለን ..

እሱ (ትልቅ) ብቻ አይደለም፣ (ታላቅ) ነው፡፡ እኛ አረቦች፣ ይህንን ትርጉም ማወቅና ትክክለኛዉ ፍቺ ጋር መድረስ እስካልቻልን ድረስ፣ ግራ በመጋባት እና በመደጋገም ጨለማ ውስጥ መደበት ለእኛ እንግዳ ነገር አይደለም፡፡ ሌሎች ተርጓሚዎች እንዲሁ

እንደ (ታላቁ) ብለዉ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች ይተረጉሙታል፤ ያዉ እነሱም ግራ ሊጋቡ ይችላሉ ለማለት ነዉ፡፡ እሱም አንዳንድ ጊዜ (ከ--ታላቅ-the greatest) ነው፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ (ትልቅ-great) ብለዉ ማለት ነዉ። መተርጎም ያለበት (ታላቅ-Greater) ተብሎ ነዉ፡፡ እንደዚያ የተሳሳቱ ትርጓሜዎች፣ በውስጡ ክፍት ተደርጎ በተተወው ባህሪው፣ እንደማንኛውም ባህላዊ ሐረግ ወደ መደበኛ ሐረግ ይለወጣሉ።

አብዛኞቹን ሙዓዚኖቻችንን እንዲሁም ሶላቱን የሚሰግዱትን ያዳምጡ፤ እና ሁሉንም (ተክቢራዎችን) በማጣመር በሚነበብባቸው ያገኛሉ፡፡ በመጀመርያው ተክቢር ውስጥ (ራ)ን ‹ዷማ› ያያካትቱና ሁለቱን ተከራካሪዎች እንደ አንድ ተክቢር እንዲታዩ "*አሏ አክበሩል ላሁ አክበር*-አሏህ ከሰዎች ሁሉ የሚልቅ ነው፣ እርሱም አይበልጥም፡፡" ብለዉ ያነባሉ ።በዚህ ውህደት የመጀመሪያውን ተክቢር ባህሪ ያጣሉ፣ ስለዚህ ለሚሰሙዋት በእውነተኛ ምስል አያዩዋቸዉም፡፡ ክፍት መግለጫ፣ የሚያስፈልጋቸው ነጥቦች የሚከተሉዋት፣ መላምቶቻችን በመጠቀም በአዕምሯችን የምንሞላት (አሏህ ታላቅ ነው…) ልክ እደዚህ ከእሷ በኋላ በሶስት ነጥቦች፡፡

ይህ የሁለቱ ተክቢራዎች ጥምረት፣ የዚህ ሐረግ የቋንቋ ባሕርይ፣ ከእውቀታችን እና ከስሜታችን የጠፋብንን እውነታ መገለጫ እንጂ ሌላ አይደለም፡፡ ስለዚህ ነዉ፣ የተቀሩትን መግለጫዎች የሚለይበት፣ ምንም ዓይነት ግልጽ ክፍተት የማይኖርበት ያደረግነው፡፡ እንግዲያውስ ተርጓሚዎች ወደ (አሏህ ትልቅ ነው) ወይም ወደ (አሏህ እሱ ትልቁ ነው) ብለዉ ቢተረጉሙ በዚያን ጊዜ ልንወቅሳቸው አይገባም ፡፡

የመጀመሪያውን የሶላት ጥሪ ሲሰሙ ከመዲና ነዋሪዎች መካከል እንደሆኑ ራስዎን ለማሰብ ይሞክሩ፡፡ በዚህ ሐረግ እና በዚህ አዲስ ባልተሟላ የቋንቋ አወቃቀር እንደተገረሙ እንዴት ነበር ምን ይሰማቸዋል እና አዲሱ ሐረግ ምን እንደሆነ ሳይነገራቸዉ፡ አሏህ ታላቅ ነው .. አሏህ ታላቅ ነው .. አሏህ ታላቅ ነው.. አሏህ ታላቅ ነው …፡ (ታላቅ) የሚለዉ፣ ከጊዜ ወደ ጊዜ ከጊዜ ወደ ጊዜ…. ባህላዊ የቋንቋ ትዝታቸው የጠበቀውን የተቀናጀ ቀጣይነት ጥማታቸው ከሌለ በኋላ ምን ይላሉ..

(አሏህ ታላቅ ነው)፣ ሶላትዎን የጀመሩበት ቁልፎች፣ በቀይ እና በሌላው ቁልፍ መካከል የመጀመሪያው ቀይ ቁልፍ ነው፡፡ ያ ከፍ ወዳለ፣ እራስዎን ወደ ሰማዩ ከፍ ለማድረግ በሶላት ጠፈር መርከብ ላይ ሲሳፈሩ ሊበሩ ያሉት፡፡

## በማንበብ እና በመከተል መካከል

አንድ ወንድም ጠየቀኝ: ለምን በሶላት ውስጥ ንባብን እናቅድም? የምናነባቸው ምን ምን ጥቅሶች ናቸዉ፣ ለምሳሌ፡

وَٱلْمُطَلَّقَٰتُ يَتَرَبَّصْنَ بِأَنفُسِهِنَّ ثَلَٰثَةَ قُرُوٓءٍ ﴿٢٢٨﴾ البقرة: 228

***"እና የተፋቱ ሴቶች ሶስት ንባቦችን ይጠብቃሉ"*** *[አል-በቀራህ 228]*

የሚሉ ሊያቀርቡልን ይችላሉ፡፡ ነገር ግን ከሚለው ምሳሌ በሶላት ውስጥ ከአሏህ ጋር ያለን ግንኙነት እና ከፊቱ በአክብሮታችን/መተናነሳችን አንፃር ጠቀሜታ ምንድን ነዉን? የኃያሉን አሏህ ጥቅሶች ማንበብ በሚጀምሩበት ጊዜ የሰው ልጅ ቃላትን እንደማያነቡ ማወቅ አለብዎት፡፡ ግን ይልቁንም መለኮታዊ ጽሑፍን ደገመው ሲያነቡ ቅዱስ ቁርአንን ለብቻ ለማንበብ አንድ የተወሰነ ድርጊት ‹እያነበቡ› ሳይሆን፣ "እየተከተሉ" መሆንዎን መረዳት ነዉ፡፡

ከተከበረው ቁርአን በፊት አረቦች በዚህ አዲስ የቁርአን ትርጉም ውስጥ "የተነበበ" የሚለውን ቃል አያውቁም ነበር፡፡ ቃሉ እነሱ ዘንድ (ተከተለ) ከሚለዉ በላይ ምንም ማለት አልነበረም፣ ስለዚህ ያላሉም፡ አንድ ሰው በእኛ ላይገባ፣ ሌላውም ተከተለዉ፡፡ ግን ቅዱስ ቁርአን ይህንን ትርጉም ከአሮጌው ወስዶ ንባቡ ውስጥ "መከተል/ተከታዮች" የሚል ትርጉም እንዲኖረው አደረገ፡፡ የቁርአን ቃላት በመጀመሪያ የተሰጡት ከዓለማት ጌታ ነው፣ ከዚያ እሱን ‹ተከትሎም› ገብርኤል(ጅብሪል) (ዐለይሂ-ሰላም) ከዚያም በማንበብ ጅብሪልን የተከተለዉ ያነበበዉ የአሏህ (ሶ.ዐ.ወ) መልእክተኛ ነዉ፡፡ እና ዛሬ፣ ከእኛ መካከል አንዱ የአላህን ጥቅሶችን ሲያነብ፣ የአሏህን መልእክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) "እናነባለን" እና ጅብሪል ባነበበለት እኛም በንባቡ ውስጥ እንከተለዋለን። ያ "የተነበበው" ጀብሪል አምላክን ተከትሎ" ያነበበውን ቁርኣን ማለት ነዉ።

የዚህን ነጥብ አስፈላጊነት አይተዋል? እሷ የ "መከተል"፣ "መከታተል" ወይም ቀጣይነት ያለዉ "ተከታታይ" የሚሉ ቃላቶች የሚያሳዩት፣ በእኛ እና ሁሉን በሚችለው አምላክ መካከል ቀጣይነት ያለው ሂደት ነው። ጥቅሱን ስናነብ በእኛ እና በእሱ መካከል ቀጥተኛ፣ የቅርብ እና ሞቅ ያለ የክብር ሰንሰለት ወይም ግንኙነት እንዳለ ይሰማናል፤ አንባቢዉ የትኛውን ቦታ ሲያነብ ከፍተኛ የክብር ቦታ እራሱን እንዳስቀመጠ ይሰማዋል፡፡

የተጅዊድ ህጎች የመተላለፉን ትክክለኛነት እና ማለቂያ የሌለውን ትክክለኛነት በመጠበቅ ረገድ ትልቅ ሚና አላቸው፡፡ ህጎቹ "ስናነብ" በሙሉ ልቦናችን እና በማከታተል መንፈስ መሆን እንዳለበት ታስተምረናለች፡፡ ይህ ማለት፡ በመዋጥ፣ በመዘርጋት፣ በማጠር፣ በመለየት፣ በማገናኘት እና በማቆም፣ ወዘተ፡፡ ትክክለኛነት እና ፍጹም ሐቀኝነት በውስጣችን እንዲዘወዘወር በሙሉ ታሰልጥነናለች፡፡ ምክንያቱም የእኛ ንባብ ከትክክለኛዉ ቅጅ ጅብሪል ከጌታው የተቀበለው የመጀመሪያ ንባብ ቅጅ ጋር እንዲጣጣም ነዉ፡፡ ከዚያም ለአምላክ መልእክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) በትክክል እንደደረሰ እና እሱ በጌታው የተቀበለው አይነት ንባብ ማለት ነው፣ ከዚያ የአሏህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ልክ ከጅብሪል እንደተቀበሉት ለእኛም አሳልፈው እንደ ሰጡን አይነት፡፡

ይልቁንም የተጅዊድ ህጎች ለንባብ ከምንሰጥ የበለጠ ለማከታተላችን (ለመከተላችን) የበለጠ ጊዜ እንድንሰጥ ያስተምረናል፡፡ እና ይህ የጊዜ ልዩነት፣ ረዥሙ ለመከተል፣ የአምላክን የጥቅሶች እና የቃላት ትርጓሜዎች ለማስተንተን/ለማጤን የበለጠ ይረዳናል፡ ፡ ስለሆነም በምላሳችን እና በከንፈሮቻችን እንቅስቃሴ ብቻ በፍጥነት አናስተላልፋቸውም፣ በአዕምሯችን እና በአስተሳሰባችን እንቅስቃሴ መካከል እናጣምራለን እንጂ፡፡ ሱራ (አል-ናስ)ን ያላ ተጅዊድ ወይም የቁርኣን አነባበብ ህግ በማንበብ ይሞክሩ፣ ከዚያ በመከተልና በተጅዊድ በማንበብ ንባቡን ይቁጠሩ ፡፡ ንባብዎን ከእንግዲህ እንዴት እንደሚያነቡ/እንደሚከተሉ ለራስዎ ለማየት ያህል ማለት ነዉ፡፡

የአሏህን ጥቅሶች በሶላትዎ ውስጥ "ከማንበብ" ይልቅ "ለመከተል" የቻሉትን ያህል ይሞክሩ፡፡ የእሷ "መከተልዎ" የራስ ሃላፊነት ስሜት እንዲሰማዎት ያደርግዎታል፣ ያዉ በበለጠ አክብሮት፣ ፍርሃት እና መተናነስን የሚገለፅ ኃላፊነት፡፡ የአሏህን ቃል በትክክል

እንደ ወረደ “በመገልበጥ” በመደጋገም እና በመቆጣጠር ፍጹም እምነት ከሚጣልበት ከጅብሪል (ሰላም በእሱ ላይ ይሁን) እንደተላለፈ መቀበልና መከተል ነዉ።

**አዲሱ የቅዱስ ቁርአን ቋንቋ**

ንባብዎን ወደ "መከተል" ደረጃ ከፍ ለማድረግ የሚረዳዎት ነገር፣ መደበኛ፣ ተራ፣ ባህላዊ፣ እና ሰብዓዊ ቋንቋችን ጋር የሚመሳሰል አረብኛን እያነበቡ እንዳልሆነ አስፈላጊ እውነታ ይገንዘቡ፡፡

የተከበረውን ቁርአን ከነቢያቸው (ሰ.ዐ.ወ) ምላስ ሲሰሙ ሙስሊሞቹን ለመጀመሪያ ጊዜ በጣም ያናወጠው የቋንቋቸው ውበት፣ የንግግር ዘየ፣ አንደበተ ርቱዕነት፣ ትርጉሞች፣ የትክክለኝነት ምት ወይም አገላለፁ አልነበሩም፡፡ የእነዚህ ሁሉ ባህሪዎች ጥምረት ጎን ለጎን ከሚደነቅ እና ከእነሱ ከሚበልጥ ነገር ጋር መገናኘት፣ በቋንቋቸው ዉስጥ ከዚህ በፊት የማያውቁት ነገር ነዉ፡፡ ይህ በራስ መተማመናቸዉ፣ በግጥማቸዉ እና ሥነ ጽሑፋቸዉ፣ በአንደበተ ርቱዕነታቸዉ ጋር አይተዋወቅም ነበር፡፡ የዚህ ቋንቋ አዲስ ነገር እና ልዩነቱ ከማንኛውም ሌላ ዐረብኛ ቋንቋ ከሚያውቁት፣ ከአላህ መልእክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) ከራሱ እንኳን የተለየ ነው።

ራእዩ ከመገለጡ በፊት ይህንን መጽሐፍ ወደ እነሱ ያመጣውን ሰው ቋንቋ ያውቁ ነበር፣ እና ቋንቋው በትንሽም ሆኖ በብዙ ከቋንቋቸው የተለየ አልነበረም፡፡ እና አንድ ቀን ጠዋት ላይ ከእንቅልፋቸው ሲነሱ፣ ከራሳቸው ቋንቋ ፈጽሞ በተለየ ቋንቋ በአንድ ጊዜ ወደ እነሱ ወጣ፣ ለእነሱም አስገራሚ ድንጋጤ ነበር፡፡ የቋንቋ መግለጫዎች፣ ውህዶች፣ ትስስሮች፣ የቋንቋ ግንኙነቶች፣ ገፅታዎ እና የአጻጻፍ ባህሪዎች በሁሉም ነገር የተለየ ነው፡፡ ይህ ተዓምራዊ እና አስደንጋጭ ገጽታ ነው፤ በሰዋሰው ላይ የተመሠረተ ንፁህ የአረብኛ ቋንቋ፤ የተደረጉበት ጭማሪዎች ሁሉ በቋሚ መሠረቶቹ የበለፀጉ ቢሆኑም፡፡ ገደብ የለሽ የእድሳት እና የልማት ዕድሎችን በተመለከተ ከእሱ በፊት እንደከፈተ የሚታወቅ ነዉ፡፡

በእነዚህ አዳዲስ ገጽታዎች በአንዱ የቋንቋ ገጽታ ላይ ትኩረት ካደረግን፣ ይህም አዲሱን የቁርአን አጠቃቀም፣ ከቁርአን በፊትም ሆኖ በኋላ፣ አረብኛ ቋንቋ የማያዉቀዉን፣ ለሰዋሰዋዊ መሣሪያዎች ማዋል ነው፡፡ ለምሳሌ፣ በንደዚህ አይነቶች አሥርት አዳዲስ ትርጓሜዎችን እናገኛለን፤ አረብኛ ከመቶኛው ክፍለ ዘመን በፊት ወይም የማያዉቀዉን

ትርጎሞዎ፡፡ እንደዚህ ይሆናል (ሆነ) ለሚለዉ ትርጉሙ፣ እንደ (አሏህ ይቅር ባይ እና መሐሪ ነበር) ባሉት ውስጥ እና (ወይ) ትርጉሙ (በርግጥ) የሚል ይሆናል፤ ለምሳሌ (አንድ ጊዜ በሰው ላይ ደርሷል ወይ...)፣ እና (የለም) እና (አይ) ትርጉሙ (አዎ) ወይም (በእውነቱ) ማለት ሲሆን፣ ለምሳሌ:(ስለዚህ በከዋክብት ቦታ እምላለሁ) ወይም (በርግጥ/ተከልከሉ የሰው ልጅ አመፀኛ ነዉ)፤ ትርጉሙ (ምንአልባትም) ወይም (እርግጠኛ መሆን) ነዉ፡፡ ለምሳሌ፡ እንደ ( ምንአልባት እነዚያ የማያምኑት ሙስሊሞች ቢሆኑ ኖሮ ደስ ይላቸዋል) የሚሉ ጥቅሶች ውስጥ፣ እና (ጊዜ) ለሚለዉ ትርጉሙ (በስተቀር) ነዉ፡፡ እንደ አንቀፆች (እና ሁላቸዉም እኛ ጋር በሚመጡ ጊዜ)፣ እና (ምንአልባት) ትርጉሙ (እንዲ..)፤ ለምሳሌ፡ በሚከተሉት ጥቅሶች ውስጥ፣ (ስለዚህ፣ የመጽሐፉ ባለቤቶች እንዲያዉቁት፣ ምንም ማድረግ እንደማይችሉ)፣ ወዘተ (በቅደም ተከተል)..

በዚህ በቋንቋ መሰረታዊ ህጎች መካከል ያለዉ ግንኙነት ላይ በመመርኮዝ እና እንዲጠበቁ በማድረግ፣ በአንድ በኩል፣ እንግዳ ውህደት ነው፣ ምንም እንኳን እድገቱ ቢኖርም፡፡ እና በውስጡ የያዘውን ከቋንቋ እና ሰዋሰዋዊ ህጎች መወገድ ልዩነት እና አዲስነት ጨምሮ፣ በሌላ በኩል፣ ልዩ ጥንካሬ አለዉ፡፡ በዚህም መሠረት በሶላታችን ዉስጥ፣ መንቀጥቀጥና መተናነስ በቂ ተአምራዊነት ነዉ። ቃላቱን በሶላታችን ውስጥ ደጋግመን እንናገራለን፣ እናም ለእያንዳንዱ የአሏህ መጽሐፍ ምዕራፍ ዉስጥ አዲስ የተከለሰ እና በውስጡ ለመግባት (መበረዝ/መደለዝ) የማይቻል መሆኑን የሚያመለክተው አዲስ እና ልዩ ስም እንዲኖር ማድረግ ነዉ፡፡ “ሱራ/አንቀፅ” ስንል ሐሰተኛ፣ አስመሳይ፣ ስም ማጥፋት እና መደለዝን የሚቋቋሙ ግድግዳዎች (ግርዶሽ) አላቸዉ፣ እናም እሱ የተመሸገ ቤተመንግስት ግንብ እንደሆነ ይመጣል ‹ሱራ›፡፡ ያ ደግሞ በዚህ አጥር (ሱወር) ውስጥ የተካተቱ እያንዳንዱ የቁርአን ዐረፍተ-ነገሮች ወይም አንቀጾች፣ አረቦች ከዚህ በፊት ከዚህ አንፃር የማያዉቁት አዲስ ስም ለመሸከም ብቁ ነበሩ፡፡ “አያ-አንቀፅ”፣ የሚል ስም ተአምራዊነቱን እና እምቢታውን (እእጃዝ) የሚያረጋግጥ ልዩ ስም ነው፡፡ ከሐሰተኛ፣ ከአስመሳይ እና ከእገታ እስከ ፍርድ ቀን ድረስ ነፃ የሆነ ስም ነዉ፡፡ *(እናም የዚህን ሐዲስ ዝርዝር ወደ መጽሐፋችን የመጀመሪያ ክፍል*

*ይመልከቱ (ታምራቱ) የሚለዉን፤ ዓለም አቀፍ የእስልምና አስተሳሰብ ተቋም ፡፡ ዋሽንግተን 2012 እ.ኤ.አ.)*

**ግልፅ ቋንቋ እና ክፍት አረንጓዴ ቦታ**

ብዙውን ጊዜ በጆሯችን የምንሰማቸው ወይም የምንደጋገማቸው እና የለመድናቸዉ ሀረጎች በሕይወታችን ውስጥ በኩራት እናልፋቸዋለን፣ ልክ እንደ ማንኛውም ተራ ቃል ወይም ሐረግ ወይም የተለመዱ ቃላት አይነት። ግን በእውነቱ ካሰላሰልን፣ ከልመዳችን እና ትዝታዎቻችንን ተጽዕኖ ዉጭ ሆነን ካየን፣ እንዲህ አይደለም፤ በዚህ ክቡር ሀዲስ እንደምንመለከተዉ:-

**-መልእክተኛዉ (ሰ.ዐ.ወ) በሩኩው እና በሱጁዱ እንዲህ ይል ነበር፡ ልህቅና እና ቅድስና በመላእክት እና በነፍስ ጌታ)** *(ሙስሊም ከአኢሻ ዘግበውታል)*

(ማጥራት-ሱቡህ) የሚል ቃል ልክ እንደ (ጥራት-ሱብሃን) ቃል ነዉ፣ አረቦች ከእስልምና በፊት የማያውቁት አዲስ የእስልምና ቃል ነው፡፡ ሁለቱም ክፍት አጠራር ናቸው፤ ትርጉሙም እኔ (ክፍት አረንጓዴ ቦታ) ብዬ የምጠራው ነገር ነዉ የሚከተለዉ፡ ፡ ምክንያቱም ቦታዉ በሩን ክፍት አድርጎ ስለሚተው ራዕያችን እና ግንዛቤዎች እንደሚፈልጉት ከእሱ በኋላ ያለውን ባዶ ቦታ በሐቀኝነት በትርጉሞች መሙላት ነው። እዚህ ላይ ጉዳያቸዉ ልክ እንደ (አሏህ ታላቅ ነው) ጉዳይ ነዉ፡፡

(ጥራት-ሱህሃን) የሚል ቃል ከ (ፉዕላን) ሚዛኑ/ንፅፅሩ ጋር ያልተለመደ ምንጭ (መሠረታዊ ቃል) ነው፣ እሱም እንደ ቃል (ሱቡህ) (ልህቅና/ኃያልነት) እንደምንለዉ ሲሆን፣ ከሱ የምናወረዉ ሰዉ ሆኖ፣ (ከማክበር) ባሕርይ ጋር ማለት ነዉ፡፡ (ጥራት ለጌታዬ) ስል ጌታዬን አጠራለሁ..) ማለት ነዉ፡፡ ነገር ግን ማጥራት ከማንኛውም ነገር እና ከማንኛውም ባህሪ ማራቅ ነዉን? ይህ በሩኩዕም ሆኖ በሱጁድ ውዳሴ ውስጥ ያልተጠቀሰው ነው፤ ሁለቱም ክፍት ተደርገዉ ነዉ የተተዉት፡፡ ሁለቱም ሐረጎች ከቋንቋ ሰዋሰው አንፃር ያልተሟሉ፣ እና በተካታታይ መላምት ርቀት የተቀመጡ፣ ከአንድ በላይ አማራጮችን እንድንሞላ በሚያስችል ርቀት፣ ምሳሌያቸዉ (አሏህ ታላቅ ነው) እንደሚለው ሐረግ ምሳሌ ነው፡፡ አለበለዚያ ልክ እንደ ተጠናቀቁት ወይም ተዘጉ ቅርጾች ይሆናል፡፡ ለምሳሌ፡ እንደ (ጥራት ለኃያሉ/ታላቁ ጌታዬ)…ከጉድለት፣ እንደ

(ጥራት ለኃያሉ/ልዑሉ ጌታዬ ይሁን)…ዉርደት፣ ከጭንቀት፣ ከበደል፣ከስህተት/ግፍ፣ ከድካም ፣ከእንቅልፍ፣ ከህመም፣ ወዘተ፣ ዝግ ይሆናል ማለት ነዉ፡፡

በሶላት ዉስጥ ቁጥራቸው በዛ ያሉ በቋንቋ ዉስጥ የልተለመዱ ሀረጎች ይኖራሉ፤ ከእነዚህ አገላለጾች ክፍት የሆኑ ቦታዎች፣ ለመላምቶችና ግምቶችና ብዙ ዕድሎች የአሏቸው ናቸዉ፡፡ እና በጣም እንግዳው ነገር እነዚህ አገላለጾች ከተሟሉ የቋንቋዎች ሀረጎች እና ሌሎች ቃላት ጎን ለጎን መምጣታቸው ነው፡፡ ሆኖም ግን በሌሎች የቋንቋ ምክንያቶች ክፍት ናቸው፡፡ እንደዚህ ዓይነት ሐረጎች እና ቃላት በአል-ፋቲሃ እና በተቀሩት የቁርአን ምዕራፎች ውስጥ ይገኛሉ ይበዛሉ፤ በኋላም እንደምናየው በኢብራሂማዊ ሰላምታ እና ሶላቶች ውስጥ፡፡

በእርግጥ፣ በየሁለት ረከዓዎች በምንፀልይበት ጊዜ ያለማቋረጥ ከ 33 ያላነሱ ሀረጎችን ደጋግመን እንደግማለን፤ በቋንቋው አንፃር ያልተለመዱትን ሀረጎች፡፡ ይህ ማላት 33 ክፍት አረንጓዴ ቦታዎች፣ ያሰብነዉን፣ የገመትነዉን፡ መላምት ለመሙላት እና በትርጉሞቿ በማሰብ፣ ለመተንበይ እና ወደ አእምሯችን ለማምጣት በቂ ጊዜ የሚሰጠን ነዉ፡፡ ይህ ቁጥር አል-ፋቲሃን፣ ሰላምታዎችን፣ ወይም የኢብራሂማዊ ሶላቶችን አያካትትም፤ እና እኛ በሰላታችን ውስጥ የምናነባቸውን ሌሎች ጥቅሶች ወይም ዉዳሴዎች እና ፀሎቶችንም እንደዚያዉ፡፡ ይህ የዚያ በሁለቱ ረከዓዎች ውስጥ ያሉት አገላለፆች ዝርዝር ነው፡-

11 አሏህ ታላቅ ነው (ከእነዚያም ይበልጣል) + 2 አሏህ ለሚያመሰግኑት ሰማ (ምስጋናዉ በዚህ ላይ) + 2 ጌታችን አንተም ምስጋና ይገባሃል (ምስጋና በዚህ ላይ) + 6 (ሁለት ሩኩእ X 3) (ክብር ለታላቁ ለአላህ ይሁን) (ለእንዲህ አይነቱ፣ ወይም ለዚህ) + 12 (አራት ሱጁዶች X 3) ክብር ለልዑል አላህ (እንደዚያ እና እንደዚህ ባሉ ላይ)፡፡

ይህ በቋንቋ ክፍት ቦታዎች ወይም ያልተጠናቀቁ የቋንቋ መግለጫዎች ጥንካሬ የንግግሩን አስፈላጊነት ያሳያል፡፡ ወይም በሶላት ውስጥ የልዩነትን ብዛት ለማበልጸግ እና ከዚያ ከፍተኛውን የትህትና (ኹሹዕ) መጠን ለመጠበቅ፣ እና የምንለውን በምገባ ለመረዳት እናም ከሰማይ ጋር መገናኘትን ታመላክታለች፡፡

ሆኖም፣ "በክፍት እና በቋንቋ የተሟላ ሐረግ" እና " በክፍት ግን በቋንቋ ያልተሟላ ሐረግ"" መካከል መለየት አስፈላጊ ነው። እያንዳንዱ በቋንቋ ያልተሟላ ሐረግ በተመሳሳይ ጊዜ ክፍት ሐረግ ሊሆን ይችላል፣ ተቃራኒው ግን ትክክል አይደለም፡፡

እንደ (ክብር ለጌታዬ) ወይም (አሏህ ለሚያመሰግኑት ሰማ) ወይም (ጌታችን ሆይ ምስጋና ለአንተ ይሁን) ያሉ አባባሎች/ሀረጎች በቋንቋው መሠረት ያልተሟሉ ናቸዉ፡፡ ስለዚህ ለሚከተሉት አረንጓዴ አግዳሚ ቦታዎች እጩ ነው፤ ምክንያቱም ለብዙ ተጨማሪ የቋንቋ አማራጮች ክፍት ሆነዉ ከዚያ በኋላ ባዶዎችን ይሞላሉ ማለት ነዉ። በአል-ፋቲሃ ውስጥ የምናገኛቸውን ክፍት መግለጫዎች ወይም አገላለጾች በቋንቋ በሰዋሰዋዊነት የተሟሉ ናቸው፡፡ እና በዚህ መንገድ ትርጉሙን ለማጠናቀቅ ምንም አግድም መደመር አያስፈልገውም፡፡ ግን ለትርጓሜዉ፣ ከአንድ በላይ በሆነ መንገድ ተገዢ ነው፣ ለምሳሌ እንደ እነዚህ ቃላት እና አገላለጾች (ዓለማት - በጣም ሩህሩህ-- የፍርድ ቀን ባለቤት፣ የተቆጣባቸዉ ሰዎች--- የባረከካቸው--- መንገድ - - - የጠፉ/የተሳሳቱ---)፣ በእነዚህ የትርጓሜ ማላምቶች/አጋጣሚዎች እና መግለጫዎች እንዲሁ ክፍት ናቸው፣ ግን ለአቀባዊ (ወደ ጎን) ማብራሪያዎች ናቸዉ፣ ምንም እንኳን በቋንቋ ህግ በቋሚነትና በጥልቀት የተሟሉ ቢሆኑም፡፡ ለማብራሪያ ክፍት ቃል ወይም ሐረግ፣ ከዚህ አንፃር፣ ልክ እንደ አንድ ነጠላ ህንፃ ነው፣ ግን በበርካታ ወለሎች፣ እያንዳንዳቸው በላያቸው ላይ፣ እና እያንዳንዱ ፎቅ የራሱ የሆነ ቀለም፣ ጣእም እና ስነፅሁፍ ያለው፡፡

## የአል-ፋቲሃ ሚና እና ንባቡ

ይህ ታላቁ ሱራ የቁርአን ጅምር ብቻ አለመሆኑን ለአፍታ ቆም ብለው አስበዉ ያውቃሉ? ይልቁንም ሶላትም ከፋች ነች እንዲሁ? ይልቁንም በቅርቡ የምንወያይበት የቁድሲይ ሐዲስ በመባል የሚታወቀው ዉስጥ አላፋቲሃ እራሷ ሶላት ናት፡-

**- "ሁሉን ቻይ የሆነው አምላክ እንዲህ ይላል፡በእኔና በባሪያዬ መካከል ሶላትን ማለትም አል-ፋቲሃ በሁለት ትካፈላለች፣ ስለዚህ ግማሸዋ እኔና ግማሸዋ ለባሪያዬ..**

ይህቺ ሱራ በሁለት ቡድኖች መካከል እንደ ቅዱስ ውል ነች ብለው አስበው ያውቃሉ? በአምላኪው እና አምላክ መካከል፣ የመጀመሪያው ወገን ለሁለተኛው ወገን -ቀጣይነት ያለው ምስጋና እና ምስጋና **(ለአሏህ ምስጋና ይሁን)** -ብሎ ቃል ይገባል እና ለእርሱ **(ለዓለማት ጌታ)** አምላክነት እውቅና ይሰጣል፡፡ እና በእዝነቱ በእርሱ ላይ አሁን **(ሩህሩህ)** ተብሎ የተገለፀ ምህረት እና ዘላለማዊ እና ዝንተ-ዓለማዊ እዝነት **(አዛኝ)** ይወርዳል፤ በሱ ፍፁም ባለቤትነት እና የነፃ አስተዳደር ብቃት፣ በትንሳኤ ቀን (የፍርድ ቀን ባለቤት)፣ እና በአገልጋይነት፣ እጅ በመስጠት እና በብቸኝነት አምላክነት (ተዉሂድ) **(አንተን ብቻ እንገዛለን)** በሚለዉ መንፈስ፡፡ ሁለተኛው ወገን በዛም፣ በሃይማኖቱ እና በዓለም ጉዳዮች ውስጥ የመጀመሪያውን ወገን እንዲተካ (መሾሙን) ያረጋግጣል፡፡ ይኻዉም፣ **(ባንተ ብቻ እንታገዛለን/እንረዳለን)** በማለት እናም (አንደኛዉ ወገን) በዚህ ዓለም ላይ ወደ (ቀጥተኛው መንገድ)፣ ወደ ፀጋዉና ብልፅግናዉ፣ ይምረዋል፡፡ የእነዚያን **(በእነሱ ላይ ከተቆጣዉ)** መንገድ እንዲሁም ከአምልኮቱ ካፈነገጡት (ከተሳሳቱት) መንገድ ይራራቸዋል/ያርቃቸዋል…ብለው አስበው ያውቃሉ?

እናም አል-ፋቲሃ እያነበቡ እያለ እንደኛ ንግግር እንዳልሆነች፣ እና እንደ አረብኛችን መደበኛ ቋንቋ እንዳይደለች፣ ወይም ታላቁ መልእክተኛ፣ በረከትና ሰላም በእሱ ላይ ይሁን፣ እየተናገረ ወደእኛ እንዳመጣው ንግግር እንዳልነበር ያስቡ ነበር?

አል-ፋቲሃ ውስጥ ማለትም፣ ሃያ ዘጠኝ አጠራር በሆነው፣ ከሃምሳ ስምንት የማያንስ ፣ ቅዱስ ቁርአን ከመውረዱ በፊት የአረቦች ቋንቋ የማያውቀው አዲስ የቋንቋ ክስተት፣ እንዲሁም የመልእክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) ቋንቋም በክቡር ሐዲሱ ውስጥ እንዳወቅነዉ አይነት ጥቅስ አለመሆኑን ከነገርኩዎትስ? ወይም ሆን ተብሎ መተርጎም፣ ወይም እንዲትን አንቀጽ፣ ወይም የአንቀጽ ክፍል መገመት ካልሆነ በቀር፡፡ *[ስለዚያው ዝርዝር መረጃ በመጽሐፋችን (ተአምራቱ) ዉስጥ ስለ አል-ፋቲሃ ስንናገር፣ ሁለተኛ ክፍል ዉስጥ ያገኛሉ፡፡ የኢስላማዊ አስተሳሰብ ጥናት ኮሌጅ፣ ዋሽንግተን 2015.)*

በሶላት ጊዜ አል-ፋቲሃን ሲያነቡ ይህንን ሁሉ ለማስታወስ ይሞክሩ፡፡ ትርጉሞቻቸውን የበለጠ ለማወቅ የቃላቶቿን መንፈስ ለመረዳት፣ እነዚህን ቃላት እየሰሩ ያሉት እርስዎ መሆንዎን እና ከአዕምሮዎ የመነጩ እርስዎ በሠሩት ነገር እንደሆነ ለማሰብ ይሞክሩ፡፡ በአእምርዎ ተአምራዊ የአሏህ ቃል፣ የሰዉን የማይመስል መሆኑን ሳይዘነጉት ማለት ነዉ፡፡ እንደዚያ ሲያስቡ፣ ውስጥዎ እየረጠበ እንደሆነ እና ልብዎ በሷ እንደሚመታ እና እርስዎም ቃላቶቿን በማንበብ፣ በትትክል የሚያምኑባቸውን ጥቅሶች ያነባሉ፤ እና ሌሎች የሚናገሩትን ቃላት የሚደግሙት ብቻ አይደሉም ማለት ነዉ፡፡ ይህ ማለት አንደበቱ ቋንቋውን ሳይናወጥ ወይም በውስጡ ያለውን ነገር ምክንያታዊነት ሳያድርበት ማለት ነዉ፡፡

ይህንን ፈተና ካለፉ የመጀመሪያውን ጎዳና ተገንዝበዋል፣ እናም እያንዳንዱ በአል-ፋቲሃ ውስጥ ያሉትን ቃል ዋጋን ማስተዋል ይችላሉ፤ የእያንዳንዱን ሐረግ ታላቅነት፣ የእነዚህ ቃላት እና አገላለጾች ትርጉሞች ታላቅነት፣ እናም የችሎታዋን፣ የብቸኝነቷን እና ልዩነቷን ዋጋ ማለት ነዉ፡፡

እናም ይህቺ ሱራ (ምዕራፍ) ከተቀሩት የቅዱስ ቁርአን ሱራዎች (ምዕራፎች) ልዩነት ያላት መሆኑን ሁል ጊዜ ያስታውሱ፡፡ ሶላትዎ ዉስጥ የፈለጉት ሱራዎች ቁጥር ማንበብ ይችላሉ፣ ግን ፋቲሃ ሊኖርዎት ይገባል። ሙሉውን ቁርአን በሶላትዎ ውስጥ ካነበቡ፣ ፋቲሃን ካላነበቡ፣ ከዚያ ለሶላትዎ ዕውቅና አይሰጥም ወይም አልሰገዱም፣ ምንአልባት የንባብ ምንዳ ሊፃፍልዎት ይሆናል፣ ግን ሶላት አይደለም፡፡

- **(በሰላት ዉስጥ)** የቁርዓን መክፈቻ የሆነችዉን **አል- ፋቲሃን ላላነበቡት ሶላት የለም** (ቡኻሪ የዘገበው ከኡባዳ ቢን አል-ሳምት)

## በአሏህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ እጅግ በጣም አዛኝ

ይህቺ ከእጅግ በጣም ቆንጆዎች የቅዱስ ቁርአን አንቀጾች አንዷ ናት፣ በጭራሽ በጣም ቆንጆ ባትሆንም፡፡ ነገር ግን መደጋገም፣ ልማድ እና መተዋወቅ በውስጧ ያለዉን ልዩ መገለጫ እንዳናየው አግዶናል፤ እና እንደ ማፌዣ ቃል ብቻ መድገም ጀመርን፤ ልክ እንደ (አመሰግናለሁ) እና (ይቅር በሉን) እና (ደህና ሁኑ)። ግን (እንደዚህ ብለን) እራሳችንን መጠየቅ እንችላለን፡ የአለም ጌታ ይህቺን አንቀፅ በሶላት ዉስጥ

የምንደጋግማት የመጀመሪያ ምልክታችን እንድትሆን ለምን መረጠ? እና ቁርአን የሚከፈተበት የመጀመሪያ አንቀፅ ለምን ሆነች? እኛ ቁርኣን የምንጀምርበት የመጀመሪያው መተላለፊያ/መክፈቻ ለምን ሆነች? እና ለምን የሱረቱ አል-ፋቲሃ አካል ሆነች?

እኛ በእነዚህ ንባቦች ሁሉ ውስጥ የበስማላችን (ብስምላህን) መደጋገም፣ እና ከዚያ በኋላ ህይወታችን ሁሉንም ንባቦች ስናነብ መደጋገማችን፣ የሚያሳየን የአንድ አንቀፅ ንባብን ከማስጀመር የበለጠ ትርጉም የሌለው ነዉ ብለን እንድናስብ ያደርገናል፡፡ ይልቁንም የቋንቋ ሰዎች በዚህ አስተሳሰብ ከኛ ጋር ናቸዉ፤ ትክክለኛውን እርምጃ ወይም ክስተት ለማድነቅ እራሳቸውን ብዙ አላደከሙም፡፡ እነሱ እንደሚሉት (በአሏህ ስም) የሚል ቃል **(በአሏህ ስም እጀምራለሁ)** እንደ ማለት ነዉ። በዚህም የእነሱ ሰዋሰዋዊ ችግር ተቀርፏል፣ ግን በእውነተኛ እና በአስፈላጊ ትርጉም ምትክ።

ጉዳዩ በአሏህ ስም የቅዱስ ሥራ ወይም ጽሑፍ ምርቃት ብቻ ከመክፈት የራቀ ነው፤ እናም የበስማላ የመጀመሪያ ሱራ/ምዕራፍ ላይ ወይም የንግድ ሥራ ለመጀመሪያ ጊዜ ስንሠራው፣ስናነበው፣ ከመጀመሪያው ትርጉሙ አተያይ አንፃር መሆኑ ምንም ጥርጥር የለውም፡፡ እናም በስመላ በእነዚህ ቦታዎች ላይ እንድትሆን የሚፈለገዉም፣ እኛንና የሰዋሰው ቋንቋ ባለቤቶችንም ወደዚህ ግምት ወይም እሳቤ ያስገባን ጉዳይ ይሄዉ ነዉ ማለት ነዉ፡፡

ጥቅሱ፣ በዋነኝነት፣ ወደ በጣም አስፈላጊው ነገር ነው ሚያመለክተው፡፡ ይኸዉም፣ ማንኛውም የምናነበዉ የቁርአን የቋንቋ ብቃት፣ ማንኛውም ትእዛዝ፣ ማንኛውም ክልከላ፣ ማንኛውም ተስፋ ፣ማንኛውም ግሳፄ፣ ማንኛውም መግለጫ፣ ማንኛውም ዜና፣ ማንኛውም ምክር እና ማንኛውም ማሳሰቢያ፣ ወዘተ፣ ይልቁንም አሏህን በመወከል፣ ልህቅና እና ክበር ይገባዉ፣ በሱ ስልጣን እና ማጣቀሻ አንደበታችን ላይ የሚንሸራሸር ነዉ እንደ ማለት ነዉ፡፡

وَإِذْ قَالَ رَبُّكَ لِلْمَلَٰٓئِكَةِ إِنِّى جَاعِلٌ فِى ٱلْأَرْضِ خَلِيفَةً ۖ ﴿٣٠﴾

የሰው ልጅ በምድር ላይ የአሏህ ተተኪ ከሆነ (እና ጌታህ ለመላእክት “እኔ በምድር ዉስጥ ኸሊፋ (ተወካይ) አደርጋለሁ ([አል-በቀራህ፡ 30)፣

ከዚያ ይህን የመሰለ ታላቅ ተግባር እያስተናገደ መሆን አለበት፡፡ በዚህች ምድር ላይ አደራ የሰጠዉን ቃላት እያነበበ፣ የእሱን ተመሳሳይ ቃላት፣ ሁሉን ቻይ አምላክ ባወጣው ተመሳሳይ ቃላትና የአነባበብ ስርዓት መሆን እንዳለበት እራሱን ማሳሰብ ያለበት፡፡ ደግሞም እሱን ለሚሰማው ሁሉ ሲያስተጋባ የሚገባዉ፣ እሱ በታች እያለ፣ በምድር ዓለም ውስጥ እያለ፡ ከሰማይ ግዛቶች ከላይ የተሰጡ ቃላትን ይልቁንም እርሱ ሁሉን ቻይ ከሆነው ዉክልና መጣቀሻ፣ እሱን በመጥቀስ እና ከሱ በተገለፀለት አኳኋን ነዉ፡፡ በዚህች ምድር ላይ ሁሉን ቻይ ከሆነዉ (አምላክ )ተተኪ ስለሆነ፡፡

አንድ ዳኛ በእጁ ውስጥ ባለው ጉዳይ ላይ ፍርዱን ሲሰጥ፣ እና ፍርዱን (በሕዝቡ ስም) የሚለዉን በማንበብ ሲጀምር፣ በዚህ ማለቱ-(እኔ የምጀምረው በሕዝቡ ስም ነው) ወይንም ይልቁንስ (በሕዝብ ስም ነው የምናገረው) ማለት ይፈልጋል? የሚናገረው ይህን ቃል እየደጋገመ (በ...ስም) እያለ (በ) ምንን እንደሚወክል ሀስቦ ያገረጋግጣል ወይም ይወስናል፡፡
ይህ ዳኛዉ የሚሰጠዉ ፍርድ ሕዝብን ወክሎ ከህዝብ በዉክልና ስልጣን ውሳኔውን ያሳልፋል/ይሰጣል፡፡ የስልጣን ምንጭን ከህዝብ ነዉ የሚወስደዉ፤ ለምሳሌ አንድ የህዝብ አካል/አባል የሆኑት ከዘመዶችዎ ለአንዱ ያቀረቡለትን ጥያቄ ወይም እንዲያሟላላቸዉ እንዲህ እያሉ፡ (እኔ በዘመዶች ስም እለምንሃለሁ)፣ ይህ ማለት፡ (ይህንን ጥያቄ ከዘመድ ሥልጣን ወይም ሥልጣን ባለቤትነት አንፃር እጠይቀሃለሁ) ይላሉ፡፡

አል-ፋቲሃ ወይም ምዕራፍ የሚጀምረው ከሚከተለው (በአላህ ስም፣ እጅግ በጣም ሩህሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው) መሆኑን ለአንባቢ ለማስታወስ ያህል፣ እነዚህ መለኮታዊ ትምህርቶች ሲያነቡ፣ የሚያነቡት (በአሏህ ስልጣን እና ዉክልና) ብቻ መሆኑን ነዉ፡፡ እዚህ (አል-ባ) ፊደልን ከቋንቋ ምሁራን አተያይና በሰዋሰው ህግ ብንገመግመዉ፣ በተጠቆመው መፍትሄ (በ...ስም ጀምሬያለሁ) እንደ ማለት ነዉ፡፡ በዚህም፣ እኛ ከመፈላሰፍና ካላስፈላጊ ሙከራ እንታደጋለን፡፡ ያ ሳይሆን ቢቀር ኖሮ፣ የቃሉን መሰረታዊ፣ አስፈላጊ እና አስደናቂ ትርጉምም እናጣለን ማለት ነዉ፡፡

በበስመላህ ሶላቴን ስጀምር፣ ይህ ማለት፣ እየጀመርኩኝ ያለዉ ነገር፣ ከእኔ የመጡ ተራ አውቶማቲክ እንቅስቃሴዎች እና ተደጋጋሚ ቃላቶች፣ የተሸመደዱ ቃላቶቼ፣ በምላሴ ላይ የተጫኑት እና በልቤ ዉስጥ ቦታ የሌላቸዉ ወዘተ እንዳልሆኑ የማንቂያ ደዉል ነዉ፡፡ ይልቁኑም ከአሏህ ጋር የሚደረግ እውነተኛ ግንኙነት ነው፤ እኔ አሁን የማደርገው፣ አሁንም በዚህ ምድር ላይ ለተተኪው ቦታ ታማኝ እንደሆንኩ፣ በእኔና በእሱ መካከል ያለውን ቃል ኪዳን ለመፈፀም መሆኑን የሚያረጋግጥበት ጉዳይ ነዉ የምፈፅመዉ ማለት ነዉ፡፡

የዚህን መጽሐፍ የመጀመሪያ ገጽ (በአምላክ ስም፣ እጅግ በጣም ሩህሩህ በሆነው እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው) የሚለውን ሐረግ ስጠቅስ፣ ከዓለማት ጌታ ዘንድ ለእኔ አስታዋሽ ነው፣ በመጽሐፉ ውስጥ ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው ቃል ድረስ ያለው ሁሉ፣ በእሱ እና በባሪያዉ መካከል በተጠናቀቀው የውል ስምምነት መሠረት ነዉ፣ ፊቱን ለመመኘት፣ ህጎቹን በማክበር እና በእሱ ገደቦች በቆምኩበት መሠረት እና በመሬቱ ላይ የተሰጠኝን የስልጣን ውሎች በማክበር ነዉ የሚለዉን በማረጋገጥ ጋር ነዉ፡፡

(በአሏህ ስም)፣ በዚህ ምድር ውስጥ እርሱ ከተወካይ ደረጃ እንደማይበልጡ በእርስዎ እና በአሏህ መካከል ያለዉ ሰነድ ነው፡፡ እና ከሱ በስተቀር ምንም ስልጣን የለም፤ እና የእሱ ንብረት በስተቀር ገንዘብ/ንብረት የለም፤ ሪል እስቴት ንብረቱ ካልሆነ በስተቀር ሪል እስቴት የለም፣ ከሱ ምግብ እና መጠጥ በስተቀር ምግብ እና መጠጥ የለም፡፡ ከሰማይ የወረዱ፣ (ምድር) ወደተባለው ትንሽ ፍየራ ውስጥ ካፈሰሰባቸው በቢሊዮኖች የሚቆጠሩ ቢሊዮኖች ትናንሽ እና ትልልቅ ፋይዳዎች፣ አካላት፣ በዚህ ዓለም ዉስጥ የተሰራጩት፣ ሁሉን ቻይ ከሆነው እና ከዋናዉ ባለቤቱ፣ ከአምላካችን አሏህ፣ በዉክልና ወደ እኛ የተመደቡ መሆናቸዉ ነዉ፡፡ እናም አንቀፆች ሳይለወጡና እንደወረዱ፣ በእሱና በኛ መካከል ያለዉ ዉክልና፣ በአጭር ጊዜ ውል መሠረት፣ እስካለ ድረስ እድናስተዳድር ነዉ፡፡ ስለዚህ ለጉዞ ለመነሳት ተዘጋጅተዋል? የሂሳብ መጽሐፍ ይዘው ለባለቤቱ ለመቅረብ ራስዎን አዘጋጁ?

ሆኖም፣ (በአሏህ ስም፣ እጅግ በጣም ሩህሩህ፣ እጅግ በጣም አዛኝ) የሚለው ታሪክ እዚህ አያበቃም። እዚህ (ፈቃድ) ወይም (መተካት) ወይም (የውክልና ውል)፣ (በአሏህ ስም) ጋር መቆም ይቻል ነበር፣ ነገሩ እንዲገባደድ፡፡ ግን ሁሉን ቻይ የሆነው አምላክ

ይህንን (ውል)፣የእሱ ወሳኝ አካል በሆነዉና በማይነጣጠል (አገናኝ) ጋር ያገናኛል፡ ከ(እጅግ በጣም ርህሩህ፣ እጅግ በጣም አዛኝ) ጋር፡፡

ከአንድ ምንጭ የተውጣጡ (እጅግ በጣም ርህሩህ) እና (እጅግ በጣም አዛኝ) መገናኘት እና እነዚህ ሁለቱ ባህሪያት በሱ እና በእርስዎ መካከል (የውክልና ውል) ደረጃ ላይ ያለዉ በስለመላ ዉስጥ በአንድ ላይ መታቀፋቸዉ፣ ባለተለመ ሁኔታ በመከፈቻ ቦታዉ፣ በሙስሊሙ እና በጌታው መካከል በጣም አስፈላጊ ለሆነ የግንኙነት መንገዶች ጥሩ ማሳያ ስለሆኑ፣ ሶላት እና ቁርአን፣ በፁሁፋቸዉ ወይም ገፆቻቸዉ ውስጥ፣ ለሰጋጁ በተለይ፣ በዙሪያዎ ላለው ለዓለምም ሁሉ፣ ከአንድ በላይ መልዕክቶችን ያሸከመናል፡

በመጀመሪያ፣እርሱ (እዝነቱ ከቁጣዉ የቀደመው) እንደመሆኑ፣ በሐዲስ ቁድሲይ ውስጥ እንደተገለፀዉ፣ የመረጠልን፡ 113 ምዕራፎች (ሱራዎች) በዚህ በሁለትዮሽ፣ አዛኝና ጀማሪ ስሞች መጀመር እንዳለባቸዉ አጥብቆ አረጋግጧል፡፡ ያዉ ሁለቱ ስሞች ተቀራራቢ እና ከአንድ ምንጭ የተገኙ ናቸው (በትርጉማቸው ግልጽ ልዩነቶች) ቢሆኑም፡፡ ያስተዉሉ፤ የሱራዎቹን የመከፈቻ አንቀፆች ከጊዜ ወደ ጊዜ ከብዙ ባህርያቱ ሌሎች ተለዋጭ ስዕሎች ጋር ወደ “ማቅለም” አልሄደም፤ ይልቁንም ይህንን ቅድመ ዝግጅት ሲመርጥ፣ ጥንካሬ እና ምህረት አንድ ላይ የሚሰባሰቡበት ሌላ የሁለትዮሽ ቦታ ቢኖርም፣ እሱ ለእርስዎ አልመረጠም፡፡ ይህ ማለት በሁለቱ ምንጮች መካከል ሚዛንን ለማሳካት ወደ ሰብአዊ እሳቤያችን ከተመለስን እንኳ፣ ሁለቱ ቃላቶች፣ በቅዱስ መፅሃፍ ዉስጥ፣ ከአንድ ቦታ ቢገናኙም

ٱلْعَزِيزُ ٱلْحَكِيمُ ﴿٣٧﴾ الجاثية: 37

(እጅግ በጣም ጠንካራ እጅግ በጣም አዛኝ) (አል-ጃሲያ፡ 37)፣ ወይም ሌሎቹ ሁለቱ

ٱلْعَزِيزُ ٱلْغَفُورُ ﴿٢﴾ الملك: 2

(እጅግ በጣም ኃያል ፣ እጅግ በጣም ይቅር ባይ) [አል ሙሉክ፡ 2]፣ ለምሳሌ፡፡
በሁለተኛ ደረጃ፣ ሁለቱ ((እጅግ በጣም ርህሩህ) እና (እጅግ በጣም ርህሩህ) የዚህ ሁሉ ታላቅ አስፈላጊነት ያገኙት፣ እነሱ ከሶላትዎ መሠረታዊ አካል ስለሆኑ ነዉ፤ እና ለሁሉም ንባቦችዎ ከፋች ነው፡፡ ይህ ማለት፣ እነሱ የእርስዎ አካል ናቸው፤ እና የእምነትዎ

መሠረታዊ ምሰሶዎች ናቸዉ፡፡ በእውነቱ ለእርስዎ በተሰጠዎት ቦታ ጋር ብቁ መሆንዎን-በምድሪቱ ዉስጥ የአሏህ ተተኪ የሚገልፁበት ነዉ፡፡

ሦስተኛ፣ እና እርስዎ በልዑሉ ፈቃድ በምድር ውስጥ ተወካይ ስለሆኑ እና እርሱ (እጅግ በጣም ርህሩህ) እና (እጅግ በጣም አዛኝ) ስለሆነ፣ ይህ (መቀበሉ) ግድ ይልዎታል፡፡ እነዚህ ሁለቱ ባህሪያት ኃያሉ አሏህ በመረጠዉ እና ከእሱ ዘንድ የተመረጡ ሲሆኑ፣ እርስዎ በላጭ ተወካይ፣ እናም እነዚህን ባህሪያት ሁል ጊዜ፣ከቁርአን አስቸኳይነት፣ ድግግሞሽ፣ ወሳኝነት አንፃር፣ አፅንዖት ለመስጠት በአደራ ወደ ተወከሉብዎት ተጠያቂነትና የተሰጠዎት የኃላፊነት ደረጃ ከፍ ማድረግ አለብዎት፡፡

እርስዎ ሙስሊም ነዎት፣ ታዲያ ዓለም የፊትዎን ፀጋ፣ የከንፈርዎን ፈገግታ፣ እና የልብዎን ርህራሄ ማየት አለበት፡፡ እናም ለቅርቡም ለሩቅም ባለዎት ፍቅር፣ ለሁሉም ባለዎት ፍቅር እና ለወዳጅዎ እና ለጠላትዎ ባለው መቻቻልና ይቅር ባይነት፣ (እጅግ በጣም ርህሩህ) እና (እጅግ በጣም አዛኝ) ትርጉም ያለው ሁሉ ሌላውን ያቀፈ፣ እና የይቅርታ፣ የፍቅር እና ሰብአዊነት፣ የመተናነስ እና እራስን ዝቅ የማድረግ ምልክት ማሳየት አለብዎት፡፡
አያችሁ፣ ዛሬ ዓለም የሚያየው የሙስሊም ተምሳሌት (ገፅታ) ይህ ነው? ይህ በእውነት ምሳሌያዊነት ነው?

## እጅግ በጣም ሩህሩህ እጅግ በጣም አዛኝ

ሁለቱ የተለያዩ የቋንቋ ዓይነቶችና አጠራሮች ናቸው፡-(ፈዕላን) እና (ፈዒል)ም ተብሏል፤ ግን ሁለቱም ከአንድ ምንጭ የተገኙ ናቸው፣ *ምህረት* ከሚለዉ፡፡ የሁለቱ ቃላት አፃፃፍ የቋንቋ እውነታ እያንዳንዳቸው የተለየ የትርጉም ባህሪ እንዳላቸው ይናገራል፣ አንዱ ከሌላው ማለት ነዉ፡፡ (እጅግ በጣም ሩህሩህ) የሚለው ቃል በ (ፈዕላን) ቅርፅ ነው የመጣ እና እሱም ብዙውን ጊዜ በቋንቋችን ዉስጥ የተለመደ፣ እንዲሁም (ዛሬዉኑ) የምንጠቀመዉ አይነት፣ ለምሳሌ (የተጠማ-ዘምኣን፣ የተናደደ-ገድባን፣እንቅልፍ የያዘዉ-ሥህራን፣ ደስተኛ-ፈርሃን ወዘተ) ከሚሉት ቃላት ጋር ይመሳሰላል፡፡ እነዚህ ቃላቶች በሙሉ የሚያመላክቱት በአንድ ገፅታ ዛሬዉኑ ወደሚለዉ መገለጫ ነዉ፡፡ የተጠማዉ ዛሬም እንተጠማ ነዉ በቅርብ ጊዜ ጥማቱ

ያበቃል፤ የተናደደዉ ዛሬም እየተናደደ ነዉ በቅርብ ጊዜ ንዴቱ ያበቃል፤ይረጋጋል ወዘተ…

(አር-ረህማን-እጅግ በጣም ሩህሩህ)፣ ስለሆነም ምህረቱ ከሰማይ በእርሱ ላይ "አሁን" የሚገለጥለት (የሚወርድለት) ሰው ነው…ማለትም እርስዎ ቃሉን በሚያነቡበት ወቅት ማለት ነዉ፡፡ ሀረጓ ከሰማይ ወደ ምድር የሚትዘልቅ፣ ቀጥ ያለ ትርጉም ያለው ነዉ፡፡ ከእርሱ ጋር ወደ እኛ በመንቀሳቀስ ምህረት ይሰማናል፣ አሁንም መንፈስን የሚያድስ ነገር ከአሏህ ዘንድ በእኛ ላይ በመውረድ፣ ከዚያ እርስዎ ይህን ትሩፋት እናም ከአሏህ ምህረት ፅዋ ጉድጓድ እንዲያጥብዎት እያሰቡ ያንብቡት፡፡ ያዉ ከእጅ አንጓው አንስቶ እስከ እግርዎ ጫማ ድረስ ባለው በምህረቱ ፅዋ ያጥብዎታል ማለት ነዉ፡፡

ስለ (አር-ረሂም፡እጅግ በጣም አዛኝ)፣ (ፈዒል) በሚለው ሚዛን ላይ የተመሠረተ ሆኖ፣ ብዙውን ጊዜ በቋንቋችን ዉስጥ ቀጣይነትን ወይም ማራዘምን እና ዘላቂነትን የሚያመለክተው ቀመር ነዉ። ለጋስ ሁል ጊዜ ለጋስ ነው፣ ንፉግም ሁል ጊዜም ንፉግ ነው፣ ትሑቶችም ሁል ጊዜ ጨዋዎች ናቸው፡፡ እርሱ፣ ስለዚህ (እጅግ በጣም አዛኝ) እናም በማንኛውም ጊዜ ነዉ፤ እዚህ ምህረቱ አጠቃላይና የቀጠለ፣ ያለፈ፣ የአሁኑ እና የወደፊት ጊዜን ያካተተ ነው፡፡ ይህ ቅፅል ከዘለአለም ወደ ዝንተ-አለም የሚዘልቅ፣ የተራዘመ አግድም ልኬት ያለዉ ነዉ፡፡ እና በዚህ መንገድ (አር-ረህማን-ሩህሩህ) ከሚለዉ ቅፅል ጋር ልኬቱን ያሟላል፡፡ ይህ ቅፅል፣ ከሰማይ ወደ መሬት የሚዘልቅ አቀባዊነት ያለዉ እና ባነበብነው ቅጽበት አዲስ የሚሰማን ተለዋዋጭ እና ተንቀሳቃሽ ትርጉም ያለዉ ቅፅል ነዉ፡፡ (ለበለጠ ዝርዝር በመጽሐፉ ሁለተኛ ክፍል ውስጥ (ሱረቱ አል-ፋቲሃ) ያለዉን ይመልከቱ *(ታዓምራቱ) IIIT፣ ዋሺንግተን: 2015. ከገፅ፡53 ቀጥሎ)፡፡*

እኛን በሁለቱ ቃላት ልኬቶች እና በመካከላቸው ባለው ልዩነት መካከል ያለው የዚህ መለያየት ትክክለኛነት የሚያረጋግጥልን ነገር፣መልእክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) ሀረጓን የሚያነቡበት አካሄድ ወይም መንገድ በመሆኑ ነው፡፡ በነቢዩ ሐዲስ ውስጥ እንዳሳለፍነዉ፡

- **የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ንባብ እንዴት ነበር? ተብሎ አነስ ተጠየቀ፡ እርሱም አለ፡ *ማራዘም* ነበር፡፡ ከዛም አነበበ፡-‹በአሏህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ፣ እጅግ በጣም አዛኝ የሆነው›፣ *የአሏህን ስም* ያስረዝማል፣ *በሩህሩህ* ያራዝማል፣ *በአዛኙ* የሚለዉንም ያራዝማል** *[በቡኻሪ የተዘገበው ከቀታዳ]፡፡*

ምንም እንኳን በተጅዊድ የተደነገጉትን ማራዘሚያ ሁኔታዎችን ባያሟሉም (እጅግ በጣም ርህሩህ) እና ((እጅግ በጣም አዛኝ) ቃላት ለእያንዳንዳቸው ገለልተኛ እና የተለየ ስብዕና ይሰጣቸዋል፡፡ ምክንያቱም እኛ እንደምናውቀው ማረዘሚያ ጊዜ-ተኮር ማለት ነው፣ ጊዜ ማለት ደግሞ መግለጫውን ከኋላው ከሚመጣው መለየት ማለት ሲሆን፣ መለያየት ማለት ደግሞ የነፃነት፣ የትርጉም እና የአቅጣጫ ልዩነት ማለት ነው፡፡

**ቀዩ ቁልፍ 2: አንተን ብቻ እንገዛለን ባንተ ብቻም እንታገዛለን**

እስቲ ከእኔ ጋር አስቡት፣ አንድ የተበደለ ሰው ሁኔታ፣ የተወሰደውን መብት ለማስመለስ ወደ መንግስት መምሪያ የሄደ፣ መብቱን ለመጠየቅ ወደ ሰራተኛው ይገባል፣ እናም ይህ ሰራተኛ ማመልከቻ ጥያቄ እንዲጽፍ እና የገንዘብ ምልክት (ፊርማ) እንዲያደርግበት እና ወደ ኃላፊ ከመድረሱ በፊት የተለመደውን መደበኛ ወረፋ እንዲጠብቅ በመምሪያው ደብዳቤ ውስጥ እንዲያስቀምጥ ይነግሯል፡፡ እናም ኃላፊዉ አንብቦ ውሳኔውን እንዲሰጥ፣ ይህ ውሳኔ ትክክልም ይሁን ስህተት፣ እና ፍትሃዊ ወይም ግፍ…

የዚህን ሰው ጉዳይ ሌላ ዕድለኛ ሰው ጋር ያነፃፅሩ፤ ከላይ ከተጠቀሰው ኃላፊ ጋር በጣም ቅርብ እና ተግባቢ ሰዉየ፡፡ እና ይህ ኃላፊ የተጠየቀው ጉዳይ ላይ የመጀመሪያና የመጨረሻ ዉሳኔዎች የሚወስን ባለስልጣን ነው፡፡ ሰዉየዉ የፍትህ ሰዉ ሀቀኛ፣ በጭራሽ የማይበድል፣ ትክክለኛ እና ብልህ ሰው፣ የማይሳሳት ነዉ።

ሁኔታው እና አጠቃላይ ሁኔታው አሁን እንደሚለወጡ ምንም ጥርጥር የለውም። ሰውየው ወደ ዋናው ጓደኛው በቀጥታ ወደ ጽሕፈት ቤቱ ውስጥ ይገባል፡፡ ለእርሱ ያዉ በተለመደዉ አካሄድ ሳያልፍ፣ ኃላፊዉ ተቀብሎት በአጠገቡ የተቀመጠ ሲሆን፣ የቡና ጽዋ እንዲመጣለት ይጠይቃል፡፡ እናም የጓደኛውን ቅሬታ በጥሞና ያዳምጣል ፡፡

ከዚያም ወዲያዉኑ እስክርቢቶ እና ወረቀት ይሰጠዉና እሱ ራሱ (ኃላፊዉ) የጥያቄውን ቃል አፃፃፍ መግለፅ ይጀምራል ‹እኔ የምነግርዎትን ይፃፉ› ይለዋል፡፡
…እና ፊደሉን ፅፎ እንደጨረሰ፣ ጥያቄውን ከእሱ ወስዶ ጠረጴዛው ላይ ከፊት ለፊቱ በማስቀመጥ ጓደኛውን ይሰናበታል፡፡ ‹አሁን በተረጋጋ ሁኔታ መሄድ ይችላሉ› ይለዋል፣ በጭራሽ ስለ ጥያቄዎ አይጨነቁ .. ሙሉ እና ያልተገደበ መብትዎን ያገኛሉ፡፡

አሏህ .. ማንኛውንም ችግር ለእርስዎ በነፃ የሚፈታ ይህ አስደናቂ “ሸምግልና” ምንድነው፣ እና በእንደዚህ ያለ ልዩ ጉብኝት መዝናናት፣ እና ከቡና ጽዋ ጋርም?!!

(ባንተ ብቻ እንታገዛለን) የሚለዉም ጉዳይም እንደዚሁ የመሰለ ነገር ነው፣ ግን በጭራሽ ማወዳደር አይታሰብም። ለአሏህ ሁል ጊዜ የላቀ እና እጅግ የከበረ ምሳሌያዊነት ነው፣ ታላቁ አሏህ የላቀ እና የከበረ ነዉ።

በተለመደ አኳሆን በመደበኛነት የሚጠየቁ የበታች ባለሙያዎች አይኖሩም፣ በቀጥታ ይፈቅድልዎታል። ይልቁንስ እሱን እንዲያነጋግሩ እና ፍላጎትዎን እንዲጠይቁት ይጠይቅዎታል፣ የሚፈልጉትን ነገር በሚፈልግበት ቀመር እንዲጠይቁት ራሱ በአል-ፋቲሃ መግቢያ ላይ በራሱ ይነግሯዎል ወይም ያዘዎታል፣ እናም ያንን ሁሉ አፃፃፍ በምላስዎ ያኖራዎታል፤ ከዚያ መጨረሻ ላይ የእርሱ አገልጋይ እንደሆኑ እንድያረጋግጡ ያደርግዎታል፡፡ እና እሱ ለእርስዎ ኃላፊነት የሚሰማው እና ፍላጎትዎንና ጥቅምዎን የሚጠብቅ ይሆናል **(አንተን ብቻ እንገዛለን)** ..

**- የአሏህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ አለ፡ “ኃያሉ አሏህ እንዲህ ይላል፡ ሶላት -አል-ፋቲሃ -ማለት ነዉ- በእኔ እና አገልጋዬ በሁለት ግማሽ ተካፍሏል፤ ስለዚህ ግማሹ የእኔ ነው ግማሹም ለባሪያዬ ነው፣ ለአገልጋዬም የጠየቀዉ (ይሰጠዋል)፡፡ ባሪያዉ፡ አሏህን አመስግናለሁ የዓለማት ጌታ ካለ፣ እንዲህ ይላል፡ ባሪያዬ አመሰገነኝ፤ እናም እጅግ በጣም ርህሩህ እጅግ በጣም አዛኝ ካለ፣ ባሪያዬ አወደሰኝ ይላል፤ በፍርድ ቀን ባለቤት ካለ፣ባሪያዬ አከበረኝ ይላል፤ እናም አንተን ብቻ እንገዛለን፤ ባንተ ብቻ እንታገዛለን ካለ፣ እርሱም፡ ይህ በእኔ እና በባሪያዬ መካከል ያለዉ ቃል ኪዳን ነው ባሪያዬም የጠየቀዉን ያገኛል ይላል፤ እናም ቀጥተኛ መንገድ ምረን፣ያ እነዚያን ያበለፀካቸዉ ሰዎች ወደ**

**መረጃቸዉ መንገድ፣ ወደ ተቆጠህባቸዉና የተጣመሙት መንገድ ሳይሆን፤ እናም እሱም ይላል፡ ይህ ለባሪያዬ ነው ባሪያዬ ብሎ የጠየቀዉን (ሁሉ) ያገኛል** *"[በሙስሊም የተዘገበ ከአቡ ሁረይራ (ረዐ))፡፡*

ስለዚህ እኛ አሁን በሱራ መካከል ካለው ጥቅስ ጋር ነን፣ ይልቁኑ የአንቀፁ መሃል የሱራዉ መሃል ነው፣ ወደ አሏህ (የምታመልኩት) የዉዳሴ፣ የአክብሮት፣የአዎንታዊ አቋም ወዘተ የሚያበቃበት ቦታ **(አንተን ብቻ እንገዛለን)፤** እናም ወዲያውኑ፣ በተመሳሳይ አንቀፅ ዉስጥ፣ የዉዳሴ፣ የስለትና የሚፈልጉትን አሏህን የሚጠይቁበት አቋም ይጀምራል፤ በእሱ ውስጥ (እርዳታ የሚፈልጉት) አቋም **(ባንተ ብቻ እንታገዛለን)፡፡**

በዚህ በአንድ ጥቅል በተሰበሰቡት ሁለት የተለያዩ አስደናቂ መልእክቶች በእውነት ነፃነት ይሰማናል፤ በንባባችን ውስጥ የመጀመሪያ አጋማሽ ላይ ለአፍታ ቆም ማለት እንዳለብን ይሰመናል **(አንተን ብቻ እንገዛለን)** ስንል እና ከዚያ በኋላ ወደ ሁለተኛው አጋማሽ **(ባንተ ብቻ እንታገዛለን)** የሚለዉ ጋር ማለት ነው፡፡ ይልቁንም በአሊ ቢን አቢ ጧሊብ (ረ.ዐ) ዘገባ (እንገዛለን/እናመልካለን) የሚል ቃል ሲነበብ "ዋው-ን እስኪያመነጭ ድረስ ዳል-ን በማሟላት" የሚለዉን ይደነግጋል *[የቁርአን ታሪክ። አብዱል ሳቡር ሻሂን. ካይሮ፣ዳር አል-ቀለም፣ 1961 ኢ.ኤ.አ. ገፅ፡ 175]* ፡፡ እና ይህ ነፃነትን ለመገንዘብ እና ከማርዘሚያ በፊት ምን እንደሆነ እና ከዚያ በኋላ ምን እንደሆነ ስብዕናውን ለማረጋገጥ ይረዳናል።

ስለዚህ እነዚህን ሁለት ሀረጎች በሶላትህ ላይ እየደጋገሙ ሳሉ፣በአንድ ጥቅስ ዉስጥ ቢመጡም፣ ሁለት የተለያዩ አቋሞች በፊት ነህ እንዳሉ ተሰማዎት፣ እና የጥቅሱ የመጀመሪያ ክፍል **(አንተን ብቻ እናመልካለን**) የሚነገርበት ዘይቤ እና የሁለተኛው ክፍል ከሚናገርበት ዘይቤ **(ባንተ ብቻ እንታገዛለን)** የተለየ መሆኑን ማለት ነዉ? አሁን፣ ከዚህ አስርት አንፃር፣ የመጀመሪያው የግል ክፍል ወደ ሁለተኛው ክፍል እየተዛወሩ መሆኑን ያስታውሱ፡፡

**(አንተን ብቻ እናመልካለን**) ሲሉ ፣በድምፅዎ ወትዎ እና ዕጣ ፈንታዎ በእጆቹ ፊት ላለዉ ሰዉ አክብሮት፣ ተገዢነት እና አድናቆት፣ ግን ለርስዎ **(ባንተ ብቻ እንታገዛለን)** የድክመት፣ የተስፋ ቃና እና ምልጃ፣ የልመና እና ተስፋ ስሜት ይሰምዎታል፡፡ ግን ያዉ ከተጠያቂዉ (ከዚህ ጠንካራ (ደጋፊ) የምህረት፣ የእፎይታ እና የእርዳታ ምላሽ እንደተሰማዎት፣ እና አሁን እሱ ከፊትዎ እንደሆነና እንዲሰምዎት ያነጋግሩታል፡፡ ያ እሱ ካንተ በተቃራኒ ከሆነ ከእናንተ ጋር ይሆናል ፣ ከእርስዎ ጋር ካለ ደግሞ፣ በተቃራኒ ይሆናል- ቀደምቶች እንደተናገሩት?!

እሱ እሷህ በእሱ እና በባሪያው መካከል የከፋፈለው አንቀፅ ነው ፣ እናም ሁሉን ቻይ የሆነው አሏህ ለአገልጋዩ እጅግ ውብ በሆነ ተስፋ ቃል ገብቶለታል፤ የወጣው ከታማኝ እና ተስፋ ሰጭው አምላክ **(እና ለአገልጋዩ የጠየቀዉ**).፡፡

**(ባንተ ብቻ እንታገዛለን)** የሚለዉን ያንብቡ እናም መልስ ለማግኘት እርግጠኛ ይኑ፤ በሙቅ ቀን ለዝናብ ፍለጋ እንደሄደው የዚያ የባርያ እምነት፣ ግን እሱ ብቻ ፣ ዣንጥላውን ከእጁ ስር ተሸክሞ።

### *ቀጥተኛውን መንገድ ምረን ፡፡ የነዚያን መንገድ ..*

አሁን፣ የምስጋና በሮች ተከፍተውልዎታል፣ ስለሆነም አመስግነዉ ነበር፣ የምህረት በሮችም እና ተባርኮዋል፤የመጠየቅ እድሎችም ጠይቀዋልም፡፡ አንድ ሰው በዚህ ሕይወት ውስጥ ሊጠይቅ የሚችለውን ትልቁን ፀሎት በአለም ጌታ በምላስዎ ላይ ያኖራል፤ ወደ ቀጥተኛ መንገድ መመራት፡፡ እና ከዚህ መንገድ ከመራቅ የበለጠ ለራሳችን የምንፈራው ነገር አለ?

እኛ በጣም ሀብታሞች እንደሆንን አስቡ፣ የመጨረሻ ሀብታም፣ እና እጅግ በጣም ብልሆች የመጨረሻ ብልሃት እና በጣም የተሟላ እና ጤናማ፣ የመጨረሻ ጤናማነት፤ እና ደስተኞች፣ የመጨረሻ ደስተኞች፣ እንደሆንን አስቡ፡፡ ከዚያ የተዉሂድ እና የመቃናት በረከት አላገኘንም እንበል፣ ስለዚህ የዚህና የዚያ ሁሉ ጥቅም ምንድ ነው? የሕይወት ደስታ? ከወዲያኛው አለም የምንከስር ከሆነ የዚህ አለም ደስታ ምንድ ነው? የምን መቶ ዓመት፣ አንድ ሺህ ዓመት ወይም ሚሊዮን ዓመት፣ ከአንድ የዘላለም

ሕይወት ጊዜ ሲነፃፀር አንድ ሺህ ወይም አንድ ሚሊዮን የዓለም ሕይወት ዓመት ምን ዋጋ አለዉ፣ ከጀነቱ ወይስ ከእሳቱ?

وَٱلَّذِينَ كَفَرُوٓاْ أَعۡمَٰلُهُمۡ كَسَرَابِۭ بِقِيعَةٖ يَحۡسَبُهُ ٱلظَّمۡـَٔانُ مَآءً حَتَّىٰٓ إِذَا جَآءَهُۥ لَمۡ يَجِدۡهُ شَيۡـٔٗا وَوَجَدَ ٱللَّهَ عِندَهُۥ فَوَفَّىٰهُ حِسَابَهُۥۗ ﴿٣٩﴾ النور: 39

**- እነዚያም የካዱ *ሥራዎቻቸዉ* በበረሃ ሜዳ እንዳለ ሲራብዱ የመጣ ሰዉ ዉሃ ነዉ ብሎ እንዲስበዉ በመጣዉም ጊዜ ምንም ነገር ሆኖ እንደማያገኘዉ ነዉ፤ አሏህም እራሱ ዘንድ ያገኘዋል፤ ምርምራዉንም ይሞላለታል..**[አን-ኑር 39]

**- በትንሳኤ ቀን ከካህዲዎች የዚህ አለም ቅንጡ ሰዎች ይመጣና ይባላል፡- በሲኦል (እሳት) ውስጥ መንከርን ንከሩት ፣ ከዛም በውስጡ ይነከራል፡፡ ከዚያ ለእሱ ይባላል፡ መቼም ደስታ አግኝተህ ታውቃለህ? እሱ እንዲህ ይላል፡-እኔ ደስታን በጭራሽ አላገኘሁም፣ ከምእመናን  በጣም በተጎዳና በተሰቃየ ይመጣና ይባላል፡-ገነት (ጀነት) ውስጥ ንከሩት አንዴ፤ ከዛም በውስጡ ጥልቀት ይነከራል፡፡ ከዚያ ይባላል: በጭራሽ ጉዳት ወይም ችግር አጋጥሞዎት ያውቃል? እሱ እንዲህ ይላል፡-እኔ በጭራሽ ችግር አጋጥሞኝ አያውቅም፣ ስቃይም፡** [*በኢብኑ ማጃህ የተዘገበ እና በአል-አልባኒ የተረጋገጠ ፣ ከአነስ ቢን ማሊክ*]፡፡

(ባንተ ብቻ እንታገዛለን) የሚለዉን በማንበባችን የሚሰማን ደስታ ወዲያውኑ (*መንገዱን አሳየን*) ከሚለዉ ደስታ የተለየ ነው፡፡ የመጀመሪያው ዓረፍተ ነገር የዓለማዊ ደስታ ጥያቄ ነው፤ ሁለተኛው ደግሞ የኣኺራ ደስታ ጥያቄ ነው፡፡ ይህ ግን ለዓለማዊ ትርጉምም ዕድል ሊያስገኝ ይችላል፡፡ የቀጥታ መንገድ ክፍት ቃል ነው፣ እሱም ለሁለትም ሊሆን ይችላል፤ ወደ ሁሉም ጉዳዮች የመሪ እና የአንድ አሏህ አምላክነት፣ ጥበብ፣ መመሪያ እና የመልካምነት ገጽታ እና የበለጠ የምድር ጸጋ  ምረን የሚለዉን ትርጉም ሊይዝ ይችላል፡፡  አንድ ሰው በሕይወቱ ውስጥ ሊጠቀምበት እና በዙሪያዉ ሌሎችን ሊረዳ የሚችል ጥሩ እና ቀና አእምሮ እንዲኖረዉ ማድረግስ?

ይህቺ በ “አል-ፋቲሃ’’ ውስጥ ያለች (መንገዱ) የምትለዉ የ(ማስከፈቻ) ቃል በእሱ ብቻ የሚትገደብ አይደለችም፣ ግን እስከ ምዕራፉ መጨረሻው ትዘልቃለች፡፡ እነማን

ናቸው (እነዚያ ያበለፅካቸዉ)፣ እነማን (ቁጣ የደረሰባቸዉ) እና እነማን (የተሳሳቱ)? እነሱ በቅደም ተከተል ሙስሊሞች፣ ከዚያ አይሁዶች፣ ከዚያ ክርስትያኖች ናቸው፣ ብዙ ተንታኞች እንደሚሉት እና በአንዳንድ ቅዱስ ሐዲስ እንደተገለፀው፡

**-..(ቁጣ የደረሰባቸዉ) አይሁዶች፣ እና (የተሳሳቱ) ክርስትያኖች** ናቸዉ *(አልባኒ አረጋግጦታል በትክክለኛዉ ተከታታይ ሀዲሱ ዉስጥ፣ ከአዲይ ኢብን ሃትም አጥ-ጧኢ፣ ከአቢ ዘር-አል-ግፋሪይ)፡፡*

ሦስቱም አገላለጾች በቋንቋ ህግጋቶች የተቃኙ ናቸው፡፡ እና ከእነሱ በኋላ ምንም ዓይነት መላምታዊ የቋንቋ ቦታዎችን የለዉም፣ ግን ከእሱ ጋር ከሚዛመዱ ከሌሎች አገላለጾች ጋር ካነፃፀርናቸው፣ በርግጥም ለሦስቱ የቁርአን መግለጫዎች ግልጽነት እና እውነታን እንታዘባለኝ፡፡

የተገነዘቡትን የቁርአን አንቀፅን እንደ አዲስ በአማራጭ በ"ዝግ" መግለጫዎች በመተካት ከእኔ ጋር ያንብቡና ልዩነቱ በሁለቱ መግለጫዎች ዘዴዎች መካከል ግልፅ ሆኖ የሚታይ ይሆናል፡
-ቀጥተኛውን መንገድ ምረን፣ የሙስሊሞች መንገድ፣ የአይሁድ ወይም ክርስትያን ያልሆነዉን መንደግ፡፡

ግልፅ እና ክፍቱ የቁርአን አገላለፅ ምን ያህል "ሰፊ" እንደሆነ አሳይተዋል? **(እነዚያ አንተ የባረካቸው)** ለሚለዉ ትርጉሙን "የሚከፍተው" ለበለፀጉ ሁሉ እና **(በእነሱ ላይ ለተቆጣው)** ለሚለዉ ትርጉም ደግሞ አሏህ ለተቆጣቸዉ ሁሉ፣ እና **(የተሳሳቱ)** ለሚለዉ ቃል ትርጉም ከትክክለኛው መንገድ ለባዘነ ሁሉ ነው? ደግሞ ይህ ትንቢታዊ ትርጉሙን ሳይሰርዝ ነዉ፤ ሆኖም ግን ሦስቱን አገላለጾች "ሳይዘጋ" እና በተወሰኑ ምድቦች ውስጥ ብቻ ሳይገደብ፤ በሰዋዊ አገላለፆች ውስጥ እንዳደረግነው ይሆናልን?

በጣም አስፈላጊ ነገር፣ **(ቀጥተኛውን መንገድ አሳየን)** የሚለዉን ጥቅስ ስናነብ፣ ማስታወስ ያለብን እሷ ክፍት ሆኗ የመጠችዉ ለመለኮታዊ ጥበብ መሆኑን ነዉ፤ በሶላታችን ውስጥ ካሉት በርካታ መግለጫዎች እና ሌሎች ግልጽ አገላለጾች መካከል ማለት ነዉ፡፡ በምድር ላይ ያሉትን ፍጥረታት ሁሉ እንዲያካትት ሶላቱን ክፍት አድርገን

ለማጥበብ እና ሁሉም አንባቢያን (እኔ) የሚለዉ ስሜት እንዲኖረዉ ማድረግ ይቻላል፡ ፡ በርግጥ እሷ በተናጥል አልመጣችም፣ ይልቁንም በብዙ ቁጥር መልክ ነበር (እህዲና-ምረን) ተብላ የመጣች። የቻሉትን ያህል ይሞክሩ፣ እናም ይህንን ተገንዝበዋል ማለት ይቻላል (እውነታው ግን በጸሎቶቻችሁ ልጆቻችሁን፣ ወላጆቻችሁን፣ ዘመዶቻችሁን እና ጎረቤቶቻችሁን ጨምሮ በዙሪያዎ ያሉትን ሁሉ በግብዣዎ ውስጥ ያካትቱ) ማለት ነዉ፡፡ ይልቁንም ጸሎትዎ ወዳጅ እና ጠላቶችን፣ ሙስሊሞችን እና ሙስሊም ያልሆኑትን ጨምሮ መላውን ዓለም ያካተተ ሲሆን፣ ሙስሊሞችን፣ እናም ጓደኞችዎን እና ጠላቶችዎን እንዲባርክ፣ ወደ ቀጥተኛ መንገድ፣ እውነትና ፍትህ መንገድ እዲመራቸዉ አሏህን ከመጠየቅ የበለጠ አስደናቂ፣ የበለጠ ውድ እና የላቀ ነገር አለን?

ያስታውሱ፣ የስም ምትክ (እኔ) መሰናከሎች መሰባበርዎ፣ ሁሉንም ሰው የሚጠቃልል መሆኑን ያስታውሱ፣ ለሁሉም ያለ ምንም ልዩነት፣ እሱ በአንተ እና በሌላው መካከል የጥላቻ እና የጥላቻ አጥርን መሰባበር እንደ ማለት ነዉ፡፡ ማለትም ቀጣይነት ያለው ማስታወቂያ፣ የዲዛይን እና የሥልጠና ልምምድ ሲሆን ያለማቋረጥ በልብዎ ውስጥ ከፍ የሚያደርጉት የፍቅር እና የመቻቻል ራዕይን ነዉ፤ የጥላቻን ዓላማ ያለማቋረጥ ከፍ ከሚያደርጉት በተቃራኒ፡፡ እነዚህ ሰዎች ልጆቻቸውን  ጡት በማጥባት ጎን ለጎን መጥላትና ምቀኝነትን ያስተምራሉ፡፡ ሙስሊሞች መሆን ከፈለጉ፡ ይህንን ወርቃማ ሕግ ያስታውሱ-እርስዎ ሙስሊም ነዎት፣ ያኔ አፍቃሪ እና ይቅር ባይ ነህ፡

خُذِ ٱلۡعَفۡوَ وَأۡمُرۡ بِٱلۡعُرۡفِ وَأَعۡرِضۡ عَنِ ٱلۡجَٰهِلِينَ ﴿١٩٩﴾ الأعراف: 199

**- ይቅርታን ይውሰዱ፣ በመልካም ይዘዙ፣ እና ካላዋቂዎች ይራቁ** *[አል-አዕራፍ: 199]*

فَمَنۡ عَفَا وَأَصۡلَحَ فَأَجۡرُهُۥ عَلَى ٱللَّهِۚ ﴿٤٠﴾ الشورى: 40

**- ስለዚህ ይቅር የሚልና ጻድቅ የሆነ ሰው፣ ምንዳዉ በአላህ ዘንድ ነዉ** *[አሹ-ሹራ፡ 40]*

وَإِن تَعۡفُواْ وَتَصۡفَحُواْ وَتَغۡفِرُواْ فَإِنَّ ٱللَّهَ غَفُورٞ رَّحِيمٌ ﴿١٤﴾ التغابن: 14

**- ይቅር ብትሉ፣ ልባችሁን ብታነፁ፣ ብትምሩ፤ አላህ መሓሪ አዛኝ ነውና**

*[አት-ተጋቡን፡ 14]*

**በአል-ፋቲሃ ምዕራፍ ዉስጥ የማራዘሚያ ቦታዎች**

እርዝማኔ በጊዜ ውስጥ ትንሽ ቆም ማለትን የሚመሳሰል ከሆነ፣ ለሆነ ቃል ወይም ሐረግ በዚህ በተጨማሪ እስትንፋስ፣ ልዩ ማንነቷን መስጠት ተፈጥሮ ነዉ፤ ጠንካራ ኃይልና እና ነፃነቷንም፡፡ ይህ የጊዜ ርቀቱ ከላይ እንደገለፅነው፣ ለማስተንተን ወርቃማ ተጨማሪ ጊዜን ለማስገኘትና የሚረዝመዉ ፊደል የሚገኝበት ሐረግን ትርጉም ለማንፀባረቅ ነዉ ማለት ነው፡፡

እዚህ ላይ በንባብ ላይ “በሙሉ ማቆም”ን፤ እና ከ "ማርዘም" መለየት አለብን፣ ይህ ልዩ የማቆም ዓይነት ወይም "ሊቆም የተቃረበ" አይነት ማራዘሚያ ስለሆነ፡፡ መልእክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) አል-ፋቲሃን ከመጀመራቸው በፊት፣ ከዚያም ፋቲሃን ካነበቡ በኋላ ሙሉ በሙሉ ያቆሙ ነበር፡ በተጨማሪም በእያንዳንዱ ንባብ መጨረሻ ላይ ሙሉ በሙሉ ይቆማል፣ እናም ይህ ማለት እያንዳንዱን ንባብ የሚለያይ ሌላ አረንጓዴ (ክፍት) ቦታ ማለት ነው። ስለ ማራዘሚያ ማቆሚያዎች ደግሞ፣ ወይም ይልቁንም ከፊል ማቆሚያዎች ጋር በተያያዘ፣ ማራዘሚያዉ አንባቢያንን ለበለጠ ኹሹዕ፣ እርጋታ እንዲሁም ሙሉ ኒያህ የሚያነሳሳ፣ በበቂ ሁኔታ ለማስተንተንና እና ለቀጣይ ትርጉም አቀባበል እንዲዘጋጁ ያደርግዎታል፡፡ በሃያ ዘጠኙ የአል-ፋቲሃ ቃላታ ዉስጥ ከሃያ አንድ ያላነሱ የቃል ማራዘሚዎች እንዲሁም በመጨረሻ አንቀፆች/ጥቅሶች አከባቢ ትናንሽ ማቆሚያዎችን ቆጥራለሁኝ፤ ያዉም ሰባት ቦታ፡፡ እንደዚህ አይነት ጠንካራና ትኩረት የሚፈልግ ማራዘሚያ በአል-ፋቲሃ ዉስጥ በቀር በተለመደው የንግግር ወይም የጽሑፍ ቋንቋችን እንብዛም አያገኙትም፡፡ በአብዛኞቹ ሌሎች ምዕራፎች ውስጥም አያገኙትም፡፡

ይህ በአል-ፋቲሃ ውስጥ የተከታታይ ማራዘሚያ ፊደል፣ ከብዙ ጊዜ የድምፅ-አወጣጥ (ተጅዊድ) ደንቦች በተቃራኒ፣ በአል-ፋቲሃ ላይ ልዩ አነባበብ ይኖሯል፤ ከመመሪያዉ አጠቃቀም አንፃርም ቢታይ እንኳን፡፡ ይህ ሲጋጁ በሚሰግደው ወቅት በማሰላሰል፣ በመታዘዝ፣ በመገዛት እና በመተናነስ ላይ በቂ ጊዜ አግኝቶ በልዑሉ ፈጣሪዉ ፊት እንዲቆም ያደርጓል፡፡

ለምሳሌ ያህል፣ በሁለት የቅዱስ ቁርአን አጭር ምዕራፎች ውስጥ ማራዘሚያዎችን (አል-ካውሠር) እና (አል-ኢኽላስ) ዉስጥ፣ በመጀመሪያዉ ከአሥሩ የሱራ ቃላት ሶስት ማራዘሚያዎች፣ እንደማይበልጥ እንገነዘባለን፣ ይቺም በ (እኛ-ሰጥተንዎታል-ጠላትህ)

ቃላት ውስጥ ነዉ፡፡ እና ሁለተኛዉ ውስጥ ከአራት ማራዘሚዎች አይበልጥም- -ከአስራ አምስት የምዕራፉ ቃላት ውስጥ (አሏህ- አምላክ- አይወለድም-ለእሱ )፡፡

እዚህ አጥብቄ ማሳሰብ ያለብኝ ነገር፣ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ያሉት ሀሳቦች እና ትንታኔዎች ሁሉ፣ "የሰው ሀሳቦች"ን የያዙ በመሆናቸው በእውነቱ ለስህተት እና ለመከለስ የተጋለጡ ናቸዉ፡፡ ትክክለኛዉ ማስረጃ እነዚህን ሀሳቦች የሚቃረን ሆኖ ከተገኘ፣ እኛ ሙስሊሞ ሁል ጊዜ ከማስረጃ እና ከጽሑፉ ጋር ስለሆንን መስተካከል ያለበት ጉዳይ ይናል፡፡

## የሩኩዕ እና የሱጁድ ማዕከላዊነት

ለመጀመሪያ ጊዜ ሀጅ ስያከናዉን አርባ አመት ሲሞላኝ፣ ከዕባ ዙሪያ ትንሽ ልጅ መስዬ እየሮጥኩ ስሄድ እራሴን አገኘሁ፡፡እና ሁለት ቀላል የጨርቅ ቁርጥራጮች በሰውነቴ ላይ ጣል አደረኩ፡፡ እዚያ ነዉ፣ ሸይጣ በራሴ ላይ ሹክሹክታ የጀመረዉ፡ በዩኒቨርሲቲ ውስጥ ያሉ ሙስሊምና ሙስሊም ያልሆኑት ተማሪዎችዎ ጨምሮ በዚህ ሁኔታ ቢያሳዩዎትስ? እንዲህ ይላሉ፡ መምህራችን ምን ሆኑ፣ ይሄ ነዉ እንዴ በመተናነሱ፣ በራስ መተማመኑ፣ እራስን ዝቅ በማድረጉና በእንቅስቃሴው ከእኛ በፊት የሚታየው፣ ይህ ነውን? የሚሉ ተመሰለብኝ፡፡ ግን ወዲዉኑ በአሏህ ቸርነት፣ የእምነት መንፈስ እና የንጹህ አገልጋይነት ባህሪ ቶሎ ቶሎ በኔ ላይ ነፈሰ። የእነዚህን ሹክሹክታ እሳት ለማጥፋት እና ሙስሊም እንደሆንኩ ለማስታወስ ቻልኩ።

እኔ ሙስሊም ነኝ፣ ትርጉሙ ተገዥ ነኝ፣ ማለትም ለአሏህ የተዋረድኩ ወይም ደካማ እና ባሪያ ነኝ፣ ወይም ይልቁንም ያ ሰማያትንና ምድርን የፈጠረ፣ ሕይወትንና ሞትን የሚሰጥ፣ ከሁሉ በላይ የሆነ ኃያል፣ እና ሁሉ ነገር ላይ ቻይ አምላክ ፊት ምንም የለም፡፡

እነዚህ ከፍ ያሉ መንፈሳዊ ምልክቶች በማንኛውም አምልኮ እራሴን ለአሏህ ባዋረድኩኝ ጊዜ ይመጡብኝ ነበር፣ እራሴን ዝቅ አድርጌ ስጸልይ፣ ስሰግድ፣ ስያጥራዉ **(ለታላቁ ለጌታዬ ክብር ይሁን)** ስል፣ከሁሉም ድክመት፣ ኢፍትሃዊነት፣ እጦት፣ ድካም፣ ቸልተኝነት እና ወዘተ... ከዚያ ከሩኩዕ ከፍ እንዳልኩና ያ መለኮታዊውንና ወርቃማ መመሪያዉን ስያስታወስ **(የሚያመሰግነዉን ሰዉ አሏህ ይሰመዋል)** ስል፣ መልሼ እሱን

ስያመሰግን **(ጌታችን ሆይ ምስጋና ለአንተ ይሁን)** ብዬ፣እሱ ስለ ፈጠረን፣ ስላቀናኝ፣ ስለሰጠኝ፣ ወዘተ…፣

ከዚያ እንደገና እሱን ለማመስገን በእያንዳንዱ ሱጁድ ላይ ለመስገድ ስል **(ክብር ለልዑል ለጌታዬ ይሁን)** ብዬ እሱን ከ…አጠረዋለሁ፣ አነፀዋለሁ…እንደዚህ ነዉ እያሰብኩ ያደርኩትኝ፤ በወሬም በተግባርም፣ ስለዚህ እፀልያለሁ እናም ጭንቅላቴ በምድር ካለው ከአሏህ የበለጠ ዝቅ ያለ ነው፣ እኔ እዚያ ሰማይ ላይ ካሉት ወደሱ በጣም ቅርብ ሆኜ፡

**- ከአምላክ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ባሪያ ከሶዉባን ጋር ተገናኘን፣ ስለዚህ አልኩ፡- ተግብሬ አሏህ ወደ ጀነት የሚያስገባኝ ተግባር ንገረኝ፣ ወይም አልኩኝ አለ፡ በአሏህ ዘንድ እጅግ በጣም ተወዳጅ ተግባራት፣ ዝም አለ፡፡ ከዛም ጠየቅኩኝ እና ዝም አለ፡ ከዚያም ሦስተኛውን ስጠይቀው እርሱም እንዲህ አለ፡ ስለዚህ ጉዳይ የአሏህን መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ጠየኩኝና እንዲህም ብሏል አለ፡‹ለአሏህ ብዙ ስግደት (ሱጁድ) ማድረግ አለብህ፣ አንተ አንድ ሱጁድ ለአሏህ አትወርድም አሏህ በዚያች ደረጃህን ከፍ ቢያደርግ፣ በሷ ሐጢአትህን ቢያራግፍልህ እንጂ አይቀርም…)** *[በሁለቱ ሼይኮች በመአዳን ቢን ጣልሃ የዘገበዉ]*

ከሰጋጆቹ መካከል በሶላቱ ወቅት ግን በረከዓና ረከዓ፣በሱጁድና ሱጁድ መካከል የሚሰርቅ ሰው አስበው ያውቃሉ? ከዚህ አይነቱ ሌባ አስገራሚ ነገር ቢኖር፣ እነሱ ከሌላ ሰዉ የማይሰረቁ መሆኑ ነው ከራሳቸው እንጂ፡

**- መጠጥ የሚጠጣ፣ ዝሙተኛ እና በሌባው ውስጥ ምን ያያሉ? ያ ቅጣቱ በእነሱ ላይ ከመውረድ በፊት ነው ፣ እነሱም አሉ፡-አሏህ እና የአላህ መልእክተኛም (ሰ.ዐ.ወ) የበለጠ ያውቃሉ፡፡ እንዲህ አለ፡-እነሱ እርኩሶች ናቸዉ፤ ቅጣትም አላቸው፤ በጣም መጥፎ ስርቆት ደግሞ ሶላቱን የሚሰርቅ ሰው ነው፡፡ እነሱም አሉ፡ እንዴት ሶላቱን ይሰርቃል? እንዲህ አለ፡ ሩኩዑንም ሆኖ ሱጁዱን የማያሟላ** *[አልባኒ በሳሂህ መደቡት፣ አት-ተርግሂብ ሶሂህ ዉስጥ፣ ከኑኡማን ኢብን ሙራ]*

ለምን አይሆንም? ሶላት ከአሏህ እንደ ስጦታ አልወረደልንም፣ እና በየቀኑ ወደ እኛ የሚዘዋወርበት "የጊዜ ሰሌዳ" በየቀኑ በጊዜያት የተወሰኑ ተግባራትን ያቀፈ፣ ከአሏህ ምንዳ የሚገኝልን፣ ወደ ኣኼራ ድምራችን ላይ የሚጨምርልን ተግባር አይደለምን?
ሆኖም ግን፣ ሶላት ዛሬ በብዙዎቻችን ዘንድ ማዘናጊያ እና ጊዜን ለማባከን መሳሪያ ሆኗል፡፡ ዘሬ እነሱ ዘንድ ከመብት ወደ ግዴታነት፣ አካላትን ባስቸኳይ ማንቀሳቀስ ብቻ፣ ከንፈሮችን በፍጥነት ማንቀሳቀስ ብቻ፣ ባስቸኳይ ወደ ማጠናቀቂያ/መጨረሻ መድረስ ብቻ ሆኖዋል፡

**ሶላቱ ከሶስት ሶስተኛ ነው የተዋቀረችዉ፣ ንፅህና አንድ ሶስተኛ ነው፣ ሩኩዕ አንድ ሶስተኛው ነው፣ ሱጁድ አንድ ሶስተኛው ነው፣ ስለዚህ በመላ መሥፈርቷ የሰገደ ሰዉ፣ ከሱ ይቀበላል እናም የተቀሩት ተግባራቶቹም ተቀባይነት ያገኛሉ፤ ሶላቱ የተመለሰበት ሰው፣ የተቀሩት ተግባራቶቹም ወደ እርሱ ይመለሳሉ** *[አል-አልባኒ አረጋግጦታል፣ በሳሂህ አል-ተርጊብ ውስጥ፣ በአቡ ሁረይራ ዘገባ]*

አሏህ... ለሩኩዕ አንድ ሶስተኛ፣ እና ለሱጁድ አንድ ሶስተኛ ከሆነ፣ ታዲያ ያኔ ለሌሎች ምን ቀረ?!

በሶላት ዉስጥ በእኛ ላይ ግዳጅ የሆኑት ሁለቱ እንቅስቃሴዎች ሩኩዕ እና ሱጁድ ብቻ መሆናቸውን አስተውለናልን? እኛ ከሁለቱ እንቅስቃሴዎች ዝም ብለን በመቆም እንጀምራለን፤ ዝም ብለን በመቀመጥ እንጨርሰዋለን፤ በሁለቱ አኳሆን ከመስገድ በቀር በሁለቱ ቋሚ ቦታዎች መካከል ምንም ነገር እይኖረንም፡፡

እናም፣በሁለቱ መካከል "እንቅስቃሴው" ከ "ዝምታ" ጋር እንደሚገናኝ በትኩረት አስተውለናልን? እያንዳንዱ እንቅስቃሴያችን መጠበቅን፣ ማስተንተንን፣ ለአፍታ ማቆምን፣ ዝምታን እና ማሰብን የሚጠይቅ ወይም ማሰብ ጋር የታጀበ ነው፣
-እኛ ደጋግመን **(አሏህ ታላቅ ነው)** እንላለን፣ እና ክፍት የመሆን ፀባዩ ትንሽ ዝም ማለት እና ማስተንተን ነዉ-አሏህ ታላቅ ነው፣ ከማን?

-እኛም እንደግመዋለን **(አሏህ የሚያመሰግነውን ሰው ሰማ)፣** ከዚያ (ጌታችን፣ ለአንተ ምስጋና ይሁን)፣ እና የነዚህም ፀባይ እንዲሁ ትንሽ ዝምታ እና ማሰብን ይጠይቃል ማለት ነው፡፡ ስለምን እናመሰግነዋለን?
-እኛ ደግሞ **(ክብር ለታላቁ ለጌታዬ ይሁን)** እና (ክብር ለጌታዬ ልዑል ይሁን) እናደጋግማለን፣ እናም የእነሱ የዝምታ ፀባይ ትንሽ ዝምታ እና ማሰብን ይጠይቃል- ለምንድነው የሚያመሰግነዉ፣ ወይም ከምንድነው የምናጠራዉ?

ከዚህ በመነሳት ከሶላት (ከፀሎት) የሩኩዕና የስጁድ ድርሻ ሁለት ሦስተኛ ነበር፡፡ እስቲ ያስቡ፣ ምን አይነት ነገር ብይዙ ነዉ የአሏህን ታላቅነት እና ኃልነት ለመጥቀስ ሊረዳ የሚችለዉ፣ በተለይ **(ክብር ለታላቁ ለጌታዬ ይሁን)** ወይም **(ክብር ለእርሱ ለጌታዬ ልዑል ይሁን)** በለዉ በደጋገሙት ቁጥር?
-የተወሰኑትን ውዳሴዎችዎን፣ እንዲያዉም ሁሉንም ሶላቶችዎን የአምልኮ ተግባር ያድርጉ፣ እና እነሱን ልማድ አያድርጓቸው።
-እና **(አሏህ ታላቅ ነው)** ሲሉ፣ የእርስዎ ዕድል (ታጋሽ ለመሆን) ከሆነ፣ ከዚያ በህይወት ውስጥ በሚገጥሙዎት ነገሮችና ችግሮች ሁሉ ጋር ለመጋፈጥ ጥንካሬ እና ኃይል ይሰጥዎታል፣ **(ለዓለማት ጌታ ለአሏህ ምስጋና ይሁን)** እና **(ጌታችን ላንተም ምስጋና)** ሲሉ፣ የእርስዎ እድል (የማስታወስ) እና (ምስጋና) ነዉ የሚሆነዉ፡፡ የአሏህን ጸጋ እና ሞገስ ለማምጣት፣
-**(ክብር ለታላቁ ለጌታዬ)** እና **(ክብር ለላቀው ልዑል ለጌታዬ)** ዉስጥ የርስዎ ዕድል (ለማሰላሰል) እና (ማስተንተን) በአሏህ ታላቅነት፣ በእርሱ ፍጥረት እና የፈጠራ ችሎታ ማለት ነዉ።

ለዓለም እና ለመጪው ዓለም በሶላትህ ላይ ኢንቬስት አድርግ፣ ሱጁድ ሲወርዱ አንደበታቸዉ ከሚያወድሱ ሰዎች መካከል ሁን፡፡ መላ አካሎቻቸዉ፣ አእምሯቸው፣ ልባቸው እና ነፍሳቸው አብሯቸው የሚሰግዱ እና የሚያመሰግኑ ይሆናሉ፡፡

## ቀዩ ቁልፍ 3: ሰላምታ ለአሏህ..

አሏህን ራሱ ሰላም ነዉ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ሙሉ በሙሉ ተገንዝበዋል? እሱ በዙፋኑ ላይ ተደላድሎ ሳለ ወደ እርስዎ ይመለከታል፣ እርስዎ ከፊቱ ተቀምጠዉ እያለ

ለእሱ የመናገር ዋጋውን ተረድቶዋልን? እዚያ ማለቂያ በሌለው የጠፈር ሥፍራ ወይም ዛፍ ዘንድ፣ የመጠለያ የሆነችዉ ጀነት ጋር? ሰላም እለሃሁ አሏህ ሆይ? ስሉ፡፡

ከዚህ በፊት ያቋረጡት እርምጃዎች፣ እነዚህን ተላላቅ አጋጣመሚዎች እንዲያሸንፉ ለማገዝ ነዉ እንጂ ለሌላ ጉዳይ አልነበሩም፡፡ እና እነዚህን ርቀቶች ሁሉ በርስዎ ሊያቋርጡ የሚችሉ በቂ መንፈሳዊ ስንቆች፣በመጨረሻም ለሌለው ለእንዲህ ዓይነቱ ያልተለመደ አቀማመጥ እና ወይም ማለቂያ የሌላቸው ልዩ የሆነው ሽልማት ለማስገኘት ነዉ እንጂ-አሏህን በማሰላመትዎ ብቻ፡፡

በወቅቱ በሁሉም ልኬቶች የምትኖር ከሆነ ራስህን የምታገኝበት እና አሏህም ሰላምታ እንደሚሰጡዎት የሚሰማዎት ሁኔታ እንዴት ያለ ታላቅ ሁኔታ ነው! እርስዎ አሏህን ያነጋገሩበት ቅፅበት- አቤቱ አምላኬ: እሰላማተሃለሁ፣ ብለዉ፡፡
እንደዚህ አይነት በስልክ መስመር እና በቀጥታ በአየር ላይ ያለ አማላጅ ወይም አስታራቂ ሳያስፈልግ ?! እናም አሏህ እጅግ የላቀ እና እጅግ የከበረ ነው ...

ምንም እንኳን ይህ ክብር በር ላይ እራስዎን የሚጠብቅ ታላቅ ልግስና ያልተከተለ ቢሆንም፣ በርግጥ የሚሆን ነው ፣ ግንኙነቱ በራሱ ፣በእውነቱ የግንኙነቱ ደስታ ከተሰማዎት፣ ከእርካታ በኋላ እርካታ የሚመጣ፣ ከደስታ እና ሽልማት በኋላ የማይቆም ሽልማት ነው።

እኛ ከ‘‘ሰላምታ’’ በሚለው ጸሎት በፊት ከአራት ታላላቅ ሰላምታዎች ዉዳሴዎች ውስጥ ነን፣ አንድ የተለየ ሰላምታ አይደለም፡፡ ከነዚህ በመጀመሪያ በእጅግ ልዩ እና አስደሳች ሰላምታ ታላቁን ፈጣሪያችንን ፊት ለፊት እናገኛዋለን **(ሰላምታ ለአሏህ)፡፡** ከዚያ በኋላ ከክቡር መልዕክተኛው (ሶ.ዐ.ወ) ጋር ነን ፣ እና በቀጥታ የሚከተለውን ጥሩ መዓዛ ያለው የሰላምታ ስብስብ ለመካከላቸው እንልካለን **(ሰላም በእናንተ ላይ ይሁን፣ ነቢዩ ሆይ!)** ፣ እና ከዚያ ሰላምታ በኋላ ብቻ ታላቁ ሽልማት መቀበል እንጀምራለን (ከዚህ አስደናቂ እቅፍ (ሰላም በላያችን ይሁን)) ስንል፤ ለሦስተኛው ሰላምታ እራሳችንን ስንቀበል ማለት ነው ፡፡ እናም ይህ ሁሉ አራተኛ የሰላምታችንን ቅዱስ ጉዞ ከማጠናቀቃችን **(የአሏህ አገልጋዮች ላይም)** ከሚለዉ በፊት ነዉ፡፡

በእነዚህ አራቱ ሰላምታዎች መካከል በርካታ “አረንጓዴ ቦታዎች” አድገዋል፣ በቀደም እንዳየነዉ በሶላት ዉስጥ ይህ በጣም አስፈላጊ የቋንቋ አካል ነው።
ይህ ሁኔታ የሰላምታን ምህዳር ለማስፋት ከፍተኛ ሚና ይጫወታል፤ ክፍት ቦታዎችን በመዝጋት ለምለም የቋንቋ ቦታዎችን በመክፈት ሰፋፊ ርቀቶች በለጓዝ ያስችለናል፡፡ በዚህም የቀደመውን አስቸጋሪ ትርጉም በመረዳት ኑፋቄዎቹን እና ቀስቃሾቹን በማስወገድ የሚስተካከል ትርጉም ነዉ፡፡

ለምሳሌ፣ (ሰላምታ) የሚል ጸሎት በፈጣን፣ በተከታታይ እና ከሞላ ጎደል ከትክክለኛ የቋንቋ ምት እንደመጣ እናስብ፡፡ ሰላምታ ለአሏህ፣ ሰላም ለነቢዩ እና በእኛ ላይ ይሁን፣ በጻድቃንም ላይ..

.. ወይም ምንአልባትም እንደዚህ ባለው በፈጣን ቀመር፣ሰላምታዎች ለአሏህ፣ ለመልእክተኛው፣ ለእኛ እና ለፃድቃን..

ሁለቱ የተጠቆሙ ፈጣን ቀመሮች ከትርጉሙ ምንም ነገር እንደማያወጡ ልብ ይበሉ፣ ግን፣ በመጀመሪያው ጽሑፉ ላይ እንደተገለጸው ብዙ የትርጉሙ ልኬቶች እና ልዩነቶች አጥተዋል፡፡

የእኛ የአጭር ጊዜ ዘዴ አምላካችን አሏህን ካሰላመትን በኋላ ለሰጋጁ በቂ የጊዜና ቦታ አይሰጥም፡ **(ሰላምታ ለአሏህ)-** የዚህ ያልተለመደ ሁኔታ ደስታ እንዲስተናገድ እና አስፈላጊነቱ እና ታላቅነቱ እንድንገነዘብ በቂ ጊዜ ይኖረናል፡፡ በሰላምታ፣ ስለዚህ፣ የምህረቱ እና የበረከቱ ስሜት እንዲሰማን ፣ በዚህ ፈጣን ምላሽ፣ የኃያሉ አምላክ በረከት በኛ ላይ ወርዶ ከራስ አናት ጀምሮ የእግሮቻችን ጫማ ድረስ እስኪያጥበን ማድረግ ማለት ነዉ፡፡ በርግጥ አሏህ ያሸዉ፣ የአማኙ ሰላምታ በሶላቱ ውስጥ ረዥም፣ ባዶ አረንጓዴ (ክፍት) ቦታ፣ ፍሬያማ፣ ወደ አንድ ወይም ሁለት አቅጣጫዎች የሚዘልቅ፣ የመጨረሻ ቃላቶች እንዲራዘሙና ዳኅስ ያሉ ትሩፋቶች እንዲገኙ ታሳቢ የተደረገ ነዉ፡፡

**(ሰላምታ...ለአሏህ...እና ሰላምታዎቱም...መልካም ነገሮቱ ... ጥራቶቹ... በረከቶቹ ...)**
እዚህ ያስታውሱ፡ ትንሹን ልጅዎን ከወንድምዎ ጋር ተመሳሳይ በሆነ አነጋገር ሰላምታ ያቀርቡልዎታል? የወንድምዎ ሰላምታ ከአለቃዎ ሰላምታ ጋር ተመሳሳይ በሆነ አጠያየቅ ጋር ተመሳሳይ ነዉን? ለአስተዳዳሪዎ ሰላምታ በሚሰጡበት ተመሳሳይ መንገድ ነዉ ለሚንስቴርዎ የሚሰጡት? ለሚንስቴርዎ እንደ ንጉስዎ ወይም እንደ ርዕሰ ብሔርዎ አይነት ቃና ያለዉን ሰላምታ ነዉ የሚሰጡት? ስለዚህ፣ እነዚህን "ሰላምታ" በመስጠት እራስዎን ይጠይቁ፡ የእኔ አነጋገር እንዴት ይሆናል፣ የነገሥታት ንጉስ እና የጌቶች ጌታን ሰላምታ ስሰጥ?

ይህ ለሚቀጥለው ሰላምታ በተወሰነ ደረጃ ተፈጻሚ ይሆናል፣ አሁን ለክቡሩ መልእክተኛው ለቃረብነው (ሰ.ዐ.ወ)፡ **ሰላም ባንተ ላይ ይን ነቢዩ ሆይ** ..

ከፍጥረተ-ዓለም አሏህ ዘንድ እና እኛም ጋር በጣም በሚወደደው ላይ ሰላምን ሲያቀርቡ፣ ሁለት ደስታ ይሰማዎታል፡ እና በጭራሽ አንዳቸዉም አያበላሹ፤ ይህንን አቋም ላለመሳት እስኪደስቱና እስኪጠቀሙ ድረስ ለራስዎ በቂ ጊዜ ይስጡ፡-
1- ለአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ፊት ለፊትህ እንዳለ ሆኖ ከሚታቀርበዉ የሰላምታ ደስታ፣ በጌታዎ ላይ ሰላምታ ሲሰጡት እንደሰማዎት እርግጠኛ በሆነው ደስታና ከእርስዎ በፊት እንደ ሆነ ሲያስቡ፣
2- ለእርስዎ የሚሰጠዉን ምላሽ በሚያስደስት ሁኔታ ሲሰማዎት፣ በተለይም አሏህ ወደ እሱ ሕይወት እንዲመልስለትና ሰላምታዎን እንደሚመልስ ሲያስቡ፡

- ***ማንም ግለሰብ በእኔ ላይ ሲያሰላምት አሏህ ወደ እኔ ነፍሴን እስከመለሰና ሰላምታዉን ስመልስ እንጂ አይቀርም፡*** *[ኢብን ተይሚያህ መጅሙአ አል-ፈትዋ ዉስጥ ዘግቦታል፣ እና አል-ነወዊም፣ ከአቡ ሁረይራ]*

ግን ከዚህ የበለጠ አስገራሚ፣ ብልሃት እና የበለጠ አስደሳች ነገር፣ ሁሉን ቻይ የሆነው አሏህ ይህንን ለጋስ ምላሽ ከነቢዩ እንደሚጋራ ማወቅ እና እራሱ ላይ እንደሚመልስ ማወቅ ነው፡፡ ያዉ ነብዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) ላይ ሰላምታን፣ጸሎቶችን እንዲሁም

በረከቶችን ካወረዱ አሏህም ምላሽ የሚሰጥዎት መሆኑን እንደሚያረጋግጥልን ከሐዲስ አል-ቁድሲይ መረዳት ይቻላል፡

***-በአርብ ቀን ሶላትዎን ያብዙ፣ ምክንያቱም አሁን ጅብሪል ሁሉን ቻይ ከሆነው ከአምላክ (ከአሏህ)፣ መጥቶብኝ (እንዲህ)አለኝ፡ ማንኛዉም በምድር ላይ ያለ ሙስሊም ‹በጁምዓ ቀኑአንድ ጊዜ ሲሰላመትህ›፣ እኔና መላእክቶቼ አሥሬ ሳንሰላመተዉ አንቀርም›*** *[አልባኒ በ ሶሂህ አት-ተርጊብ አረጋግጦታል፣ ከአነስ ኢብን ማሊክ]*

አሏህ .. ምን አይነት ሰላም! እና ምን አይነት ሶላት ! እና ምን ዓይነት ሽልማት ቢሆን ነው! .. በምናባዊዎ ዉስጥ፣ ምን ያህል ዋጋ እንደሆነ መገመት ይችላሉ? አሏህ በእርስዎ ላይ ሰላምታ የሚሰጥበት ዋጋ? ከዚያ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ የአሏህ መላእክት ለአንድ ጊዜ ሳይሆን፣ ግን ለአሥር ተከታታይ ጊዜያት፣ በእርስዎ ላይ ሲያሰላምቱ ምን ያህል ዋጋ ይኖሯል? እና ከዚያ እነዚያን መለኮታዊ ሰላምታዎች፣ በአላህ መልእክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) ላይ በእያንዳንዱ ጊዜ ደጋግመዉ ያወርዳሉ፡፡ በአት-ተህያት ሰላምታም ሆኖ እና ከሰላምታ ውጭ በየትኛው የሶላት ጊዜ?

## ቀዩ ቁልፍ 4፡ ሰላም በእኛ እና በፃድቃኑ የአላህ ባሮች ላይ ይሁን

ይህቺ ሰላምታ ብቻ አይደለችም፣ ይልቁንም ወደ አሏህ ለመግባት የተቀበሉት ታላቅ ሽልማት ምልክት ነች። ለተከበሩ መልዕክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) ላቀረቡት ሰላምታዎ ነች፣ ፕሬዚዳንቱን ወይም ንጉሱን ሲጎበኙ ከቤተመንግስቱ ብዙውን ጊዜ ለጎብኝዎቹ የሚሰጥ ጨዋ ንጉሳዊ ወይም ፕሬዝዳንታዊ ክብር በር ላይ አስቀምጠዉልዎት፣ ሲወጡ ያገኛሉ እነድ ማለት ነዉ፡፡ ይህቺ መደበኛ ስጦታ አትሆንም፣ ግን የለጋሽን ሁኔታ የሚትመጥን ስጦታ ነች።

የነገሥታት እና የገዥዎች፣ የምድር እና የሰማዩ ፈጣሪን ስጦታ ሰላምታዎ ምክንያት ሊቀበሉ ሲመጡ ምን ዓይነት ስጦታ ይሆን? አይ፣ ከሚገምቱት በላይ ትልቅ፣ ግዙፍ እና ጮማ መሆን አለባት ... በቢሊዮኖች የሚቆጠሩ ቢሊዮኖች ሽልማቶች ናቸው፡፡

አሏህ፣ ከአዳም ፍጥረት ጀምሮ እስከ እለተ-ትንሳኤ ድረስ፣ በፈጠራቸዉ ባሮች፣ ጻድቆች፣ በሰማይና በምድር ወዘተ ቁጥር ብዛት ያህል ሽልማቶችን ያገኛሉ፡፡ ይህ አንድ ሰው ወይም ባሮች ወይም ፃድቃኑ ባሮች ሰላምታ በማዉረዳቸዉ፣ ከአሏህ ዘንድ መልካም *ሥራ* ወይም *ሥራዎች* ከሚያገኙ ቁጥር ነዉ፣ የአሏህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንደነገሩን፡

‹ሰላም ለእናንተ ይሁን› ካሉ፡፡ አሥር መልካም *ሥራዎች* ይኖርዎታል፣ እና ‹ሰላም በእናንተ ላይ ይሁን፣ የአላህ እዝነትም› ካሉ፣ ሃያ መልካም ስራዎች ይኖርዎታል፣ እና ማንም ‹ሰላም ለእናንተ ይሁን እና የአሏህ ምህረት እና በረከቶችም በእናንተ ላይ ይሁን› ካሉ፣ ሠላሳ መልካም *ሥራዎች* ይኖርዎታል፡፡ *[በሳሂህ አል-ተርጊብ ውስጥ በአል-አልባኒ ተረጋግጧል፣ በሱሃይል ቢን ሀኒፍ ዘገባ]፡፡*

ይህንን ተደራራቢ ሰላምታ በሶላትዎ ውስጥ ሲደጋግሙት፣ በእርስዎ ላይ የሚወርድ እጥፍ የክብር ስሜት ሊሰመዎት ይገባል፡-
1-ማለቂያ የሌለውን መለኮታዊ ሰላም የማዉረድዎት ክብር እና በእርስዎ እና በቤተሰብዎ ላይ ሰላምታ-እናም በርስዎና በጓኞችዎ ላይ **(ሰላም በእኛ ላይ ይሁን)** ሰላም እንዳወረደ ይሰማዎታል፣ ስለሆነም እርሱንና እነርሱን በምህረቱ፣ በቸርነቱ፣ በማጽናናት እና በሰላም ያጥባቸዋል ማለት ነዉ።
2- ይህን ማለቂያ የሌለውን መልካም *ሥራ* የማግኘት ጸጋ እና ስሜታቸው በእርስዎ ላይ በምስተናገዱበት ወቅት፣ ፊትዎን በነዚህ በዛ ያሉ **(የፃድቁ የአሏህ አገልጋዮች)** ቁጥር ላይ በማሰላመትዎ ልክ ከራስዎ አናት እስከ እግሮችዎ ድረስ በእርጋታ ይታጠብዎታል፡፡ እነዚህ ቁጥራቸዉ በዛ ያሉ ባሮች ላይ ሰላምታ በማዉረድዎ ምክንያት፡፡

በሌላ ጊዜ፣ አሁንም ቢሆን ሰላምታ በእርስዎ ላይ ብቻ እንዳልነበረ መገንዘብ በጣም አስፈላጊ ነው፣ እዚህ ጋር የብዛት አመላካች ‹በኛ ላይ› የሚል የስም ምትክ አለ፡፡ እናም ለራስዎ ብቻ ሰላምታ መስጠት እና በአካባቢዎ ላሉት የምትወዳቸው ሰዎች፣ ዘመዶችዎ እና አማኞች ሁሉ ሰላምታ መስጠት መካከል ልዩነት አለ፡፡ ከዚያም በእነዚያ ስፍር ቁጥር በሌላቸው የአሏህ አምላኪዎች ላይ ሰላምታ ሲያወርዱ ከጻድቃን፣ በምድር፣ በሰማይ እና በመካከላቸውም ባሉት ላይ ማለት ከእያንዳንዳቸው ምንዳ ይደርስዎታል ማለት ነዉ፡፡

በመጨረሻም፣ “ሰላምታዎን” የሚለዉን ያንብቡ ወይም “ምስክርነትዎን” እና “ ኢብራሂማዊ ሰላማታዎች”ን ያንብቡ፣ በመስጠትና በመቀበል መርህ፡፡ እርስዎ በሶላትዎ ውስጥ ዝም ብለው አይሰጡም፣ ወዲያውኑ በሚናገሩት ቃል ሁሉ ሽልማትዎን እንደተቀበሉ ማረጋገጥ አለብዎት፡፡ ከዚያ ለዚህ ዉዳሴ ምንዳ ለመቀበል ለአፍታ ያቁሙ፡፡ ይህንን ያንብቡ፣ ከዚያ በኋላ በሚያነቡት እያንዳንዱ ክፍል ልክ እንደዚያዉ ያቁሙ፣

- እድል ይስጡ፡ (ሰላምታ ለአሏህ...) ከዚያ ይጠብቁ እና የተከበረዉን ምላሽ በማግኘት ይደሰቱ፣

-እድል ይስጡ፡ (እና ሰላምታዎች...) ከዚያ ይጠብቁ እና የተከበረዉን ምላሽ በመቀበል ይደሰቱ፣

-እድል ይስጡ፡ (እና መልካም ነገሮች ...) ከዚያ ይጠብቁ እና መልካም ምላሽ በማግኘት ይደሰቱ ... እና ወዘተ ...

-እድል ይስጡ፡ - (አላህ ሆይ ሙሐመድን ባርክ ...) ከዚያ ምንዳውን እና የተከበረውን ምላሽ በመቀበል ይጠብቁ እና ወዘተ ...

-እድል ይስጡ፡ (እና የመሐመድ ቤተሰቦች ላይ ...) ከዚያ ይጠብቁ እና ለጋስ ሽልማት በማግኘት ይደሰቱ ...

አሁን፣ ከዚህ ሁሉ በኋላ፣ ለሶላት በሚነሱበት ጊዜ፣ ከትከሻዎ ሊያስወግዱት ወደሚፈልጉት የቤት ሥራዎ ያስባሉ፤ ወይስ በዓለም ላይ ካሉት ሽልማቶች ሁሉ የላቀ እና የገዘፈ ሽልማት እንደሚቀበሉ ይሰማታል፤ ከሁሉም ንብረቶች/መብቶች ሁሉ የሚበልጥ?

ሶላትዎን ስያበቁ ዳግም እንደተወለዱ ንፁህ ካልሆኑ፣ በርግጥ ብዙ ጥሩ ነገር አምልጥዎታል ማለት ነዉ፡፡

## የጸሎት እና ዉዳሴ ክፍለ ጊዜ

ጸሎት (ዉዳሴ) የሶላት መንፈስ ያለው ግን መደበኛ ማዕቀፎች እና ህጎች የሌለዉ ቀለል ያለ የሶላት ዓይነት ነው፡፡ ዉዳሴ ለጥቂቶች ከባድም (ሲንቀሳቀሱ) ቀለልም የሚል፣

በማንኛውም ጊዜ እና ቦታ እርስዎ የሚያዳብሩት፣ በየትኛውም ሁኔታ ውስጥ ቢሆኑም ለመፈፀም ቀላል የሆነ የሶላት ዓይነት ነው፡፡

ሁለቱም (ሶላትና ዉዳሴ) በእንግሊዝኛ ("ጸሎት") ናቸው፣ እናም በዚህ ድብልቅ እና መቀላቀል ውስጥ ግልፅ የቋንቋ ምልክት ልዩነት ያለ ሲሆን፣ ልመናው (ዉዳሴ)፣ በአፈፃፀሙ ውስጥ ያለው ንግግር ወደ አሏህ የሚቀርብ እስከሆነ ድረስ፣ የሶላት ዓይነት እንደሆነ ነዉ፡፡ ምንአልባት ይህ የነብይን (ሰ.ዐ.ወ) የጸሎት ቋንቋን ልዩነት ያብራራል፣ ትንቢታዊ ንግግሩ ለአሏህ በተነገረው ስለሆነ፣ ከነብያዊ የሀዲስ ቋንቋ፣ የተነገረው ትንቢታዊ ንግግሩ ለኛ የተነገረው ስለሆነ ነዉ ሊያስብል ያችላል፡፡ የትንቢታዊ የዉዳሴ ቋንቋ፣ ልምድ ያለው ሰዉ እንደሚረዳ ሁሉ፣ እና ልምድ ያለው ተቺው ትርጉሞችን እንደሚገነዘበውና የአረብኛ ሰዋሰወ እና የአጻጻፍ ልዩነቶችን እንደሚናገረዉ ሁሉ፣ ከአነጋገር፣ ከውበት፣ ከምት፣ ከስሜታዊነት አንፃር፣ ከነብያዊ የሀዲስ ቋንቋ ልየት ያሉ ናቸዉ፡፡ ነገር ግን፣ የተከበረው የሐዲስ ቋንቋ በውበት እና በቃላቱ አነጋገር አረብኛን ከፃፉ የሰው ልጆች ሁሉ ዘዴዎች በላጭ ነዉ፡፡ በዚህ ውስጥ በጣም ቀላል ነገር፣ አንድ የቋንቋ ሰዉ የሀዲሱል-ቁድስ ቋንቋ እና ተራ የሐዲስ ቋንቋም እንዲሁ መለየት መቻሉ ነዉ።

በጸሎት ቋንቋ፣ በአኳሆኑ እና በመንፈሱ መንፈሳዊ ምት እናስተውላለን፤ ልክ ሰማይ በመፍጠሩ ላይ የተሳተፈች ይመስል፣ ጉዳይ እንዲሁ ልክ እንደ ሀዲሱል ቁድሲይ ነዉ፡፡ የአሏህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ጓደኞቻቸውን እንዲጸልዩ ለማስተማር ከፍተኛ ፍላጎት ነበራቸውና ቃል በቃል እንዲይዙ እና ቃላቱን ያለ ምንም ለውጥ መጠበቅ አስፈላጊ መሆኑን በማስጠንቀቅ ላይ ነበሩ፡፡ እና በጸሎት ዉስጥ (መልክተኛው) የሚለዉ ቃል (ነቢዩ) በሚለዉ እንዲተካ፣ ሁለቱም ዞሮ ዞሮ መልእክተኛዉን የሚገልፁ ቢሆኑም፣ እንዴት ሰምተዉ እንዳስተካከሉ ያሳያል፡-

**በአል-ባራ ቢን ኣዝብ (ረ.ዐ) አለ፡ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡ ‹‹ወደ አልጋህ ከመጣህ ከዚያም የሶላት ውድእህን አድርግ፣ ከዚያ በቀኝ በኩል ተኛ፣ ከዚያ እንዲህ በል: "አምላኬ ሆይ! እራሴን ለአንተ እሰጣለሁ፣እናም ፊቴንም ወደ እናንተ አቀናሁ፣ ጉዳዬን ለእናንተ ወከዬአለሁ፣ ጀርባዬን ወደ አንተ አስጠጋሁት፣ መሸሸጊያ እና እኛ ከአንተ ብቻ በመከጀል፣ ካንተ መሸሺያ ወይም ነፃ መዉጫ የለም፣ ወደ አንተ እንጂ፣**

**ባወረድከው መጽሐፍህ እና በተላከው ነቢይህ አመንኩ፡፡ ”በዝያች ምሽት ከሞቱ እርስዎ ትክክለኛ ሃይማኖት ላይ ነዎት፣ እና እርስዎ የሚናገሩት የመጨረሻ ነገር ያድርጓቸው። አል-ባራ አለ፡-ለነቢዩ ደገምችው (ሰ.ዐ.ወ) እና ሲደርስ “በወረደው መጽሐፍህ አመንኩ” ብዬ አልኩ “በመልእክተኛህም”፣ እሱም አለ፡ ኣይ፣ “እና በላከዉ ነቢይህ”** *[በሁለቱ ሼይኾች የዘገበ]*

ሰሀቦች ነብይ (ሰ.ዐ.ወ) የቁርአን ሱራዎች እንደሚያስተምሯቸው ሁሉ አንዳንድ ዱዓዎችን (ዉዳሴዎችን) እንዴት እንደሚያስተምሯቸው ይተርካሉ፡፡ በተለይ በጸሎቱ ቋንቋ ላይ በመጥቀስም ሆኖ በመደመር ምንም ለውጥ ሳያደርጉ ትጉ ፍላጎት ነበራቸዉ ማለት ነዉ፡፡

**- ከኢብኑ አባስ (ረ.ዐ.) የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ከቁርአን ምዕራፍ እንደሚያስተምሯዉ ሁሉ ይህን ጸሎት ያሚያስተምሯዉ እንደነበር ሲገልፅ እንዲህ ይላል፡-“በሉ፡ አቤቱ አምላካችን ሆይ! እኛ እንጠበቃለን፣ (በሌላ ዘገባ እጠበቃለሁ)፤ ከጀሃነም ቅጣት፣ ከመቃብር *ሥቃይ* በአንተ እጠበቃለሁ፣ ከአድ-ደጃል ፈተናም በአንተ እጠበቃለሁ፣ እናም ከሕይወት እና ሞት ፈተናም በአንተ እጠበቃለሁ** *[ሙስሊም ዘግቦታል]*

**- የአሏህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) አት-ተሸሁድን ልክ የቁርአን ምዕራፍ እንደሚያተምረን አድርጎ ነዉ ሲያስተምረን የነበረዉ** [በኢብኑ ማጀህ የዘገበ፣ አልባኒ የተረጋገጠዉ፣ ከአብደሏህ ኢብን አባስ] **(በሌላ ዘገባ ከአብደሏህ ኢብን ዑመር፡ አንድም ፊደል እንዲጨመር ወይም እንዲቀነስ አይወድም)** ይላል፡፡

### ሚዛኑ

አየህ፣ ከእኛ መካከል አንዱ ሶላቱን አጠናቆ ሲወጣ እስክሪብቶ በመያዝ ከአሏህ ጋር የተናገረበትን ቅፅበት በተወሰኑ ስሌቶች ለመመዝገብ ወይም ለመቅዳት ሞክሯልን? እና ሶላት ዉስጥ በእውነት እንዳለ የተወሰነ ግንኙነት እንደተከሰተ የተሰማው እና ልቡ የረጠበበት፣ ሰውነቱ የተንቀጣቀጠበት ጊዜያት የተሰማው ካለ ፈትሸዋልን? ምንም እንኳን ለአንድ ጊዜ ብቻም ቢሆን፣ ለአንድ ሰከንድ ወይም ከፊል ሰከንድም ቢሆን፣

በመጨረሻም፣ እነዚህን ጊዜያት ቆጥሮ፣ ሃሰቦ፣ በግምትም ቢሆን፣ ከአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ጋር ባቀረቡልን የጊዜ ሰሌዳ መሠረት፣ምን ያህል ምንዳ እንዳገኘ አዉቋልን?

- ከአማር ቢን ያሲር ከመልእክተኛው (ሶ.ዐ.ወ) እንደተናገረው "**አንድ ሰው ከሶላቱ ሲነሳ፣ የሚፃፍለት ነጥብ አንድ አስረኛ፣ አንድ ዘጠነኛ፣ አንድ ስምንተኛ፣ አንድ ሰባተኛ፣ አንድ፣ ስድስተኛ፣ አንድ አምስተኛ፣ አንድ አራተኛ፣ አንድ ሶስተኛ፣ ወይም ግማሽ ቢሆን እንጂ አይፃፍለትም**›› *[በአቡ ዳውድ እና በአል-ነሳኢ ዘግቧል፣ እና በአልባኒ አረጋግጦታል፣ ከአማር ቢን ያሲር]*

ከእነዚህ ደረጃዎች በተወሰነ ደረጃም ቢሆን እስካልተሰማዎት ድረስ ሶላትዎን ትተዉ ላለመውጣት ይሞክሩ፡፡ በመጀመሪያው ረከዓ ካመለጥዎ፣ በሁለተኛው፣ ከዚያም በሦስተኛው፣ ከዚያም በአራተኛው ውስጥ ይሞክሩ፡፡ በሱና ውስጥ ከወደቁ በግዴታ ሶላት ይሞክሩ፡፡ በሱብሂ ሶላት ከወደቁ፣ ከዚያ በዙሁር ሶላት፣ ከዚያ በዐስር፣ ከዚያ በመግሪብ፣ ከዚያ በእሻዕ፣ ከዚያ ቢያንስ በናፍቆትዎ ውስጥ በአንዱ ሶላት ላይ ካላለቀሱ ወይም ካልተደናገጡ ወይም በአንዳንዶቹ ውስጥ ልብዎ ካልተንቀጠቀጠ፣ ወይም ከኃያሉ አምላክ ጋር በመገናኘት ደስታ ካልተሰመዎት እንዳይወጡ፡፡ እናም ያ ደካማ የእምነት (ኢማን) ነዉ። ከዚያ በላይ ከጨመሩ እና መጨመሩ የተሻለ ስለሆነ፣ ከዚያ የተቻሩት ፀጋዎች እና ያገኙት ትሩፋቶች በወደፊት ሕይወትዎ ሚዛን ላይ ምንኛ የሚደመሩ ነበሩ፡፡

አንዳንድ ጊዜ አንዳንድ ዋና ዋና መደብሮች ደንበኞቻቸውን ለመሳብ የሚያስችሏቸውን ጠቃሚ የማስተዋወቂያ ሽልማቶችን ያስተዋውቃሉ፡፡ ከመጋዘኑ ከመነሳትዎ በፊት አድራሻቸውን እና ስልካቸውን የሚገልጽ ቫውቸር ሞልተው ማሳወቅ ይኖርብዎታል፣ ከዚያ ሽልማቱን ለማሸነፍ ይወዳደራሉ፡፡

እርስዎ በሶላት ዉስጥ ሲሆኑ በመለኮታዊ መደብር ውስጥ ነዎት፣ ለአሏህ ታላቅ ምሳሌያዊነት ይሁን፣ እና ለእያንዳንዳቸው አሥር ቫውቸሮችን የሚሞሉበት ሲሆን፣ እያንዳንዱ ድርሻ ሽልማት አለዉ፡፡ በንግድ መደብር ሽልማቶች እና በመለኮታዊ መደብር ሽልማቶች መካከል ያለው ልዩነት ግን ከብዙዎቹ አንዱ ክፍል ነው፡፡ ያም እርስዎ በመጨረሻ፣ ከብዙ ሽልማቶች ውስጥ ለአንዱ ብቻ "እጩ" አይደሉም፣ ግን

ይልቁንም እነዚህ ሁሉ ሽልማቶቹ ለእርስዎ 100% የተረጋገጡ ናቸው፣ ሆኖም ግን…ቫውቸዎቻቸውን በትክክል ከሞሉ ብቻ ነዉ፣ ከዚያ በላይም በታችም ምንም የለም፡፡

እርስዎ ትርፍ ለማግኘት እና ለእነሱ ዋስትና ለመስጠት ወደ ትልቁ የኢንቨስትመንት (ልማት) ፕሮጄክቶች ሊገቡ ነው፣ እንዲያዉም በዝቅተኛ ወጪዎች፡፡ ይህ የንግድ ድርጅት የሚያስፈልገው ግዙፉ የገንዘብ ዋጋ ዜሮ ነዉ ማለት ይቻላል፡፡ በዘካ ውስጥ ቢያንስ 2.5% ገንዘብዎን መክፈል ያስፈልግዎታል፤ ሐጅ ለጉዞ፣ ለመኖርያ እና ለጉዞ የማይናቅ ወጪ ያስፈልግዎታል፤ በጾምም ከምግብ እና ከመጠጥ እንዲሁም ከሌሎች ከልተፈቀዱ ብዙ ነገሮች መታቀብ ያስፈልጋል፣ በተጨማሪም መጨረሻ ላይም ዘካት አል-ፊጥር መክፈል አለብዎት፡፡
ለሶላት ደግሞ፣ወጭዎ በምትታጠብበት ውሃና ሶላት ሲፈፅሙ ከሚያሳልፉት ጊዜ አይበልጥም፡፡ ያ ነው፣ ተጨማሪ ምዝገባዎች፣ ክፍያዎች እና ታክሶች የሉም፣ ተጓዳኝ ትርፉ ግን፡ ወደ ሂሳብዎ ውስጥ የሚገቡት ከፍተኛ ትሩፋቶች፣ እንዲዉም አንዳንዶቹን ወዲያውኑ ከሶላት ከመውጣትዎ በፊት የተወሰነውን በእጅ ይቀበላሉ፡፡ ለምሳሌ፡ የሥነ-ልቦና ምቾት፣ ጤና፣ እና እርጋታ፣ የአእምሮ ግልፅነት እና እንደገና እንደ ተወለዱ የሚሰማዎት ስሜት፣ ሌሎች ደግሞ ተሸፍነው ወደሚያማምሩ ሣጥኖች ተልከው ይቀመጡልዎታል፡፡ ወይም በዚህ ዓለም ውስጥ ወዳለው አድራሻዎ ደግሞ፡ ስኬቶች፣ በረከቶች፣ ደህንነት፣ የተለያዩ ፀሎቶች አስቸኳይ መልስ ማግኘት ወዘተ ሲገቡ፣ የወዲያኛው ዓለም ትሩፋቶችን በተመለከተ፡ ከዚህ በፊት የነበሩትን ኃጢአቶቻችዎን በማበስ እና ስፍር ቁጥር የሌላቸውን መልካም ሥራዎችን ወደ እርስዎ ሚዛን በመጨመር ነዉ የሚሆነዉ፡፡

እንዲህ ያለው ፕሮጀክት ትርፍ እና ኪሳራ ለመመዝገብ ልዩ የሂሳብ መዝገብ ማዘጋጀት አይገባንምን? እዚህ ያሉ ኪሳራዎቹ እኛ የምናዉቃቸዉ አይነት ስሜት ያላቸዉ ኪሳራ አይደሉም፣ የካፒታል ቅነሳም አይደሉም፣ ግን ይልቁንስ በትርፍ ላይ መጨመር የቻልነው የገንዘብ ዋጋ የቁጥር መቀነስ ናቸው፡፡ ዋና ገንዘባችን በከፋ ሁኔታ ይቀራል፤ ሶላታችን የፉገራ፣ የአመፅ፣ የግብዝነት እና ማታለል፣ የእዩልኝታ፣ አሏህ አያምጣብንና፣ ካልሆነ በስተቀር፣ ዋና ገንዘባችን (ምንዳችን) ሙሉ በሙሉ ይኖራል፣ የኪሣራና ቅናሽ እጅ ወደ እሱ አይዘረጋም፡፡

በዚህ በአዲሱ የኢንቬስትሜንት ፅንሰ-ሀሳብ ለትርፍ እና ለኪሳራ ስሌት ላይ በመመስረት፣ አሁን በእያንዳንዱ ሶላት መጨረሻ ሊያገኙት የቻሏቸውን ትሩፋቶች ተመጣጣኝ ግምቶችን እንዲሁም ያመለጡዎትን ግምት ማድረግ ይችላሉን? እንዲሁም እነዚያን ለጥቂት ጊዜ ከትቅሉ ሊያገኙት ከሚችሉት ትሩፋቶች እራስዎን ያሸነፈዎት ነገሮች እና ከሶላትዎ ያዘናግዎትን መገመት ይችላሉን?

## መገጣጠሚያዎችዎ እስኪረጋጉ ድረስ..

በመንገድ ላይ በሚጓዙበት ጊዜ ትከሻዎችዎ ከሚገባው በላይ ተሳስረዉ፣ ክርኖችዎ ከግንድዎ ከሚገባዉ በላይ ርቀዉ፣ የእጅዎ ጣቶችዎ በጣም ከሚገባዉ በላይ የታጠሩ መሆናቸውን አስተውለው ያውቃሉ? ያ ትዝ ብልዎት ከተገነዘቡ እና እነዚህን አካላትን ወደ ቦታቸዉ ከመለሱ በኋላ እንኳን፣ ወዲያውኑ ቀስ በቀስ ወደ ነበሩበት እንደተመለሱ ያገኟቸዋል፡፡ እነሱ የእርስዎ ነርቮች፣ በአከባቢዎ ባለው የከባድ የሕይወት ምት ተጽዕኖ ስር የወደቁ፣ ምልክቶቻቸውን በሰውነትዎ ክፍሎች ላይ የሚያሳዩ እናም አካላትዎትን የሚዘረጉ፣ የሚያጥፉና የሚያጠናክሩ ጡንቻዎች ናቸው፡፡

በመልእክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) ሀዲስ ውስጥ **(የእሱ መገጣጠሚያዎች እስኪረጋጉ ድረስ)** የሚል ሐረግ ሦስት ጊዜ እንዴት እንደተደጋገመ ልብ ይበሉ፡፡ ሀረጉ የሶላት እንቅስቃሴዎችን ምን መሆን እንዳለበት ያስረዳልናል:( **...ከዚያ ይላል፡ አሏህ ታላቅ ነው፣መገጣጠሚያዎቹ እስኪረጋጉ ድረስ ረከዓ ያደርጋል፤ ከዚያ ቀጥ ብሎ እስኪነሳ ድረስ እንዲህ ይላል፡ -አሏህ የሚያመሰግኑትን ያዳምጣል-፣ ከዚያም ይላል፡-አሏህ ታላቁ ነው፣ በኋላም መገጣጠሚያዎቹ እስኪረጋጉ ድረስ ሱጅድ ያደርጋል፤ ከዚያ እንዲህ ይላል፡ -**‹አላሁ አክበር› **አሏህ ታላቅ ነዉ-፣ እስኪቀመጥ ድረስ ጭንቅላቱን ያነሳል፣ ከዚያ እንዲህ ይላል-**‹አላሁ አክበር› **አሏህ ታላቅ ነዉ- ከዚያ መገጣጠሚያዎቹ እስኪረጋጉ ድረስ ይንበረከካል፣ ከዛም ጭንቅላቱን ከፍ በማድረግ ተክቢር ያደርጋል፣ ያን ካደረገም ሶላቱ ተጠናቀቀ** *[በአቡ ዳውድ ከሪፋአ ቢን አር-ራፊዕ የዘገበ ሲሆን በአል-አልባኒም ተረጋግጧል- የአል-ሙንዝሪ አንድ ዘገባ-እስኪረጋጉ- ከሚለዉ አረፍተ*

*ነገር በኋላ በእያንዳንዱ ጊዜ* ***(ዘና ይበሉ)*** *የሚለውን ቃል የሚጨምር አለ -* ***(እንደዚሁ መገጣጠሚያዎቹ ዘና እንዲሉ የሚል አለ]***

በእውነቱ እኔ መጀመሪያ ላይ ሐዲሱን ያነበብኩ ሲሆን በዚህ አስደናቂዉ ትንቢታዊ ሐረግ ላይ ብዙም አላቆምኩም፡፡ እና በሚቀጥለው ንባብ ቀና ብዬ እያየሁት ሳስብ፣ የመገጣጠሚያዎች ምቾት ወይም መረጋጋት ምንድነው? ለምን ነፍሱ እስኪረጋጋ አላለም፣ ወይም ልቦናዉ፣ ወይም ሁኔታዉ፣ ከሶላት ጋር ያሉ የመገጣጠሚያዎች፣ የጡንቻዎች እና የአካል ክፍሎች ግንኙነት ምንድነው? ብዬ እራሴን ጠየኩ፡፡

ከዚያ (የተረጋጋ) የሚል ቃል የቋንቋ ትርጉሙ (መቀነስ) መሆኑን አስተዋልኩ፣ እናም ከምድር የተቃረበ የታችኛው ሜዳ መሆኑን ተረደሁ፡፡ እናም እዚህ ላይ ግልፁ ነገር መልእክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) በሁለቱም ትርጉሞች ንግግራቸው በአስተማማኝ ሁኔታ ምላሽ እንደሰጡ ነዉ፡፡ ይህ ነብያዊ ቃል ከቁርአን ትርጉም ጋር ቃል በቃል በትክክል ይዛመዳል፡፡ ማለትም ኹሹዕ (መተናነስ፣ እራስን ዝቅ ማድረግ፣ አክብሮት) ከሚለዉ ቃል ጋር ማለት ነዉ፡፡ አሏህ፡ (ከአሏህ ፍርሃት ሲዋረድ እና እራሱ ዝቅ ሲያደርግ ታየዋለህ) ይላል፡፡ ይህ በራሱ በቃሉ (መረጋጋት፣ ምቾት) ትክክለኛ ትርጉም ላይ ግልፅ የሆነ ማብራሪያ ያስቀምጥልናል፡፡ አሏህ፡ **“አዋጅ፣ ስሙ፣ በአሏህ ዉዳሴ ነዉ ልቦች የሚረጋጉት”** ይላል፡፡
የሰውነት መገጣጠሚያዎች እና ጡንቻዎች መረጋጋት፣ ማለትም ዘና ማለት የነፍስን ማረጋጋትና ማዝናናት፣ እርካታ፣ ሰላምና ደህንነት ያስገኛሉ፡፡ ነፍስ ስትረጋጋ እና ሲመቻት ደግሞ ልበ ሙሉነት፣ በምቾት፣ ደስታ እና ደህንነት ይከተላሉ፡፡ ይህ በልብ እና በአንጎል ላይ ይንፀባርቃል፣ እናም አንጎል ወደ ጡንቻዎች ምልክቱን ይልካል፡፡

እነሱ ዘና እያሉ ወደ መገጣጠሚያዎች ይስፋፋሉ እና ይቀንሳሉ፣ እና ይህ ሁሉ የነፍስና የሰውነት መረጋጋት ለመላዉ አካል ጤናማ እና ፈውስ ነው፣ይህ ሁሉ የተፈጥሯዊ አካላዊ ቅርፅ ተግባራት ነው።ለባሪያዉ ቀላል የሚሆነዉ፣ የሶላቱን ሀረጎች በሚፈለገው ኹሹዕ በመድገም በእውነቱ ስኬታማ ከሆነ፣ ሶላቱን ሲሰግድ ማስተዋል ያለበት ነገር፣ በተለይም በሱጁድና እና በሩኩዕ ደረጃዎች ወቅት መልእክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) እንዳብራሩልን፣ እንቅስቃሴዎችን በእርጋታ፣ በዝግታና በተከታታይ ወደ ተለያዩ የአካል ክፍሎቹ ማዉረድ አለበት፡፡

ኣስብ፣ ትከሻዎ በድንገት በሶላት እንዴት እንደሚወርድ ልብ ይበሉ፣ ልክ ወደ ኹሹዕ ሁኔታ ሲገቡ፣ እና የአሏህን ምህረት፣ እርዳታ እና ጥበቃ ሲጠይቁ፣ ከዚያ ትከሻዎና ጀርባዎ ይከተላል፣ ከዚያ አንገትዎ፣ ክርኖችዎ፣ የእጆዎ ጣቶች፣ በሰውነትዎ ውስጥ ያሉ እያንዳንዱ ጡንቻ እና መገጣጠሚያዎች እና ተጓዳኝ የሰውነትዎ አካላት፣ ከዚያም በእያንዳንዱ ህዋሳትና መንፈሳዊ  አካላት፣ መከላከያ እና ፈዋሽ ምግብዎች ይከተላሉ ወዘተ… ክቡር ነቢያችን (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) በሶላት ዉስጥ (ሥነ-መለኮታዊና መንፈሳዊ ጠቀሜታዎችን ከዓለማዊውና አካላዊዉ መካከል አገናኝተዋል፡፡ ከአሏህ ጋር መገናኘትዎን መገንዘባችሁ እና ከዚያ እርሱን በመገናኘት ስሜት፣ በሽልማቱ እና በሞገሱ ስኬታማ መሆነዎን ሲያስቡ፣ የተሳካ መረጋጋት እና ደህንነት ስሜት በመገጣጠሚያዎችዎ ላይ፣ በአንጎል ሴሎችዎ፣ በነርቭ ኔትዎርኮች፣ የልብዎ ጅማቶች፣ በመላ የሰውነትዎ ተፈጥሯዊ አካላት ላይ ዘና የሚያደርግ ስሜት ይፈጥራል፣ እርካታና እርጋታን ያመጣል፡፡

በሶላት ዉስጥ የምላስዎን አካላዊ እንቅስቃሴ፣ የዚህ ምሰሶ የመጀመሪያ ልኬት የሆነዉን ማለት ነዉ፣ በራስዎ ውስጥ ወደሚሰምዎት ትርጓሜ እና ወደ ሌሎች በፊትዎ እና በተቀረው የሰውነትዎ አካል ላይ ወደሚንፀባረቀዉ መለኪያዎች ሲተረጉሙ፣ የዛኔ ነዉ የማንኛውንም አምልኮችንን እና በመሠረቱ ላይ ያለውን የሶስትዮሽ ትርጉም ሁለተኛ ደረጃን በጥሩ ሁኔታ ማሳካት የቻሉት፡፡ የዚህ ዋነኛዉ ጉይ ሶላት ሲሆን፣ የሶስትዮሽ ትርጉም ልኬት ማካቱ ግድ ይላል፡፡ ማለትም ሶስተኛው እና  አስፈላጊዉ እርምጃ የእነዚህን ትርጉሞች ወደ መሬት ማስተላለፍና መለማመድ ላይ ነዉ የሚሆነዉ፡፡

## የሶላቱ የሶስትዮሽ ትርጉም

ትርጉም የሌለው ቋንቋ አለ? ምንም መልእክት የማይሰጡ ትርጉሞች አሉ?
የቃላቱን ትርጉም ሳያውቅ የሚያሰግድ የአንድ ሰው ሶላት ትርጉም የሌለዉ ቋንቋ እንደሚናገር ሰው ነው ፡፡ እነዚያም አረብኛ የማይናገሩትም ቢሆኑ፣ እናም በሶላት ውስጥ የሚደጋገሙትን ግዴታ የመረዳት ችግር ስለሚያጋጥማቸዉም ጭምር፤ በአእምሮአቸውና በልባቸው ሊረዱት ስላለባቸዉ ትርጉሙን ማወቁ እጅጉኑ ጥሩ ነዉ፤ ምክንያቱም የሶላት ቃላት አፍዎን ያነፃሉ፣ ነፍስዎን ያረካሉ፣ ልብዎን በጨለማዎች ያበራሉ፣ የሚፀልዩ የአሏህን ቃል እያነበቡ ነዉ፤ በክቡር ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ወደ ሰማይ

ባረጉ ጊዜ የሰገዱበትን ዉዳሴዎችና ፀሎቶች ወደ እኛ በመምጣት በአምስቱ ሶላቶች እንድንሰግድበት ያደረጉንን በመጠቀም ነዉ፡፡

የእነዚህን ቃላት ትርጓሜዎች በአዕምሮው የተገነዘበ የአንድ ሰው ሥራ፣ ከዚያ በኋላ በምድር ላይ ውጤት እንዳላቸዉ አናያቸውም፣ ትርጉም ባለው ግን ምንም ማለት በማይችል ቋንቋ እንደሚናገር ሰው! እናም ቋንቋው መገናኛ መሳሪያዎች ስለሆኑ በአለም ላይ ሁሉም ሰዉ የሚስፈገዉን ተግባር ያከናውንበታል፡፡ አምላኪው ባሪያ እውነተኛ ባሪያ እስኪሆን ድረስ፣ያዉ ልክ እንደ ኤሌክትሮኒክ ሮቦት ያላ ህይወትና ልቦና እንዳይሆን ነው፡፡ እንዲሁም የሶላትና የንባብ ቃላቶች የሚፃፉና የሚተረጎሙ በሶስቱም አቅጣቻዎች መሆን ሲገባቸዉ አንድም መሥፈርት ከጎደለ ምንም ማለት የማይችሉ ትርጉሞች ያሉት ቋንቋ ሆኗል፡፡

በዚህ ትርጉም ውስጥ የመጀመሪያው ልኬት የምላስን አካላዊ እንቅስቃሴ ወደ አእምሯዊ እንቅስቃሴ ማዛወር ነው፣ ስለሆነም እኛ የምንለውን ነገር አእምሮ እንዲገባዉ ማለት ነው፣ እናም በዚህ ትርጉም ውስጥ ወደ ሚቀጥለው ልኬት ድልድዩን ማቋረጥ እጅግ አስፈላጊ ልኬት ነው የሚሆነዉ፡፡ የምላስ መንቀሳቀስ፣ ልብ አብሮ ካልተንቀሳቀሰ፣ ምንም ማለት እንዳልሆነ ብንናገርም፣ ስንት አምላኪ/ባሪያ ነዉ የመናገር በረከትን የተነፈገው፤ ከንፈሩ ወይም ምላሱ ሳይንቀሳቀስ በልቡ ብቻ ይጸልይ ስለነበረ፡፡ ሁለተኛው ልኬት የአእምሮ እንቅስቃሴ ትርጉም ነው፤ ይህ በመጀመሪያው ልኬት ውስጥ ትርጉሞችን እና ሀሳቦችን ይዘን የገባነው ሆኖ፣ ልብና አእምሮ ጋር የሚገናኝበት ሀሳብና እንቅስቃሴ እንዲሁም ዓይኖች እና የተቀረው የሰውነት ክፍል፣ አክብሮት፣ መዝናናት፣ መተማመን እና ሰላም የሚረጋገጠዉ በልቦና ትርጉም ነዉ ማለት ነዉ፡፡

ሦስተኛው ልኬት ይህ በይነተገናኝ ስሜታዊ እንቅስቃሴ መሬት ላይ ወደ ተግባር መተርጎም ነው፡፡ የሶላቱ ሕይወት ከራሱ፣ ከሰዎች እና ከአሏህ ጋር ያለው ግንኙነት እንዲጠናከር፣ ማለትም ስለሚደግመው ነገር በተግባራዊነት እና በሐቀኛ ስዕል በመለኮታዊ እና ትንቢታዊ ትርጓሜዎች እንዲገለፅ፣ እና የሰዉ ልጅ በልቡና አካሉ በአክብሮት እና በሙሉ እጅ መስጠትን በሚያረጋግጡ ነገሮች በእጆቹ ሲገኙ፣ በትዕዛዞች እና ክልከላዎች ምላሽ ይሰጣል። ሶላት ከጊዜ ጋር ከመተዋወቅና መደጋገም ወደ ቅኔያዊ ቃላቶች እና እንቅስቃሴዎች መለወጥ ሲችል፣ በእነዚህ ልኬቶች መጀመሪያ ልኬት ከመመሳሰል ይለያል፡፡ ምላስ ወይም ከንፈር ከሚንቀሳቀስበት እንቅስቃሴ

አያልፍም፣ ልብ፣ እጅ እና ስራ ስለማያረጋግጠዉ፡፡ ያቺማ ሟች ሶላት ናት፡፡ ሶላቱ እውነተኛ ሰላት እንድትሆን የሚፈልግ ሰዉ ሶላቱን ህያው ለማድረግ የግድ ሶስቱን የትርጉም ዘዴዎች ማስነሳት አስፈላጊ ነው፡፡ ምክንያቱም የጠፋው መንፈሱን በሚያነቃቃበት እና ትርጉሞቹን እንደገና በሚያድስበት ልኬቶች ስለሆኑ ነው፡፡

ሁላችንም፣ ሙስሊም ሆኖ በተወለደው የሶላት አየያዝ ለውጥ እና በአዲሱ ሙስሊም አየያዝ መካከል ግልጽ ልዩነት ልብ ብለን እናስተውላለን፡፡ የኋለኛው፣ ከመጀመሪያው በተለየ፣ ለራሱ በመረጠው አዲስ ሃይማኖት ውስጥ እያንዳንዱን ቃል ወደ መጀመሪያ ቋንቋው ይተረጉመዋል፣ ከዚያ ያጠናው እና በአዕምሮው እና በሕሊናው ይይዟል፤ ከዚያ ወዲያውኑ ተግባራዊ ሕይወት ውስጥ ለማስቀመጥ ይሞክራል፤ ያለበለዚያ ለምን የቀድሞ ሃይማኖቱን ይለውጣል?

የእስልምና ታሪክ ነበልባል ዉስጥ አረብ ያልሆኑ ሙስሊሞች በሚሰልሙበት ጊዜ፣ ከአረብ ሙስሊም ወንድሞቻቸው በበለጠ ብሩህነትን መሠረቶችን ሁሉ ያስመሠክሩ ነበር፡፡ እስልምና አዲስ ማህበረሰብን በሚነካበት ጊዜ ሁሉ ይህ ህዝብ ጽሑፎችን፣ ጥቅሶቹን እና አምልኮቱን ወደራሱ ቋንቋ ወይም ወደ አዲሱ ቋንቋቸዉ በመተርጎም፣ ቃላቶቹ በጆሮዎቻቸው እና በልቦቻቸው ላይ እንዲወድቁ (ልክ ለመጀመሪያ ጊዜ ከሰማይ ወደ ምድር መልእክት ለሙስሊሞች ሲያስተላልፍ ከነቢያቸው (ሰ.ዐ.ወ) የሰሙ የመጀመሪያው መልእክትን ያህል) በጥሞና እንዲቀበሉ፣ እንዲረዱ ያደርጋል፡፡

የዚህ ዓይነቱ የሥስትዮሽ ትርጉም አካል የእስላማዊ ታሪክ እንቅስቃሴ መሠረታዊ እና ውጤታማ አካል ነበር ፡፡ በምስራቅ በአረቦች ሙስሊም ድል አድራጊዎች ልብ ውስጥ ድክመት መስፈር ሲጀመር፣ከመጀመሪያው የሂጅሪ ክፍለ ዘመን መጨረሻ እስላማዊው ገጽታ መንቀጥቀጥ ጀመረ፤ የመጀመሪያው፣ በኡመያው እና በአባሲድ ገዥዎች መካከል በከሊፋነት ላይ በተነሳውን ግጭት ተከትሎ፣ በመግሪብ (ሞሮኮ) ውስጥ ታሪቅ ኢብኑ ዚያድ የተባለ አንድ በርበሪይ ጀግና የአንዳሉሺያን ድል በእጁ ለማጠናቀቅ ሰንደቅ ዓላማዉን ይዞ ተነስቶ ነበር፡፡ የመጨረሻው የአረብ ግዛት የመጨረሻ ውድቀት ግራናዳ እ.ኤ.አ.በ 1492 ሲቃረብ፣ የኦቶማን ኢምፓየር አገር ግዛት ጅምሮች በምስራቅ መነሳት ጀመረች፡፡ እናም የባይዛንታይን ግዛት ዋና ከተማ እና የአውሮፓ ዋና ከተማ ቆስጠንጢኖል በ 1453 በወጣት ቱርካዊ መሪ መሐመድ አል-ፋቲህ እጅ ይወድቃል፡፡

እናም አረቦች ኢየሩሳሌምን እና ፍልስጤምን ከሺህ ዓመታት በፊት መጠበቅ ሲያቅታቸው፣ ሰንደቅ አላማዎቻቸዉ ከወራሪ የአውሮፓ በፈረሰኞች ስር ወድቀ፡፡ የአረብ አመራሮቹ ድል ለማድረግ ያልቻሉትን ነገር፣ ከኩርድ አዩቢድ በሳላህ አል ዲን አል አዩቢ የሚመራው ግዛት ብቅ አለ/ ተነሳ እና አል-ቁድስ፣ አል-አቅሳ እና ሻምን ከጋዛ የመስቀል ጦር ነፃ አወጣ፡፡

ይህ የእስልምና ሕዝቦች በመካከላቸው ተግባራዊ ያደረጉት “የሦስትዮሽ የጋራ ትርጉም” ነው፡፡ ይህም በአረቦች እና በአረብ ባልሆኑት መካከል የእስላማዊው ስልጣኔ በአስገራሚ “የማስተላለፊያ ስርዓት” ነዉ ሲሸጋገር የነበረዉ፡፡ ይህ ሰጋጁ በሶላቱ ውስጥ የምላሱን እና የከንፈሩን አካላዊ እንቅስቃሴ ሲተረጉመው በራሱ ላይ ሊለማመድ የሚገባዉ ገፅታ ሲሆን፣ ከዚያ ወደ አእምሯዊ ወይም ስሜታዊ እንቅስቃሴ በመቀየር፣ በተግባር ወደ መሬት የሶላቱን ቃላቶች ወደሚተረጎም ወደ ተግባራዊ እንቅስቃሴዎች ያወርዳል፡፡

ይህንን ሶስት ትርጉም በሶላታችን ውስጥ ስንለማመድ እና የአሏህን መጽሐፍ ንባብን ተግባራዊ ስናደርግ፣ እናም ልምምዱም እያሳደግን እንሄዳለን፡፡ ሌሎች የእኛ የአምልኮ ተግባራት በትምህርት ቤቶቻችን፣ በዩኒቨርሲቲዎች፣ በትምህርታዊ መጽሐፍት እና በትምህርታዊ ሥርዓቶች ዉስጥ ሲቀበሉ እና ለምሳሌ በባህላዊ፣ በሃይማኖታዊ እና በቁርአን ውድድሮቻችን ማስተዋወቅ ስንችል፣ እና ቅዱስ ቁርአንን ለማፈዝ (ለመሸምደድ) የተቀመጠው የፍላጎት፣ እንቅስቃሴዎች እና ሽልማቶችል ቁርአንን በመለየት፣ ትርጓሜውን እና ዓላማዎቹን ለመረዳት ወደ ውድድሮች ከሥነ-ምግባር፣ ከዚያም ወደ ተግባር ማዉረድ ያስፈልጋል፡፡ ያ ምንድነው? ከግብይቶቹ፣ ከትእዛዞቹ እና ከዓላማዎቹ ጋር ላይ የሚሄዱትን ጉዳዮች ሁሉ መሬት ላይ ተግባራዊ በማድረግ) በመስራት፣ (እና ይህን ቁርአን ያንብቡና ይከልከሉ፣ መከልከል ካልቻሉ አላነበቡም) ሀሰን ቢን አሊ (ረ.ዐ) እንዳሉት እና እንዳመኑ)፡፡ የዛኔ ነዉ ወደ ተባለዉ አዲስ የእስልምና ሥልጣኔ ሚና የሚመልሰን ነገር በመጀመሪያ ደረጃ ለራሳችን መሳል እንችላለን፡፡ ከዚያም እንደገና ለዓለም ማቅረብ አለብን፡፡

## ከሶላት ፕሮግራም የተገኙ ጥቅማጥቅሞች

በመጀመሪያ የሶላት ሂሳብዎን በሚገመግሙበት ጊዜ፣ ያቀረብናቸውን አምስት እቀዶችን አይርሱ፡፡ ምን ያህል በእያንዳንዱ እቅድ ላይ እንደተጣበቁ ለማየት፤ ለምሳሌ፣ የጊዜ እቅድ፣ የምላስ እቅድ እንዲሁም የሰውነት እቅድ፣ የልብ እቅድ፣ እና የሥራ እቅድ እና በሶላትዎ ውስጥ ካጠፉት የደቂቃዎች ብዛት አንጻር ይህንን ግምገማ ማድረግዎን አይርሱ።

ሁለቱን ረከዓዎች በሁለት ወይም በሶስት ደቂቃዎች ከጨረሱ ተመልሰዉ ይስገዱ፣ ምክንያቱም ስላልሰገዱ፤ በነዚህ ደቂቃዎች ዉስጥ ከማስመሰል ካልሆነ በስተቀር ሶላትዎን ፊደላትንና ትርጓሜዎችን ለመረዳት፣ እና ግንዛቤ ለማግኘት በቂ ሰዓት አልነበረዎትም፡፡ በሌሎቹ የአራት አካላት እንቅስቃሴዎችም አይዳረስም፡፡

እያንዳንዱ ሙስሊም፣ ከእያንዳንዱ ሶላት፣ ግምታዊ የአፈፃፀም ክብደት የሚለካበትን ሚዛን ለራሱ መወሰን አለበት፡፡ ሶላቱ እንዴት እንደነበረ እርሱ ብቻ ነዉ የሚያዉቀዉ፡ ፡ እናም ለዚህ ነዉ የሶላታችን የመጨረሻ ውጤት ክብደት ሀሳብ ያቀረብኩት፡፡ ሀሳቡ በትንሹ ሰዉ ሰራሹ ሚዛንን በመመካከርና በመታገዝ የእያንዳንዱ ሶላት መሰብሰቢያ እርስዎ በእውነት በሚመዝኑት ሁነታ እንዲፈጠር ማድረግ ማለት ነዉ፡፡ ምንአልባት የሶላታችን የመጨረሻ ዉጤት እዉነታ የሚያዉቀዉ በዚህ ሶላት ወደሱ የዞርን የምንሰግደዉ፣ ያ ሁሉን አዋቂ፣ ዉስጥ አዋቂ፣ ገምጋሚ፣ በእዉነተኛ ሚዛን መዛኝ፣ አሏህ እነጂ፣ ሌላ የለምና፡፡

1. እጆቼን እያነሳሁ እና የመግቢያ ተክቢራን እያደረኩ ሳለ፣ ሁሉንም ነገር ትቼ ከምድር ዓለም ጋር የማይገናኝን ሌላኛው የላይኛው ዓለም እንዳአየሁ፣ ተሰምቶኛል?
2. ስንት ጊዜ ነዉ **(አሏ አክበር-አሏህ ታላቅ ነው)** ከሶላት ከሚያዘናጉኝ ነገሮች አውጥቶኝ ፣ከገባሁበት አዲሱ ዓለም ሊያዘናኝ ስለነበረ ከሁሉም በላይ በከፍተኛ አዘናጊዉን ጉዳይ ያስወገደልኝ፤ እናም ከዱንያ ማዘናጊያዎችና ማደናቀፊዎች ወደ ከፍታና ኃያልነት ክፍ በማለት ‹አሏህ ታለቅ ነዉ› አልኩኝ?
3. ስንት ጊዜ ነው **(እጅግ በጣም ርህሩህ)** የሚል ቃል በብርሃን አምድ ወደ ጎን ሊያጥበኝ የቻለ (ከሰማይ የሚወርድ ምህረት አንደ ማለት ነዉ)፣ ስንት ጊዜ ነው (እጅግ በጣም አዝኝ) የሚል ቃል በዘላቂነት በአግድም ከኃጢዓት ሊያጥበኝ

የቻለው (ማለት ዝንተ-ዓለማዊ እዝነት)፣ ስለዚህ ሁሉንም የአካል እና የነፍሴን ክፍሎች መንጻት በመለኪያዎቻቸው ያጠቃልላልን)?

4. ስንት የቁርዓን አንቀፅ ወይም ምዕራፍ አነበብኩኝ፣ ከአል-ፋቲሃ ውስጥ ወይም ከሚከተሉት ምዕራፎች **(የዓለማት ጌታ አሏህን አመስግናለሁ፣ የፍርዱ ቀን ንጉስ--- አንተን ብቻ እንገዛለን - - -)** ወዘተ፣ ብዬ ታመልክቻለሁኝ? … ስለዚህ ትርጉሙንም አሰብኩኝ እና በራሴ ውስጥ ተመለከትኩኝ?፣ እና በፊቴ የተገለጠውን የአሏህን ታላቅነት አነሳሁኝ? ስለዚህ ሳነበው አንድ ነገር በውስጤ እንደተለወጠ አለኝ፣ ወይም ተሰማኝ?
5. ስንት የቁርዓን አንቀፅ ወይም ምዕራፍ አነበብኩኝ፣ ከአል-ፋቲሃ ውስጥ ወይም ከሚከተሉት ምዕራፎች፣ ትርጉሙን ለመያዝ እና ለማሰላሰል የሞከርኩት፣ እና በቂ የጊዜ ርቀት የሰጠኋቸው?
6. (ቀጥተኛውን መንገድ አሳየን) ብዬ ስል ቤተሰቦቼን፣ ዘመዶቼን፣ ጓደኞቼን፣ ሙስሊሞችን እና ሙስሊም ያልሆኑትን እና ጠላቶቼን በልቤ አስባለሁኝ? ይህቺ የምረት ፀሎት እንዲትደርሳቸዉ ማለት ነዉ፡፡ ለእነሱ ያለኝን ንፁህ ልቦና ወይም ማጽናኛ ማረጋገጫ  ስያደርግ የአስቸኳይ ሽልማት ደስታ ወደ እኔ ሲወርድ ተሰማኝ?
7. ምን ያህል ነዉ ከእያንዳንዱ ዉዳሴና ሱጁድ በኋላ (አሏህ ታላቅ ነው) ስል በፍሬያማ ትሩፋቶች አእምሮዬንና ልቤን በሚገባ ለመሙላት የምችለዉ?
8. በሶላቴ ወቅት ከሚቀጥሉት አዝራሮች ውስጥ ስንት ቀይ ቁልፍ ተጫነባቸው እናም ወደ ልቤ ገብተዉ በጥልቀት ያናውጡኝ ወይም ልቤ ይንቀጠቀጥ) የደረሰዉ ወይም ያስለቀሱኝ?፡

- **(ባንተ ብቻ እንታገዛለን)** የሚለው ቁልፍ? ከዚህ ሀረግ በኋላ በምጠይቀው ሁኔታ እንዲሰማኝ ምን ያህል ሰከንዶች ሰጠሁ? እናም እንደዚሁ በዚህ ጥያቄ የተሸፈኑትን የራሴን እና የሰዎችን ገፅታ ባጠቃላይ ሁኔታ እንዲያስታወስ (እርዳታ እንፈልጋለን) የተደረኩኝ?
- **(አት-ተህያቱ- ሰላምታ ለአሏህ)** ቁልፍ? እነዚህን ሁለት ቃላት በመናገር፣ ከዚያም በኋላ፣ የፈጀዉ የጊዜ ርዝመት ምን ያህል ጊዜ ነበር፣ ከዚያ

የሚቀጥለውን ክፍል (ወስ-ሰለዋቱ-እና ሰላምታዎች)፣ ከዚያም ሦስተኛው (ወጥ-ጧይባቱ-እና ጥሩ ነገሮች)፣... እናም በዚህ አስደናቂ ትዕይንት በነፍሴ ላይ ለመውረድ ለራሴ ጊዜ ለመስጠት እሞክራለሁ ነበር፣ ወደ አሏህ መግባት፣ ከዚያ እሱ እንዳስተማረኝ በተመሳሳይ መልኩ ሰላምታ መስጠት እና ይህን ሰላምታ ለእርሱ ስያቀርብ ደስታ ይሰማኛል፤ ከዚያ ሁሉ ቻይ ከሆነዉ አሏህ ለእዚህ ሰላምታ ፈጣን ምላሽ የመቀበል ደስታ ይሰመኛል?

- **(የአሏህ ምህረት እና በረከት በእናንተ ላይ ይሁን)?** ለሚለዉ ቃል? ይህንን ሰላምታ ለማንበብ ምን ያህል ጊዜ ፈጀ፣ በተለይም የሚራዘሙ ቃላቶች (ሰላም- አሏህ እና በረከቱ) በቻልኩት መሠረት ስያነብ፣ ያዉ ስሜቱ በነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሰላምታ ማዉረድና፣ እና ከዚያም የሱንም ሰላምታ መቀበል ጋር ያለዉ ስሜት ነዉ**?**
- **(ሰላም በእኛ እና በፃድቁ የአሏህ አገልጋዮች ላይ ይሁን)** የሚለዉ ቁልፍ? እና እኔ ይህንን ሰላምታ በላዬ ላይ እና በዙሪያዬ ባሉ ሰዎች ላይ አወርዳለሁ፣ ከዚያ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ የአሏህ አገልጋዮችና ትውልዶች፣በምድር ላይ እና በሰማይ ያሉ ጻድቃን በሆኑት፣ በየትኛውም ቦታ እና በማንኛውም ጊዜ በሚኖሩት ላይም፣ አንድ ንፁህና ቅዱስ የ(ሰላምታ) ጥይት በእኔና እነሱ ላይ ይወርዳል፣በመጀመሪያ የእኔን ዉስጥ እና ዉስጦቻቸዉን ከሁሉም ነገር (ከሚጎዳኝ እና ከሚጎዳቸዉ) ያጸዳል፣ እና ያን ከተቀበልኩ በኋላ ወዲያውኑ ሌላ ንጹህ ጥይት ከሰማይ ለጋስና የሚንዳ ሽልማት ያጥለቀልቀኛል፤ እርሱም ከራሴ አናት እስከ እግሮቼ ጫማ ያጥበኛል፤ ከዚያም ማንኛውንም ራስ ምታት፣ ህመም፣ ድካም፣ ጭንቀት ወይም ፍርሃት ይወገድልኛል**?**

9. በሱና ረከዓቶች ውስጥ ከእነዚህ ነጥቦች ያመለጠኝን ማካካስ በሌሎች ረከዓቶች ልተካ ችያለሁኝ/እችል ነበር፣ ወይም ምንአልባት በተቃራኒ?
10. እና በመጨረሻም፣ በዚህ አዲስ የትእግስት እና የትኩረት ስልጠና ተሳክቶልኛል? ተሰማመኝ? አዲስ የትዕግሥት ክፍያ በእኔ ላይ እንደ ተጨመረ፣ እና የሆነ ነገር በእኔ ነፍስ እና በአካሌ፣ በሥነ ምግባር፣

ትዕግሥትና ጥበብ ረገድ እንደተለወጠ ተገነዘብኩኝ? ይህ ለውጥ ምንም ያህል ትንሽ ቢሆንም?

## ከሶላት ጥቅማጥቅሞ ያመለጣችሁ ነገር

1. ከሶላቴ የሚያደናቅፈኝን ሳልሸነፍ ስንት (ተክቢር-አሏህ ታላቅ ነው) ናፈቀኝ?
2. ስንት ጥቅሶችን አንብቤ አልፌያለሁ ትርጉማቸዉን ሳላስታውስና ምንም ትርጉም በዉስጤ ሳላስቀር?
3. ስንት ምስጋና፣ ሩኩዕ ወይም ሱጁድ፣ ወይም ሀረግ ወይም ሰላምታ ደገምኩ፣ ግን ለጣፋጭነቱና ለመልካም ትርጉሙ ቦታ አልሰጣሁም፣ በዉጤቶቿ ስሳይ ሳልጠቀም?
4. ለሱጁድ በሚወርድበት ጊዜ ልብሴን፣ ሱሪዬን ወይም ፀጉሬን ለማሰብሰብ ስንት ጊዜ ፈቅጃለሁ እና ምን ያህል እጄን፣ ነፍሴን ወይም ማንኛዉንም አካላቶቼን አንቀሳቀስኩ፣ ያን ሳላደርግ በሙሉ ኒያና ኹሹዕ መስገድ እችል ነበር?
5. ከፊት ለፊቴ ባሉ መስመሮች፣ ስዕሎች፣ ቀለሞች ወይም ነገሮች፣ ወይም ስሰግድበት በነበረበት የሶላት ምንጣፍ ዙሪያ፣ ከሶላቴ ስንት ጊዜ ተማርኬ ነበር?
6. በሶላቴ ወቅት ስንት ጊዜ ነዉ ዓለማዊ ነገራቶች ተሸንፌ እንድፈልገዉ ሳልሰግድ የቀረሁትን?
7. ከእኔ ጋር ያሉት፣ በመስጊድ ውስጥም ሆነ በሌላ ቦታ፣ ወይም በጎንዮሽ ውይይት ወይም በየቴሌቪዥን ወይም ሬዲዮ ድምፅ፣ ወይም ስልክ መደወል ወይም በር ማንኳኳት ወዘተ ከሶላቴ ስንት ጊዜ አዘናግተዉኝ ነበር?
8. የትኛው የአምስቱ የሶላት መስመሮች በሶላቴ ወቅት ባቡር ያለፈኝ ቢሆን ነዉ ሌሎች መስመሮች፡ ማለትም ጊዜ፣ ምላስ፣ አካል፣ ልብ ላይ ሳልሰራ ያሳለፍኩት?

9. ከሶላቱ በኋላ፡ ማንኛውንም ማለማመድን ይከለክለኛል የምል ተጨማሪ የበሽታ መከላከያ ወይም ለጌታዬ ስሰግድ ከሠራሁት ጋር የማይጣጣም ድርጊት አጋጥሞኛል?
10. ከሶላት በኋላ፡ በቆራጥነት፣ በትዕግሥት፣ በትኩረት እና በትዕግስት ዑደት ውስጥ ተሳክቶልኛል? ወይስ ወደ ሶላት በገባሁት አኳሆን ወጣሁ? ብለዉ ይጠይቁ፡፡

* * * *

በመጨረሻም፣ በቀንዎ መጨረሻ ላይ እራስዎን ትራስ ላይ ስያደርጉ እና ከአሏህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) የተኙትን የእንቅልፍ ፀሎቶች ሲያነቡ ከአንድ ደቂቃ በላይ በማይፈጅ ፈጣን ሂደት፣ ከዚያን ቀን ጸሎቶች ውስጥ ለራስዎ ያስመዘገቡዋቸው ነጥቦችን ድምር ለማሰባሰብ መሞከርን አይርሱ፤ በተለይም ከቀይ ቁልፎች ጋር የተዛመዱትን፡፡ ውጤትዎን ከፍ እንዳደረጉ ለማየት ይህንን ድምር ከመጨረሻው ቀን ጠቅላላዎ ጋር ያነፃፅሩት፣ ዕለታዊው ዉጤትዎ ወደፊት ወይስ ወደ ኋላ ተመልሷል የሚለዉን እንዲመለከቱ፡፡ ስለዚህ በሚቀጥለው ቀንዎ ያመለጠዎትን ነገር ለማካካስ ይሞክራሉ፣ ስለዚህ የነጥቦችዎ ሰርጠረዥ እየጨመረ እንዲሄድ ማለት ነው። እና በሳምንቱ መጨረሻ የሳምንቱን ውጤት በሙሉ ለራስዎ መስጠት ይሞክሩ፣ ከዚያ ያንን ውጤት ካለፈው ሳምንት ውጤት ጋር ማወዳደር ላይ መሆንዎን ለማረጋገጥ፣ በአሏህ ኢንቬስትሜቶችዎ ትርፍ ላይ የማያቋርጥ እድገት ያስቀጥሉ፡፡

**ሕይወትዎ በሶላት የተሞላ ይሁን**

ወደ ልቦናዬ በሚመጣ ነገር በነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ወደ ሰማይ ባረጉ ሌሊት ሶላት በሕግ መደንገጉንና ከፍተኛ ትዕዛዞችን መቀበሉን የሚያበስረን የተከበረ ሀዲስ ነዉ፡፡ ትዕዛዙ መጀመሪያ ላይ፣ ነቢዩ (ሰለላሁ አለይሂ ወሰለም) እንደነገሩን ሃምሳ ሶላት መደንገጉ ነገር፣ ከዛም ክቡር ነቢዩ ለህዝባቸዉ ስለሚከብድ እንዲቀነስላቸዉ ደጋግሞ ይጠይቁ ነበር፤ ያዉ አምስት እስኪደረግ ድረስ፡፡ እኔ ይህ ሐዲስ በትዉስታዬ በመጣ ጊዜ ሁሌ እጠይቅ ነበር፣ ምናልበት እናንተም ስትጠያየቁ የነበራችሁ ይሆናል፡፡ ለያችሁ፡በየቀኑ አምሳ ጊዜ ወደ እንዴት መስገድ እንችላለን፣ ሰዓትስ ከሶላት ዉጭ ለሌሎች ጉዳዮች

ይበቃናል፣ መቼ ነው የምንበላው፣ የምንጠጣው፣የምንተኛበት፣የምንነቃው፣ የምንማረው እና የምንነጋገረው፣ የምንሰረ፣ የምንገነባ፣ ምድርን የምናለማ፣ የምንደሰተዉ፣ እና አንዳችን ቤተሰቦቹን እና ጓደኞቹን እንጎበኛለን? ወዘተ፡፡ በመጨረሻም ሶላትን እውነታ፣ ምንነቷ፣ እና ከራስ እና ከህይወት ጋር የመተባበር ሚኗ ሲገባኝ፣ እናም ሰጋጁ ከሶላቱ የሚወጠበትን ውጤት ስገነዘብ፣ ሶላት ሕይወት እንደሆነ፣ ሕይወትም ሁሉም ነገሯ፣ ዝርዝሮቿ እና ክፍሎቿ፣ አንድ ዓይነት፣ ግን የተለያዩ እና ቀለሞች ያሏት ሶላት ዓይነቶች እንደሆነች ደረስኩበት።

-ከእንቅልፍዎ ሲነሱ እና በነበሩበት አጭር እንቅልፍ ከሞቱ በኋላ አሁን በሕይወት እንደኖሩ ሲገነዘቡ፣ ከእንቅልፍ ላስነሰዎ ጌታ ምስጋና ይሰማዎታል፡፡ የዛኔ አንተ ትሰግዳለህ፣

-የልጆችዎን ወይም የሌሎችን ልጆች ፊት ሲመለከቱ እና በእድገታቸው ምስጢር እና በእድገታቸው አስገራሚ ነገሮች ግራ ሲጋቡ፣ በየቀኑ አዲስ ቅጽ፣ አዲስ ችሎታ፣ አዲስ ቃላት እና ሀረጎች ሲለምዱ፣ እናም እርስዎ ሶላት ዉስጥ ነዎት፣

-ቤተሰቦችዎን ወደ ጥሩነት ሲመሩ እና በጥበብ እና በጥሩ ምክር ወደ አሏህ ሲጋብዙ፣ ከዚያ በኋላ ቢታዘዛም ወይም ቢያምፁም፣ በሶላት ውስጥ ነዎት፣

-ወንድምህን፣ የሥራ ባልደረባህን ወይም ጎረቤትህን በሐቀኝነት እና ከልብህ በአንተ ላይ ለሠራው ኃጢአት ይቅር ስሉ፤ ከዚያ ኃጢአተኛ እንደሆንክ ነገር፣ እርሱን ይቅርታ ስጠይቁ ፣ በሶላት ውስጥ ነዎት ፣

-ስድብዎን በጆሮዎ ሲሰሙ ካልመልሱባቸው እና በአሏህ ላይ ያስቡዋቸው እንደሆነ፡፡ ከዚያ እርስዎ በሶላት ውስጥ ነዎት፣

-የሞቶዉን የወንድምዎ ሥጋ ከሚበላበት ስብሰባ ሲወጡ እና መከላከል ወይም መለወጥ ሞከረዉ የማይችሉ ሆነው ካገኙ፣

ከዚያ እርስዎ በሶላት ውስጥ ነዎት፣

-ሙስሊም ያልሆነው ቀጥተኛውን መንገድ እንዲመራው ሲጣሩ፣ ከመዋጋት፣ ከመቃወም እና ከመጥላት ይልቅ፣

ከዚያ እርስዎ በሶላት ውስጥ ነዎት፣

ሙስሊም ያልሆነን የእስልምናን ምህረት፣ የእስልምናን መቻቻል፣ የእስልምናን ጣፋጭነት እና የእስልምናን ፍቅር

የእስልምና ሥልጣኔ፣ የእስልምና ሥነ ምግባር እና የእስልምና ፈገግታ፣ሲያሳዩ፣ ከዚያ እርስዎ በሶላት ውስጥ ነዎት፣

-ሙስሊም ባልሆነ ሀገር ውስጥ ቢሆኑም እንኳ እርስዎ የሚኖሩባቸውን የአገሮች ስርዓቶችንና ንብረቶችን ሲጠብቁ፣ ግዴታዎን ሲወጡ፣ ገንዘብን፣ በግብርን እና በሥነ ምግባርን ሲጠብቁ፣ ሲያስጠብቁ፣ ከዚያ እርስዎ በሶላት ውስጥ ነዎት፣

-መጥፎ ነገር ከየአቅጣጫው ሲከበብዎት፣ በዉስጥዎ ሲጠሉት፣ ከዚያ በእጅዎ ወይም በአንደበትዎ መለወጥ ካልቻሉ እንኳን፣ ከዚያ እርስዎ በሶላት ውስጥ ነዎት፣

-ቤተሰብዎን እና በዙሪያዎ ያሉትን ለማርካት ሲጥሩ፣ በትጋትዎ ወይም በተሳሳተዎ ጊዜ፣ እርስዎ በሶላት ውስጥ ነዎት፣

-ከአላህ ጋር ያላችሁ ጉዳዮች ሁሉም ጥሩ እንደሆኑ በሚተማመኑበት ጊዜ፣ መልካም እንጂ ሌላ ነገር አያስቡም፣ ያለእናንተ ሽይጧን ምንም ያህል መጥፎ ቢያደርግብዎትም፣ እርስዎ በሶላት ውስጥ ነዎት

-አሏህን ስለሰጠህ እና ስለ ቅታትህ ሲያመሰግኑ፤ ከዚያ እርስዎ በሶላት ውስጥ ነዎት ፣

-በሁሉም አቅጣጫ በእሱ ፈተናዎች በሚከበቡበት ጊዜ እይታዎን ዝቅ ሲያደርጉ፤ ከዚያ እርስዎ በሶላት ውስጥ ነዎት፣

-በህመም፣ በድህነት፣ በችግር ሲሰቃዩ፣ ከዚያ እርስዎ በጸሎት ውስጥ ነዎት፣

-ደም በሚለግሱበት ጊዜ፣ ከአንድ ሚሊዮን ለአንድ ጠብታ ጠቃሚ ሊሆን ይችላል ብለዉ እንኳን፣ ከዚያ እርስዎ በሶላት ውስጥ ነዎት፣

- ሙስሊሞች ወይም ሙስሊም ያልሆኑት በአገሮቻቸው በሚኖሩበት ጊዜ ሲቀላቀሉት፣ በጭንቀቶቻቸዉን ፣ በስቃይ እና በሀዘናቸዉን በድምጽዎ ፣ በስሜትዎ ወይም በልመናዎ እንኳን ለማቃለል ሲሞክሩ በሶላት ውስጥ ነዎት ፣

- አንድ ታካሚ ሲጎበኙ በጸሎት ውስጥ ነዎት፡፡ ነብዩ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ላለው ሶላት ውዱእ እንድታደርጉ አልመከሩም?

-ከአዲሱ የሥራ እና የግንባታ ሥራ ዝግጅት መጥተዉ ለመተኛት ሲያርፉ፣ ሰውነትዎን ከረጅም ቀን ችግር ሲያላቅቁት፣

ከዚያ እርስዎ በሶላት ውስጥ ነዎት፡፡

ነብዩ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ላለው ሶላት ውዱእ እንድታደርጉ አልመከሩም?

-እና በመጨረሻም ፣ ከመተኛትዎ በፊት እራስዎን ተጠያቂ ሲያደርጉ ወይም ሲገመግሙ፣ ያ ቀን ምን የእርስዎ የነበረው እና በርስዎ የነበረ ከዚያ እርስዎ በሶላት ውስጥ ነዎት፡፡

-በአምላኪው ዓይን በትክክል ከተመለከቱ እና ካለዉ የተፈጥሮ እዉነታ ጋር መስተጋብር ከቻሉ፣ ህይወትዎ በሙሉ ሶላት ነው፡፡ በሚያጋጥምት ሁኔታ፣ ቦታና ማእዘናት ሁሉ ሶላቶች አያምልጥዎት፣ ስለዚህ የትኛዉም የሕይወት ክፍሎች ስለ ፈጣሪ ታላቅነት የሚናገሩ፣ ኃያልነቱን የሚያወድሱ፣ ለበጎነቱ የሚያመሰግኑ፣ የበረከቱን ፀጋ የሚመሰክሩ፣ለአገልጋዮቹም ዘወትር ወደ እርሱ እንዲዞሩ ማሳሰቢያ ፣በቋሚነት ሶላት ላይ እንዳሉ፣ወዘተ መሆናቸዉ ግልፅ ነዉ፡፡

አንድ ሰው ቢያናድድዎት አይናደዱ እና አይጠሉት፣ ግን እራስዎን ይልቁኑ ያንን እየደጋገሙ ውዳሴ እና ጸሎት ያድርጉት-

ክብር ለአሏህ ይሁን፣ እኔ፣ እኔ እና ያ ሰው ነኝ? ከአሏህ ፍጥረታት ነኝ? እያንዳንዳቸውን ምን ዓይነት ታላቅ ላባ፣ የተለያዩ ቅርጾች፣ ተፈጥሮዎች እና ሥነ ምግባሮች ፣ የተለየ ስብዕና ያላቸው በቢሊዮን የሚቆጠሩ የሰው ነፍስ ሊሰጥ ይችላል? ባያስተውሉትም እንኳ በዙሪያዎ የሚያጋጥሙትን፣ የሚሰሙትን ወይም የሚተርኩትን ሁሉ ለአሏህ ውዳሴ ያድርጉ፡፡ በአሏህ የተሠራ አመለካከት፣ ፍጥረት ወይም ሥነ ምግባር እንዴት ነው መነቃቃት የምችለው? የእኔን እይታ የሚያርገበግብ መብረቅና እና ልቦዎን የሚያነጎድጓድ የሙብረቅ ድምፅ እና ተፈጥሮ የሚያሻሽለው አመፅ፣ ፍርሃትና አብዮት ወዘተ ቢሆን እንኳን፣ በዉስጥዎ ሌሎች ውዳሴዎችን ብቻ የሚያንፀባርቁና ወደ አሏህ ያለኝን ቅርበት ይጨምሩ ቢሆኑ አንጂ እንዳይኖሩ ያድርጉ፡፡ በሁሉም እንቅስቃሴዎቻችሁ እና መኖሪያዎቻችሁ፣ በአቋማችሁ እና በመቀመጫችሁ፣ በምግብዎ እና በስጦታዎ፣ በሚያገኙት ገቢ እና ወጪዎ፣ በመስማትዎ እና በአይን እይታዎ

እና የእርስዎ አነጋገር፣ ሀሳብዎ እና አስተሳሰብዎ የዚህ ቅዱስ አመስጋኝ፣ ፀላይና አምላኪ፣ ቋሚ ሰጋጅ ወዘተ ፍጥረታት አካል ይሁኑ፡፡ በህይወትዎ እስካሉ ድረስ በጸሎት ውስጥ ነዎት፣ እና በህይወትዎ ውስጥ ህገ-መንግስትዎን እነዚህን ወርቃማ ህጎች ያድርጉ፡-

-በቤትዎ ውስጥ ዓለምዎን ለማስተካከል ከቤትዎ ውጭ አንድ እርምጃ አይወስዱም የወደፊት ሕይወትዎን ለማስተካከል አንድ እርምጃ ካልወሰዱ በስተቀር፣

- አንድ ሰዓት ጊዜዎን አያባክኑ፣ ከዚህ ሰዓት የሚያንስ ሕይወት እንደማይኖርዎት ካላሰቡ በቀር፣

- እግሮቻችሁን በዙሪያዎ ካለው ቆሻሻ አያጥቡ፣ ከግርጌው ስር በውሀደት ካልታጠቡ በቀር፣

- አንድን ቃል በጸሎትዎ ውስጥ አይድገሙ፣በስራዎ ከዚያ በኋላ ለመተግበር ከወሰኑ በስተቀር፣

- ሶላትዎን በትህትና አያስጎንብሱ፣ በህይወትዎ ውስጥ እራስዎን በትህትና ካልያዙ በስተቀር፣

- ከጥቂት ጊዜ በፊት ወደ መስጂድ የገቡት እርስዎ መሆንዎን ካላረጋገጡ ከመስጂድ አይውጡ፣

-በሕይወትዎ ውስጥ አለመታዘዝን ካሰናበቱ እና ታዛዥነትን ከጨመሩበት በስተቀር ለረመዳን ወር አይሰናበቱ፡፡

- በግራዎ ላይ መጥፎውን ካልከፈለ በቀር በቀኝ እጅዎ ጥሩ ሥራ አይስሩ

- ወደ ገሃነም ሊያቃረብዎ የሚችል ኃጢአት ከእሱ ጋር ካልሠዉ በቀር ወደ ገነት የሚያቀርበዎትን መስዋእት አይረዱ፡፡

- ከብርድ፣ ከበሽታ ወይም ከረሃብ ለማዳን እሱን ፈልጎ የሞተውን እስካላስታውሱ ድረስ አንድ ተጨማሪ ሳንቲም አይስጡ፡፡

-ግማሹን ብቻ እንደምትጠጡ ካወቁ ኩባያውን እስከ ጫፉ ድረስ አይሙሉት ፡፡

-ምንም ጠብታ ውሃ አይባክኑ፣ በተመሳሳይ ጥማት የሞተውን ሰው ካስታውሱ በቀር ።

-የምግብ ጉርሻ አፍዎ ውስጥ አያስገቡ፣ ምግብ አጥተዎ የሞቱትን እስካላስታወሱ በቀር፣

-ፍርፋሪውን ከጠረጴዛው ላይ አይጣሉ፣ አሷህ በጠረጴዛው ላይ ካለው ሁሉ ሊያሳጣዎት እንደሚችል እርግጠኛ ካልሆኑ በስተቀር፣

-በየትኛውም የዚህ ዓለም ፍሬዎች አትደሰቱ፣የወዲያኛው ዓለም ፍሬዎች እንዲደሰቱ የሚያነሳሳ ካልሆነ በስተቀር፣

-ባገኛችሁትና ባጠፉት ሀብት አይደሰቱ፣ በሰጠሁት እና ባኖሩት ልክ እንደሚደሰቱ ካልሀነ በቀር ፡፡

-የሚለብሱት ተስማሚ ጫማዎች ከሌሉዎት አይናደዱ፣ አንዳንድ ሰዎች ሁለት እግር ስለሌላቸው፣

-በቤትዎ ውስጥ አንድ መሳሪያ ወይም የቤት እቃ ከተበላሸ ቅሬታ አያቅርቡ፣ ቤት የሌላቸው ሰዎች ስላሉ፣

-በምግብዎ ላይ ጨው አይጣሉ በቃላትዎ ላይ ስኳር ካላከሉ በቀር፣

- ለማንም መጥፎ ቃል አይናገሩ፣ ሌላ ሰው ስለእርስዎ በተመሳሳይ መልኩ እንደሚያወራው እርግጠኛ ካልሆኑ በስተቀር፣

-አንድ ቀን ከልጅዎ ይህን የመሰለ ነገር ለመስማት የማይራሩ ካልሆነ በስተቀር ለአንድም ወላጅዎ መጥፎ ቃል አይናገሩ፡፡

-ከበታችዎ ያሉትን አይንቁ አሏህ ከእርስዎ የበለጠ ዝቅ ለማድረግ እንደሚችል እስካላወቁ ድረስ፣

- መብቱን የበደሉ ከሆነ ይቅር እንዲል አሏህን አይጠይቁ፣ መብትዎን የበደሉትን ይቅር ለማለት ቅድሚያውን ካልሰጡ በስተቀር፣

-ትንሽ ጥላቻ እንኳን ከልብዎ መስኮት እንዲገባ አይፍቀዱ ወደ ሌላ መስኮት በጣም አፍቃሪ ነገር እንዲገባ ካልፈቀዱ በቀር፣

-ለሚወዷቸው አይጸልዩ ከዚህ በፊት እንደምትወዳቸው ወይም ለሚጠራጠሩአቸው ወይም ለሚጠራጠሩአቸው ሰዎች ካልሰገዱ በስተቀር

- ለረጅም ትዕግስት አይታገሉ  ስለ ታላቅ ሽልማት እና ቅርብ እፎይታ እርግጠኛ ከመሆንዎ በስተቀር፡፡

በመጨረሻም፣ የተከበረው የነብያችን (ሶ.ዐ.ወ) ትእዛዝ መፈጸምዎን አይርሱ- አሏህን እንደምታየዉ አድርገዉ ያምልኩ፣ እራስዎን ከሞቱት ይመድቡ፣ በእያንዳንዱ ድንጋይ እና በእያንዳንዱ ዛፍ ዘንድ

አሏህን አስታወስ፣ መጥፎ ስራ ከሰሩ ከዚያ መልካም ስራን በእሱ ያስከትሉ፣ ሚስጢርን በምስጢርነቱ፣ ገሀድና በገሀድ ፡፡

*[አል-አልባኒ በሙአዝ ቢን ጃበል በሳሂህ አት-ታርግሂብ ውስጥ ሀሰን ብሎ መድቦታል]*

## ለራስዎ የመንገድ እቅድ ያስቀምጡ

የመጽሐፉ የመጀመሪያ እና የሁለተኛ እትም ከታተመ በኋላ ብዙዎች ስለ ቀጣይነትና የማያቋርጥ የመተናነስ ግዴታ መርዳት ስለሚቻልበት መንገድ ጠየቁኝ፡፡ እነሱ ይህንን ብዙ ጊዜ እንደሞከሩ እና ሁል ጊዜም ጸሎታቸውን እንደጀመሩ ከአሏህ ጋር የመተናነስ እና የመግባባት መስፈርቶችን ለመተግበር ቆርጦ እንደሚነሱ ነገሩኝ፡፡ ከዚያ ትኩረታቸውን ስቶ፣ ሼጧን ካሸነፋቸው በኋላ ሶላትን ያጠናቅቃሉ፡፡ ያሰቡትን ደስታ፣ ምቾት፣ ጥንካሬ፣ ጤናማነት፣ እና ለትልቅ ምንዳ ማግኘት አልቻሉም ነበር፡፡

እኔ ራሴ በደረሱባቸው መከራዎች ተፈትኛለሁ አሁንም እየተፈተንኩ ነዉ፣ ያጋጠሟቸውን ልምዶችም አጋጥመዉኛል፣ እናም በመጨረሻ ደረጃ በከፍተኛ እቅድ ታግዤ ከዚህ ህመም ወጥቻለሁ፡፡ እቅዱ ከሸይጧን ሸክም፣ በራሴና ትኩረቴ ላይ ከተጫነዉ፣ ለማቃለል በተወሰነ ደረጃ ረድቶኛል፡፡ በአንባቢው እጅ ውስጥ ለማስቀመጥ የምሞክረው የመጀመሪያዎቹ ተሞክሮዎች የሚከተሉት መስመሮች እና ውጤቶች ናቸዉ፡፡
የአክብሮትና መተናነስ እቅድ ከማዉት በፊት በመጀመሪያ ራስን የመከላከል እቅድ ማቀድ አለበዎት፡፡ የመጀመሪያው እቅድ የሁለተኛው እቅድ ስኬት መሠረት ነው፡፡

በሰባት ዓመቴ መስገድ እንደጀመርኩ አስታውሳለሁ እናም በዘጠኝ ዓመቴ ከፀኑት ጋር አንዱ ነበርኩኝ፡፡ እናም አሥራ ሦስት ወይም አስራ አራት ዓመት ሲሆነኝ የእድሜዬ ጉዳይ ለጸሎቴ የበዛ እንደሆነ ተሰማኝ፡፡ አንድ ቀን ማታ መተኛት እየሞከርኩ ጭንቅላቴን ትራስ ላይ ከጫንኩ ይህንን ጉዳይ ፈትሻለሁ ግን አልቻልኩም፡፡ የዛን ቀን ሶላቶች ያልፉኝ ዘንድ በጣም ተጨንቄ ነበር፡፡ ጉዳዩ ለሁለተኛ ጊዜ ተደግሟል፣ ከዚያም ሦስተኛው ጊዜ።
የዐይን ሽፋኖቼን መዘጋት የማልችልበት ምሽት እስኪሆን ድረስ አንድ ወር ወይም ሁለት ወር አለፈ፡፡ በከፍተኛ ጭንቀት እያሰብኩ ነው የሚቆዉ-ሸይጧን ባሏምን ወዴት ይወስደዎል? እጅግ አስፈላጊው ውሳኔ ነበር፡፡
መመለስ የማልችልበትን ነገር ሌሊት ከራሴ ጋር ቃል ኪዳን ገባሁ፣ እናም በእኔና ሁሉን በሚችለው አምላክ መካከል ቃል ኪዳን እንደ መጋባት ነበር። አንድ ጊዜ ሶላት ቢያመልጠኝ ከአንድ ይልቅ ሁለቴ በመስገድ እራሴን እቀጣለሁ) ብዬ ወሰንኩኝ፡፡ (እንደ አለመታደል ሆኖ እንደዚህ ነው በዚያን ወቅት እንደገባኝ ሶላት እንደዚያ መስሎኝ ነበር፣ አሁን ብዙዎች እንደሚረዱት-ግዴታ ወይም ቅጣት ሆኖ ወደ እሱ ይለፍ በሚል) ከአሏህ ጋር ከዚህ ቃል ኪዳን በኋላ ውጤቱ ምን ነበር?
ከዚያ ጊዜ በኋላ ይህንን ቅጣት በራሴ ላይ አንድ ጊዜ ብቻ ጫንኩኝ ፣ ከዚያ በኋላ እንደገና አልደገምኩም ነበር፡፡ እና አሏህን ይመስገንና ያ ነገር እንደ ገና አልተደገመም ፡፡ ከአንድን ሶላት ችላ እንደምለው ሸይጧን በሹክሹክታ በሚወሰዉሰኝ ጊዜ ሁሉ፣ አሏህ ጋር የገባሁትን ቃል ኪዳኔን አስታወሳለሁ፤ እናም እኔ ለራሴ፡ ‹በሷም ሆይ እስቲ አሁን አንድ ጊዜ ስገድ ፣ አለበለዚያ ነገ ሁለቴ ትሰግዳለህ› እላለሁ፡፡

ለኹሹዕ መንገድዎን ሲያቅዱ ይህንን ያስታውሱ፡፡ በእርስዎ ቆራጥነትዎን እና በራስ መተማመንን ያረጋግጡ፡፡ ከራስዎ እና ከአሏህ ጋር የገባዎትን ቃልኪዳን ለመፈፀም መቻልዎንና በራስ በመተማመን እና ቁርጠኝነት ያዳብሩ፡፡ ያዉ ከእያንዳንዱ ሶላት ጅማሮ ጋር በትዕግስት ላይ ስልጠና ኮርስ፣ በሌላ ስልጠና የትኩረት ኮርስ እየወሰዱ እንደሆኑ ያስቡ እና በዚህ ሶላት ውስጥ ትልቁን የነጥብ ብዛት ወይም ግቦች ማስቆጠርና በመጨረሻው ሚዛንዎ ላይ መደመር ይጠበቅብዎታል፡፡ በሁለቱ ክፍለ-ጊዜዎች ውስጥ ማን የመጀመሪያ እና የመጨረሻው እንደሆነ ሲወሰን፣ የመጨረሻው እንዳይሆኑ ይሞክሩ፤

እና በዚህ ሙከራ ውስጥ የመጀመሪያ አሸናፊ ለመሆን በመሞከር አቅሞዎና ብልህነትዎን ይጠቀሙ፡፡ በአሏህ ፊት የመቆም ደስታን ስሜት መያዙም እንዲሁ አስደሳች ወርቃማ እድልዎ መሆኑን ልብ እያሉ ማለት ነዉ፡፡ ወደ እሱ መቃረብን፣ ከእሱ ጋር መነጋገርን እና ትልቅ ምንዳን ማሸፍዎንም ያስታዉሱ።

ጉዳዩ አወዳዳሪ መሆኑ ይቀጥላል፣ ነጥብ ማስቆጠር እና ውጤት ማስመዝገብ እስካለ ድረስ የሚረዳዎ ሁኔታዎች ተፈጥሯሉ፡ ከእነዚህ ነጥቦች ውስጥ ትልቁን ቁጥር ያስመዝግቡ፡፡ እቤት በሌሉበት ጊዜ ብቻዎን በሚያከናውኗቸው እጅግ በጣም አስፈላጊ በሆነ ጊዜ የመጀመሪያ ሶላትዎን (ሱናን) መጀመር ይችላሉ፡፡ ወይም ይህን ስልጠና ከሰዎች ርቀው በመስከ ውስጥ መጀመር ይችላሉ፡፡ ጫጫታ እና ትኩረትን የሚከፋፍሉ ነገሮች ጊዜ፣ ወይም ምንአልባት መስጊድ ውስጥ ሰጋጆች በሌሉበት ጊዜ ወዘተ፡፡

## የመጀመሪያው እርምጃ

ምንአልባት ባለፈው ባሳለፍነዉ አላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ሀዲስ ዉስጥ (ወደ ሶላት ሲነሳ እጆቹን እስከ ጆሮዉ ትይዩ ወይም ከትከሻው ደረስ ከፍ ያደርግና ተክቢር ይላል፣ ከዚያም ሩኩዕ ማድረግ ከፈለገ አሁንም እስከ ከትከሻው ትይዩ ደረስ ከፍ ያደርጋቸዉ) ነበር…

ስለዚህ እሱ (ነብዩ) በመጀመሪያ እጆቹን በማንሳት ይጀምራል፣ ከዚያ ያንን በተክቢር ያስከትላል። በዚህ የመጀመሪያ እርምጃ እና በነዚያ ጥቂት ጊዜያት፣ ማለትም እጆችዎን በማንሳት እና በተክቢር ማድረግ መካከል ያሉትን ሰከንዶች (ምንአልባትም ከ 3-4

ሰከንድ) ውስጥ፤ እድልዎን ይጠቀሙ፣ ለአሏህ ቃል ይግቡ፣ በእራስዎ እና ለአሏህ መካከል ማለት ነዉ፡ ስለሚናገሩት ነገር እና ለሚፈጽሙት ቃል በማሰብ በአክብሮትና በመተናነስ ለመተግበር ሞክሩ፡፡ እንደገና እችላለሁ፡ “የምችሉትን”፡፡ ይህን በመካከልዎ ያለውን ቃል ኪዳን መረዳትዎን እርግጠኛ ከሆኑ እናም ለመተግበር ከልብ የመነጨ ቁርጠኝነትዎን በያሳዩ ጊዜ መሆን አለበት፡፡ ምክንያቱም ከአሏህ ጋር የሆነ ቃል ኪዳን ስለሆነ፡፡ ስለዚህ በዚህ ሀሳብ ላይ ሳሉ ተክቢር ያድርጉ፡፡

በጭራሽ በተክቢር አይጀምሩ፣ ይህንን ስለመፈፀምዎ ሙሉ በሙሉ እስኪያረጋግጡ ድረስ እጆችዎን ወደ ላይ ከፍ ያድርጉ፣ ከዚያ ተክቢር ማድረግን ይጀምሩ፡፡ ትክክለኛዉ፤ (አሏህ ታላቅ ነው) ለሚለዉ ትርጉም በጥቂቱ ብትመረምር፣ ትርጉሟ በሚያስደንቅ መልኩ መሆኑን ትገነዘባለህ፤ በአንተና በአሏህ መካከል የቃል ኪዳን ዓይነት መሆኗ እንደምናውቀው ነው:: (አሏህ ታላቅ ነው) ማለት-በዚህ ሶላት ዉስጥ ከአሏህ በቀር ሌሎቹን ሁሉ መተው ማለት ነው፣ ምክንያቱም እሱ ከሁሉ የላቀ አምላክ ነዉና፡፡ ይህ ማለት ትኩረቴን ሊነጥቁኝ ከሚችሉ ነገሮች ሁሉ “ታላቅ” እና የላቀ ስለሆነ ነው ፣ ያዉ ለሚቀጥሉት ጥቂት ደቂቃዎች ከነዚህ ዝንባሌዎች መራቅ ማለት ነዉ፡፡
በአሁኑ ጊዜ በአእምሮዎ ውስጥ ምን እየተካሄደ እንዳለ አውቃለሁ ፣ በርግጥ አውቄዋለሁ እና ከእርስዎ ጋርም እስማማለሁ፡፡ አዎ፣ በሶላት ውስጥ ሻይጧን ከዚያ በኋላ ሺህ ጊዜ ደግሞ ደጋግሞ ከመጸለይዎ በፊት ይን ያስታዉሱ፣ ያን ያስታዉ እያለ፣ ከዚያ በፊት ያላስታወሱትን ነገራቶችን እያመጣ እንዲዘናጋህ ግልፅ ነዉ፡፡ የአሏህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) አሁን እንዳየን አስቀድሞ ነግሮናል፣ እናም በመጀመሪያ ሙከራዎ ውስጥ የእርስዎ ኹሹዕ (መተናነስ) ከእያንዳንዱ አቅጣጫ ከእርስዎ ያመልጣል። አይጨነቁ፣ አስፈላጊው ነገር ምንም እንኳን ለኹሹ ጥቂት ጊዜያትም ቢሆን ወይም ለአፍታ እንኳን ቢሆን ይህንን የመጀመሪያ ተሞክሮ ማሸነፍ ነው ፡፡

እዚህ እና እዚያ ከእጅዎ ያመለጡትን የአክብሮትና መተናነስ (ኹሹዕ) እናም በሶላት አካባቢ የተሰራጩትን ጊዜያት ለማስተካከል በዚህ የመጀመሪያ እርምጃ ይሞክሩ፣ እነዚህን አፍታዎች በእያንዳንዱ እርምጃና የሶላት ደረጃዎች ይያዙ፡፡ በሚቀጥሉት አስር ቁልፍ ቦታዎች ላይ በተቻለዎት መጠን ያተኩሩ፡-

- ከእያንዳንዱ ተክቢር በኋሊ በሀሳብዎ ዝግጁ መሆን፣ ቢያንስ ከአንድ ተክቢር በኋላ፣ ከመጀመሪያው እርምጃ ቀደም ብሎ ማለት ነዉ፣ በርግጥ አሏህ ታላቅ መሆኑን ያላ ምንም ፍርሃትና ማስፈራሪያ ወይም ጭንቀትና ዉጥረት ወይም ጉዳት፣ ወይም ኢ-ፍትሃዊነት፣ ስጋትና ዛቻ ወዘተ የሚበልጥበት እውነታ መኖሩን ማረጋገጥ ነዉ፡፡ ከማንኛውም ተክቢር በኋላ፣ እነዚህን አማራጮች ለማስተዋል ይሞክሩ፣ በዚያ ቅጽበት የደህንነትን ፣ የሰላም ፣ ራስን አሳልፎ መስጠትን ፣ መዝናናት እና ጤናን ማምጣት እንደሚፈልጉ የሚሰማዎትን ያህል እጅግ በጣምበራስዎ ይተማመኑ ፡፡

- ከእያንዳንዱ ውዳሴ በኋላ፣ ወይም ቢያንስ ከአንድ ውዳሴ በኋላ በራስዎ ምስጋና ለዓለማት ጌታ ማስገባት አለብዎት፡፡ በጸሎት/ሶላት ከምትደግሙት ( ምስጋና ለዓለማት ጌታ ይን- አምላካችን ምስጋና ይገባሃል-ክብር ለአሏህ ይሁን - - አመሰግንሃለሁ ..) ማለት አለብዎት፡፡ ስሜትዎ እርስዎ ፈጣሪን የሚያመሰግኑ፣ የሰጧችትን ነገር ስለወደዱ መሆኑን ያሳያል፡፡ በዚህ ዉዴታና ፀጋ ምክንያት፣ በመረጋጋት እና በመዝናናት አምላክዎትን ስለሚያሲግኑ፣ደህንነት እና ፈውስ ይሰጣቸኋል፣

أَلَا بِذِكۡرِ ٱللَّهِ تَطۡمَئِنُّ ٱلۡقُلُوبُ ۝٢٨ الرعد: 28

"አዋጅ፣ በአሏህ ዉዳሴ/ማስታወስ ነዉ ልብ የሚረጋ"] አል-ራአድ 13)

- እናም (በጣም ርህሩህ) ከዚያም (በጣም አዛኝ) ቃላቶች በአል-ፋቲሃ ውስጥ ሲደግሙ፣ በመካከላቸው ያለውን ዉጣዉና ዉጫዊ ልዩነት አስታውሱ ፡፡

-የበለጠ በራስ መተማመን ፣ ጤናማ እና ደህንነት እንዲሰማዎት ሁሉን ቻይና ጠንካራን እሱን ይለምናሉ፣ "በፍርዱ ቀን ንጉስ" የሆነዉ በሁሉም ዓለማዊ ጉዳዮችዎ ለርስዎና ለሚወዷቸው በዙሪያዎ ላሉ ሰዎች ጥበቃዉንና ችሮታዉን ይሰጥዎታል፡፡ "ባንተ ብቻ እንዳገዛለን?"

-የበለጠ የመተማመን ስሜት፣ እፎይታ እና እርካታ በማምጣት እንዲሁም ይህ ስሜት የሚያመጣውን ጠቀሜታ ለመቀስቀስ በራስ የመተማመን፣ የጥንካሬ፣ የመፈወስ ስሜት እና ጽኑ እምነት እንዲኖርዎ፣ በወዲያኛው ዓለም ሆኖ በሩቁ ዓለም ትክክለኛውን መንገድ እንዲመሩዎት፣ ለሚወዷቸው እና ለሁሉም ሰዎች አሏህን መፀለይ ይኖርብዎታል፡፡

-ከእያንዷንደ ውዳሴ በኋላ ወይም ቢያንስ ከአንድ ዉዳሴ በኋላ (ክብር ለጌታዬ ታላቅ-ክብር ለጌታዬ ለልዑል ይሁን) ስሉ፣ ሁሉን ቻይ የሆነውን አሏህን እያወደሱ እንደሆነ ወይም - ይያነፀህ እንደሆነ (ስለ ሰው ድክመት፣ አለፍጽምና፣ ቸልተኝነት፣ ግፍ፣ ድካም ወይም እንቅልፍ ፣ ወይም ቸልተኝነት፣ ወይም መርሳት፣ ወይም የሚያሳዩትን ነገር ወይም በደረትዎ ውስጥ የሚደብቁትን አለማወቅ ወዘተ)፣ ወይም፣ በሌላ አገላለጽ (ክብር ለእርሱ ይሁን)፣እያላቁት መሆንዎን ያረጋግጡ፤ (በአንድነቱ፣ ወይም ታላቅነቱ፣ ወይም ትሎታዉ ወይም በእሱ ልግስና፣ በልህቀቱ፣ በጥበቡ፣ በፍጹምነቱ ወይም ፍትህ በመሆኑ…) እያተለቅዎት መሆንዎን፣ እና ያንን ተከትሎ የሚፈጠርብዎት ስሜቶች በበለጠ እምነት፣ እርካታ፣ ደስታ፣ መተማመን እና ጤናማነት ማስተዋል ይኖርብዎታል።

- (አተሀያቱ ሊላሀ-ለአሏህ ሰላምታ) በሚደጋገሙበት ጊዜ በእውነቱ በአሏህ ፊት እንደሆኑ ስሜቱ ሊሰመዎት ይገባል፡፡ እናም የሚናገሩትን እያንዳንዱን ቃል እንደሚያዳምጥ አዉቀዉ ሲደሰቱ፣ ከዚያ በኋላ እሱን ሰላምታ መስጠት ያስደስትዎታል፣ እንዲሁም ሰላምታዎትን መስማቱን በማረጋገጥ ይደሰታሉ፡፡ ከዚያ የሚጠብቀዎትን ትልቁን ሽልማት ሊያገኙ እርግጠኛ ስለሆኑ በምስጋና እና እርካታ ደስታ ይፈነድቃሉ። እናም ለሠላምታዎ ሁሉን ቻይ የሆነው ምላሽ መስጠቱን፣ ግልጽ ድክመትዎን (ከዚህ መለኮታዊ ምላሽ መጠን፣ ተፈጥሮ እና ታላቅነት አንፃር) ስለሚያነፃፅሩ ማለት ነዉ፡፡

-በአላህ መልእክተኛ ላይ (ሰ.ዐ.ወ) (አሰላሙ አሌይከ አዩሀነቢዩ-ነብይ ሆይ ሰላም ባንተ ላይ ይሁን) ስሉም እንደዚያዉ ሰላምታ ሲሰጡም በተመሳሳይ መልኩ በመቃብሩ (ሰ.ዐ.ወ) ውስጥ ሆኖ እንደሰማዎ ስለሚያረጋገጡ የደስታ ስሜት ይሰማዎታል፡፡ ከዚያ አሏህ ወደ እሱ  ህይወትን መልሶ በመስማት ምላሽ እና ሰላምታ መመለሱን ሲያዉቁ ደስታዎ፣ እርካታዎ፣ ጤናማነትዎ፣ ሰላምና ደህንነት የተትረፈረፈ ይሆናል።

-ለራስዎ፣ ለምትወዳቸው እና ለጻድቁ የአሏህ አገልጋዮች ሰላምታ (ሰላም) ሲሰጡም እንዲሁ ያው ነው፡፡ (በእኛና በፃድቁ የአሏህ አገልጋዮች ላይ ሰላም ይሁን) ሲሉም እንዲሁ፣ በተለይም በምድር ላይና በሰማይ ዉስጥ ካሉ ጻድቅ የአሏህ አገልጋዮች (የአኖችም ሆነዉ ያለፉት) ጋር በማሰላመትዎ የሚገኙትን ምንዳዎች በሚሃስቡበት ጊዜ የሚሰማዎትን ስሜት ሲኖር፣ ያኔ በተባረካችሁ ጸሎቶችዎ ምክንያት አሏህ የሚሰጣችሁ ታላቅ ሽልማት ይሰማዎታል።

-በክቡር ነቢዩ ኢምራሂም ላይ በምትጸልዩ ጊዜ የትልቁ ሽልማት ጥፍጥና ከሀያሉ አምላክ የሚጊኙትን ሲሃስቡ የሚሰማዎትን ስሜት አንድ ጊዜ ሲጸልዩላቸዉ አሏህ አስር ጊዜ እንደሚፀልይላችዎ (አንድም ስለ እኔ የሚሰግድ ሰዉ አሏህ አስር ይፀልይለታል) ያስቡ፡፡

በዚህ የመጀመሪያ እርምጃ ከተሳካልዎት እና ከእነዚህ ውስጥ የተወሰኑትን አስር ቁልፍ ነጥቦችን ማስቆጠር ከቻሉ፣ የእርስዎ የሙከራ ጸሎት፣ ሱናም ይሁን የግዴታ ሶላት፣ እና እነዚህ ነጥቦች ጥቂትም ወይም ብዙ፣ እና እነሱ ብዙ ከሆኑ ተመራጭ ነው፣ ከዚያም በየቀኑ በተግባር ማስከተል ከቻሉ፣ ወይም በግማሽ ቀኑም፣ ለአንድ ወር ያህል፣ ይህ ወደ ቀጣዩ ደረጃ መንገዱን ሊከፍትልዎት ይቻላል ማለት ነዉ፡፡

## ሁለተኛው እርምጃ

በመጀመሪያ-ደረጃ መርሃግብር ላይ አንድ አዲስ ነገር በማከል ይጠናቀቃል፤ በእርግጥ የቀደመውን ፕሮግራም ማስቀጠሉ እዳለ ሆኖ፤ ከቀጣዩ ፕሮግራም ጋር ጎን ለጎን እንዲሆን ማለት ነዉ፡፡ ያ ተጨማሪ አካልም “ ቀጣይነት ያለዉ ትኩረት” ነው። ማለትም በአንድ ረከዓ ዉስጥ የተሟላ እና ቀጣይነት ባለው መልኩ መተናነስን ለማግኘትና “በሚያቋርጥ” አይነት መሆኑ ነዉ፡፡ ምንአልባትም ከሱናዎችዎ አንድ ረከዓ ብቻ ይሁን፣ ለምሳሌ ፣በየቀኑ ሶላታችንን የምንጨርስበት የዊትር የመጨረሻ ረከዐ ይሁን፤ ብቻ እያንዳንዱን ሐረግ እና ቃል በመረዳት እና በማስታወስ የሰገዱ መሆንዎን እርግጠኛ ለመሆን ይሞክሩ፡፡በዚህም የደስታ፣ የእርካታ፣ ሥነ-ልቦናዊ ምቾት፣ የመከላከል እና ፈውስ ስሜት እንደተሰምዎት ያረጋግጡ፡ በመጨማሪም በአላህ ፍቃድ ታላቅ ወሮታ ሁሉ የሚጠብቁ መሆንዎን እርግጠኛ ይሁኑ፡፡

ይህንን ዕቅድ በየቀኑ ካሳኩ፣ ወይም በግማሽ ቀንም ማለት ይቻላል፣ እና ለሌላ አንድ ወር እንዲሁ ማከናወን ከቻሉ፣ ቀጣዩን እርምጃ ለመውሰድ አሁን በቂ መተማመን እንዳለዎት ያረጋግጡ፡፡

## ሦስተኛው እርምጃ

አምስቱን ሶላት ሲሰግዱ ሶላትህ የተሟላና ቀጣይነት ባለው መልኩ እንዲሰገድ ለማረጋገጥ ቆርጦ ይነሳሉ፡፡ በተመሳሳይ መልኩ የመጀመሪያውን እና የሁለተኛ ደረጃ መርሃግብሮችን ቀጥተኛ በሆነ መንገድ ለመተግበር ቁርጠኛነትዎን ለማረጋገጥ ያሻሉ፡፡ በመቀጠል በዚያም አያበቁም፡፡ ማለት የተወሰኑ ነጥቦችን ብቻ በማስቆጠር አይደለም፡፡ የመጀመሪያውን እርምጃ እንዳደረግነዉ ሁሉ፣ ምንም ነጥብ ሳያስቀሩ በተቻለዎት መጠን ሰግዶ ለመውጣት ለራስዎ ቃል ይግቡ፡፡ ነገሩ ከመተናነስና እና የመደሰት ተግባራት ዋናዉ ስሆነ፡፡ ማለትም፡ የተሟላ ትኩረት፣ ሙሉ አክብሮት፣ ከአሏህ ጋር የማያቋርጥ ግንኙነት፣ ፍሬያማና የተሟላ ውስጣዊ ደስታ፣ እና ሁሉን ቻይ ከሆነው አምላክ ታላቅ ሽልማት የማግኘት ስሜት ይፈጠርብሃል።

እነዚህን ምርጥ ውጤቶች ለማረጋገጥ፣ ይህንን ዕርምጃ ለመጀመሪያይቱ የዕለት ተዕለት ሶላታችን (ሱብሂ) ተግባራዊ ማድረግ እንድንጀምር ይመከራል፡፡ ማለትም በጣም አጭር የሆነው የንጋት (ሱብሂ) ሶላት ነው፡፡

ይህንን ሶላት ሲሰግዱ በሁሉም ዘንድ ተተናንስ ይፈጠራል ወይም ይቻላን ማለቴ አይደለም፤ ወይም ለእርስዎ ቀላል ነው ማለት አልችልም (የዚህ መጽሃፍ ሀሳቦች ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ሶላት ዉስጥ እያለሁ፣ በሚያሳዝን ሁኔታ ወደ እኔ እንደመጡ) አምናለሁ፡፡ ነገር ግን ይህ እውነታ እና የሰው ልጅ ድክመት እንዳለ ቢሆንም፣ በትክክል እዉነተኛ ከሆኑ እርሰዎ የፍላጎትዎን አቅም ቢጠቀም ያንን እንደምያሳኩ አምናለሁ፡፡ ጥንካሬዎን እና ተሞክሮዎን በትዕግስት እና በትኩረት ዑደት ውስጥ ካስገቡና እስከ አሁን ባሰቡት ነገር ለእርሶ በአሏህ እርዳታ ለእራስዎ በቁርጠኝነት ቃል ከገቡ፡ “ይህ ሶላት ከእሷ ምንም ቅንጣት ታክል በጭራሽ አይጠፋም›› ብሎ ካሉ እርሶ በአሏህ እገዛና እና ጸጋ ይህንን ለማሳካት ይችላሉ፡፡ ምንም እንኳ አንዳንድ ጊዜ ቃሉን፣ ሐረጉን ወይም ጥቅሱን እና ምንአልባትም መላውን አል-ፋቲሃ ወይም መላውን ተሻሁድ ካንዴም ሁለቴ ወይም ከዚያ በላይ ሚያነቡ ቢሆኑም፡፡ በመጨረሻ ግን የሚፈልጉትን ማግኘትዎ አይቀርም፡፡

## ደረጃ አራት

አሁን በሶስት ወራት ውስጥ የአጠቃቀም ነጥቦችን የማስመዝገብ ዘዴን የተካነ መልኩ ማስተካከል ችያለሁ፡፡ በምንዳ ፍሬዎች መጠቀሚያ ነጥቦችንም ልክ እንደዚያዉ፣ እነዚህ ነጥቦች በተናጥል ወይም ስብስብ ደረጃና በአንድ ረከዓ ዉስጥ ወይም በሁሉም የአምስቱ ሶላት ረከዓዎች ዉስጥ፣ የግዴታ ወይም የሱና ሶላቶች ቢሆኑ የማተኮር ችሎታን መቆጣጠርና እና በራስ መተማመን እንዳለዎት ለራስዎ ማረጋገጥ አለብዎት፡፡

ከዚህ ታላቅ እና ስኬታማ ዉጤት በኋላ፣ ከመጀመሪያ ተክቢራ ጀምረህ እስከ ማሰላመቻ ድረስ ሌላ መተናነስና ስኬትን የሚታኙበትን ሶላት በማከል፣ ልክ እንደ ሱብሂ ሶላት፣ ታላቅ ስኬትና ምንዳ (አጅር) ማግኘት ትችላለህ፡፡ በዚህ ጊዜ መግሪብ ሶላትን እንዲመርጡ ሀሳብ አቀርባለሁ፣ምክንያቱም ከፈጅር ሶላት የበለጠ አንድ ረከዓ ብቻ ነው ያላት፡፡

እነዚህን አራት ደረጃዎች ከጨረሱ እና ለአራት ወራት ከተለማመዱ በኋላ፣ በአሏህ ፍቃድ አስቸጋሪ ሆኖ አያገኙትም፡፡ እነዚህን የመተናነስ ህጎች ቀስ በቀስ ወደ የተቀሩት ሶላቶችችና ሱናዎች ማዉረድ አይከብድዎትም፡፡

የሚከተሉትን የአሠራር ዘዴዎች መከተል ጠቃሚ እና በዚህ መስክ የተመረጡ ሊሆኑ ይችላሉ፡-

1 - የሚያዘናጋዎት ሸይጧን ቢያደናቅፍዎት፣ ሲያነቡ አንዲትን ቃል ቢያስረስዎት፣ ትርጉሙ የተዛባ ሆኖ ያገኙዎታል፣ በድንገት መተናነስን ሳያመጡ ወደ ሌላ ሐረግ ሲያስተላልፍዎት ያገኙታል፡፡ እናም ከአንዴም ሁለቴ ደጋግሞ ያንብቡና ማስተካከል ይሞክሩ፡፡

2- በሶላትዎ ላይ የበለጠ ለማተኮር፣ ከመሳሳት ለመራቅና ከዛም አነባበቡና መግለጫዎች ከእጅዎ የማያመልጡ ይሆናሉ፤ ምንአልባትም ከሶላትዎ የተጠናቀቁ ራካዓቶች በቸልተኝነት ተዘንግተዉ የተተኩ ብዛት ሶስት? ወይስ አራት? ተብሎ ማስታወስ ያስፈልጋል፡፡ በአንዳንድ ረከዓዎች ውስጥ ለራስዎ በሚፈጥሩት የአእምሮ ንቃተ-ህሊና መረዳት ጠቃሚ ነው፡፡ ምን ያህል ራካቶች እንደሰገድክ ስለሚያስታወስዎ፡፡ በአንድ በኩል የሚሰግዱትን የራከዓ ቁጥር

እንዲያስታውስዎት እና ትርጉሞቿን ሳያስቡ ከማንበብ ወይም በሌላ በኩል በፍሬዎቹ ካለመደሰት ያላቅቅዎታል፡፡

ከዚህ መካከል ለእርስዎ የማቀርበው የአእምሮ ሁኔታዎች፡- - ከቁርአን አንፃር በሚወዱትን ሱራዎች በሶላትዎ ወቅት ለያንዳንዱ ረከዓ ደጋግሞ ያንብቡ፡፡ ለእያንዳንዱ ሶላት-አንድ ሱራ ለመጀመሪያው ረከዓ፣ ሌላ ለሁለተኛው ራከዓ፣ ወይም ለመጀመሪያው ግማሽ ሱራ እና ሌላ ግማሽ ሱራ ለሁለተኛው፡፡ ለምሳሌ ሱራ አል-ዱሃ በመጀመሪያው ረከዓ ለማንበብ ማቀድ ይችላሉ፣ ከዚያ (አል-ሻርህ) በሁለተኛው ረከዓ፣ እና ሱራት (አል-አዲያትን) በሌላ ሶላት ለማንበብ፣ ከዚያ (አል-ቀሪአህ)ን፣ እና በሌላ ሶላት ሱራ (አል-ሁመዛ) ከዚያም (አል-ማዑን)፣ ወዘተ፡፡

ይህ በራስዎ በእያንዳንዱ ሶላት ውስጥ በሚያነቡት ላይ እንዲያተኩሩ ይረዳዎታል፡፡ ይህ የሚሆነዉ ነቅተህ ሳለህ በራስህ ላይ እቅድ ለመተግበር የተነሳሳህ እንደሆንክ ነዉ፡፡
- አሁን አንደኛዉ ረከዓ የትኛውን ምዕራፍ አነባለሁ፣ በሁለተኛውስ የትኛው ምዕራፍ ነው? በዚህ ንቃት፣ዝግጁነት እና ትኩረት ሶላትዎን ከጀመሩ፣ በዚህ ትኩረት ውስጥ እንዲቆዩ እና ከዚያ በእያንዳንዱ ሶላት ውስጥ ተገዢ (እራስዎን ዝቅ የሚደርጉ) ለመሆን ይረዳዎታል፡፡
- ይህ እራስዎን በቀላሉ ሶላትዎ ላይ እንዲያተኩሩ ይረዳዎታል። ብዙ ጊዜ እራስዎ በሶላት ውስጥ ጥያቄ ይፈጠርቦታል፡፡ ስንት ረከዓዎች ሰገድኩ ሁለት ወይስ ሁለት ረከዓዎች እያሉ፡፡ ይህ ከተከሰተ እንዲህ እያሉ እራስዎን ለመጠየቅ ይረዳል፡-አሁን ሱረት (አል-ዱሃ) እና (አል-ሻርህ) ሁለቱም ሶላት ዉስጥ? ወይስ (አል-ዱሃ) ብቻ? ያ የማይረዳዎት ከሆነ፤ ይህንን ቁጥር ለማግኘት እርስዎ የመረጡትን ሱራ ማንበብዎን ለመለየት ሊረዱዎት ይችላል፡፡ ያዉ አንድ ወይ ሁለት ሱራ ነዉ ያነበብኩት በማለት ያስታወሳሉ፡፡
-በጣም ጠቃሚ የሚሆነዉ እነዚህን ጥንዶች (ትናንሽ ምዕራፎች) በሳምንቱ ቀናት ውስጥ በአንዱ ሶላትዎ ውስጥ ማከፋፈል መጀመር ነው፡፡ ለምሳሌ፡ (ሱራት ፈጅር እና አል-በለድ) ለአርቡ ኢሻዕ ሶላት፣ (ሱረቱ ሸምስ እና ሌይል) ለቅዳሜ ኢሸዕ፣ እና (ዱሃ እና ሻርህ) ለእሁድ ኢሸዕ፣ (ሱረቱ-ኒን እና ዘልዘለህ) ለሰኞ ኢሸዕ፣ እና (አዲያት እና

አል ቀሪዓ) ማከሰኞ ኢሽዕ፣ (አልቀደሩ ወት-ተካሱር) ለረቡዕ ኢሽዕ፣ እና ሱረቱል ቡሩጅ እና ባይነህ ለሐሙስ ኢሽዕ በማድረግ ይጀምሩ፡፡ በሳምንቱ ቀናት እንዲሰራጭ ሱራዎቹን በበቂ ሁኔታ በልብዎ ካልያዙ፤ በሶስት፣ አራት ወይም አምስት ሱራዎች ሊበቃዎት ይችላሉ፡፡ ያዉ በተከታታይ ለበርካታ ቀናት ደጋግምዎ ማንበብ ነዉ፤ በሳምንቱ ቀናት መገደብ ሳያስፈልግዎ ማት ነዉ፡፡

- ከዚያ የእነዚህ ጥንዶች ምዕራፎችን ወደ ሌላ ሶላት ማስፋት ይችላሉ፡፡ ከዚያ በኋላ ደረጃ በረጃ ለአምስቱ ዕለታዊ ሶላት ሁሉ፡፡ ለፈጅር ሁለት ሱራዎች፣ ለዙህር ደግሞ ሌላ፣ ለአስርም..ወዘተ፡፡

ዕድሜዎ፣ ትጋትዎ እና የቁርአን ትዝታዎ በእርግጥ እነዚህን የመሰሉ ነገሮችን እንዲያገኙ ባስቻልዎትና ቁርዓንን በመስታወስ ችሎታዎ መጠን እየጨመሩ ይሄዳሉ፣ እና ሱራዎቹን በማደራጀት እና በሳምንቱ ቀናት በሙሉ ሱራዎቹን ጸንተው ለመጠቀም ዕለታዊ የአእምሮ እንቅስቃሴ ይሆንልዎታል፡፡ ይሄ እንዲሁም ዕድሜዎ እየገፉ ሲሄድና ወደ እርጅና አባት እየተቃረቡ የማስታወስ ችግሮችን ለመቋቋም የሚረዳዎ ነው፡፡

-በባለአራቱ ረከዓ ሶላቶች ውስጥ፣ ከእያንዳንዱ ሶስተኛ ረከዓ ከተነሱ በኋላ ዱኣእ ወይም የሚነበብ ውዳሴ ይመድቡ፣ወይም ከዚህ የመጨረሻ ሐረግ በኋላ (ጌታችን ሆይ ምስጋና ለአንተ ይሁን)፡፡ ለምሳሌ የሰው ልጅ ሥነ-መለኮታዊ ልመና እንደ፡ (ብዙ ምስጋናና እና የተባረከ ውዳሴ በዉስጡ ይኑር) ወይም ከዚያ በኋላ የሚጨምሩት የነበሩ የፀሎት ወይም የውዳሴ አይነቶች ከሦስቱ ቅዳሴዎች በኋላ ሊካተቱ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ እንደ (አቤቱ አምላክ ሆይ፣ ኃጢአቶቼን ሁሉ ይቅር በለኝ፣ ትንሹንም ትልቁንም እና ጅማሬውንም መጨረሻውንም የሚሉ (ወይም በሁለቱም ቦታዎች) ሊጨመሩ ይችላሉ፡፡ ከላይ የጠቀስናቸውን የነቢዩን ልመናዎችና ፀሎቶችን መጠቀም ምንም ጉዳት የለውም። ለምሳሌ “የሩኩዕና የሱጁድ ማዕከላዊነት” የመጡ ማናቸዉንም ፀሎቶችን መጠቀም ይቻላል)

እነዚህ ተጨማሪዎች፣ ለፀሎትዎ በሚዘጋጁበት ጊዜ እነሱን ለመተግበር እቅድ አውጥተው ራስዎን አዘጋጅተዋል፤ በዚህ ሶላት ውስጥ ሙሉ በሙሉ እና በተከታታይ እራስዎን ለማተኮር እና ለማንበብ ብቻ ይረዳዎታል ማለት አይደለም፤ ትርጉሙን ሳይገነዘቡ ፈጣን በሆነ ሁኔታ ላለመስገድም ብቻ አይሆንም፣ ነገር ግን የረከዓን ብዛትና ስንተኛ ረከዓ ላይ እንደሆኑ ለማወቅ እንደረዳዎት ሁሉ ከረሱም ለማስታወስ

ይረዳዎታል፡፡ ከዚያ በኋላ ነዉ ላለፈዉ(አንደኛና ሁለተኛ) ረከዓ ተጨማሪ ዱኣዎችን አብቤአለሁ ወይ ከሱጁድ በኋላ የተለመደዉን ዉዳሴ አንብቤአለሁ? ብልዎ እራስዎን ይጠይቃሉ፣ መልሱ ኣዎ ከሆነ የዛኔ እርስዎ በአራተኛው ረከዓ ላይ ነዎት፡፡

-እነዚህን ጥንድ ሱራዎችን ለማደስ ይሞክሩ፤ እነዚህን ተጨማሪዎች እና የአዕምሯዊ ምሰሶዎችንም እንደዚያዉ ፣ወይም እንደገና ያስተካክሉ፣ ወይም በእነሱ ላይ ይጨምሩ፣ ወይም በየአመቱ ሱራዎችን ይለውጡ፣ ከጊዜ በኋላ ድግግሞሽ ከበዛ ምላስዎን ያበራዋል ብለው ከፈሩ ማለት ነዉ።

3 - በመጨረሻም፣ የረመዳን ወር ከአመቱ እንደዚህ አይነት ለውጦች የሚጀምሩበት ቀን የእርስዎ ይሁን፣ ነገር ግን እያንዳንዱ ቀንዎ አዲስ አምልኮዎ እና ማስታወስዎ ተግባርዎን የሚጨምሩበት ቀን ይሁን፡፡ አሁንም ክፉ ነገሮችን በማስወገድና በዚህ ዓለም ላይ ሃይማኖትዎን እና ሥነ ምግባርዎን ከሚያሰናክል ነገር የሚያርቅህ እና በመጨረሻው ዓለም ከአሏህ ዘንድ ሚዛንዎን የሚጨምር ተግባር ይሁን፡፡

ሕይወታችን እኛን በሚያስጨብጡን ክስተቶች፣ ጭንቀቶች፣ ብስጭት እና ንዴቶች የተሞላ ነው፣ እናም በሽታን በነፍሳችን እና ሰውነታችን የሚያስተላልፉበት ነው፡፡ እና በሶላትህ ውስጥ የምትደጋግመው እያንዳንዱ ቃል ወይም ሀረግ ለዚህ ሕይወት በነፍስም ሆነ ሰውነት የመከላከያ መድሃት ነው፡፡ እንዲሁም እያንዳንዱ ሶላት ከአምስቱ ሶላትዎ መካከል ለሰጋጁ ግላዊና መንፈሳዊ ጓደኛ ነዉ፤ በዘመናዊ ህክምና በሚወስዱት መድሃኒት በላይ ለርስዎ ሕክምና የሚረዱ መድኃኒቶች የሚገኝበት ጠቢብ ነዉ፡፡

ይህ ግንኙነቶች ለዓለምም ሆነ ለመጭው ዓለም እንደ ጥሩ ኢንቬስትሜንት የሚደረጉበት የስኬት ካርታ ፕሮፖዛል ነው፡፡ ይፍጠን ይቆይ፣ እራስዎ ለራስዎ አማራጭ ዕቅድ ወይም እቅድ ማዘጋጀት ይችላሉ፡፡ ያዉ ከአከባቢዎ ሁኔታዎች እና ከግል ችሎታዎ ጋር የሚስማማ ሆኖ ካገኙት ማለት ነዉ፡፡

ደግሞም ለእያንዳንዱ አምልኮ ዕቅድ ሊኖርህ ይችላል፣ ይልቁንም ሌሎች የዕቅዶች አይነት በተለይ በረመዳን ዉስጥ ሊጨምሩ ይችላሉ፡፡ እናም በሕይወትዎ ውስጥ የበለጠ መልካም ተግባራት መጨር ነዉ፣ እና ተጨማሪ ኃጢአቶች እና ስህተቶች ከእርስዎ ይራገፋሉ?

ሶላትዎን ሁል ጊዜ ይስገዱ፤ ወደ ሠርግዎ ይንቁ፣ እና ብዙ ገንዘብ ባከለው ሰው ስሜት ተሞልተው ሂሳብዎን ይሙሉ፤ ከትከሻው ላይ ከባድ ሸክም የማስወገዱ ስሜት

አይኖርም፡፡ እናም ያንን የስኬት እና ተስፋ ሁልጊዜ ቃሉን በጭራሽ የማያፈጽም ያልሆነዉን የአምላክ ቃል ያስታውሱ፡-

قَدْ أَفْلَحَ ٱلْمُؤْمِنُونَ ﴿١﴾ ٱلَّذِينَ هُمْ فِى صَلَاتِهِمْ خَٰشِعُونَ ﴿٢﴾ المؤمنون: 1-2

- ምእመናን ተሳክቶላቸዋል፤ እነዚያ በጸሎታቸው ትሑታን የሆኑ (ሙኡምኑን 1-2)

إِنَّ ٱلْإِنسَٰنَ خُلِقَ هَلُوعًا ﴿١٩﴾ إِذَا مَسَّهُ ٱلشَّرُّ جَزُوعًا ﴿٢٠﴾ وَإِذَا مَسَّهُ ٱلْخَيْرُ مَنُوعًا ﴿٢١﴾ إِلَّا ٱلْمُصَلِّينَ ﴿٢٢﴾

المعارج: 19-22

- የሰው ልጅ ፈሪ ሆኖ ተፈጠረ፡፡ ክፋት ከነካው ጊዜ ያዝናል፤ በጎ የሚነካዉ ከሆነ ደግሞ ንፉግ ይሆናል፡፡ ሰጋጆች ሲቀሩ [አል-መአሪጅ 19-22] * * *

እና ከዚያ፣ እያንዳንዱ የሕይወትዎ እስትንፋስ ሶላት መሆኑን ያስታውሱ። በህይወትዎ በሁሉም ሁኔታዎች እና ውጣ ውረዶች ውስጥ፣ ለነፍስ ሊጸልዩ አካልዎን ሲያነፁ ለሶላት ዝግጁ ይሁኑ፤ በንፁህ ነፍስና ደም የአሏህን ምንዳ ይፈልጉ፡፡ እያንዳንዱ የአካል ጅማቶች፣መገጣጠሚያዎች፣ ሕዋሶችና ጡንቻዎች ሁሉ ፈጣሪን ያመሰግናሉ፣

ሶላትዎን ማስተዳደር ሕይወትዎን ማስተዳደር እንደሆነ ይወቁ። እስልምናው የመጀመሪያ ምሰሶ የሰጣህ ኣኼራህን ለማረጋገጥ እንድትእል ነዉ፡፡ ሁለተኛ ምሰሶውን የሰጠዎት ደግሞ የቅርቢቱን ህይወትና አኼራን ልታረጋግጥበት ነዉ፡፡ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ያሉት ጥቃቅን ቁልፎች ብቻ ሆነዉ ይህንን በእጅህ ይዘህ የአስተሳሰብዎን ካዝና እንድትከፍትበት ነዉ፡፡ ከዚያም ከአሏህ ጋር በህልምዎ ዓለም እንድትበር ነዉ፤ የማሰብ ባህር ዉስጥ ከአሏህ ፍጥረታት ጋር እንድትዋኝ ነዉ፡፡ በዚያም ሶላትዎን ለማስተዳደር እና ሕይወትዎን ለማስተዳደር ልዩ መፅሃፍ ይኖርዎታል።

አቤቱ አምላኬ ሆይ፣ ወደ አንተ በተጻጸትኩበት ኃጢአት ይቅርታ እጠይቃለሁ፣ ከዚያ ወደዚያ ተመለስኩ፡፡

እናም ከራሴ ስለሰጠሁትና ላላሟለሁት እንደሆን ይቅርታ እጠይቃለሁ፡፡

እናም ለሰጠኸኝ በረከቶች ሁሉ ይቅርታህን እጠይቃለሁ፤ ስለዚህ እኔ እንዲያዉም በዓመፅ ላይ በበረታሁ ነገርም፡፡

እና ፊትህን በፈለግኩት መልካም ነገር ሁሉ ይቅርታን እለምናለሁ፡፡ ካንተ ካልሆነዉ ነገር አጥረኝ፡፡

## ሶላትን እንደገና ማወቅ
## (ሶላትን ማስተዳደር)
### *መጽሓፉ ላይ ያለኝ ሀሳብ፡*

መጽሓፉ በሶላት እና በምእመናን መካከል ያለዉን ግንኙነት ቁልጭ አድርጎ ያሳያል፣ ማለትም፡

- ትክክለኛ ሶላትን ለመስገድ ምእመናን የሚያደርጉትን ተጋድሎና የሸይጧንና የነፍሲያ ተቃርኖ፣
- በሸይጧን እና በነፍሲያ ዉትወታ እና ማዘናጋት ምክንያት፣ አብዛኛዉ ምእመናን ሶላትን በአካላቸዉ እንጂ በልቦናቸዉ መስገድ እንደሚከብዳቸዉ፣
- ምእመናን ህያዉ እና ትክክለኛ ሶላትን ለመስገድ ትዕግስት፣ እርጋታ፣ ትህትና (ኹሹዕ) እና ፕሮግራም ሊኖራቸዉ እንደሚገባ፣
- ሶላት የሁሉም ስኬቶች መሠረት መሆኑን እና አሏህም አፅዕኖት ስለሰጠዉ ነብዩን (ሰ.ዐ.ወ) ወደ ሰማይ ወስዶት ሶላትን የሰጣዉ መሆኑን፣

እና ሰፋ ያሉ ከሶላት ጋር የተያያዙ ልምዶችን፣ ተሞክሮዎችን እና ትምህርቶችን የያዘ በመሆኑ፣ችግሩ ደግሞ የሁሉም ምእመናን እና ስር-ሰደድ ስለሆነ፣ ይህንን ለማስተካከል በመጽሓፉ ዉስጥ የተካተቱ ምክሮችና ተሞክሮዎች ከፍተኛ ሚና ስለሚጫወቱ ቋንቋዉን የሚችል ሁሉም ሙስሊም ምእመናን ቢያነቡ መልካም ነዉ እላለሁ፡፡ አሏህ የበለጣ አዋቂ ነዉ!